# እርካብና መንበር



ዲራአዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

# ማውጫ


## ክፍል አንድ 1

### ምዕራፍ አንድ 2

የዘመኑን ሥጋትና ጥሪ መጋፈጥ 2

### ምዕራፍ ሁለት 17

ጀግንነት፣ ጀብዳዊ ጭካኔና ጀብዳዊ ቅንነት፡- 17

## ክፍል ሁለት 28

ከመሪው በፊት ኃይል ይቀድማል፤ ኃይል ግን ህልው ይሆን ዘንድ መሪውን ይጠብቃል 28

### ምዕራፍ ሶስት 29

ኃይልና ሥልጣን 29

ኃይልና የኃይል አጠቃቀም 33

ሥልጣንና የሥልጣን አጠቃቀም 40

### ምዕራፍ አራት 47

ኃይልና ሥልጣን በኢትዮጵያ 47

ሥልጣን በሀይማኖት... ኃይል በወታደር... 48

ጀብዳዊ ጭካኔ` የነገሠበት የኃይልና ሥልጣን ሥርዓት 50

ዳግም `ጀብዳዊ ጭካኔ` ወዳጠላበት መንበረ ሥልጣን 55




t.me/OLDBOOKSPDF

ከጀብዳዊ ጭካኔ መልስ 66

ጀብዳዊ ቅንነት ጭካኔን ሲሸር 70

አዲስ ነገር ያላሳየቸን ዓለም እና ጎህ የቀደደባት አገር 72

## ክፍል ሶስት 77

መሪ መሆን የሚችሉ ሰዎች ግን የመምራት ሥራቸውን የሚጀምሩት ዛሬውኑ ነው። 77

### ምዕራፍ አምስት 78

ሥልጣንና ኃይልን ለመጠቀም ከልብ መሪ መሆን ያስፈልጋል 78

የተሳካላቸው መሪዎች መገለጫ ባህሪያት 97

### ምዕራፍ ስድስት 121

ነብይ በሀገሩ አይከበርም፤ ታላቅ መሪም ሁልጊዜ በህዝቡ አይወደድም፤ 121

## ክፍል አራት 137

### ምዕራፍ ሰባት 139

የኑሯችን ጀልባ የሚገፋበት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ርዕዮትና አጠራጣሪው መዳረሻ 139

የኒዮ ሊበራሊዝም ጽንሠ-ሀሳብና ውጤቶቹ 141

የልማታዊ መንግሥት ጽንሠ-ኃሳብና ውጤቶች 149



እርካብና መንበር

የልማታዊ መንግሥት ስኬት በምስራቅ እስያ 152

የልማታዊ መንግሥታት ውድቀት በላቲን አሜሪካ እና አፍሪካ 154

## ስንብት 164

## መንገድና ድልድይ 169



t.me/OLDBOOKSPDF

# መታሰቢያ

በምድር ላይ ላለን ፍጡራን ሁሉ ዓለማችን ብቸኛ ቤታችን ናት። ምትክ አልባ ጣራችን ልንላትም እንችላለን።ከእርሷም ውጭ ማንም ምንም አይደለንም። በዚህ ደረጃ በልጅነት ወቅት ትዝታዬ በሕልም ፈቺነት ያላበሰችኝን ሠፊ ራዕይ፣ የቀረፀችውን ፅናት በዕውቀት ዘመኔ ደግሞ በዝናዬ አለሁ ባይነት ተደግፎና ተበረታቶ ለፍፃሜ የድል ማግስት መብቃቱን በልበ-ሙሉነት እመሰክራለሁ። ከመመስከር በላይ እነዚህ ሁለት ጀግኖች፣ ምትክ አልባ ሕልም ፈቺዎችና ዓላማ አስጨራሽ መሆናቸውን በማመኔ የዚህች መጽሐፍ መታሰቢያነት ለሁለቱ የሕይወትና የፍቅር ፀበል መፍለቂያ ምንጭ ለሆኑት ለትዝታና ዝናዬ ይሁንልኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF

# የልብ ምስጋና

በውስጣችን ያለውን የለውጥና የመለወጥ ስሜት በጠንካራ የሥራ ባህል በመደገፍ ለውጤት መብቃት መቻሉን አምናለሁ። ከሁሉም ውጤታማ ሥራዎች በተለይም ለሕትመት ከሚበቁ የሥነፅሁፍ ሥራዎች ጀርባ ይህን አሻራ ፈልጎ ማግኘት ከባድ አይደለም። እኔ ግን እላችኋለሁ፣ እርካብና መንበር- ከእናንተ ከወንድም እህቶች የጋራ ድጋፍ ውጭ በምንም መልኩ የሚታሰብ አልነበረም።

ከመነሻ ምዕራፍ አንስቶ ጉዞዬን በመንፈስ አብራችሁ በመጓዝ ረቂቁን በማረምና በማቃናት አእምሮዬ አድማስ ቀስተ-ደመና በመዘርጋት ስለፈጠራችሁልኝ መነቃቃት በተለይም በድካምና ተስፋ መቁረጥ ወቅት ማረፊያ እልፍኝ እና መጠለያ ታዛ በመሆን ብርታት ለሆናችሁኝ ከሁሉም የላቀው ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF

## መቅድም

በማንም አይን ቢታይና ቢፈተሽ ልብን በኩራት መሙላት የሚችል ጥንታዊ ሥልጣኔና አልፍ ዘመናትን ያስቆጠረ ታሪክ የተላበሰች ሀገር ባለቤቶች ስለመሆናችን ኢትዮጵያውያን መስካሪ አያሻንም። እናውቃለን፣ ያውቃሉ። በዚያው መጠንና ልክ ዛሬ የደሃ ደሃ መሆናችን አንገታችንን ያስደፋ የታሪካችን ጠባሳ መሆኑን የሚጠፋው ይኖራል ተብሎ አይታሰብም።

ያን መሠል ጥንታዊ የነጻነትና የሥልጣኔ ታሪክ የተላበሰች ሀገር በምን መዓታዊ መቅሰፍት ክብሯ ተገፎ ፣ዝናዋ ደብዝዞ አሁን ለምንገኝበት የኋላቀርነት ውርስ እና ቅርስ ተዳረገች የሚለው ጥያቄ እንደትናንት ሁሉ ዛሬም እንቆቅልሽ ሆኖ በብዙዎች አንጎል ይመላለሳል። ይጠየቃል፣ መልስ ይሰጣል። መልሱ እንደመላሹ የተለያየ ቢሆንም የአንበሣውን ድርሻ የሚይዘው መዓታዊ መቅሠፍት ከተከተልነው የተሳሳተ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዞ ጋር ብርቱ ቁርኝት እንዳለው በዘመን ሂደት መሻሻል ያላሳየው መንግስታዊ አስተዳደር የደሃ ደሃ መሆናችን ምስክር ሊሆን ይችላል።

ግና ስለምን የተሳሳተ አቅጣጫ ተከተልን? መሪዎቻችን ስለተከተሉት፣ ጫንቃችን ላይ በሃይል ስለጫኑት ። ስለምን ኋላ ቀር ሥርዓት በላያችን ላይ ጫኑብን? ከድንቁርና ጋር በመጋባታቸው?!! ይህቺን ጥንታዊ ታሪክና የሥልጣኔ ባለቤት የሆነች ሀገር እንደምን ከድንቁርና ጋር በሰማንያ ጋብቻ የፈፀሙ



t.me/OLDBOOKSPDF

መሪዎች ሊዘውሯት ቻሉ? እንደዚህ እያለ... ጥያቄው መልስ፣ መልሱ ደግሞ ጥያቄን እየወለደ ይቀጥላል። ማጠቃለያና መደምደሚያ ነጥቡ ግን 'ዞረም ተዟዟረ ' ፤ 'አረረም መረረ ' ከጨቋኝና አምባገነን ገዥዎቻችን እናት የሚወርድ አይሆንም። ምክንያቱም መንበር ወይም ኃይልና ስልጣን በዜጎች ሕይወት የላቀውን ተጨባጭ ተፅዕኖ መፍጠሪያ መሳሪያዎች ናቸውና። አበው በተረታቸው «መሪዎች ሲከፉ ዘመንም ይከፋል!» ማለታቸውም በዚሁ የተነሳ ነው።

በእርግጠኝነት ትላንታችንን ከዛሬያችን ጋር አስማምቶ እንዲያገናኘልን የተገነባው የዘመን ሀዲድ ስብራት ያለው መሆኑ ብዙም አከራካሪ አይደለም። ያ ስብራት የቱ ጋ እንደሆነ በትክክል መለየቱ እና መጠገኛ መፍትሄ የማፍለቅ ጥረት የየዘመኑ ትውልድ አብይ የቤት ስራ ቢሆንም ባላዋቂ ሳሚነት መፍትሄው ቀውስ፣ መድሃኒቱ መርዝ እየሆነብን ካለንበት ዘመን ለመድረሳችን ዛሬም ከድሮ የባሰች የመሆኗን እውነት ለመረዳት ሰው መሆን እና በአካል ዘንድሮን ኖሮ ማለፍ ይበቃል።

እኛ "የአባቶቻችን ልጆች ነን!" ለማለት የሚያስደፍር ሞራላዊ ጥንካሬ የለንም። የተሻልን መሆናችንን የሚያስረዳ አዲስ ማንነትም መፍጠር አልሆነልንም። ይህም ቢሆን ራሳቸውን ጨምሮ በአንዱ ጭነት ላይ ቁልል የመከራ ጭነት ከሚደራርቡብን ጨቋኝ ጌቶቻችን እናት የሚወርድ አይደለም። ይሁንና ወቀሳ ብቻውን መፍትሄ ሊሆን ባለመቻሉ ከመከራችን የሚገላግለን አዲስ ዕይታ ያስፈልገናል።

በምንም ስሌት ቢሆን ለዛሬ ችግሮቻችን ፊታችንን ወደኋላ በማዞር ብቻ የተሟላ መፍትሄ እናገኛለን ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ትናንት የዛሬ ችግራችንን የምንፈታበት የመፍትሄ ቁልፍ በክብር የተቀመጠበት ካዝና አድርጎ ማሰብም ብዙ አያስኬድም።እርግጥ ነው የዛሬ አይታችንን በመቅረፅ ትናንት ትልቅ ድርሻ ይይዛል። ለዛሬ መፍትሄ ፍለጋ መንደርደሪያ ቁልቁለት የሚሆነውም በዚህ





የተነሳ ነው።ግን ደግሞ ሚዛን እንዳያስቱን እንዲሁም እሱን ብቻ በማለም አቅምና ጉልበታችን ጨርሰን ከዛሬ ጋር ሳንገናኝ እንዳይመሽብን መጠንቀቅ ያሻናልና እንንቃ።

በስሜት ሳይሆን በእውቀት ብርሃን የዕይታ አድማሳችንን በማስፋት ለችግሮቻችን የመፍትሄ አማራጮችን ለማመንጨትና ተግባራዊም ለማድረግ መትጋት ያሻናል።

በቀጣይ ምዕራፎች የሚቀርቡት ጽሁፎችም ለዚህ ድምር ሀሳብና ጉዟችን ደጋፊ ስንቅ በመሆን አንዱ ጥያቄ ከሚወልደው መልስ ስር የሚበቅለውን አዲስ ጥያቄ በማንሳት የማንነት ፍተሻው ይቀጥላል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## መግቢያ

የኃይልና ስልጣን፤ የእርካብና የመንበር ታሪክ ከሰው ልጅ ውስጣዊ ማንነትና ማህበራዊነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ሰዎች በጋራ በሚሆኑበት ጊዜና ቦታ የመሪና የተመሪ ግንኙነት ተፈጥሯዊ በሆነ ሂደት በራሱ ጊዜ እንደሚጀምር ጥናቶች ያመላክታሉ። ከትንሹ ቡድን ፣ለምሳሌ ከቤተሰብ ጀምሮ ወደ ህዝብና ሀገር የሚዘረጋው የመሪ - ተመሪ ግንኙነት በጊዜ ሂደት በባህሪው የተለያየ መልክና ቅርፅ በመላበስ እንደ ሁኔታውም እየተቀያየረ አሁን ከምንገኝበት ምዕራፍ ደርሷል። የመምራት፣ መመራት የጽንሰ ሀሳቡ ተፈጥሮ መሠረትም ይኸው ነው።

‹እርካብ› ረከበ፣ ወጣ ከሚለው አረብኛ ቃል የመጣ ሲሆን ከፈረስ ጀርባ ኮርቻው ላይ ለመውጣት በእግር አውራ ጣት ተረግጦ ጋላቢ ከኮርቻው ላይ ለመደላደል ረግጠው የሚፈናጠጡበት መሰቀያ ነው። ‹መንበር› ደግሞ ወንበር ለሚለው ቃል ወይም ሀሳብ አቻ ፍቺ ነው ብንል ልክ ተደርጎ ይወሰዳል። ለምሳሌ ሊቀ-መንበር ማለት ባለ ወንበር፣ የጉባኤ አለቃ እንደ ማለት ነው። ስለዚህ በየትኛውም የስልጣን ደረጃ ላይ በሚገኝ ወንበር ላይ ለመውጣት ወይም ለመሠየም እርካብን ረግጦ መሆኑን ልብ ይሏል። የስልጣንን ወንበር የሚያስገኘው ኃይል ነው። ኃይል የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ግንኙነት ዋነኛ ቁልፍ ሞተር ሲሆን የዚህ ሞተር አይነተኛ ግብ ደግሞ በሌሎች ባህሪ ወይም በሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ በማሳረፍ አዎንታዊ አለያም አሉታዊ ለውጥ የሚያመጡበት መሳሪያ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ስለዚህ ከመሪው በፊት ኃይል ይቀድማል። ነገር ግን ያለ መሪ ኃይል ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም። ስልጣን በማህበረሰብ እርከን በግልፅ የተቀመጡ ማህበራዊ ኃላፊነቶችን ለመወጣት እርካብን ረግጠን መንበር የምንቆናጠጥበት መንገድ ነው።

የርካብና መንበር መመላለሻ መንገድና ትርጓሜ በሁለት ግዙፍ ፅንፎች የተወጠረ መደላድል ሆኖ እናገኘዋለን። በአንድ በኩል ስልጣንን፣ ህብረተሰብንና አገርን ለማገልገል የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙበት ወገኖች የመኖራቸውን ያህል በሌላኛው ጫፍ ሥልጣንን የግል ጥቅምንና ክብርን ከሌሎች በላይ ለማስቀደም የሚንጠላጠሉበት መሰላል አድርገው የሚቆጥሩት ራስ ወዳዶችም ከነዚህ ቅኖች የሚልቅ ቁጥር ያላቸው የመሆናቸው እውነታ የነባራዊው ዓለም ነፀብራቅ ነው። እነዚህ በሁለት ፅንፍ የሚቀመጡና፣ ከሂትለር እስከ ጋንዲ፣ ከኢዲያሚን እስከ ማንዴላ ድረስ የሚሰመሩ አይደረሴ ርቀቶችን በመታዘብ ደግሞም ለኑግያቸው በመስጋት 'ምናልባት በዚህ መሃል ሚዛኑን የጠበቀ መንገድ ይኖር ይሆን ወይ?!' ብለው ሲጠበቡ ውለው፣ ሲጠበቡ የሚያድሩ ብዙዎች ናቸው። በዚህ መጽሀፍ ለመግለፅና በዜጎች ልብ ውስጥ አድምቆ ለማተም፣ እትጥም ነፍስ እንዲዘራ ለማድረግ የተከተበው ዋነኛ ቁምነገርም ከዚሁ የሃሳብ ባህር የተቀዳ በቅንነት የምንፀበልበት ምንጭ ለመፍጠር ነው።

መፅሃፉ በርካብና መንበር ጉዞ፣ በቆይታና መደላድሉ እንዲሁም በመንሸራተቱ ቁልቁለት ዙሪያ ዓለም አቀፍ ተጨባጭ አተያዮችንና አከራካሪ ፍሬ ጉዳዮችን ከማንሳት ጀምሮ ኃይልና ስልጣንን በመተንተን የዘመናችንን ሥጋትና ጥሪ ይዘረዝራል።በዝርዝሩም መነሻ ሥጋትና ጥሪን አንጥሮ መጋፈጥ የምንችልበትን ዕውቀታዊ ሥንቅ ሰራሥ ዜጎች ሊያቀብል ይሞክራል። ከጥንቱና ከልማዳዊው የጥልፍልፎሽ አዙሪት «ሳትቀደም ቅደም» ወይም «ለምሳ ሲያስቡህ ለቁርስ አድርጋቸው» ከሚል ኋላቀር ዕይታ ወጥቶ፣ ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ከርዕዮተ ዓለማዊ ቀኖና በተለየ፣ በአዲስ ዕይታ፣ በፍልስፍናዊ ለዛ፣ ከአገር፣ ከርካብና መንበር መንፈስ ጋር





በማገናኘት የተግባር ልምድን ለማጋራት ታልሞ የተዘጋጀ ነው። መፅሀፉ።

በመቅድሙ ላይ እንደተመለከተው ሕዝባችን ገገርዎቹ በጫኑበት የመከራ ቀንበር ትከሻው ከመጉብጥ አልፎ በተነጠቀው የነገ ተስፋ ጫንቃው ደድሮ እንደባይ አግር ንቃቃት ማውጣቱ ያደባባይ ሚስጥር ነው። ጉዞውም ሁሌም ከድጡ ወደ ማጡ ሲሆን በቀውስ አዙሪት ሲሽከረከር ዘመናት ተቆጥረዋል። ያም ሆኖ ቀስ በቀስ በሂደት እየሰጠመ ካለበት የጨለማ ባሕር በመውጣት ብርሃን ማየት ይመኛል።ለዚህም በሽከሙ ላይ ተጨማሪ ሸከም እንዳይጫንበት ዘወትር ይፀልያል። ህልው የመሆን የሰው ልጅ ጥልቅ ሚስጥር ከማይነጥፍ ጽኑ ተስፋ ጋር በመንፈስ ተሰናስሏልና አሁንም ወገን ተስፋ ያደርጋል፤ "መቼስ ተስፋ መቁረጥ ነው..." እንዲል ሎሬቱ ጸጋዬ ገብረ መድህን፣ እንዳለመታደል ሆኖ ታዲያ ሕዝባችን በተለይም ወጣቱ ምኞቱ ቅዠት ሆኖ የተደመደመበትን እንጂ ፍሬ ከሚሰጥበት አጋጣሚ ጋር መገናኘት ከራቀው ዘመናት አልፈዋል።

የጣሊያኑ የህግ ሊቅና ፈላስፋው ሲሰሮ፣ ታሪክን ስለማወቅ አስፈላጊነት ሲናገር፣ "እርሱ ከመወለዱ በፊት ስለነበረው ታሪክ የማያውቅ ማንኛውም ሰው እንደህፃን ይቆጠራል" ብሏል። ታሪክን ማወቅ ትናንትን በከፋ መልኩ ላለመድገም ትምህርት የሚገበይበት ምቹ የልምድ መሸመቻ ገበያ ነው። በነፍስና ሥጋ እልፎ እልፎም እየቆረቆረን የምንጓዝበት መንገድ እንዳንዴም ተደላድለን እረፍት የምንወስድበት ባለ ጥላ አፀድም ነው ማለት እንችላለን።

እስከፈውና እሳዛኙ እውነታ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ታሪክ ተደላድሎ ማረፊያ አፀዳችን ከመሆን ይልቅ የሾህ መንገድነቱ የሚልቅ ይመስላል። ለራሷ ለውዲቷ ሀገራችንም ቢሆን ታሪክ ጌጧ ብቻ ሳይሆን ሸከሟም ጭምር ነው። ጉያዋ ቀዝቅዞ፣ ብርሃኗ ደብዝዞ እንደደጋን ጎብጣ ከምናገኛት የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጉስቁል ገላ ላይ የምናነበው የቅኔ እሻራ ይኸንኑ መራራ ዕውነት ይመሰክራል፡



t.me/OLDBOOKSPDF

፡ ሀገሬ፣ አሁን የምትገኝበት ድንቁርናና ችጋር፣ ሠላም ማጣትና ኋላቀርነት ምክንያቶች ሁሉ የሚቀዱት ከእርሱ 'ታሪክ' ከሚባለው ጥልቅ የትላንት ባህር ውስጥ እንጂ ከሌላ ከየትም ሊሆን አይችልም፣ ፡ ...ከዚያው ነው፣ በረከታችን ከመሆን ይልቅ መርገምት ሆኖ ከተጣባን ከእድሜ ጠገቡ የመከራችን ኩሬ፣ በአንድ ቃልም ከታሪካችን ተብሎ ይጠቀለላል።

በዘመናችን የርካብና መንበር መመላለሻ መንገድ የተጓዙት ጨካኝ መሪዎቻችን በጊጡ እየደመቁ የህዝቡን ሸክም ግን አብዝተው እና አጠንክረው ጫንቃው ላይ ቆልለው በማለፋቸው፣ ስልጣንም በኃይል እና በጉልበት እንጂ በፍቅርና በእውቀት የሚመላለሱበት ስላልነበር እርሱም ሳያንስ ይህ ቅንነት የታጣበት መንገድ በድንቁርና ታጅሎና በስውር ደባ ተጠላልፎ ዘመናትን እንዲሻገር በመፍቀዳቸው፣ በግሪክ አፈ ታሪክ ውስጥ ቁጥኝ ድንጋይ ከተራራ እግር ሥር ወደ ተራራ እናት እድሜ ልኩን እንዲገፋ በአማልክት እንደተፈረደበት ምስኪን ዜጋ እኛ ኢትዮጵያውያንም የተጫነንን የታሪክ ቋጥኝ ሥንገፋ ዘመናት ተቆጥረዋል። ከተራራው እግር ሥር ያነሳነውን ቋጥኝ ከተራራው ጫፍ በታላቅ ሲቃይ አውጥተን አደረስን ብለን ለአፍታ እንኳ እረፍት አግኝተን ልባችን ሳይሞላ ድንጋዩ ወደነበረበት የተራራ እግር ስር ተንከባሎ የኋሊት እየተመለሰ ይሄው ዘላለም ዓለማችንን ከተራራው ጫፍ ተደላድሎ የማይረጋ እና አፎይታ! የማይሰጥ የመከራ ቋጥኝ ስንገፋ አለነው።መኖር ከተባለ።

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ የዘመናችን ትውልድ ልቡ ከዚህ በላይ መገፋትን፣ ጫንቃው ከዚህ በላይ መጫንን ፤ ከንዱ በተራራ እናት ከማይረጋ አለት ጋር መዋደቅን ማስተናገድ በቃ! የሚል መንፈሳዊና አካላዊ ዓቅምን የታደለ አይደለም። በመሆኑም በእርካብና መንበሩ መመላለስ የሚሻ የዚህ ዘመን ሰው በሙሉ ከዘመኑ ጋር አሰላለፉን ማሳመር ይገባዋል። ከዘልማዳዊው የርካብና መንበር ሰሳቢ ወጥቶ በጊጡ አብሮ ለማጌጥ፣ ከጭነቱም አብዝቶ ለመሸከም ጫንቃን ማዘጋጀትም ያስፈልጋል። ለዚህ የተቀደሰ ተግባር በአካልም





በመንፈስም ራስን ለማዘጋጀት እርቆ ማስተዋልን ገንዘቡ ያደረገ፣ ቆራጥ፣ ብልህና አስተዋይ መሆንን ይሻል። ከማንንምና ከምንም ነገር በላይ ራስን ለአገልጋይነት መሞሸርና በፈቃድ መስጠት የውዴታ ግዴታ ይሆናል። ለዚህ መሰሉ የተቀደሰ ተግባር፣ ሰብዓዊነትን ለተላበሰ የእውቀት ሙሽርና ሁሉም ራሱን ያዘጋጅ ዘንድ ይህ መፅሀፍ በጃችን እንዲገባ በማድረጉ ደራሲው የዜግነት ኃላፊነቱን እና ግዴታውን ተወጥቷል።

መልካም ንባብ!!

t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል አንድ

*"ችግሩን በፈጠረው አስተሳሰብ፣ ችግርን መፍታት አይቻልም"*

አልበርት አንስታይን

የአበው ውብ ብሂል...

ከችግር አላቆ መፍትሄን ቢጠራም

እሾህን በእሾህ ለችግር አይሰራም።

እናም...

መንገዱን ለውጦ

ሌላ ሀሳብ ለማዝመር

ልብ ካልቆረጠ... ከሆነ ስስታም

በችግር አምጪ ሀሳብ

ችግሩ አይፈታም።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አንድ

## የዘመኑን ሥጋትና ጥሪ መጋፈጥ

ተምሳሌት (metaphor) በሰዎች ዘንድ በቀላሉ ግንዛቤን ለመፍጠር የምንጠቀምበት አይነተኛ መንገድ ነው። ከዓለም እንዲሁም ከኢትዮጵያ ጋር በቀላሉ የሚመሳሰል ተምሳሌት ጥቀሱ ቢባል አውቁ ፀሃፊ፣ ተውኔት የዊሊያም ሼክስፒር ስራ ከሆነው ከሐምሌት መስተካከል የሚችል ጥበባዊ ስራ ማግኘት እጅጉን ከባድ ነው። ትያትሩ ከገሀዱ ዓለም የተቀዳ እና እሱት ለነፍስ የሚያሳይ ሁነኛ ስራ ነው። በቴአትሩ መጨረሻ፡ በሁሉም ዘንድ ጭካኔ ሰርጾ እርስ በእርስ ይጫረሳሉ። ታማኝነት ቦታውን ሲይዝ፣ መጥፎ የሰሩት እርስ በእርስ ይተላለቃሉ። በጊዜ ቆይታ ከስተቶች ልማድ ሆነው በግልፅ ይተገበራሉ። እውነት ተጣማ ሁኔታን እንድትመስል ይደረጋል። እውነታን አፍርሶ በመገንባት እንደገና ከሀሰት ጋር ያመሳስሏታል። ትራጀዲው ይቀጥላል፤ አይቀሬው ጉዳይ ግን ተመልሶ ይመጣል፣ አይቀርም።

ሰው በራሱ ዓለም በሰመመን ይሰምጣል። ክስተቶች እርስ በእርስ እየተደጋገፉና እየተመጋገቡ ወደፊት ይጓዛሉ። በዚህም ሁኔታ ምንም ነገር ማመን እራስን ማጥፋት ይሆናል። ተከታዮች ፍላጎታቸውን ያልፋሉ። በውጤቱም ስብዕና ማንነቷ ተገፎ ሌሎች እንዳሻቸው የሚዘውሯት ተጎታች ጋሪ ትሆናለች። መሪዎች በየጊዜው በሚያመነጩት አመክንዮና ራስን ማሳመኛ ዘዴ ተስፋ ከመቁረጥ ይድናሉ ወይም የዳኑ መስለው ይታያሉ። በሂደትም





የሁኔታው አካል ይሆናሉ። የተፈጥሮ ዕውቀት ይታወራል። ስልጣንም የባይተዋርነት ምንጭ ይሆናል። ምንም እንኳ ጨለማው ገለልተኛ የነበረ ቢሆንም መጨረሻ አካባቢ ግን አጥቂ ይሆናል። በትውና ውስጥ ሌላ ትውና… ይቀጥላል።

በትክክል የታሪካችን ወንዝ መፍሰስ የጀመረበትን መነሻ ዘመን ከወሰድን ኢትዮጵያ ሺህ ዓመታትን የተሻገረ አኩሪ ታሪክ ያላት አገር ናት። በአጭር ምድራዊ ርቀት ከዳሎል እስከ ራስዳሽን የሚቀያየር የአየር ንብረት፣ መልክዓ-ምድር ፣ወንዝና ፏፏቴ፣ ዕፅዋትና እንስሳ ፣ጥንታዊ እምነት ከቱባ ባሕል ጋር አጣምራ የያዘች፣ በተፈጥሮ ለግብርና ተስማሚ መልክዓ ምድር እና የአየር ንብረት የታደለች ሀገር ናት። ከህገሪቱ ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ዜጋ በአምራች ዕድሜ ላይ የሚገኝ ወጣትና ከ27 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በትምህርት ገበታ ላይ ያለባት ሀገርም ነች። ይህንን አምቅ ኃይል ከስራ አጥነት፣ ከኢ-ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ተላቆ ወደ ምርት ቢገባ ለውጥን የሚያቀጣጥል ከፍተኛ የፖለቲካ ኃይል ሊሆን መቻሉ አያጠያይቅም።

ታዲያ ለምን ኢትዮጵያ የዓለም ድሀ ሀገሮች ጭራ ሆነች? የሺህ ዓመታት የነጻነት ጎህ የፈነጠቀባት አገር ስለምን እስከ አሁን በጭቃ ውስጥ ተቀርቅራ ቀረች? ዙርያ ገባችንን እንመልከት። ሀገሪቱ ያላት ጂኦ-ፖለቲካል አቀማመጥ፣ መልከዓምድርና የህዝብ ቁጥር የአፍሪካ የኢኮኖሚ ዋልታ ሊያደርግ የሚችል አምቅ አቅም በውስጡ ያቀፈ ነው። ነገር ግን ዛሬም ሀገራዊ መሠረተ-ልማት መዋቅሮቻችንን ከማሳቀቅ ወደ ሚያስመካ ከፍታ ማሳደግ የሚያስችል መንፈሳዊ ዝግጅት ውስጣችን አልተፀነሰም። ፍቅራችን የበቀልንበትን፣ የተሳሰርንና የተፈተልንበትን የሹሩባ ጉንጉን ከማጠንከር እና ከማስረዘም ይልቅ ውሏችንን የሚያሳጥር ትስስራችንን የሚያላላ ከአድማሳዊ ዕይታ ይልቅ በመንደር ጣጣ የተደፈቀ፣ ከአፀድ ይልቅ ምሽግን ሙጥኝ ማለትን የመረጠ ሆኗል።

ማህበረሰባችን በተቃርኖ ዋልታዎች ላይ ሰፍሯል። የብሄር፣

ሀይማኖት፣ የጾታ፣ የኑሮ ደረጃ ልዩነቶቻችን ስር እየሰደዱ ነው፡፡ አውቀታችን ችግራችንን የምንፈታበት ከመሆን ይልቅ የሌላ ችግር መፍለቂያ ምንጭ ሆኗል፡፡ ዛሬ ሀገራችን ላይ ዋነኛ የጸብ ምንጭ እየሆኑ የመጡት የሀይማኖትና የብሄር ግጭቶች ፊደል ቆጥረው ድግሪ በጫኑ ኢትዮጵያውያን ፊትአውራሪነት የሚዘወሩ ናቸው፡፡ ውጤታማ የምንለው ተቋምም፣ ሥርዓትም ሆነ የዕውቀት ማኀበረሰብ መገንባት አልሆን ብሎን አገልግሎት መስጫ ተቋሞቻችን እያረጁ፣ እየበሰበሱ፣ በአድካሚ ቢሮክራሲ እየተተበተቡ፣ ከአርኪታ ይልቅ የምሬት እና የብስጭት ምንጭ ከመሆናቸውም በላይ የሙስናና የብልሹ አሰራር ቋት ሆነዋል፡፡ የህግ የበላይነት እለት በዕለት ዕየተሸረሸረ ቀጥኖ ሊበጠስ ሲቃረብ የግለሰቦች ህግ አበጦ ይፋፋ ጀምሯል፡፡ መፃፍ ካልደከመን በቀር የችግር ዝርዝሩ አይቆምም፤ ይቀጥላል፡፡ የምንገኝበትን ሀገራዊ እውነታ ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገው የተተበተብንበት ችግር እያልቁ መሆን ብቻ አይደለም፡፡ የከበበን አስፈሪ ሉላዊ እውነታም እንጂ፡፡

ዓለማችን በተለይም አሁን ባለንበት ዘመን እጅግ ብዙ መልካም ነገሮችን እንደመያዟ መጠን ከፊቷ የተጋረጡ ብዙ መሰናከሎችም ዙሪያ ገባዋን ከበዋት ይገኛሉ። ሀገራት ከሀገራት ጋር የሚያደርጉት ግጭት፣ የት ይደርሳሉ የተባሉ የግዙፍ ተቋማት ውድቀት፣ እንዲሁም የፖለቲካ ሽኩቻ ለዓለማችን ራስ ምታት ከሆኑ ሰነባብተዋል። በተቃራኒው ደግሞ በሰው ልጆች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ውስጥ እጅግ ብዙ ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎች እዚህም እዚያም ፍሬቻቸው ፈንጥቆ መታየትና መለመድ ጀምረዋል። እጅግ አስገራሚው ነገር የሰው ልጆች የስልጣኔ ጥግ ይባሉ የነበሩ ነገሮች እንኳን ከአሰራራቸው እስከ አጠቃቀማቸው ተቀያይረው ዛሬ ኋላቀር ለመባል በቅተዋል።

ይህንንም አስመልክተው ቼክ ሪፐብሊክን እ.ኤ.አ ከ1993 እስከ 2003 በእንደራሴነት ያስተዳደሩት ፀሐፊ ተውኔቱ ቫክላቭ ሃቨል እንዲህ ሲሉ አስቀምጠዋል። "እኔ እንደማስበው ይህ ዘመናዊ ዓለም





ለማብቃቱ ማሳያ የሚሆኑ ጥሩ ምክንያቶች አሉ። ዛሬ ሁሉም ነገር በሽግግር ጊዜ ውስጥ እያለፍን እንደሆን ያሳያል፡፡ አንድ ነገር ሲጃጅና ከግልጋሎት ውጪ ሲሆን በተጓዳኝ ሌላ ነገር በስቃዩ ውስጥ ምጡን ጨርሶ ሊወለድ ይሞክራል፡፡ ይህ አንድ ነገር መስረቱ እየተናደ፣ እየበሰበሰ እና ራሱን እያዳከመ ባለበት ሁኔታ በተቃራኒው ሌላ አንድ ድንቅና ምንነቱ ተለይቶ ያልታወቀ ነገር ከፍርስራሹ ስር ፈንቅሎ ለመውጣት እየሞከረ ነው፡፡"

ይህ የሥነ-ሥርዓትና የመረጋጋት እንቅፋት በየትኛውም ጊዜ የሚቀረፍ መሆኑን ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎችን አልፎ እየወጣ ያለውን የሰው ልጅ አሸናፊነት መመልከት ብቻ በራሱ በቂ ነው። አስራኤላውያን፣ የሰው ልጅ በቂ ውሃ በማጣት ምክንያት በረሃብ ማለቅ የለበትም፤ ብለው ዝናብን እንደፈለጉ ለማዝነብና ለማቆም የሚያስችል ቴክኖሎጂን ሰርተው ተግባራዊ ሊያደርጉት የመቃረባቸው እውነታ ላነሳነው ሀሳብ አንድ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። የዘመናችን ትልቁ ስጋት ሀገራት እርስበርስ የሚያደርጉት ግጭት ብቻ ነው፤ ተብሎ የሚታለፍ አይደለም። ምክንያቱም 'ግጭት' አሸናፊና ተሸናፊው የማይለየምበት፣ አትራፊና ከሳሪው የማይለይበት መሆኑን ዓለማችን ከተረዳች ሰነባብታለች። ለዚያም ነው፤ በየቦታው ያሉ አለመግባባቶችን በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት ተቀዳሚና በላጩ ምርጫ በማድረግ ሙከራዎችና ጥረቶች እየተደረጉ ያሉት። በአንፃሩም ከአንዳንድ አካላት ዘንድ የሚንጸባረቅ አጥፊ አስተሳሰብ እንዲሁም በህብረተሰቡ የጋራ ጉዳይ ላይ ፈላጭ ቆራጭ በመሆን ውሳኔ ሰጪ የሆኑ አካላት በዓለማችን ላይ ከፍተኛ የግጭት ሥጋት ጥላውን እንዲያጠላ ተጠቃሽ ምክንያት ሆነው እናገኛቸዋለን።

ትርታው ከፍ እያለ የመጣውን ግፊትና በአንጻሩ እየቀነሰ የመጣውን ነጻነት ከተረዱ በኋላ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ተወልደው የሚያድጉበት፣ በዓለም ምጣኔ ሀብታዊ ሥርአት ላይ ትርጉም አዘልና ፍትሀዊ የሆነ የነቃ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው በሚያደርግ ሁኔታ ውስጥ እንዲያልፉ የሚጋብዘውን የዚህ ተመሳሳይ ሥርዓት

ሌላ ገፅታ በጉልህ ታትሞ ይገኛል። አብዛኞዎቹ የዓለም አንቅፋቶች ድህነትን ተገን አድርገው የተወለዱ በመሆናቸው ድህነት ዓለማችን ላይ ከፍተኛ ሥጋትን መፍጠሩ አልቀረም። ዓለማችን ይህንን ክስተት ተረድታ አልባት ከመስጠት ይልቅ ለባለጸጋዎቹ አንቀላፏን ለድሆቹ ደግሞ ኩርፏን በመስጠት ዕድልና በረከቷን ቀን ለሞላላቸው እንካችሁ ማለቷን ገፍታበታለች።

ምንም እንኳን አንዳንድ ሀገራት ህዝቦቻቸው የበለጸጉ ቢሆኑም በተቀረው ዓለም የሚገኙ የሰው ልጆች ግን ድህነት በሚባል ሠንሰለት ተጠፍረው፤ አሰቃቂ በሆነው የርሃብ፣ የዝቅተኝነት፣ በይሉኝታ የመሸበብ እና በጠባቂነት አለንጋ እየተገረፉ፤ የማይሽር ቁስላቸውን እያስታመሙ፤ የማይፋቅ ጠባሳቸውን እያስታወሱ ፤ የማይታበስ ዕንባቸውን እያፈሰሱ እና ነገን በተስፋ እያለሙ፤ ሲነጋ ሲል በሚጨልም ፅልመት ውስጥ አንገታቸውን ደፍተው እናገኛቸዋለን። በአጠቃላይ የምንኖርባት ምድር 80 በመቶ የሚሆነውን ህዝቧን በድህነት ጫንቃውን አጉብጣ የእንፉዳይ እያስኳተነችው ትገኛለች።

ቁጥራቸው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የዓለማችን ህፃናት ምኞት በሚነሱና አሰቃቂ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እየተሰቃዩ የሚገኙ ከመሆናቸውም ባሻገር በየቀኑ ህፃናት ለሞት መዳረጋቸው ከሰው ልጅ አሳዛኝ ክስተቶች መካከል ተጠቃሹ ነው። ይህንንም ነጥብ የሚያረጋግጡ መሰረታዊ ጭብጦችን በማሳያነት ለማቅረብ ልሞክር።

- በግብርናና በምግብ ምርት አቅርቦት አስተማማኝ ደረጃን ለመጨበጥ ከፍተኛ ሃብት የሚታፈስበት ሥርዓት ያለ ቢሆንም በሌላም በኩል በህይወት የማያቆይና ዝቅተኛ ጥራት ያለው እንዲሁም አካልንም ሆነ አካባቢን ለብክለትና ጉዳት የሚዳርግ ምግብ ማምረት የቀጠለበት ሁኔታን ልብ ይሏል፤





- የትምህርት ሥርዓትን ለማጎልበት ቀላል የማይባል መዋዕለ ነዋይ የሚፈስ ቢሆንም የሰዎችን መጻኢ እድል የሚወስኑና ቅርፅ ለማስያዝ የሚያስችሉ ትምህርት ቤቶችን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን እና የትምህርት ሥርዓትን መፍጠር አለመቻሉን በተጨባጭ መታዘብ ይቻላል፤

በእጭሩ ባነሳነው ሀሳብ ላይ ተንተርሰን ጥቂት ገፋ እናድርግና ከሌላኛው ፅንፍ ጋር እያነፃፀርን መመልከታችንን እንቀጥል። ዓለም ለአንዱ ፊቷን ለሌላኛው ጀርባዋን ሰጥታ የምናገኛት መሆኑ እሙን ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለማችን ህጻናት የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በምግብ እጦት እንደ ቅጠል በሚረግፉበት አለማችን ውስጥ ከዚህ ትዝብታችን ብዙም ሳንርቅ ምግብ ተትረፍርፏቸው ወደ ገንዳ እና ጉድጓድ የሚደፉ አያሌ ምዕራባውያን አገራት እንዳሉ መዘንጋት አይኖርብንም።አሁኑ ወደ እኛም እየመጣ ያለበት ትዕይንት ይስተዋላል፡፡

ዓለማችን እስከ ፕላኔት ማርስ ድረስ መጓዝ የቻሉና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የተማረ ኃይል ቢኖራትም ከላይ የተወሱትን ክስተቶች የሚሸፍና እንደ ልባሽ ጨርቅ አውልቀን እንጥል ዘንድ ያስቻሉ ጠቢባንን ግን ማፍራት አልተቻላትም። ለሰው ልጆች ችግር መፍቻው ቁልፍ በሰው እጅ የመሆኑን ያህል ችግሮቹን ከናካቴው ለማስወገድ እንዳይቻል ካደረጉ ምክንያቶች አንዱ ራሱ ሰው ነው። ገሚሱ ለችግሮች መፍትሔ ሲያፈላልግ ገሚሱ ደግሞ የመፍትሔው ማርከሻ ችግር ማፈላለግ ላይ ተጠምዶ ይውላል። የኮምፒዩተራችን ቫይረስም ሆነ እሱን መከላከያው ጸረ ቫይረሱ የሚሰራው ያው በኛው በሰዎች አይደለምን? አበው ብሬ ካራጁ! ፣ እንደሚሉት አሌታሽና አስሌታሹ፣ ገዳይ እና ሟች፣ አጥፊ እና ጠፊም አንድ ላይ በመሆናቸው ችግሩን የመቅረፍ ስራ ያው ከ«ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ» የዘለለ አልሆነም።



t.me/OLDBOOKSPDF

አሁን ላይ ዓለማችን በብዙ ጥልፍልፍ ውጣውረዶችና በተለይም በፖለቲካና በሀይማኖት አክራሪዎች ሳቢያ የሥጋት ቀጠና ከመሆን ከፋ እጣ ፈንታ ጋር ለመኖር ተገድዳለች፡፡ ምንም እንኳን የሽብርተኝነት ህግ ቢወጣም፤ ከፍተኛ በጀት ቢመደብ፣ በየአቅጣጫው ጥበቃው ቢጠናከርም፤ ከእነዚህ አካላት በሚሰነዘሩ ጥቃቶች ብዙ ቦታዎች ላይ ሰዎች መሞታቸው ቀጥሏል። ብዙዎች የወጡበትን ዓላማ ሳያሳኩ በወጡበት ቀርተዋል፤ ብዙዎች የሚወዱትን ወዳጅ ዘመድ ተነጥቀው ልባቸው ተሰብሯል፤ ብዙዎች በየቀኑ ከቤታቸው መውጣታቸውን እንጂ ወደ ቤታቸው መመለሳቸውን እርግጠኛ መሆን ተስኗቸዋል፤ ብዙዎች ነገን እሾግረው ቢያልሙም ምንጩን በቅጡ ባልተረዱት የሽብር ጥቃት የናፈቁትን ነገ ማየት ሳይችሉ ዛሬ መጨረሻቸው ሲሆን በቅቷል፡፡ - የሞት ፅዋን ከመጎንጨት ያመለጡ ተሰፈኞችም ቢሆኑ ከመኖር ወድያ እና ከመሞት ወዲህ ተጥለው የልዕለ ተፈጥሮን ረድኤት ይጠብቃሉ፤ ብዙዎች ቤት ንብረታቸው ወድሞ ባልተጠበቀ ሁኔታ ኑሯቸው ተመሰቃቅሎ አሁን ብቻ ለሚኖሩበት ጊዜያዊ መጠለያ ካምፕ፣ ግሚሱ ለባይተዋርነትና ስደት፣ የተቀረው ደግሞ ሰብዓዊነት ለራቃቸው ነፍሰ በላዎች የገቢ ማስገኛ አዲስ የስራ ዘርፍ መፍጠሪያ በመሆን የመከራ እና ሰቆቃ ህይወት መግፋት ዕጣ ፈንታቸው ለመሆን በቅቷል፡፡

በቀድሞ ጊዜ ዓለማችን ትታወቅባቸው የነበሩ በጎም ሆነ መጥፎ ነገሮች ዛሬ መልካቸውን ቀይረዋል። ማህበራዊ መስተጋብሮቿ ሁሉ አዲስ አቅጣጫን ይዘዋል። እነዚህ ለውጦች ባህላዊ እና ዘመናዊ በሚባሉ ሁለት ሚዛኖች መሀል እየተናጡች ትገኛለች። ምንም እንኳን ዘመናዊነት ይዞ የመጣቸው ብዙ መልካም ነገሮች ቢኖሩም ያጠፋቸው ነገሮችም እንዳሉ ብዙዎች ይስማማሉ። በምዕራቡና በሌሎች አገራት የተነሳው የአክራሪነት ፅንፍ፣ በሚቀነቀነው የአስተሳሰብ አቅጣጫ እና በለውጡ የተማረሩ አካላት መኖራቸው አንዱ ማሳያ ነው። እነዚህ አካላት፣ ለዓለማችን ቁሳዊ አምልኮት እንደማያዋጣ ሽንጣቸውን ገትረው ይሰብካሉ፤ ለዘመናት አብሮን የቆየ ክብራችን፣ የአኗኗር ዘይቤያችን እንዲሁም የህይወት





ትርጉማችን የማንነታችን መገለጫ በመሆኑ ወደ ቀደመው የህይወት ዘውጋችን መመለስ እንደሚኖርብን ይመክራሉ፤- 'ዘመናዊነት' እነዚህን ማንነቶች እየቀማን በመሆኑ 'አንፈልገውም' ሲሉም ይደመጣሉ።

'ዓለማችን አንድ መንደር ትሆናለች' የሚለው የአንድ ወቅት ሃሳብ አሁን አሁን እውን እየሆነ መጥቷል። በመሆኑም የግለሰብም ሆነ የአገር ዕጣ ፈንታ የዓለም አቀፍ ተፅዕኖ ሰለባ መሆኑ እርግጥ ነው። በዚህ ዘመን በተለይም ስልጣኔዋል የሚባሉት የምዕራባውያኑ ባህልና አስተሳሰብ በዓለማችን ላይ ከፍተኛ አሻራውን እያሳረፈ መምጣቱ ግልጽ ነው። በተለይም ባላደጉ ሀገራት ውስጥ የሚገኘው ወጣቱ ትውልድ የማያውቀውን ሀገር ናፋቂ ከመሆኑም በላይ የራሴ የሚለውን ደግሞ እንዲጠላ እያደረገው መጥቷል። በራስ ማንነቱ የማይኮራ፣ ጭራሽ ማንነቱ የሚያሳፍረው፣ እራሱን ለመደበቅ የሌሎችን ጭንብል የሚያጠልቅ፣ እይን እያለው በዳበሳ የሚኖር ወጣት ቁጥር ጨምሯል። አካሄዱ፣ አለባበሱ፣ አነጋገሩ፣ የአኗኗር ዘይቤው፣ ስላምታ አሰጣጡ፣ ለነገሮች ያለው እይታ ሁሉ... ከነዚህ ሀገራት የፕሮፓጋንዳ ማሽን የተቀዳ እንጂ በውል እንኳን ያልተኮረጀ ግማሽ ልጮ ግማሽ ቁንጮ አይነት አጉል አዚም እየሆነ መጥቷል። ይህ ሁኔታ አፍሪቃዊነትን አጠልሽቶ ምዕራባዊነትን ጭፍን የእድገት እና የስልጣኔ መንገድ አድርጎ የሚያሳይ አደገኛ ክስተት እየሆነ መጥቷል። በመሆኑም እንደ አገርም፣ እንደ ዜጋም ማንነትን አስጠብቆ ከሚፈለገው ደረጃ ለመድረስ ብርቱ ትግል ማድረግ ለነገ የማይባል አስቸኳይ የቤት ስራ ሆኖ እንደ ጋሬጣ ከፊታችን ቆሟል፡፡

በሉላዊነት መንደር መጠቃለል ማምለጫ የሌለው ምርጫ በሆነበት በአሁኑ ዘመን ዜጎች ቁልፍ የመወዳደሪያ አካል ናቸው። በዚህ ውድድርም ዘወትር ተገዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ዜጎች ለሀገራቸው የሚኖራቸው ጥልቅ የሆነ ፍቅር፣ ሀገራቸውን የእድገት ምሰሶ ላይ የመሰቀል ፅኑ ፍላጎት፣ በሚያጋጥማቸው መልካም ያልሆነ ምላሽ የማይናድ ቁራጥነት፣ በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆኖ ለመዝለቅ ከቁጭት



t.me/OLDBOOKSPDF

የመነጨ አምቢኝ ባይ ልቦና እና ሰላም ተንሳሽነታቸውን የሚያበረታላቸው አጋዥ ነገር በሙሉ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የሉላዊነት ሐሳብ ከማንነታችን ጋር ያለውን ርቀትና ተቀራኖ እንዲያሳይልን በዕውቀቱ ስዩም የተቀኘትን አንድ ግጥም ልምዘዝ፦

**የጋራችን ዓለም የጋራችን ሰማይ**

**የብቻችን ህመም የብቻችን ስቃይ፡፡**

የኢንዱስትሪ አብዮትን ተከትሎ ልዕልና ያገኘው የካፒታሊስት ሥርዓት የዓለማችን ብቸኛ የኢኮኖሚ ርዕዮት አማራጭ ተደርጎ እንዲወሰድ በተጨባጩ ዓለም ያስመዘገባቸው ውጤቶች ቢረዱትም ዛሬ ከሚገኝበት ምዕራፍ ለመድረስ ከፍተኛ የሰው ህይወት መጥፋትና የንብረት ውድመቶችን ማስከተሉ ይታወቃል፡፡ ዓለምን ዛሬ ከአድማስ አድማስ የሚንጣት የመከራ ሽል የዚሁ ርዕዮት ነቀርሣዊ ጽንስ ከመሆን አይዘልም፡፡ በመሆኑም ይህ ርዕዮት በውስጡ የነገሱትን አጥፊ ግድፈቶች በስልጡንና ሰብዓዊ አካሄድ አጥርቶ ወደላቀ ከፍታ ይሸጋገራል? ወይስ ልክ እንደቀድሞው በማይፈቱ ቅራኔዎች ተደነቃቅፎ ወደማይቀረው ሕዝባዊ አመፅ፣ አውዳሚ 'ጦርነት' ይሸጋገራል? አለበለዚያስ 'ጥበብና አስተዋይነት' ተላብሶ የጋራ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ' ቦታውን ያስረክባል? የሚለው ጥያቄ ሲደርቅ እንደተዘጋጀ እርጥብ የፍየል ቆዳ በሁለት ፅንፍ ዓለምን ወጥሯታል፡፡

ይህ ሁኔታ ዓለማችን ከሁለቱ ፅንፎች አንደኛውን መምረጥ እንዳለባት ያሳያል፡፡ የመጀመሪያው አማራጭ 'ልዩነትን በጥበብ ማስታረቅ' አልያም 'ባለመስማማት መስማማት' ሲሆን፤ ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ 'ዓለም በኔ አመለካከት ዙሪያ መሽከርከር አለባት' ብሎ ሶስተኛውን የዓለም ጦርነት ማስነሳት ነው፡፡

በብዙዎቻችን ልብ ውስጥ ተስፋ መቁረጥ ተደላድሏል፡፡ ከወጣነው የድል ከፍታ ይልቅ የሥመጥንበት የመከራ ጉድጓድ ጥልቅ ሆኖ





ይታየናል፡፡ ነባሮቹን ችግሮች አስወግደን ሳይሆን ቆጥረን ሳንጨርስ ሌላ አዳዲስ ችግሮች በላያችን ይጫናሉ፡፡ በእጃችን ያለውን የመፍትሄ ቁልፍ ማየት እስኪያቅተን ድረስ በዙሪያችን መከራና ችግር እንደተራራ ተቆልሏል፡፡ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ሕዝብ እና ሠብዓዊነት የሚለው ተፈጥሯዊ ትስስር በድንገት ሳይሆን ታስቦበት እንዲፈረካከስ የተደረገ ይመስል መበታተኑ አይሏል፡፡ በወዲህም ሆነ በወዲያ ከዝምድና ይልቅ ጠላትነት ነግሷል፡፡ በተለይም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወታችን ውስጥ የጋራ ተጠቃሚነታችንን የሚያረጋግጥ የኃላፊነት ቀንበር የተጫኑባቸውና ለርሱም ተፅእኖ መፍጠሪያ ኃይልና ሥልጣን በጃቸው የጨበጡ ቀዳሚዎች፣ አስተዳዳሪና መሪዎች ለአፍ ካልሆነ በቀር በተግባር ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዋል፡፡ በሙሉ ዓይን ከችግራችን ጋር መተያየት አቁመዋል፡፡

በዘመን ሂደት ያልተፈታ ችግር በዘመን ሂደት የችግር ካንሰር ይሆናል የሚል አንድ አባባል አለ፡፡ እውነት ይመስላል፡፡ ካንሰር በዘመናዊ መድሃኒት ፈውስ ሊያገኝ ስላልቻለ ተስፋ ቆርጠው የሚቀበሉት ብዙዎች አይደሉም፡፡ በዘመናዊ ሕክምና በማይድን በሽታ የተለከፈ ዜጋ በሕይወት ተስፋ ቆርጦ አይቀመጥም፡፡ ይልቁንም መፍትሄን ከባሕላዊ መድሃኒት ለመፈለግ ወደዚያ ያቀናል፡፡ከሆነለት ሌሎችም የሱን መንገድ እንዲከተሉ ይሰብካል፡፡ ትክክለኛ መፍትሄ ያልተሰጣቸው ችግሮቻችን ዘመን ሲያስቆጥሩ ትክክል ያልሆነን መፍትሄ የችግር መፍቻ አድርገው ቢወስዱ አያስገርምም፡፡ በዚህ ሂደት መወቀስ ያለበት ለችግሩ መፍትሄ ያጣው በሽተኛ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ መፍትሄን የነፈጉት ሐኪሞችም ጭምር መሆናቸው እሌ አይባልም፡፡ውጤቱም የዜሮ ድምር ነው፡፡

የዓለማችን የነፃነት ፋና፤ የዘርና እምነት መቻቻል መሰረት ተደርጋ በምትቆጠረው ሀገረ አሜሪካ ግኝኙነቱን የሚቆርጥ ግንብ እሳንፃለሁ፤ ሀይማኖትን መሠረት አድርጌ ቪዛ ሥርዓቱን እለውጣለሁ፤ ለማለት የደፈረ ፖለቲከኛ መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን

ሁለት መቶ ዓመታት ያስቆጠሩ የፓርቲ እጩዎችን አሸንፎ ለፕሬዝዳንታዊ ዕጩነት ዶናልድ ትራምፕ መብቃታቸው፤ ከዚያም አልፎ ወደ ድል የተሸጋገሩት በዚሁ የተነሳ ነው። ከዚህ መሠሉ ተስፋ አስቆራጭ እውነታ ወጥተን ብርሃንን ለመፈንጠቅ በትናንቱ የችግር መፍቻ ዘዴ መፍትሄ ማግኘት አይቻለንም። በተለወጠ ዓለም ውስጥ ለነባሮቹም ሆነ ለአዲሶቹ ችግሮቻችን መፍትሄ ለመሻት ቀዳሚው እርምጃ የተለወጠ የአተያይ መንገድን መፍጠር እንደሚያሻ ምሁራን ያስረዳሉ። ሰብዓዊነት በትናንትናና ነገ መሀል የሚዘረጋ ድልድይ እንጂ በዛሬ ውስጥ ተለይቶ የሚቆም በድን ሕንፃ አይደለም። በመሆኑም ጥበባዊ ዕይታ፤ በሥጋና ነፍስ መሃል ያለውን የተደላደለ ሚዛን እንደምን የዕለት ተዕለት የሕይወታችን አንድ ገጽታ አድርገን እናስቀጥለዋለን? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል።

'ንድፍን አልቆ ማያ ዕሳቤ' በሚል ርዕስ ሮትማን መፅሄት ላይ የሰፈረው ፅሁፍ እንዲህ ይለናል።

ዙሪያችንን የከበቡት ቁሳዊ ጉዳዮች ብቻ አይደሉም - ፖለቲካዊ ሥርዓትና የኢኮኖሚ ፖሊሲ፤ የሕክምና ምርምሮች የሚካሄዱበት መንገድ ሳይቀር - ሁሉም ነገር ለኢኖቬሽን የተጋለጠ ነው። ተቋማት በዓለም ላይ ዘላቂ ተወዳዳሪነታቸውንና የመሪነት ቦታቸውን ጠብቀው ለመቀጠል ጥራትን፤ የአፈፃፀም ደረጃ እና ዋጋን ብቻ የሚተጉበት ዘመን ተቀይሮ ንድፍ አዲሱ የመወዳደሪያ መሳሪያና ቁልፍ የኢኖቬሽን አራማጅ መሆን ጀምሯል።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የከፍተኛ ትርፍ ምንጩ በከፍተኛ መነሻ ሀብት ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን መገንባት እንደነበር ይታወቃል። የችግር አፈታት መንገዱም በዋናነት ለተለየው ችግር ቁሳዊ መፍትሄ ሠጪ መሳሪያ መፍጠር፤ ተወዳዳሪነትን በዋጋ፤ በጥራት፤ በውጤታማ አመራረት በማረጋገጥ ብቻ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል። በዚህ አቅጣጫ ችግር እየተፈታ፤ ትርፍ እየተገኘ ብዙዎች ሕልውናቸውን አረጋግጠው መዝለቅ ችለው ነበር። ዛሬ ይህን የችግር መፍቻ አቅጣጫ መተግን ብቻውን በቂ አይደለም።





በምርትና አገልግሎቶቻችን ውስጥ የተጠቃሚዎቻችንን ባህል፤ ስጋዊና መንፈሳዊ እርካታን ማስገኘት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የመወዳደሪያ ነጥብ መሆን ጀምሯል።

የውሃ መከፈቻና መዝጊያ በተለምዶው አጠራር ' ቧንቧ' የምንለው የውሃ ላንቃ ተግባሩ ውሃ መከፈቻና መዝጊያ የነበረበት ዘመን ሩቅ አይደለም። ዛሬ ቧንቧ ከመከፈትና መዝጋት ባሻገር ለአይን በሚማርክ የዲዛይን ውበቱ፤ ለመከፈትና መዝጋት ባለው አመቺነት፤ በውሃ መልቀቅ ወቅት በሚፈጥሯቸው ፏፏቴዎችና ለጆሮ በሚያደርሳቸው ድመፆች ጭምር ተፈላጊነቱ ፣ በገበያ ያለው ተወዳዳሪነት የሚወሰንባቸው ታሳቢ መመዘኛዎች ሥራ ላይ መዋል የጀመሩበት ዘመን ነው።በዛሬዋ ዓለማችን ሉላዊነትን ወደፈቀዱት አቅጣጫ የሚዘውሩት ተዋንያን እንደቀድሞው የከፍተኛ ሀብት ባለቤትና ታላላቆቹ ኩባንያዎች ብቻ ሳይሆኑ ነባርና አዳዲስ ዕውቀቶችን መሠረት አድርገው አዳዲስ ምርትና አገልግሎትን የሚያስተዋውቁ ኢኖቬተሮችም ሆነዋል።

በአንድ ወቅት ምርት እንጂ አገልግሎት፤ አገልግሎቱ ከሚሰጥበት ምድር ባሻገር 'አይሸጋገርም ' የሚለው ኢኮኖሚያዊ ንድፈ ሀሳብ ፈጣን እድገት ባሳየው የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተሰውጦ ለአውሮፓና አሜሪካ የስልክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች፤ በሕንድ ምድር የተቀመጡ የሕንድ ኦፕሬተሮች አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። ካናዳ ላይ ሕክምና ለማግኘት ምርመራውን ያካሄደ ታማሚ የተነሳው ራጅ ወይም ኤክስሬይ በሽተኛው ከካናዳ ሆስፒታል ሳይንቀሳቀስ የራጅ ፊልሙ ሕንድ ተልኮ የበሽተኛው ኤክስሬይ በሕንድ ዶክተሮች ተተንትኖ ውጤቱ ከወንበሩ ሳልተነሳው የካናዳ በሽተኛ በውጤትነት ይቀርብ ጀምሯል። በአሜሪካ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት የድንበር ርቀት ሳይገድባቸው የትምህርት አገልግሎትን በዌብ ግንኙነት የአፍሪካን ተማሪዎች ማስተማር ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በርግጥም ያለንበት ዘመን እንደ ቀድሞዎቹ ዘመናት ለአብነትም



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ኢትዮጵያና ጣልያን አንዱ ጦርና ጋሻ ሌላው ደግሞ የጅምላ ጨራሽ መሣሪያ ባለቤት ሆነው የሚፋለሙበት ዘመን አይደለም። ይልቁንም ሁሉም በየፊናው 'ሁሉቱ ብትመታኝ እንዴ' አላጣህም' አይነት ፉከራ የሚያስማበት የድርቅታ ጊዜ ላይ ነው። ሲብሰም መላ ዓለምን በቅጽበት ዶግ አመድ ሊያደርጉ የሚችሉት የኒውክለርና የኬሚካል አቶማቲክ በምብ መኖራቸው የውድመቱን መጠን የቱን ያህል የሠፋና የከፋ ሊያደርገው እንደሚችል መዘንጋት አይኖርብንም።

በሰላም ዙሪያ ምርምር የሚያካሂደው ጆሀን ጋልተንግ ለዛሬው ማህበራዊ መዋቅር መበስበስ መገለጫ የሚሆኑ ምክንያቶችን 'አኖማይ'ና 'አቶማይ' ሲል ያስቀምጣቸዋል። 'አኖማይ' ማለት የባህል (ወግና ልማድ) መጥፋት ሲሆን 'አቶማይ' ደግሞ የማህበራዊ መዋቅር መንኮታኮት ነው። እርግጥ ነው፣ የባህልና የማህበራዊ መዋቅር መሳሳት ለሙብት ጥሰቶች መበራከት፣ ለጥላቻ መንሰራፋት፣ ለሽብርተኛነት እና አጥፍቶ መጥፋት ስር መስደድ እንዲሁም ለእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት እየሆነ ይገኛል። እንደ እምነት አባቶች አገላለጽ ደግሞ ምድር በተፈጥሮ መቅሰፍቶች እንድትመታ መዓትን የሚጠሩ ክስተቶች በዝተዋል። ታዲያ እነዚህ ኩነቶች እያስከተሉ ያሉት ጉዳቶች በእነዚህ ሀገራት ታጥሮ የተቀመጠ ነው ፣ ልንለው አንችልም። ምንም እንኳን መጠኑ ቢለያይም ሁሉም ሀገራት የችግሩ ገፈት ቀማሾች ሆነዋል። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ለማደግ በሚውተረተሩ ሀገራት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ችግር ቀለል ተደርጎ ሊታይ የሚችል አይደለም።

ነገሩ ሁሉ፣ ልክ ቫክሊቭ ሃቨል እንዳስቀመጡት ነው፤ የአንድ ነገር መጀጀትና ከግሊጋሎት ውጪ መሆን ለሌላው ነገር የምጡን ስቃይ ሸሮ የሚመጣ ውልደት ነው። ሲኒጋ ሲል እንደሚጨልመው ግግር ጨለማ የሚያስፈራ፣ እንደ ጥላሞት የሚከብድ የጭንቅ ምጥ ይሆናል። ጭንቁ የቱንም ያህል ቢበዛና ቢያስፈራም ቅሉ፣ ያ የከበደ አዲስ ምጥ ውላጅ በፍጹም መወለዱ አይቀርም። በየመንደራችን፣ በየቤታችን እና በየራሳችን ውስጥ ሊወለድ የተዘጋጀው ይህ





የለውጥ ጽንስ ዓይናችን ስር ህልው ለመሆን እየተቃረበ ቢሆንም ወቅቱ ካልደረሰና ገፍቶ ካልመጣ በስተቀር በውል አንረዳውም።

እንደተራራ ፊታችን ከተከመረው ፍርሰራሽ ስር እየተቀሰቀሰ ያለው የለውጥ ፅምጥ ምንድን ነው? ከእነዚህ ለውጦች ጋር እንዴት መናበብና አብሮ መጓዝ ይቻላል? በተወሰኑ አካላት፣ እንዲሁም ትስስርና ዝምድና በፈጠሩ ግለሰቦች መካከል ድንገት ሳይታሰብ ብቅ በማለት ላይ ያለ አዲስ አይነት ኃይል የፈጠረው ጥያቄ ይሆናል፡፡ ይህ ክስተት የተለየ ጥራት ያለው ተዛምዶ፣ ከትላንት ንድፎች አሻራ ተሞክሮ የተወሰደበት፣ ጥልፍልፎቹ በጠበቁበት ዛሬ ላይ አንዱ ከሌላው ጋር ባለው ትስስር ሳቢያ አብሮ የመሆን እና የማንነትን መደመር በብርቱ ይሻል።

መግኢ. ዕድሉን በጥሩ መሠረት ላይ ለመገንባት የኅብረተሰብን ተሳትፎ ማረጋገጥ መቻል ወሳኝ ነገር ነው። የሀገር ጉዳይ የኔ ጉዳይ ነው፣ ብሎ የሚያምን ኅብረተሰብን መፍጠር የቻሉ ሀገራት ያሉባቸውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች በቀላሉ መቋቋም ተችሏቸዋል። ምክንያቱም እኒህ ዜጎች ለሀገር ደህንነት ዘብ ናቸውና። ነገር ግን ህዝብን ወደኋላ ገሸሽ የሚያደርጉ መንግሥታት በየአቅጣጫው ለሚከሰቱ ፈታኝ ሁኔታዎች በውስጥ ችግሮቻቸው ሳቢ ተገቢ ምላሽ መስጠት ይሳናቸዋል። በአንፃሩ በአንድ ፖለቲካ ፓርቲ ወይም በጥቂት አዋቂ በሚባሉ አካላት ከሚደረግ የተናጠል ጥረት ይልቅ በጋራ የሚደረጉ ጥረቶች እጅግ ውጤታማ መሆናቸው እሙን ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ምዕራፍ ሁለት

### ጀግንነት፣ ጀብዳዊ ጭካኔና ጀብዳዊ ቅንነት፡-

**ያልዘሩት አይበቅልም!**
**ፈሪ ሰው አልወድም**
**ያልገደለ አልወድም**
**አብሬው ስተኛ ይመስለኛል ወንድም!**

**......**

**ምነዋ ብኮራ ምነው ቢጀንነኝ**
**ተጋዳይ አጋዳይ ያገኘሁ እኔ ነኝ፤**
**ቀና አድርገህ ተኩስ ወርች ነው ብልቱ**
**እዚህ ሆኜ ታየኝ እኔ እንኳን ሴቲቱ።**

(እንዲህ ያለው ግጥም በሀገራችን ህብረተሰብ ውስጥ ሲቀነቀን የኖረና ሴቶች ወንድ ባላቸው በመግደል የሚገኘውን ጀግንነት እንዲቀዳጅ የሚገፋፉበት፣ ፈሪ የሚሉትን ደግሞ የሚያጣጥሉበት ነው።)

በዓለም አቀፍ ደረጃ 'ጀግኑ' ወይም 'ጀብድ ሰሩ' እየተባሉ ከትውልድ ትውልድ፣ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ድረስ የሚነገርላቸው በርካታ ግለሰቦች እንዳሉ ታሪክ ያስረዳል። በጀግንነታቸውም ዝናርና ቀበቶ ያስፈቱ፥ ሱሪ፣ ቀሚስ ያስወለቁ፥ ገና ሲታዩ ያብረከረኩና ይበል



t.me/OLDBOOKSPDF

ያሰኙ የጀግና ቁንጮዎች እንደነበሩም እሙን ነው። ነገር ግን የጀግንነት ትርጉምና ስርወ-አመጣጡ ባህላዊ ወይም ዘልማዳዊ እንደሆነ በዌብስተር የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ላይ ሰፍሮ እናገኘዋለን። ይኸውም 'ጀግንነት' ወይም 'ጀብድ' የሚለው ቃል አመጣጡ አፈ-ታሪካዊ ሲሆን ትርጉሙም ከአምላክ ዘንድ ኃይልና ጉልበት መሰጠት ወይም ልዩ ኃይል መሞላትን ያመለክታል። በሌላ በኩል መንፈሰ ጠንካራ የሆነ ጦረኛ ማለት ሲሆን የተለየ ጥንካሬና ብቃት በተፈጥሮ የተቸረው በጣም ደፋር የሆነ ሰው እንደሆነ መዝገበ ቃላቱ ያስቀምጣል። ቢሆንም ግን የቃሉን ትርጓሜ ይህ ነው፤ ብሎ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ባለመቻሉ ምክንያት ሁሉም የዓለም ክፍል የቃሉን መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ሳይለቁ የተለያዩ ድርጊቶችን ለመግለፅ ይጠቀሙበታል።

ስለ ጀብድ ሲነሳ ወደ ታላቋ ግሪክ፣ መቄዶኒያዊት መንደር አቅንቶ ወደ ሆሜር ዘመን በመሻገር የሆሜርን የስነ-ፅሁፍ ሥራዎችን መመልከት በጣም አስፈላጊ ይሆናል። ሆሜር በዘመኑ ድንቅ የሚባሉ ሥራዎችን ጥሎ ያለፈ ባለ ቅኔና ገጣሚ ሲሆን ከሥራዎቹም መካከል ስለግሪክ አፈ-ታሪክ ባሰፈረበት 'ኢሊያድ' መፅሃፉ ውስጥ የጀብደኝነትን ሥርወ አመጣጥና አፈጣጠር ፍንትው አድርጎ ያሳየናል። ሆሜር ስለ ጀብድ ባነሳው ሃሳብ ላይ ሌላ ለማከል መሞከር የፀሐይን ብርሃን ለመደገፍ ባትሪ እንደማብራት ከንቱ ድካም ስለሚሆን የርሱን የጀብድ መሠረት ሃሳብ ጨብጦ ጥቂት ምዕራፍ መጓዝ እና ማብሰልሰል ግድ ይሆናል፡፡

በግሪክ አፈ-ታሪክ 'ዜውስ' ማለት የግሪክ የመንፈስ አምላክ ሲሆን እርሱም ከዕለታት አንድ ቀን ሊድ ከምትባል አንዲት ሴት ጋር ሌሊት በህልሙ ወሲባዊ ግንኙነት ያደርጋል። በዚያም ሌሊት ሄለን የምትባል አንዲት የዓለም ቆንጆ ተፀንሳ ታድራለች። ሄለንም ተወልዳ ካደገች በኋላ በውበቷ በዓለም ነገሥታት ላይ ተፅዕኖ የምትፈጥርና ከውበቷም የተነሳ የዓለም ነገስታትን የምታንበረክክ ድንቅ ሴት ትሆናለች። በታሪኩ ውስጥ ከሄለን ፍቅር የተነሳ በርካታ ነገስታት እንዲሁም ገበሬዎች እራሳቸውን እስከመሳት ይደርሱ





እንደነበረ፤ በምሳሌ ሲያስረዳ በውበት ስበቷ ኃያልነትና በፍቅሯም ከመፍዘዛቸው የተነሳ ገበሬዎች በእርሻቸው ላይ ጨው ይዘሩ እንደነበር ይናገራል። የሄለንን መንፍሣዊ ሥርወ ማንነት በሚያውቁና ተጋሪም መሆን በሚሹ፤ በሌላም በኩል በቁንጅናዋ በተማረኩ ሁለት ነገስታት መካከል አንድ ታላቅ ጦርነት ሊነሳ ቻለ። ይኸውም «የትሮይ ጦርነት» በመባል ይታወቃል። ይህ ጦርነት ስለ ሄለን ከተካሄዱ ታላቅና ጀብደኛ ጦርነቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ሲሆን ሄለን አግብታ ትኖር ከነበረችበት ከስፓርታ ንጉስ ሜሎስ በትሮይ ንጉስ ልጅ፤ ልዑል ፓሪስ ተጠልፋ ወደ ትሮይ ከተማ በትወሰድ የስፓርታው ንጉስ በትሮይ ላይ ባደረገው የጦር ዘመቻ በሁለቱም ወገን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደር ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል። ነገር ግን በጦርነቱ ታሪክ ውስጥ ከሁሉም በላይ በጣም ጀብድ ሰርቷል፤ የሚባለው አርኪለስ ሲሆን ጀብደኛውም ልዩ ኃይል የተሞላበትና የዜውስ ስርወ ዝርያ ያለው እንዲሁም በቀላሉ ሊሞት የማይችል ጀግና እንደነበር ታሪኩ ያስቀምጣል። አርኪለስ ከጀግንነቱ የተነሳ በጦር ቢወጉት፤ በጎራዴ ቢከፍሉት እንዳልሞተና በመጨረሻም ቁርጭምጭሚቱን በጦር ተወግቶ ሊሞት እንደቻለ አፈ-ታሪኩ ያስረዳል።

የግሪክ ነገሥታት ሄለንን ጨምሮ የግሪክ አምላክ ነው፤ ብለው ከሚያምኑት ዜውስ ጋር የቅርብ ዝምድና አለን ብለው ስለሚያምኑ በታሪኩ ውስጥ ጀብድ ይሰራ ከነበረው አርኪለስ ጎን እራሳቸውን ለማሰለፍ እንደሚሹ ታሪክ ያመለክታል። የጀብደኝነት ጥማትና ጀብደኞች በሰፈሩበት ባህረ መዝገብ ላይ ለመከተብ የሚደረግ የጀብድ ረሃብ ከዚህም በላይ ርቆ ይሻገራል፡፡

የሄለን ታሪክና የዜውስ ሥርወ መንግሥት እስከዚህ የዓለም ታሪክ ድረስ ተሻግሮ ሊዘልቅ እንደቻለና ጠባሳውም ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ እንደመጣ ማየት ይቻላል። የአርኪለስ ታሪካዊ ጀብደኝነት ግና በጨቅላነት ዕድሜው ናላውን ያዞረውና መንበረ ስልጣኑን ለመቆናጠጥ በስርወ መንግስት ፍቅር ወደ ተነደፈው ታላቁ እስከንድር ያመራናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሄለናዊ መስተዳድር ያላት ታላቋ ግሪክና መቄዶንያ ተብላ የምትጠራውን የስልጣኔ ቁንጮ አገር ለመግዛት በርካታ ሰልፎች በታሪክ ተካሄደዋል። በዚህም ውስጥ የምናየው በሄለናዊ መስተዳድር ልቡ ስለተነካው ታላቁ እስክንድር ይሆናል። በመሆኑም እስክንድር ዓለምን ለመግዛት በነበረው ጽኑ እምነት በወጣትነቱ ሁሉን ሊቆጣጠር «ሀ» ብሎ ሊጀምር ችሏል። የእስክንድር ዓላማ በልጅነቱ ይነገረው የነበርውን ሄለናዊ መስተዳድርን በዓለም ላይ መዘርጋት ነበር።

ታላቁ እስክንድር የተወለደው በ356 ከክርስቶስ ልደት በፊት በፔላ መቄዶንያ ነበር። አባቱ ንጉስ ጳግማዊ ፊሊፕ ሲሆን እናቱ ደግሞ ኦሎምፒስ ነበረች። እናቱም የመቄዶንያ ንግስታት የግሪክ አምላክ የሆነው የዜውስ ልጅ የሄርኩለስ ዝርያዎች መሆናቸውን ለእስክንድር ታስተምረው ነበር። እንደ እናቱ አባባል ከሆነ የእስክንድር ቅድመ አያት አሲያድ በሚባለው የሆሜር ግጥም ውስጥ የተገለፀው ጀግና አርኪለስ ነው። በመሆኑም ወላጆቹ ድል የማድረግና ንጉሳዊ ክብር የመቀዳጀት ምኞት ስለቀረፁበት ወጣቱ እስክንድር በጊዜው ወደ ጦር አምባ ፊቱን ለመመለስ በጦር ግንባርም ለመሰለፍ ሊገፋፋ ችሏል። ምንም እንኳን የዘመኑ ፈላስፋ አርስቶትል እስክንድርን ፍልስፍና ሊያስተምረው ቢፈልግም እስክንድር ግን የጅብደኛው አርኪለስ ዝርያ ነኝ የሚለው የጅብደኝነት መንፍስ በውስጡ ስላደረበት ጦረኛ ለመሆን ተገደደ። ስለ ዘሩ ለማወቅ ከፍተኛ የማንበብ ልምድ የነበረው እስክንድር ከሆሜር ግጥሞች ውስጥ 16 ሺህ የሚሆኑ ስንኞችን በቃሉ እንደያዘ ይነገርለታል። በዚህም የተነሳ በ20 ዓመቱ የድል አክሊል ለመቀዳጀት የቻለና ትልቅ ጅብድ የሰራ ወጣት ንጉሥ ሊሆን እንደቻለ ብዙ ተነግሮለታል።

ዛሬ፣ በዚህ ዘመንም እንኳን ቢሆን ስለ እስክንድር ጅብድና ጀግንነት በሰፊው ይወራል። አርሱንም ለመምሰል በዓለም ዙሪያ በርካታ ነገሥታትና መሪዎች እንደሚፈልጉ የሚፈጽሟቸው ተግባራትና የሚዘረጉት ፓለቲካዊ ሥርዓት በግልጽ ያሳያል። በዚህ ባለንበትና ከትላንት የማይሰምር ሌላ ዘመን በጠባበት እንግዳ የዕድሜ ካብ ላይ ሆነን እንኳን ከአርኪለስ እስከ እስክንድር በሚዘረጋ የ«በሆንኳቸው» ጅብደኛ ምኞት ጋዲ ታስረው ሳይተኙ የሚያልሙና የሚቃዡ እዚህም እዚያም ብቅ ሲሉ ማስተዋል እንግዳ ክስተት አይደለም።

በዚያው መጠን በዘመናችንም ልክ እንደ ታላቁ እስክንድር ዓለምን የመግዛትና በዘመነ ግዛቱም በምድር ላይ ትክክለኛና 'የተከበረ' የሚለውን የዘር ሀረግ ብቻ እኑሮ እንዲመጻደቅ በማድረግ በተቃራኒው ደግሞ 'ነውረኛ' እና የተናቀ ዘር ብሎ የፈረጀውን የዘር ሀረግ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ታጥቆ የሚነሳ ከፍልም አለ።

ሂትለር ከታላቁ እስክንድር ጋር የሚያመሳስለውንና አንድ የሚያደርገውን መሰረታዊ ነጥብ በጥልቅ መመልከቱ ስለ ሁለቱ ሥርወ መንግሥት አመጣጥ በግልጽ ለማየት ይጠቅማል። ሂትለር ልክ እንደ እስክንድር በወጣትነት እድሜው፣ ገና በጨቅላነት የብስለት ደረጃው የናዚን ጦር ለመቀላቀል የወሰነ ሲሆን ዓላማውም ዓለምን በመግዛት የአርያን ዘር ነው፣ የሚባለውን የቅድመ አያት ዝርያውን በመላው ዓለም እንዲበዛ ማድረግና ዘሩም ተከብሮና ተፈርቶ እንዲኖር ማስቻል ነበር።

ሂትለር በልጅነቱ በሥዕልና በዕደ ጥበብ ሙያ የተካነ ቢሆንም በዚህ ሙያውም ብዙ የመሥራት ህልምና እቅድ ቢኖረውም ዘርን መሠረቱ ያደረገ ንድፈ ሃሳባዊ ርዕዮተ ዓለም ይሰብክ፣ ያስተምር በነበረው 'ጎንተርስ' አስተምሮት መንፈሱ በመማረኩና አመለካከቱም በመቀየሩ ልቡ ወደ ዘረኝነት አጥፊ ልክፍት ሊኮበልል ችሏል። እንደናዚው ጎንተር የዘር አስተምሮት ከሆነ የአውሮፓ እና የእሲያ አገራት የዘር ግንድ አርያን የሚባል ሲሆን ትርጉሙም ከሁሉ በላይ የሆነና የተከበረ ዘር ማለት ነው። ምንም እንኳን የአርያን ዘር ሜዲትራኒያን፣ ኖርዲክ፣ ደናቲክ፣ አልፈያንና የምስራቅ ባልቲክ በሚል አምስት ንኡስ የዘር ሀረግ ቢከፈሉም ከአምስቱ ውስጥ ኖርዲክ የሚባለው የዘር ሀረግ ከሁሉም የሚበልጥና የናዚዎች







t.me/OLDBOOKSPDF

ቅድመ እያት መሆኑ በሂትለር ላይ ትልቅ የዘረኝነት መነሳሳት ሊፈጥርበት ችሏል።

ገና በጠዋቱ የጨለኝነት ጅብዳዊ መንፈስ የተጠናወተው ሂትለር የተከበረውን የአርያን ዘር ለማብዛት በተቃራኒው ደግሞ የተናቁ የሚላቸውን የአርመን፣ የግሪክ እና የአይሁድ ዝርያዎችን ለማጥፋት ብሄራዊ እርምጃ በማድረግ 10,000 ጀርመናዊያንና 9,000 ኖሮዊዥያን የአርያን ህጻናትን በባዮ-ቴክኖሎጂ የማዳቀል ሥነ ዘዴ ማፍራት ችሏል። ሂትለር በዚህ አኩይ ተግባሩ ከአምስት ሚሊየን በላይ በሚሆኑ አይሁዳዊያን ህጻናት ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ፈጽሟል። ሂትለር ከዚህም በማለፍ ከንዱን በዓለም ላይ ዘርግቶ የናዚውን ጦር ይዞ በመዝመት በርካታ አውዳሚ ጦርነቶችን አድርጓል። ቢሆንም ግን በዘረኝነት ልክፍት ተነዞ ካሰመው ሳይደርስ በመንገድ የቀረው ጀርመናዊው ናዚ ጀብደኛ እንደነበርና እርሱንም ለመምሰል የሚታትሩ የዚህ ዘመን መሪዎች እንዳሉ የዓለም ገጽታ ያሳያል።

የሰው ልጅ በነገሩት ተረትና ባነበቡለት አፈ-ታሪክ ወይም ደግሞ ተጨባጭ ነው፣ በሚለው ታሪክ እራሱን ዋና ተዋናይ በማድረግ ታሪኩን ለመምሰልና የአመፅ ትርክቱን ጀብዳዊ ድርጊት እንድም በቅንነት አሊያም በከፋት ተግባር መፈፀም በሚያስችለው ደረጃ አመለካከቱ ሲቀየር፣ ልቦናው ሊጋረድ እንደሚችል የሥነልቦና ባለሙያዎች ይናገራሉ። የሰው ልጅ የሚሰማው፣ የሚናገረው፣ የሚያየውና የሚማረው ወይም የሥርዓት ትምህርቱ ድግግሞሽ መጠን አመለካከቱን ሊያጣምሙት ወይም ደግሞ ሊያቃኑት እንደሚችሉም ይታመናል። በተለይም የትርክቶቹ ቁርኝት ከሚዛናዊና አስተውሎትን ከሚጠይቁ ተጨባጭ የሕይወት ባህር ከመቀዳት ይልቅ ከስሜታዊ መንፈሱ ጋር የተቆራኙ በሚሆኑበት ጊዜ ተጎሳሽነቱ ከፍተኛ ይሆናል።

"አንድ ሞኝ የተከለውን ሺህ ብልህ አይነቅለውም እንዲሉ እውነት የሚመስሉ ነገር ግን ከእውነታ የራቁ በየመድረኩ፣ በየመገናኛ



ብዙሃኑ የሚነገሩና ወደ ህዝቡ የሚወረወሩ ስለት ያላቸው ንግግሮችና በርካታ ተረት ተረት ምሣሌዎች የሚመነጩት ከጥቂት ሰዎች አዕምሮ ውስጥ መሆኑን እርግጠኞች መሆን እንችላለን። እነዚህ ውል አልባ ተረቶች ግን በጥቂቶች ቢፈጠሩም ቅሉ የሚያስተዛዝላቸው እና በጅምላ የሚሸፍራቸው ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሆኑ ልብ ይሏል፡፡ ስለ እርግጠኝነት ሲነሳ አንድ ታሪክ ትውስ አለኝ።

ያኔ ልጅ እያለሁ፣ ጨረቃ ተወልዳና አድጋ ትልቅ ሆና ደምቃ በምትታይበት ቀን አባቱ በረንዳ ላይ ይቀመጥና ከወንድሜ ጋር በምትታይበት ቀን ያጫውተን ነበር። ይኸውም ሁላታችሁም ወደ አንድ ትርኢት ያጫውተን ነበር። ይኸውም ሁለታችሁም ወደ ተለያየ አቅጣጫ ጨረቃ እንጋጣችሁ እየተመለከታችሁ ወደ ተለያየ አቅጣጫ ተንቀሳቀሱ ይለናል። እዛው በቆምንበትም ቦታ ሳለን አባታችን ጨረቃዋ ከማንኛችሁ ጋር ነች? በማለት ሲጠይቀን፣ ወንድሜም እኔም "ከእኔ ጋር ነች… ከእኔ ጋር ነች" በማለት በስሜት እንከራከራለን። በመጨረሻም አባታችን ስለ እውነታው ሊያስረዳን ሁለታችንንም ወደ እርሱ ይጠራንና አሁን ጨረቃዋን እንደምታይዋት በሁላችንም አቅጣጫ እንጂ ወደ አንዳችን ያዘነበለች አይደለችም። እውነታው ይህ ነው፤ ቢሆንም ግን ስትንቀሳቀሱ ጨረቃዋ በእናንተ እናት ላይ ብቻ የተቀመጠች ሆና ይታሰባችኋል። ይህን ሁነትም ከአልበርት አንስታይን የአንጻራዊነት ህግ ውጪ ማብራሪያ ልናገኝለት አንችልም፡፡

በዚህ ታሪክ ውስጥ በዘመኑ አጠራር የአልበርት አንስታይን አንፃራዊነት ህግ እጅግ ያጓላዋል፤ ዓለም አንጻራዊ ነው። በእጃችን ስላለውና ስለጨበጥነው እውነታ ወይም ደግሞ ስለውሳኔያችን ትክክለኛነት እርግጠኛ መሆን የምንችለው በአንፃራዊነት ነው። ስለ ጨረቃዋ አለመንቀሳቀስ እርግጠኛ የምንሆነው ከእኛ እንቅስቃሴ ጋር አመክንዮ ማመን ስንችል ብቻ ነው። ስለ ጀርባ ስለተፈጠረው አመክንዮ ማመን ስንችል ብቻ ነው። ስለ ጥቂት ንጉሳዊ ቤተሰቦች ንግግር ማመን የምንችለው ከንጉሶች በስተጀርባ ስላለው ምስኪን ህዝብ እርግጠኛ መሆን ስንችል ብቻ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

ከላይ የጠቀስናቸው የእስክንድርና ሂትለር የስልጣን አነሳስ ገና በጨቅላነት ዕድሜያቸው ይሰሙትና ይነገራቸው የነበረው የተረት ተረት አስተምሮት ውጤት እንደሆነ ግልጽ ነው። በሰሙት፣ በእዩትና በተማሩት ነገር ተነሳስተው የፈፀሙት ጅብዱ ህልማቸውን ከዳር ቢያደርስም ጅብዳቸው ግን በጭካኔ የተሞላ ነበር። በተቃራኒው ደግሞ በበጎ አመለካከት በጅብዳዊ ቅንነት የተሰለፉና የተቃና ማህበረሰብ ለመፍጠር ሌት ተቀን የሚታትሩ በርካታ ግለሰቦችና መሪዎች እንደነበሩ፣ እንዳሉና ወደፊትም እንደሚኖሩ የማይካድ ሃቅ ነው።

በማህተመ ጋንዲ የተቀጣጠለው ፀረ ሂትለር እና ፀረ እስክንድር ሥራ ስለ አፈ-ታሪክ ጅብዳዊ ቅንነት ወደ አፍሪቃ መንደሮችም ዘልቋል። እዚህ ጋ ከጋንዲ ተነስቶ የኔልሰን ማንዴላን ቤት እንኳኩቶ የዘለቀው ቅንነት የወለደውን ጅብዳዊ ጅግንነት ማየቱ መልካም ይመስለኛል። "ልጅ የሚበላውን ይመስላል" እንደሚባለው ሁሉ ጋንዲም በልጅነቱ ወቅት የእናቱ ፑትሊባ ሃይማኖታዊ የቀናና ጺድቅነት ከፍተኛ የመንፈስና የሞራል ጥንካሬ እንዳሳደረበት ጸሃፊዎች ያስቀምጣሉ።

ከዚህም በተጨማሪ ጋንዲ የሃይማኖት ስብጥርና የዘር ልዩነት ባለበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመከታተሉ የቅንነት እና አብሮ የመኖር መንፈስ በውስጡ ሊያቆጠቁጥና ሊያድግ እንደቻለ አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ። ህይወት የህልውና መሠረቷን የምታቻችልበት እና የተፈጥሮ ሚዛኗን የምትጠብቅበት ተፈጥሯዊ ሚዛን አላት። ሂትለርን አስቦ የበገነ ጋንዲን ሲያስብ ደግሞ በእፎይታ እየሰከነ ህይወት ትቀጥላለች።

ጋንዲ የዘርና የሃይማኖት ብዝሃነትን የሚናፍቅ፤ በዘርፉም ለዓለም ትልቅ ጅብድ ሰርቶ ያለፈ ህንዳዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ መሪ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ከጋንዲ በፊት የነበረውን የተከበረና የተናቀ በሚል የተከፈለ የዘር ልዩነት ርዕዮተ ዓለምን በማንኮታኮት በምትኩ ፍቅርና መተሳሰብን ለዚህ ዓለም አስተምሮ ያለፈ ጅብደኛ





ነው። የጋንዲ አስተምህሮት ሰብአዊነትን የተላበሰ ስለነበረ ሰው የሆነ ሁሉ ያን ርዕዮት ለመከተል እና ለማራመድ ፍቃደኛ ነበር። በመሆኑም ጋንዲን ሳያውቃቸውና በጋንዲ ሳይማር የጋንዲን ፍልስፍና መከተልና ማራመድ ስለጀመረው የደቡብ አፍሪቃው ማንዴላ ብዙ ነገሮችን ማንሳት ይቻላል፤ ተገቢም ነው።

ማንዴላ ስለ ጋንዲ መዘግብት በማገላበጥ የጋንዲን ብሄራዊ አጀንዳ፣ የጋንዲን ሥርአተ አስተምሮትና የጋንዲን የነጻነት ፈለግ ለመከተል የፈለገ የደቡብ አፍሪቃ ፀረ-አፓርታይድ መሪ ነበር። በጋንዲና በማንዴላ ዘንድ ስለ አገር ነጻነትና ክብር የሚደረገው ሁሉ ጅብዳዊ ጅግንነት እንደሆነ በሙሉ እምነታቸው ይናገራሉ። ከ1922 ጀምሮ በየእስር ቤቱ ይወረወሩ የነበሩት ጋንዲ ስለ አገሬ ፍቅርና ነጻነት ብዬ ወደ እስር ቤት ስገባ እንደ ታላቅ ጅብድ ወይም ክብር ይሰማኛል፤ ሲሉ በንግግራቸው አስቀምጠዋል።

ማንዴላም ቢሆኑ ስለ ጥቁር አፍሪቃዊ ነጻነትና እኩልነት ሲሉ ከ27 ዓመታት በላይ በሮበን ደሴት ላይ ታስረው በግዳጅ የጉልበት ሥራ እና በህመም ሲሰቃዩ የቆዩ እና አህጉራዊ ጅብድነትን ያስመሰከሩ ከመሆናቸውም በላይ ለትውልድ ጥለው ያለፉት የቅንነትና የአብሮነት ጅብዳዊ ታሪክ ዛሬም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሆነና ወደፊትም ይሄው ሊቀጥል እንደሚገባ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በንግግራቸው ላይ አስምረውበት አልፈዋል። ወደፊት የማንዴላን ፈለግ የሚከተሉ በርካታ ጥቁር አፍሪቃዊ መሪዎች እንደሚኖሩም ጥርጥር የለውም።

ከደቡብ አፍሪቃ ተነስተን ወደ ጋና በማቅናት ከዋሜ ንኩሩማን እንዴት ነዎት፣ ብለን፤ በኬንያ በኩል ጆሞ ኬንያታን እጅ ነስተንና ተሰናብተን ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ተጉዘን ብንመጣ ብዙ ጅብዳዊ ታሪክ ያላቸውን መሪዎችንና ግለሰቦችን ማግኘት መቻላችን ምንም ጥርጥር የለውም።

የአገራችን ማህበረሰብ ለጅብዳዊ ቅንነትና ጅብዳዊ ጭካኔ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከላይ የጠቀስናቸው የእስከንድርና ሂትለር የስልጣን አነሳስ ገና በጨቅላነት ዕድሜያቸው ይሰሙትና ይነገራቸው የነበረው የተረት ተረት አስተምሮት ውጤት እንደሆነ ግልጽ ነው። በሰሙት፣ በአዩትና በተማሩት ነገር ተነሳስተው የፈፀሙት ጀብዱ ህልማቸውን ከዳር ቢያደርስም ጀብዳቸው ግን በጭካኔ የተሞላ ነበር። በተቃራኒው ደግሞ በበጎ አመለካከት በጀብዳዊ ቅንነት የተሰለፉና የተቃና ማህበረሰብ ለመፍጠር ሌት ተቀን የሚታትሩ በርካታ ግለሰቦችና መሪዎች እንደነበሩ፣ እንዳሉና ወደፊትም እንደሚኖሩ የማይካድ ሃቅ ነው።

በማህተመ ጋንዲ የተቀጣጠለው ፀረ ሂትለር እና ፀረ እስከንድር ሥራ ስለ አፈ-ታሪክ ጀብዳዊ ቅንነት ወደ አፍሪቃ መንደሮችም ዘልቋል። እዚህ ጋ ከጋንዲ ተነስቶ የኔልሰን ማንዴላን ቤት እንኳኩቶ የዘለቀው ቅንነት የወለደውን ጀብዳዊ ጀግንነት ማየቱ መልካም ይመስለኛል። "ልጅ የሚበላውን ይመስላል" እንደሚባለው ሁሉ ጋንዲም በልጅነቱ ወቅት የእናቱ ፑትሊባ ሃይማኖታዊ የቀናና ጻድቅነት ከፍተኛ የመንፈስና የሞራል ጥንካሬ እንዳሳደረበት ጸሃፊዎች ያስቀምጣሉ።

ከዚህም በተጨማሪ ጋንዲ የሃይማኖት ስብጥርና የዘር ልዩነት ባለበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመከታተሉ የቅንነት እና አብሮ የመኖር መንፈስ በውስጡ ሊያቆጠቁጥና ሊያድግ እንደቻለ አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ። ህይወት የህልውና መሠረቷን የምታቻችልበት እና የተፈጥሮ ሚዛኗን የምትጠብቅበት ተፈጥሯዊ ሚዛን አላት፡፡ ሂትለርን አስቦ የበገነ ጋንዲን ሲያስብ ደግሞ በእፎይታ እየሰከነ ህይወት ትቀጥላለች፡፡

ጋንዲ የዘርና የሃይማኖት ብዝሃነትን የሚናፍቅ፣ በዘርፉም ለዓለም ትልቅ ጀብድ ሰርቶ ያለፈ ህንዳዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ መሪ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ከጋንዲ በፊት የነበረውን የተከበረና የተናቀ በሚል የተከፈለ የዘር ልዩነት ርዕዮተ ዓለምን በማንኮታኮት በምትኩ ፍቅርና መተሳሰብን ለዚህ ዓለም አስተምሮ ያለፈ ጀብደኛ





ነው። የጋንዲ አስተምህሮት ሰብአዊነትን የተላበሰ ስለነበረ ሰው የሆነ ሁሉ ያን ርዕዮት ለመከተል እና ለማራመድ ፍቃደኛ ነበር። በመሆኑም ጋንዲን ሳያውቃቸውና በጋንዲ ሳይማር የጋንዲን ፍልስፍና መከተልና ማራመድ ስለጀመረው የደቡብ አፍሪቃው ማንዴላ ብዙ ነገሮችን ማንሳት ይቻላል፤ ተገቢም ነው።

ማንዴላ ስለ ጋንዲ መዘግብት በማገላበጥ የጋንዲን ብሄራዊ አጀንዳ፣ የጋንዲን ሥርአተ አስተምሮትና የጋንዲን የነጻነት ፈለግ ለመከተል የፈለገ የደቡብ አፍሪቃ ፀረ-አፓርታይድ መሪ ነበር። በጋንዲና በማንዴላ ዘንድ ስለ አገር ነጻነትና ክብር የሚደረገው ሁሉ ጀብዳዊ ጀግንነት እንደሆነ በመሉ እምነታቸው ይናገራሉ። ከ1922 ጀምሮ በየእስር ቤቱ ይወረወሩ የነበሩት ጋንዲ ስለ አገሬ ፍቅርና ነጻነት ብዬ ወደ እስር ቤት ስጣል እንደ ታላቅ ጀብድ ወይም ክብር ይሰማኛል፣ ሲሉ በንግግራቸው አስቀምጠዋል።

ማንዴላም ቢሆኑ ስለ ጥቁር አፍሪቃዊ ነጻነትና እኩልነት ሲሉ ከ27 ዓመታት በላይ በሮቢን ደሴት ላይ ታስረው በግዳጅ የጉልበት ሥራ እና በህመም ሲሰቃዩ የቆዩ እና አህጉራዊ ጀብድነትን ያስመሰከሩ ከመሆናቸውም በላይ ለትውልድ ጥለው ያለፉት የቅንነትና የአብሮነት ጀብዳዊ ታሪክ ዛሬም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሆነና ወደፊትም ይሄው ሊቀጥል እንደሚገባ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ በንግግራቸው ላይ አስምረውበት አልፈዋል። ወደፊት የማንዴላን ፈለግ የሚከተሉ በርካታ ጥቁር አፍሪቃዊ መሪዎች እንደሚኖሩም ጥርጥር የለውም።

ከደቡብ አፍሪቃ ተነስተን ወደ ጋና በማቅናት ክዋሜ ኑኩሩማን እንዴት ነዎት፣ ብለን፣ በኬንያ በኩል ጆሞ ኬንያታን እጅ ነስተንና ተሰናብተን ወደ አገራችን ኢትዮጵያ ተጉዘን ብንመጣ ብዙ ጀብዳዊ ታሪክ ያላቸውን መሪዎችንና ግለሰቦችን ማግኘት መቻላችን ምንም ጥርጥር የለውም።

የአገራችን ማህበረሰብ ለጀብዳዊ ቅንነትና ጀብዳዊ ጭካኔ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚሰጠው ትርጓሜና ማህበረሰቡ ከወለዳቸው ልጆቹ የሚፈልገው ማንነት የትኛውን ነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ እጅግ አስገራሚ መሆኑ አይቀርም፡፡ የማህበረሰብ ስነ-ልቦና ባለሙያዎች ስብዕና በዋናነት በጨቅላ ዕድሜ በቤተሰብ፣ በጎረቤትና በማህበረሰቡ የሚነገሩ፣ የሚተገበሩና ትምህርት የሚሰጥባቸው ወጎች፣ ልማዶችና ታሪኮች በወደፊት የስብዕና ማንነታቸው ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑን በልጅነት የሚነገሩ ተረቶች ናቸው፡፡ይህ ትርክት ሁኔታዎችን በቃላት፣ በድምጽ ወይም በምስል ኪነ-ጥበባዊ ለዛ በማላበስ ትምህርትን፣ ባህልን፣ ወግንና የሞራል እሴቶችን ለትውልድ የምናስተላልፍበት የማህበረሰብ ሃብት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ማህበረሰብ በገጠርም በከተማም፣ በተለያዩ ብሄሮችም ሆነ ሀይማኖቶች ለልጆች በጨቅላ አዕምሯቸው የሚነገሩ ተረቶች ታሪክ ምን ይመስላል? አብዛኛውን ጊዜ በተረቶቹ ውስጥ ገጸ ባህሪ ሆነው የሚቀረጹት እንስሳት እነማን ናቸው? የሚወከሉት የህይወት ጠባይስ ምንድነው? የሚለውን ወስደን ጥናት ብናከናውን በጣም ከሌሎች ጎልቶ የምናገኘው መልስ በአህያ፣ ጦጣና አንበሳ ዙሪያ የሚሽከረከር ነው፡፡ አህያ በላቡ ጥሮና ግሮ የሚኖር እንስሳ እንደሆነ ቢታወቅም በተረቶቻችን ውስጥ ያለው ውክልና ግን እንደ ጅል፣ የማይረባ እና ሁልጊዜም ተሸናፊ ተደርጎ ይቀርባል፡፡ በተቃራኒው ጦጣ ብልጣብልጥ፣ አጭበርባሪና ተንኮለኛ ተደርጋ የምትቀርብ ሲሆን ብዙ ጊዜ ሁኔታዎችን በአሸናፊነትና በበላይነት እንደምታከናውን ይተረካል፡፡ አንበሳ ደግሞ ጉልበተኛ፣ ደፋርና አስፈሪ ተደርጎ ይሳላል፡፡ በመሆኑም የአገራችን ትርክት የአህያን ማንነት ሳይሆን የሚያበረታታው የጦጣንና የአንበሳን ማንነት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በላቡ ለፍቶ ጥሮ ከመኖር ይልቅ አጭበርብሮና ቀልጣፋ ሆኖ በብልጠት መኖርን ወይም ደግሞ በጉልበት አስፈራርቶ፣ ቀምቶና ተደባድቦ መኖርን የሚደግፍ በመሆኑ በአብዛኛው የማህበረሰብ እርከን ማለትም በንግዱ ዘርፍ በተሰማሩ፣ በፖለቲካና ማህበራዊ ጉዳዮች አመራርነት ላይ በሚገኙ ወይም በጠቅላላው ማህበረሰብ ዘንድ ይህ ስብዕና ተገንብቶ ይታያል፡፡







t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል ሁለት

**ከመረው በፊት ኃይል ይቀድማል፤ ኃይል ግን ህልው ይሆን ዘንድ መረውን ይጠብቃል**

**እግዜር ለጥበቡ**

**ለእኩይ ለሰናይ ኃይልን የቀመረ**

**ስልጣንን ያኖረ፤**

**ጋንዲና ሂትለርን**

**ባ'ንድ ዓለም ፈጠረ።**

**ቀዳሚው ፍሪ ኃይል**

**በያዘው ሲዘወር - ሲመራ ባ'ጉል ቃል**

**የማንዴላ በትር ናዚም ላይ ይወድቃል፤**

**ያሳዝናል።**





## ምዕራፍ ሶስት

### ኃይልና ሥልጣን

የኃይልና ሥልጣን አጠቃቀምን ለማሳየት ከሊባኖሳዊው ባለቅኔ ከካሕሊል ጅብራል መፅሀፍ የተወሰደውንና በህዝብ ላይ ስለሚመፃደቅ አንድ ንጉሥ የሚያትተውን ታሪክ በማንሳት እንጀምር። ይህ ንጉሥ በህዘቡ ላይ እጅግ ከመመፃደቁ የተነሳ ሕዝቡን በሙሉ አሳብዶ እርሱ ብቻ በግዛቱ ላይ ጤነኛ ሆኖ መኖር ይፈልግና ይህን እኩይ ሃሳቡን ዳር ለማድረስ ሊያግዘው ወደሚችል አንድ አዋቂ ሰው ዘንድ ይሄዳል። አዋቂውም ለንጉሡ መድኃኒት ይሰጠውና ህዝቡ በሚጠጣው የውሀ ታንከር ውስጥ እንዲበጠብጠው ይመክረዋል። ንጉሡም በአዋቂው ምክር መሠረት እንደተባለው አደረገ፤ ህዝቡም 'አበደ'። ከዚያም 'ያበደው' ህዝብ 'የእብድ' ቋንቋ መናገር ይጀምራል። ቀስ በቀስም ህዝቡ አዲስ በፈጠረው የእብድ ቋንቋ መግባባት ችሎ ነበርና በራሳቸው የእብድ ማህበራዊ ሕይወት መኖር ሲጀምሩ ንጉሡን ከመፍራት ይልቅ ናቁት... አዋረዱት። ንጉሡም በውርደት ላይ ብቸኝነት ሲደረብበት ብቻውን ከራሱ ጋር ማውራት ጀመረ፤ በመጨረሻም ራሱ አበደ።

*ሥልጣን ያባልጋል!* እውነት ነው፤ ፍጹማዊ ሥልጣን ደግሞ የባሰጌ ባለጌ እንደሚያደርግ የሮማ ካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጎርጎሪዮ ሶስተኛ የተናገሩት ሀሳብ ግሩም ምስክር ይሆናል። ነገር ግን፣ ይህም ታውቆ እንኳን ዛሬም እንደ ትላንቱ 'ስልጣን' የአያሌዎችን ልብ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያጓጓች፣ ልክፍት በሚመስል እስፈሪ ፍቅሯ እንደማግኔት ትስባቸዋለች። ድሮም ሆነ ዘንድሮ የመንበር ጥማት ያው የመንበር ጥማት ነው፤ ከብዙዎች ልብ ተፍቆ አልወጣም። ስልጣን፣ ቢሰሩባትም ባይሰሩባትም እርካቧን የረገጡ፣ ኮርቻውን የተቆናጠጡ፣ መንበሯ ላይ የተደላደለ ሁሉ (ቢያንስ አብዛኛው) በሞቱ እንጂ በፈቃዱ ሊለያት የማይሻ 'ጠሰኛ ፍቅሯ' ተቆፍድዶ ይኖራል። አፍቃሪዋም ዘመኑን ሁሉ ሲጨንቅና ሲጠበብ ዕድሜውን የሚገብርላት፣ የክብሩ ዘውድ፣ ወይም የመራራ ውርደቱ ፅዋ ትሆናለች፣ ሥልጣን። ይህ ጤነኛ ያልሆነ የሥልጣን ፍቅረ ሲመት ምናልባትም ጀርመናዊው ደራሲና ባለቅኔ ፍሬደሪክ ኒቼ 'ዊል ቱ ፓወር' ሲል በመፅሃፉ እንደገለፀው፣ 'የሰው ልጅ ወደደም ጠላም፣ አውቆም ይሁን ሳያውቅ የህይወቱ ጥሪና ታላቅ ግብ ሥልጣንና ሥልጣንን እድርጎ በደመ ነፍሱ ሊመራ ይችላል' ይላል። የዓለማችን የኃይልና ስልጣን ታሪክም በዚሁ እቅጣጫ ሳይቋረጥ የሚፈስ ወንዝ እንጂ ድንገት ቦግ ብሎ ድርግም የሚል የክረምት ነጎድጓዳዊ ብልጭታ አይደለም።

ወደ አገራችን መለስ ስንል፤ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የመግዛት ሕልም ከነበራቸው ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ የነበረውን የሥልጣን ጥማት ስንመለከት ከላይ ባለቅኔው እንደተናገረው ደመ ነፍሳዊ ቅኘት እንጂ በሰከነ አዕምሮ የተፈፀመ ሥርዓታዊ አካሄድ ነበር፣ ማለት አይቻልም። ካሣ ሀይሉ እራሳቸው፣ የመፅሃፍ ቅዱሳዊ ሥርወ መንግሥት ባለቤት እንደሆኑ በማመን፤ ልክ እንደ መዝሙረኛው ንጉስ ዳዊት ያለ፣ ጦረኛ እና የህዝቡን እንባ ሊያብሱ የመጡ ዳግማዊ ቴዎድሮስ እንደሆኑ በየአደባባዩ የሚያውጁ፣ ሥልጣንና መንበርን አብዝተው የሚሹ ንጉሥ እንደነበሩ በዘመኑ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ የነበረው ሄነር ደፋቶን በፃፈው መፅሐፍ ላይ አስቀምጦታል።[1]

በአፄ ምኒልክ እና አፄ ዮሐንስ መካከል የነበረው የሥልጣን ጥማትና ሥልጣንን ከሀገር ጥቅም በላይ የማስቀደም አባዜያቸው ተመሳሳይ

1 The barefoot emperor (2007)





ነው። አፄ ዮሐንስ ሟቹን ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስን ሊወጋ የመጣውን የእንግሊዝ ሠራዊት በመርዳት ከሸኚ እና ስንቅ ጋር በግዛታቸው እንዲያልፍ በማድረጋቸው ወሮታውን ከድሉ በኋላ በዘመናዊ መሣሪያ፣ መድፍ እና ጥይት አበልጽጓቸው ሲሄድ በጊዜው ከነበሩት መሪዎች ሁሉ የላቀ ኃይል ለማግኘትና የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ እጃቸው ለማስገባት አመቻቸላቸው።

አፄ ምኒልክም ቢሆኑ ኢትዮጵያን ጠቅልሎ የማስተዳደር ፍላጎታቸውን ለማሟላት ንጉስ ከመሆናቸው በፊት በተለያየ መንገድ ግዛታቸውን በደቡብ እና በምዕራብ አቅጣጫ እያስፋፉ ኃይላቸውን ከምዕራባዊያን ከሚያገኙት እርዳታ በዘመናዊ መሣሪያዎች እያታጠቁ ቀናቸውን ሲጠብቁ ኑረው በስተመጨረሻም ፍላጎታቸውን አሟልተዋል።

አፄ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያና ህዝቧን፤ መሬትና አየሯን ሳይቀር ርስታቸው አድርገው በሥልጣን ርካብና መንበር ከልጅነት እስከ ዕውቀት የተጓዙ የቅርብ ዘመን ንጉሥ ነበሩ። ንጉሡ ከ44 ዓመታት በላይ በመግዛት ቢዘልቁም በኋላ፣ እረጀሁ፣ ደከምኩ... ብለው በህዝብ ለተመረጠ መሪ ማስረከብ ቀርቶ ከአብራካቸው ለወጣውና አልጋ ወራሽ ላደረጉት ልጃቸው እንኳን ማስተላለፍ ሳይችሉ ከዚያው፣ 'ሞቴም ሕይወቴም' ካሉለት መንበር በደርግ መጀመሪያ ወደ ወህኒ ቀጥሎም ወደ መቃብር ተሸኝተዋል።

ዚምባቡዌን ከእንግሊዞች የቅኝ ግዛት በማላቀቅ በርካብና መንበር ወደ ስልጣን የመጡት ሮበርት ሙጋቤም ቢሆኑ ዛሬም በዘጠና ሁለት አመታቸው እየተደነቃቀፉና እየተወለካከፉ 'ሥልጣን ወይም ሞት!' ብለው መጨረሻቸው ባይታወቅም ዚምባቡዌን መግዛታቸውን ቀጥለዋል። እውነት ይህ መንበር፤ ይህ መደላድል እንዲህ ምትሃታዊ ልክፍት የለውም ይሆን?! ብለን እንድንጠይቅ መንሻ የሚሆነንም ይኸው ከልክ ያለፈ አባዜ ነው። የዛየሩ መሪ ሞቡቱ ሴሴኮ፣ የግብጹ ፕሬዝዳንት ሁስኒ ሙባረክ፣ የኢራቁ ሳዳም ሁሴንና የሊቢያው መሪ ሙአመር ጋዳፊ የርካብና መንበር ታሪክም

መላምቱን ያጠናከር እንደሆን እንጂ አያስሳልሰውም።

ከዚያም በራቀው ዓለምም ጭምር ለአሜሪካ የፕሬዝዳንታዊ ውድድር ዕጩ ሆነው ምረጡኝ በማለት አሸንፈው ወደመንበር በማምራት ላይ ያሉት 'ዶናልድ ትራምፕ' በሃብትም በእድሜም የደረጁ ሰው ናቸው። የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በመሆናቸው የበለጠ ቢሊየነር ሊያደርጋቸው የሚችልበት መንገድ የተዘጋ ባይሆንም ያን ያህል ሥራ አስፈትቶ ሰው ፊት ሲያስገርፋቸው የነበረው መንበር ለቀሪ ዕድሜያቸው ስንቅና ትጥቅ እንደማይሆናቸው የታወቀ ነው። ከርሳቸው ጋር ተፎካከረው በለሥ ያልቀናቻቸው ሂላሪ ክሊንተንም ቢሆኑ ርካብና መንበር ብርቃቸው አልነበረም።ይኸውም በፕሬዝዳንቱ ባለቤታቸው የተነሳ ቀዳማዊ እመቤት ሆነው ነጩን ቤተመንግስት ለተከታታይ ስምንት አመታት ኖረውበታል። ፕሬዝዳንት ባይሆኑም ከሴኔተርነት እንስተው እስከ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት በመዳዝ፤ አሁን በስተመጨረሻ ደግሞ ፕሬዝዳንት በመሆን እርካብና መንበር ጥርሳቸውን የነቀሉበት መሆኑ ሳይበቃ ሆኖም ግን ስልጣን ልክፍት ነውና በስተርጅናቸው ዘመንም ሊሞሸሩበት፤ አለያም ሊጦሩበት እስከመጨረዋ ላብ ጠብታ ሌት ተቀን ማስነዋል።

እርግጥ ነው፤ ሥልጣን ያባሊጋቸው፤ መንበር አይታቸውን የጋረደባቸው፤ እርካቡን ካልረገጥኩ 'ሞቼ እገኛለሁ!' ባዮች እንዲህ በቀላሉ ተቆጥረው አያልቁም። ያም ሆኖ፤ በተቃራኒው ከዚህ እባዜ የፀዱ ሰዎችንም ዓለማችን አፍርታለች። ከዚህ በመነሳት እነዚህ ከመስመር የወጡ የስልጣን ጥምና የልክፍት እባዜ የዚያው የግለሰቡ ጣጣና ግላዊ ባህሪ እንጂ የርካብና መንበር መገለጫ ባህሪ እንዳልሆነ መገመት ይቻላል። ሥልጣንን ለዝናና ክብር ሳይሆን ህዝብን ለማገልገል ሲሉ ብቻ የሚፈልጓት ጥቂቶችም ቢሆኑ መኖራቸው ግን ሃቅ ነው። ለጭቦና በደል፤ ለመከራና ግፍ ሳይሆን በተፅዕኗቸው ሀገርና ሕዝብን ለመለወጥ ሌት ተቀን የሚለፉ መሪዎችም ነበሩ፤ አሁንም አሉ። ማህተመ ጋንዲን እንድ ብለን ብንነሳ፤ ቼጉቬራን፤ ጎርባቾቭን፤ ሻከላሽ ሃቬልንና ማንዴላን በአርዓያነት መጥቀስ





እንችላለን።

በተጨማሪም 'መንበሩን ከምለቅ ወገቤ ይላቀቅ!' ከማለት ይልቅ፤ ልክ እንደዚያው እንደተራው ወንበር በማየት ሳይሞቱለት ወይም ሳይገድሉ በቃኝ! ብለው የሚሰናበቱ መሪዎችንም ዓለማችን አስተናግዳለች። የታንዛኒያው ጁሊየስ ኔሬሬ መንበሩን በገዛ ፈቃዳቸው ደህና ሰንብት ብለው ወደ ትውልድ መንደራቸው ተመልሰው ገበሬ በመሆን ለአፍሪካ የመጀመሪያው መሪ ናቸው። የእንግሊዙ ልዑልና አልጋ ወራሽ እንዲሁ ፍቅሬ ይበልጥብኛል፤ በማለት ዘውዱን ከአናቱ አውርዶ ከፍቅረኛው ጋር አሜሪካ ገብቷል። የቫቲካኑ ሊቃጳጳስ ጆን ቤኔዲክትም ቢሆኑ ከስልጣን መንበር የገዳም ፀሎት በስንት ጣዕም! በማለት በገዛ ፈቃዳቸው ለተተኪ አስረክበው ገዳም ገብተዋል።

በአንድ መልኩ ጨብጠን እንዳንረዳው ጉራማይሌ ገጽታ በመላበስ አዚያና አዚህ የሚያወዛውዘንን ኃይልና ሥልጣን ምን ማለት እንደሆነ በትክክል መረዳት እንድንችል የምልከታ አድማሳችንን ጥቂት በመለወጥ ሰፋ ባለ መልኩ ስለ ምንነቱ ፍተሻ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ከዚህም ባሻገር የትኛውም ጠቃሚ ጉዳይ አጠቃቀሙን ካላወቁበት በስተቀር ለበረከት ያሰቡት ነገር መርገምት ይዞ ሊመጣ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም ኃይል ብቻውን ለእሉታም ለእዎንታም ሊውል የሚችልበት ዕድል ከመኖሩ ላይ ከተስማማንና ይህንን የጠራ እውነትም እንደ ጋንዲና ሂትለር ባሉ የአንድ ዓለም ልጆች ሁለት ተቃርኖዎች ማሳያነት ካጸናን ዘንዳ የዚህን ኃያል ኃይል አጠቃቀም እንዴትነትን በዘወርዋራም ቢሆን ትብኙቶ ማለፉ እጅግ ሲበዛ አስፈላጊ ይሆናል።

## ኃይልና የኃይል አጠቃቀም

አንዳንድ ሰዎች 'ኃይል' የምንለው ሌሎች ላይ ተጽዕኖ የማሳደር ችሎታ እንደሆነ አድርገው ያምናሉ። አንድ ሰው ወይም መንግስት በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ከቻለ በርግጥም 'ኃይለኛ' ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

ልንለው እንችላለን። በሌሎች ተጽዕኖ ሥር የወደቀ አካል ደግሞ 'ደካማ' ነው፤ ማለት ነው። ለሌላዎቹ ደግሞ ኃይል የሚለካው በተከታዩ ህዝብ ቁጥር፤ በግዛት ስፋት፤ በተፈጥሯዊ ሃብት፤ በኢኮኖሚ ጥንካሬ፤ በወታደራዊ ኃይል እና በማህበራዊ መረጋጋትና በመሳሰሉት፤ በሁሉም ወይም ከሁሉም በአንዱ ነው። በዘመናችን አገራትና መንግስታት ኃይልን ሲያስገኝልኝ ይችላል ብለው የሚያስቡትን ነገር ሁሉ የግላቸው ለማድረግ አቅማቸውን እሚጠው እንደሚጠቀሙ ይታወቃል። ምክንያቱም ኃይል በዓለም አቀፍ ደረጃ አንደኛ ባያደርግ እንኳን ቢያንስ በመከባበር ለመዝለቅ ያግዛል። በእርግጥ ይህን መሰሉ ኃይል ቁሳዊና ኢ-ቁሳዊ በሚሉ ክፍፍሎች ስር እንደሚወድቅ የሚገልፁ አሉ።

መንግሥታት የሚፈልጉትን ውጤት ለማምጣት የማስፈራሪያ በትራቸው አድርገው 'ኃይልን' ሲጠቀሙ ይስተዋላል። ነገር ግን፤ ውጤታማነቱ የሚለካው በስሩ ባለው ሃብት ብቻ ሳይሆን በአጠቃቀም ጥበቡ ጭምር ነው። እንደ እምባገነናዊው ሂትለር 'እኔ ማንም ሊመከተኝ የማይችል ኃያል ነኝ' ብሎ መደንፋት የሚያመጣው መዘዝ ውድቀት ነው። "ትልቁን ጎሊያድ የጣለችው የትንሹ ዳዊት ትንሽ ጠጠር፤ ወፍራሙን ብልኮ የበሳችው ትንሿ መርፌ ናት" እንዲሉ፤ የውድቀት መነሻው ከየት እንደሆነ መተንበይ አዳጋች ይሆናል። አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው ኃይልን በቀጥታ ወስዶ ከመጫን ይልቅ በዘዴ መጠቀም ውጤታማ እያደረገ መጥቷል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ "መስፍኑ፤ ከሚወደድ ይልቅ ቢፈራ የበለጠ ደህንነቱ ይረጋገጣል" የሚለው ማኪያቬሊያዊ አስተሳሰብ ዓለማችንን ተቆጣጥሯት ቆይቷል። ይህ አስተሳሰብ 'ዘ ፕሪንስ' የተሰኘውን መፅሀፍ የፃፈው የኒኮሎ ማኪያቬሊ አሳቢ ሲሆን ብዙዎች ተጠቅመውበታል፤ አሁንም እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

አንዳንዶቹ ደግሞ መፈራትንም ሆነ መወደድን አጣምሮ መያዝ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ ይከራከራሉ። ነገር ግን፤ ይህን መሰል ጣምራ ባህሪ መላበስ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ





የሚወዱትን አይፈሩትምና። ይሁንና ተወዳጅ ሆኖ ልፍስፍስ ከመሆን ይልቅ ተፈሪ ሆኖ የተጠላ መሆን ይሻላል፤ ሲል ማኪያቬሊ ለአምባገነኖቹ ምክሩን ይለግሳል።

አንዳንድ ጊዜ በፍቅር ላይ የተመሰረተ ግዛት ልል ነው። በውዴታ የተሳሰረን ሠንሰለት መበጣጠስ ቀላል የሚሆንበት ጊዜ ያለ ሲሆን ፍራቻ ከታከለበት ግን ሁኔታዎች ምንም ሆኑ ምን ቅጣቶችን በማሰብ ወላዋይነት እንዳይኖር ያደርጋል። ያም ሆኖ አዲስ ነገር በተፈጠረ ጊዜ ለማመጽ ቀላል ይሆናል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት የሠው ልጅ በተፈጥሮው ምስጋና ቢስ፤ ከዳተኛ፤ ድብቅ እና ብዙ ለማግኘት የሚመኝ መሆኑ እንደ ሠበብ ተደርጎ ይወሰዳል። ህዝበ እስራኤል እንኳን በባርነት ቀንበር ጠፍሮ ይገዛቸው ከነበረው ከፈርኦን እጅ አምላካቸው ነፃ ቢያደርጋቸውም፤ በበረሃ ውሀን ከዓለት እያፈለቀ ጥማቸውን ቢያረካ፤ ከሠማይ መናን እያወረደ ቢመግባቸው የተደረገላቸውን በጎ ነገር ሠለቹ። "አንተ ከምታቀርብልን መና እና ከምታፈልቅልን ውኃ ይልቅ እየተገረፍን የምንበላው የግብጽ ሽንኩርት ናፈቀን" ሲሉ ተሰምተዋል። ይህም የሠው ልጅ እንኳን እርሱን ለመሰለ አኩያ ፍጡር ስለተደረገለት ነገር በሙሉ ተዝቢ ምስጋና ማቅረብ ይቅርና ከምንምነት ወደ ህያውነት ላሸጋገረው፤ በዋጋ የማይተመኑ ፀጋዎቹን በእርሱ ላይ ላዋለለት አምላኩ እንኳን አመስጋኝ አለመሆኑን ታሪክ ምስክር የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ስለዚህ ከፍቅር ይልቅ በትር ለመከበር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ይህ ማለት ግን "በምድር ላሉት እዘኑ በሰማይም ያለው ያዝንላችሁ ዘንድ" የሚለውን አስተምህሮ ወደ ጎን በማለት ወሰን ማለፍ እንደሚገባ ለማሳየት አለመሆኑን መረዳት ያሻል።

በትርን ብቻ ተመራጭ አካሄድ አድርጎ መውሰድ የራሱ ድክመት እንዳለው ኒኮሎ ማኪያቬሊ ይናገራል። ምክንያቱም መስፍኑ ህዝቡን በማስፈራራት ከሱ ጋር ማድረግ ቢችልም የችግር ቀን ግን መጀመሪያ አሳልፎ የሚሰጠው ያኔ በመንቀጥቀጥ ሲሰግድለት የነበረው ህዝብ ስለሚሆን ነው። ለዚህ ደግሞ የደርግ መንግሥትን



t.me/OLDBOOKSPDF

የመሰለ ማሳያ አይገኝም። ይህ መንግሥት እጅግ የሚፈራና ለአፍሪቃም ጭምር ሥጋት የነበረ ሲሆን ህዝቡም ወዶ ሳይሆን የሚጠብቀውን በትር በመፍራት ነበር፣ ቀዋ ለጥ ብሎ ሲገዛ የነበረው። ታዲያ ይህንን ያህል ጠንካራና ጉልበተኛ መንግስት የወደቀው ተቃራኒው በጦር ስለበለጠው አልነበረም። ህዝብ አብሮት ስላልነበረና ጉያው ስር ያለ ሽምቅ ተዋጊ በመሆኑ እንጂ!

አንዳንዴ ደግሞ መስፍኑ የተለበጠ ማንነት ሊኖረው ይገባል። ሰዎች የሚያውቁት የላዩን ብቻ ሲሆን አስፈላጊ የሆነ ጊዜ ግን ሁለተኛውና ድብቁ ማንነት ይገለጣል። በመልካሙ ጊዜ ህዝብን በፍቅር መያዝ አስፈላጊ ነው። ፍላጎታቸውን በመፈጸም የልብ ትርታቸውንም በማዳመጥ ደስ የሚያሰኛቸውን ነገር በማድረግ በህዝብ ልቦና ውስጥ ተደላድሎ መቀመጥ ይቻላል። ነገር ግን ይህ አካሄድ አንዳንዴ ችግር አያጣውም። ታዲያ የአመጽና የመከዳት ምልክት የታየ ጊዜ፣ በሁለተኛውና በተለበጠው ማንነት መገለጥ ተገቢ ይሆናል። አስተማሪነት ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣትን ተግባራዊ በማድረግ በፍቅር ወቅት መልዓክ በአመጽ ጊዜ ግን ሰይጣን ሊሆን እንደሚችል ማሳወቅ አለበት። ማንም ውሃ እና እሳት አብረው ቀርበውለት እጁን ወደ እሳቱ መከተትን ምርጫው አያደርግም። ያንቀላፋ ሰይጣንንም ቀስቅሶ በራሱ ላይ ችግርን ማምጣት የሚሻ ይኖራል፤ ተብሎ አይታሰብም። ቢኖር እንኳን የሚተባበረው ስለሚያጣ ብቻውን ይቀራል።

መቼም ሥልጣን ዝም ብሎ አይገኝም። መሃሉ ላይ መውጣትና መውረድ፣ መውደቅና መነሳት ይኖረዋል። የተሳካለት ባለሟል ግን ሥልጣን የመያዝ ፍላጎት እንዳለው ሳያሳብቅ ጥሩ ተዋናይ በመሆን በትረ ሥልጣንን መጨበጥ የቻለ ነው። ሕጋዊ ተቀባይነት የለዘብተኛ ኃይል ማዕከላዊ ነጥብ ነው። ዜጎች እና አገራት ለምናደርጋቸው ነገሮች ህጋዊ እውቅና ከሰጡ ማስፈራሪያና ጉብ ሳናቀርብላቸው ዓላማችንን ደግፈው ከጎናችን እንዲቆሙ ማድረግ ቀላል ነው። በዚህ መንገድ ተቃዋሚዎቻችንን ለመደምሰስ ወታደራዊ ኃይልን ማሰለፍ አስፈላጊ አይሆንም። ሰልፉስ ለማነው?





ውጊያውስ ከማን ነው? ሰይፉስ ወደት ነው? የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ሀሊናዊ አመለካከት ካለው አንድ አካል የሚጠበቁ አይደሉምን? ከፊት ለፊት ራሳቸውን ገልጠውና ደረታቸውን ገልብጠው ሥልጣን ፈላጊነታቸውን በገሀድ አውጀው ሲንቀሳቀሱ ከመጋረጃው ጀርባ በሚደረግ የማሳመንና የመተማመን ሥራ ብቻ አሸንፎ ለድል መብቃትን ይጠይቃል።

በዚህ አካሄድ የሚያገኙትን ትንሽና ትልቅ ሳይሉ ጊዜ ሰጥቶ ታላቅነትን እንዲቀበሉ ለማድረግ ትዕግሥትንና ጥበብን የተላበሰ አካሄድን መከተል ያስፈልጋል። ሆኖም ግን፣ ተግባር የሌለበት ወሬ እንዲያውም በሰዎች ዘንድ ተዓማኒ እንዳይሆን መሰናከል ከመሆኑ በቀር የሚፈይደው ነገር አይኖርም። በመሆኑም ጠቃሚና አዳዲስ የሆኑ ተግባራትን ማሳየት እኔ ለበታው እመጥናለሁ ብሎ ከመለፍለፍ ይልቅ ተቀባይነትን ያላብሳል።

በወታደራዊ ኃይል በጦር ለመዋጋት መሞከርና ተከታዮችን ለማፍራት መድከም በየበታው የጠላት ኃይሎች እንዲያቆጠቁጡ በር ይከፍታል። ይህ ደግሞ ምንም የጠላት ቡድን የማሸነፍ ብቃቱ ባይኖረውም እንኳን የተረጋጋ የሥልጣን ዘመን እንዳይኖር የማድረግ አድሉ ከፍተኛ ይሆናል። ሌሎችን በሃሳብ አሸንፎ ወደራስ አስተሳሰብ ማምጣት ግን የተቃዋሚ ወገኖችን ከንፍ የመንቃቀል ያህል ዋጋ ሊሰጠው ይችላል።

ተቀናቃኞችን በሃሳብ መርታትና ወደራስ ጎራ እንዲመጡ ማድረግ በራሱ አንድ ጥበብ ነው። ምክንያቱም ለሥልጣን ምቹ መደላድል ከመሆኑም ባለፈ አካሄድን በሌላ አይታ ለመቃኘት፣ የሰዎችን የልብ ትርታ ለማዳመጥና በሰዎች ጫማ ላይ ሆኖ ስለ ሰዎች ህመም ጭምር ማወቅ ስለሚያስችል ነው። ሆኖም ግን ተቀናቃኝ ሁሉ በሃሳብ በመርታት ወይም በመረታት የሚያምን አይደለም። እንደዚህ ካለው ጠላት ጋር ሀሳብን እንደ መሣሪያ ተጠቅሞ ማሸነፍ ከባድ ነው። ስለዚህም አማራጭ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ግድ ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ውሻ፣ ጠላት ላይ በመጮህ ማምለጫን ማመቻቸት ዘላቂ መፍትሄ ባይሆንም ለጊዜው ይጠቅማል። ምክንያቱም እንዳይመለስ ሆኖ ያልተሸኘ ጠላት ጊዜ ጠብቆ ዳግም ለማጥቃት እንደሚመጣ ጥርጥር የለውምና። ታዲያ ጊዜው ሲደርስ ልክ እንደ ነብር ኮቴን ሳያሰሙ ከጀርባ ቀብ ማድረግና ህልሙን ባንድ ጀንበር ማምከን መረሳት የለበትም፤ ወይም ስውር የሆነ ወጥመድ ማዘጋጀት ይበጃል። ሰዎች ራስ ወዳድ ናቸውና በጥቅም ሂድባቸው። የሚፈልጉትን ነገር እያሳየህ ወደ ምትፈልገው ስፍራ ውሰዳቸውና ጣላቸው። ከዚያም "በሬ ሆይ! ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ" የሚለውን ተረት ተርትባቸው። ይህን መሰሉ ለዘብተኛ የኃይል አጠቃቀም ዘዴ ሠላም ሳይበጠበጥ ህዝብም ሳያጉረመርም የተደላደለ ስልጣን ባለቤት ለመሆን ያግዛል።

የተሰባጠረ የኃይል አጠቃቀም ሌላኛውና ዘመናዊው የኃይል አጠቃቀም ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ የከፍተኛ ኃይል አጠቃቀምና የለዘብተኛ ኃይል አጠቃቀም በአንድ ላይ ስናጣምራቸው የምናገኘው ኃይል ነው። ከፍተኛ የሆነ ኃይልን መጠቀም በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖር ተቀባይነትንና ታማኝነትን ከማጉደሉም በላይ ጠላትን የሚያፈራ በመሆኑ፤ እንዲሁም ለዘብተኛ ኃይል አጠቃቀምም ቢሆን ለብቻው አመርቂ ባለመሆኑ ነው፤ እነዚህን ሁለት የኃይል አጠቃቀም ዘዴዎች በአንድ ላይ መጠቀም ያስፈለገው። ይህ ዘዴ በዲፕሎማሲያዊ ጥረት ሀሳብን ማስፈጸም፣ አቅምን በመገንባት ለሚመጡ ችግሮች ዝግጁ ሆኖ መጠበቅን፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ተጽዕኖ መፍጠርን እንዲሁም ጉልበትን ከማሳየት ይልቅ በህጋዊ መንገድ ፍላጎትን ማስፈጸምን አካቶ ይይዛል።

ሁሌም ኃይልን መጠቀም የራሱ ጉዳት አለው። ሣርና ሰንበሌጥ ባህር ዛፍ አውሎ ንፋስን እኩል አያስተናግዱትም። ባህር ዛፍ ግትር ስለሆነ አውሎ ነፋስ በመጣ ጊዜ ኃይሉን ሊያሳይ አጉል ስለሚገዳደር ተመልሶ እንዳይነሳ ሆኖ ይወድቃል። ሠንበሌጥ ግን እንደባህር ዛፉ አይደለም፤ ያለውን ኃይል መጥኖ ነው፣ የሚጠቀመው፣ ንፋሱ





እስኪያልፍ አጎንብሶ ይቆይና ዳግም ይነሳል። ጥበብ ያልታከለበት ኃይል ጊዜው ይርዘም እንጂ ለውድቀት መንስኤ መሆኑ አይቀሬ ነው። ለዚህ ነው፣ ባለንበት ዘመን አገራት ይህንን ስብጥር የኃይል አጠቃቀም ዘዴ የሚመርጡት። 'የእኔን ፍላጎት ካልተገበርክ የምጽዓት ቀን ይሆናል!' ብሎ ከማስፈራራት ይልቅ በጠረጴዛ ዙሪያ በመነጋገር ሃሳብን በሃሳብ መርታት የዘመኑ ፖለቲካዊ ብልህነት ነው። ይህ አካሄድ የተሳካ እንዲሆን የሌሎችን የልብ ትርታ አድምጦ፣ የራስንም ፍላጎት በጥበብ አስረድቶ፣ ለመስጠትና ለመቀበል ራስን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። አብሪተኛ ከመሆን ይልቅ ለሌሎች በጎ በመሆን የደነደነ ልብ ያላቸውን ተጠራጣሪዎች ለራስ ፈቃድ ማስገዛት ይቻላል። የበጎነት እና ታማኝነት ሰብዕና የተላበሱ ሰዎችን ለማዘናጋት፣ በቀላሉ ለመሸንገልና ለመደለል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በዚህ ረገድ ርዕዮተ ዓለማዊ የበላይነት ከምናረጋግጥባቸው ሠንነዶች መካከል አንዱና ዋነኛው ፕሬስ ሲሆን በቤተ እምነቶች፣ በቤተ መዕሃፍት፣ በትምህርት ቤቶች እና በማህበራት ላይ አተኩሮ መስራትም ሳይቀር ተጽዕኖ ማሳደሪያ ለዘብተኛ ኃይል ተደርገው ይወሰዳሉ። አንዳንዴ ህይወት በችግር የተሞላች ልትሆን ትችላለች። ታዲያ በእነዚህ የችግር ጊዜያት ቀድሞ መገኘትና አስደሳች ሁኔታዎችን መፍጠር በበረሀ እንደበቀለች አበባ በፍቅር ለመታየት ያበቃል። በማንኛውም ጊዜ አብሮን የሚሆን አካል አለን፣ የሚለው ስኑ እምነታቸውን ለማግኘትም ያበቃል። በተለይም ወዳጅና ጠላት የሚለየው በችግር ቀን ነው፣ ብሎ በሚያምነው ህዝባችን ልብ ውስጥ ከነዕድፍ ተደላድሎ ለመቀመጥ በችግር ጊዜ መድረስን የመሰለ ጥሩ አጋጣሚ አይገኝም። መንግስት በሚገዛቸው ህዝቦች ላይ የሞራል፣ የፖለቲካና የአይዲዮሎጂ የበላይነት እንዲኖረው ያስችለዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሥልጣንና የሥልጣን አጠቃቀም

ስልጣን ማህበራዊ ኃላፊነትን በውክልና ከመያዝ የሚገኝ ሲሆን ቦታውን የያዘው አካል በስሩ የሚገኙትን የማዘዝና የመምራት ኃይል ያገኛል። ሆኖም ግን የተለያዩ መንግሥታትን በሥልጣን አጠቃቀማቸው ብንቃኛቸው የተለያዩ ምላሾችን ልናገኝ እንችላለን። ምክንያቱም በተለያዩ ዘመናት የተፈጠሩት እነዚህ መንግሥታት ሥልጣናቸውን በተለያየ መልኩ ለተለያየ ዓላማ ተጠቅመውበታል።

ለጀርመኑ ሂትለር 'ስልጣን' ዓለምን ሁሉ የበታች አድርጎ መርገጫ የሆነ የብረት ጫማ ነበር። ይህ ሰው ጀርመንን ባስተዳደረበት ዘመን ጀርመናዊነት ምርጥ ዘር (የአርያን ዘር) እንደሆነ የሚያምን፣ እንዲያውም ጀርመናዊነት 'ከአማልክት በታች፣ ከሰው ዘር በላይ' እንደሆነ የሚቆጥር በመሆኑ ይህ ሃሳብ የዘወትር ዝማሬው ነበር። ታዲያ የአገሪቱን የበላይነት ለማረጋገጥ ዓለምን ወደ አዲስ የጦር አውድማነት ከመቀየሩም ባሻገር በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዳውያን እጅግ በሚያሳቅቅ ሞት እንዲረግፉ አድርጓቸዋል። ናዚ እሁንም ድረስ የጨካኝ መንግሥት ምሳሌ ነው።

ለሂትለር ያቀረብነውን ጥያቄ የቀድሞይቱን ህንድ ላስተዳደረው ማህተመ ጋንዲ ብናቀርብ የምናገኘው ትርጓሜ ፍፁም ተቃራኒ ሊሆን መቻሉ አያጠራጥርም። ይህ ሰው በመንፈስ ከፍታ ውስጥ የነበረ መሪ ልንለው እንችላለን። 'የሰው ልጆች እኩል የሆኑ ፍጥረታት በመሆናቸው በዘር፣ በሀይማኖት እንዲሁም በእመለካከት አንዱን ትልቅ ሌላውን ደግሞ ትንሽ ልናደርግ አይገባም' የሚል ጽኑ እምነት ነበረው። በመሆኑም ሙስሊም፣ ሂንዱና ክርስቲያን ወንድማማች እንጂ ጠላት እንዳልሆኑና፣ በመካከላቸውም ምንም ዓይነት ግጭት ሊኖር እንደማይገባ እየተናገረ ያስተምር ነበር። ከታሪኩ እንደምንረዳው ለማህተመ ጋንዲ 'ሥልጣን' የራስን ፍላጎት ወደ ጎን ገሸሽ አድርጎ የህዝብን ፍላጎት የሚያስቀድሙበት መሣሪያ ነው።





በ12ኛው ክፍለ ዘመን በዛግዌ ሥርወ መንግሥት ኢትዮጵያን ይመራ ለነበረው ንጉስ ላሊበላ 'ሥልጣን' ማለት ሁለት ነገር ነው። አንድም ራስን ገቶ አድርጎ ለፈጠረው አምላክ ሲያገለግሉ የሚኖሩበት ነው። ከዚህ አለፍ ሲል ደግሞ ዘመን የማይሽራቸው ብርቅዬና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ አስገራሚ ሥራዎችን ሠርቶ የሚታለፍበት ጥሩ አጋጣሚ ነው። ይህ ንጉስ የሰራቸው አስራ አንድ ውቅር አብያተ ክርስትያናት እሁንም ድረስ ስሙን ከማዘከራቸው ባሻገር ለአገሪቱ የቱሪዝም መስህብ በመሆን ጭምር እያገለገሉ ይገኛሉ።

ኃይልና ሥልጣንን የጋራ ተጠቃሚነታችንን ማረጋገጥ የሚያስችል አቅም አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ ከጥፋትና ከፋት ምንጭ የሚገኝ፣ የሚጨበጥና የሚዘልቀውም የተሻለ በመሥራት፣ አብዝቶ በመስጠት፣ በላቀ ቅንነት ሳይሆን በሽብር፣ በውድመት፣ በማጥፋት እንደሆነ ሲነገረን ኖሯል። በቀዳሚነት በሌሎች ላይ ተፅዕኖ የማሳደር አቅም የሚነጠቅ ሳይሆን በፈቃድ የሚሰጥ የጋራ ድምር ውጤት ነው።

ከግለሰብ እስከ ቤተሰብ፣ ከቤተሰብ እስከ ማህበረሰብ፣ ከማህበረሰብ እስከ አገር፣ ብሎም እስከ ዓለም በተዘረጋው ትስስራዊ ሂደት ሥልጣን የላቀውን የጋራ ተጠቃሚነት እያቻቻለ፣ እያረጋገጠ እንጂ ለጥቂቶች ወግኖ፣ በብዙሃን ጫንቃ ላይ የሚጫን ቀንበር አይደለም። ። ከሁሉም በላይ በከፍተኛው የአመራር እርከን ያስቀመጥናቸው ፖለቲከኞች ኃላፊነታቸውን መሳት አይኖርባቸውም። እንደጠንካሮች ሁሉ ለደካማዎቹ የኅብረተሰብ ክፍሎች እለኝታ መከታ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ለፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ሕይወታችን መሻሻል መትጋት፣ ለችግሮቻችን መፍትሄ የማመንጨት ግዴታ አለባቸው። ለዚህም በታላቅነት ውስጥ አውቀት፣ በታላቅነት ውስጥ መስጠት፣ በታላቅነት ውስጥ ማካተት መኖሩን መረዳት ግድ ነው። በየትኛውም የሥርዓትና የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ የአሃዝ ልዩነት ካልሆነ በቀር ሕዝብ በአንድ ወጥ ስዕል ተፈርጆ የተሰራ አይደለም። ሁሉ ታጋይ፣ ሁሉ የድል አርበኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለም:: ተሸናፊ አለ፣ ደካማ አለ:: በተለይም በዕውቀት ዘመን ከአሸናፊዎች በቁጥር የሚያይሉ ዜጎች በመኖራቸው የሚዘጉ ጥቂቶች አይሆኑም::ስለሆነም እይታችን የተዘጉትን ጥሎ የሚጓዝ ሳይሆን አካቶ ደግፎ የሚዘልቅ ሊሆን ይገባዋል:: እስቸጋሪና ፈታኝ ቢሆንም ታላቅ ነገና መደገፍ ይኖርብናል:: ከችግሮቻችን ገበያ ፊትን በማዞር ሳይሆን የምንረታበትን ብልሃት መፈለግ የሚኖርብን ለዚህ ነው:: ስልጣን የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያጎላ ኃይልና ተፅእኖ የሚሆነው በዚህ ጊዜ ነው:: መንፈግ ሳይሆን መስጠት፣ ቅጣት ሳይሆን ይቅርታ፣ በጥላቻ ምትክ ፍቅርን ገንዘባችን ልናደርገው ይገባል:: ፍቅር ጥላቻን ድል ይነሳልና::

በተቃራኒው እጃችን ለዚህ ሲባል የገባው አቅም ምክንያቱን፣ ትርጓሜውን መረዳት ሳይሆንልን ሲቀር በታላቅነታችን ውስጥ ዕውቀት፣ መስጠት መደገፍ ሲጠፋ ለጋራ ጥቅም መስራት ስናቆም ችግር መፍታት ሲሳነን ሕዝብ ይሁንታውን ይነፍገናልና በመራራ የቅጣት በትር ካልሆነ ተፅዕኖ አይረጋም እንላለን:: ወደ ተሻለው ዓለም ለማንቀሳቀስ ልንጠቀመው የሚገባን ኃይል ከተፅዕኖችን ባፈነገጡትና ለማፈንገጥ በሚያመነቱት ጀርባ ላይ ለማሳረፍ ስንቆፍር እናድራለን::

ሀገራት አንድ አይነት የኃይል አጠቃቀም ስልትን አይከተሉም። አንዱ ፍጹም ዴሞክራሲያዊ ሲሆን አንዱ ደግሞ ረግጠህ ግዛ ዓይነት ይሆናል። አንዱ ያለውን ኃይል ዓላማውን ለማሳካት በግልጽ፣ በይፋ ሲጠቀምበት ሌላው ደግሞ የሀጋዊነትን ጭንብል ለብሶ ውስጥ ውስጡን ግን ለማመን እንኳን አስቸጋሪ የሆኑ ድርጊቶችን ይፈጽማል። የኃይል አጠቃቀም የተለያየ የሆነው ያለ ምክንያት አይደለም። ህብረተሰቡ ያለበት የንቃት ደረጃ፣ መንግስት ስልጣን ላይ ያለው አመለካከት፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ አገር ቀድሞ የነበረችው ፓለቲካዊ ሥርዓትና የመሳሰሉት ሁኔታዎች የኃይል አጠቃቀም ላይ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አይደለም። ንቃተ ህሊናው ያደገ ህብረተሰብ መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ ያውቃል። በመሆኑም መብታቸው ሲረገጥ ድምጻቸውን





አሰምተው ተቃውሟቸውን ያቀርባሉ። ስለዚህ መንግሥታቱም ስልጣናቸውን ያለ ገደብ እንዳይጠቀሙ ልጓም ይሆኑባቸዋል። እንደ አፍሪካ ያሉ አንዳንድ ቦታዎችን ስንመለከት ግን ከላይ የጠቀስናቸው ነገሮች ተቃራኒውን አቅጣጫ ይዘው እንመለከታቸዋለን። ይህ ለመሆኑ ብዙ ነገሮችን እንደ ምክንያት ልንጠቅስ ብንችልም በዋነኛነት ግን የህብረተሰቡ ንቃተ ህሊና በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉ ዓብይ ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን። የመብት ረገጣ ሲካሄድበት ለምን ብሎ ሲጠይቅ አይታይም። አባብ ያየ በልጥ በረየ እንደሚባለው ሁሉ ህዝቡም የዕውር ድመት ኑሮ ሆኖበት፣ ነጋ ሲል ዳግም እየጨለመበት፣ ነገሮች የፈለጉትን ነገር የመፈጸም መብት እንዳላቸው አምኖ የተቀበለ ይመስል አይቶ እንዳላየ፣ ሰምቶም እንዳልሰማ ይሆናል። ጉቦ ካልሰጠ ባለሥልጣናቱ የሚገባውን አገልግሎት እንደማይሰጡት ስለሚያምን ለእምነታቸው ያደሩት እንኳ ጉቦ እንዲቀበሉት እግራቸው ስር ድፍት ይላል።

የተለያዩ አገር መንግሥታት ሥልጣን ላይ ያላቸው አመለካከት የኃይል አጠቃቀማቸው ሁኔታን በእጅጉ ሲወስነው ይስተዋላል። 'ስልጣን የህዝብ ነው' ብለው የሚያምኑ መንግሥታት ኃይላቸውን ልጓም አልባ አያደርጉትም። ምክንያቱም ወደ ላይ ያነሳቸው ህዝብ የትዕግስቱ ጽዋ የሞላች ቀን ወደ ታች እንደሚያወርዳቸው ጠንቅቀው ያውቃሉና። ከዚህም ባሻገር ራሳቸውን የህዝብ አድርገው ስለሚቆጥሩ ኃይላቸውን ያለ አግባብ ለመጠቀም ህሊናቸው እሺ አይላቸውም። ለእነዚህ አይነት መንግሥታት ሥልጣን አገርን መወከያ፣ ህዝብን ማገልገያ፣ ልማትን ማቀጣጠያ፣ አገርን ማስከበሪያ፣ ሰንኮፎችን ማስወገጃ ወዘተ መሳሪያ ነው። ይሁንና በዓለማችን ታሪክ እንከን አልባ መንግሥት ተፈጥሮ አያውቅም።

አንዳንድ መንግሥታት ሥልጣንን የዘላለም ርስታቸው አድርገው ከማሰባቸውም ባሻገር ህዝብንም ከመጤፍ የማይቆጠር አድርገው ይወስዱታል። ይህ አስተሳሰባቸው ስልጣናቸውን ያለ ምንም ገደብ እንዲጠቀሙበት ያደርጋቸዋል። አገር እንዴት ትለማለች?

ህብረተሰቡስ እንዴት ይሰለጥናል? ትምህርትን እንዴት ልናስፋፋ እንችላለን? ህብረተሰቡንስ እንዴት ከአስከፊ ድህነት ልናወጣው እንችላለን? ብለው ከማሰብ ይልቅ የሚያሳስባቸው ነገር ኃይልና ስልጣናቸው እንዴት ተከብሮ መቆየት እንደሚችል ሲሆን የመንግስታቸው እጅ ስፋትም ለጉርሻ ሳይሆን ለጥፊ እና ለጡጫ ይበልጥ ይመቻል፡፡ በመሆኑም በስልጣናቸው ለሚመጣና የተለየ አስተሳሰብ ለሚያራምድ ማንኛውም አካል የቆመበት ምድርን የምጽዓት ቀን (እርማጌዶን)[2] የደረሰበት ያስመስሉታል።

አገር ቀድማ የገነባችው የፖለቲካ ሥርዓት በመንግሥታት የጉልበት አጠቃቀም ላይ መልካምም ሆነ መጥፎ ተጽዕኖውን ሲያሳድር እንመለከታለን። ዴሞክራሲያዊ በሆኑ አገራት ላይ አዲስ የሚመጣው መንግሥት 'በእርግጠኝነት ዴሞክራሲያዊ ነው' ብሎ ከሁሉ በፊት አውቆ መናገር ባይቻልም የመሆን እጋጣሚው ግን ከፍተኛ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም በተዘረጋለት መሥመር ብቻ እንደሚፈስ የቧንቧ ውሃ ዴሞክራሲም በተዘረጋለት ሥርዓት ላይ መሠረቱን አድርጎ የሚቀጥል ስለሆነ ነው። ምናልባት ቀድሞ የተዘረጋው ሥርዓት ፈላጭ ቆራጭ ከነበረ ዋጋ እስከፍሎ እንጂ እንዲህ በቀላሉ በአንድ ጊዜ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊሸጋገር አይችልም። አሜሪካንን እንደ ምሳሌ ብናነሳት የምርጫው ሂደት፣ መንግሥት የሚሰጠው የኃላፊነት ልክ ወይም ሥልጣን፣ የመንግሥት ተጠያቂነት፣ ሚድያውና ፍርድ ቤቱ በአንጻራዊነት ነጻ መሆናቸው፣ ህብረተሰቡ መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ ማወቁ ወዘተ... አገሪቱ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንጂ ረግጠህ ግዛ ዓይነት ሥርዓታዊ አስተሳሰብ ምቹ እንዳትሆን አድርጓታል።

እንደ ማህበረሰብም ይህ አስተሳሰብ በብዙዎች ውስጥ የሰረፀ ይመስላል፡፡ ለዚህ እንደ ማሳያ የቅርቡን የዶናልድ ትራምፕና የሂላሪ ክሊንተንን ፉክክርና እሱን ተከትሎ ያስተዋልናቸውን እውነታዎች ማንሳት እንችላለን፡፡ በዚህ የምርጫ ፉክክር ወቅት ለስድስተኛ ጊዜ ፊትለፊት ተገናኝተው ያደረጉት የፍጥጫ መድረክ ላይ የተፈጠረው

2 ታላቅ የዓለም ፍፃሜ ጦርነት ማለት ነው።





አንድ ክስተት ዶናልድ ትራምፕን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፈላቸው ሲሆን ደጋፊዎቻቸውን ጭምር አስደንግጧል፡፡ በዚህ የመጨረሻው መሟገታቸው ወቅት እንደሁልጊዜ ሁሉ አጩዎቹ የምርጫውን ዉጤት በይፋ ይቀበሉት እንደሆን ለቀረበላቸው ጥያቄ ዶናልድ ትራምፕ አዎንታዊ ምላሽ አለመስጠታቸው ድፍን አሜሪካዉያንን ያስደነገጠ ነበር፡፡ ክስተቱም አሜሪካዉያን በምርጫ ሥርዓቱ ላይ ያላቸው ፍጹማዊ እምነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

አንዳንድ መንግሥታት በህገ መንግሥታቸው ላይ የሚያስቀምጡት ሀሳብ ለመንግሥት ከለላ ከመሆን በቀር ሌላ ምንም ነገር እንደማይፈይድ በተለይም ባላደጉት ሀገራት ዘንድ በግልጽ የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ምንም እንኳን ህገ መንግስት፣ ህይማኖትና መንግሥት የተለያዩ መሆናቸውን በግልጽ ቢያውጅም፣ ህግ አውጪ፣ ህግ ተርጓሚ እና ህግ አስፈጻሚ የተለያዩና አንዱ ከአንዱ ነጻ ናቸው፣ ቢልም... በጣም ዴሞክራሲያዊ ነኝ ቢልም መንግሥትም ሆነ ሌላው አካል ሁሉም አካላት ከህግ በታች ናቸው፣ ቢልም... በቡድን ተደራጅቶ ፖለቲካዊ አስተሳሰባቸውን ያለምንም ተፅዕኖ የማራመድ መብት አላቸው፣ ብሎ ቢያስብም እውነታው ግን የተገላቢጦሹ ሆኖ ይታያል፡፡ የእምነት ስፍራውም ሆነ የህግ አስከባሪ አካላት መንግሥቶቹ ለሚሏቸው ኃይሎች የተለጎመ ፈረሶች ሆነው ያገለግላሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አራት

## ኃይልና ሥልጣን በኢትዮጵያ

በቀደመው ምዕራፍ 'ሥልጣን ምንድን ነው? ' በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር የጀማመርነውን የኢትዮጵያን የሥልጣንና ኃይል አጠቃቀም ታሪክ እዚህ ስር በስፋት እንቃኛለን፡፡ የተሻለ ግንዛቤ መፍጠር ይቻል ዘንድም በዘመን ታሪክ ላይ አካሄዳችንን ወደ ፊት አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ ም ወደ ኋላ እየተመለስን ምልከታችንን የምንቀጥል ይሆናል።

በኢትዮጵያ ሶስት ሺህ እና ከዚያ በላይ ዘመናትን ያስቆጠረው ታሪካችንን በተለይም ደግሞ የሥልጣንና ኃይል አጠቃቀሙን የተመለከትን እንደሆነ ከሞላ ጎደል ሁለት ጉልህ ባህርያት ሲንፀባረቁበት ይስተዋላል። የኃይልና የሥልጣን ቅርፁ በወታደራዊ አቅሙ የተመካና በሃይማኖት የተደገፈ ሆኖ የምናገኘው አንደኛው መልኩ ሲሆን ከጀብዳዊ ቅንነት ይልቅ ጀብዳዊ ጭካኔ የጎላበት ሌላኛው መልኩ ሆኖ እናገኘዋለን። በእነዚህ ሁለት የስልጣንና ኃይል አጠቃቀም ባህርያት ላይ ተመሥርተን እያንዳንዱን ጉዳይ በፈርጅ ከፋፍለን የታሪክ ፍተሻችንን እንጀምር።

ወደ መጀመሪያው ጎራ በመመለስ... በወታደሩና በሃይማኖት ትከሻ ላይ ተፈናጦ ወደ መንበር የመጣውን የሥልጣንና የኃይል አጠቃቀም እንይ!



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሥልጣን በሀይማኖት... ኃይል በወታደር...

በትክክል መገንዘብ እንደሚቻለው ያሳለፍናቸው ሁለት አልፍ ዘመናት መንበርና ሥልጣን መሠረቱን ወታደራዊ ኃይል ላይ የጣለና ሀይማኖትን ምርኩዙ አድርጎ የጨበጠ ሆኖ እናገኘዋለን። ከንግስና ስያሜው ብንጀምር በትረ ስልጣኑን የሚጨብጠው ንጉሥ ነገዱን ከእስራኤላዊው ሰለሞን፣ የተሾመውም በእግዚአብሄር እንደሆነ ይገልፃል። 'ሞአ አንበሳ፣ ዘእምነገደ ይሁዳ፣ «ስዩመ እግዚአብሄር አገሌ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ»የሚል ተቀፅላ ይኖረዋል። ይህንንም በየአደባባዩ እየሰበከና እያሰበከ ይኖራል።

ይህም የሚሆነው ተራው ህዝብ በፈሪሃ እግዚአብሔር እየተሸበበ የሥልጣን ይገባኛል ጥያቄ እንዳያነሳና ድምፁን አጥፍቶ እንዲገዛ ለማድረግ ነው። በሌላም በኩል ፈሪሀ እግዚአብሄር አብዝቶ የተጫነውን ህዝብ ይበልጥ በሚፈራውና በሚያመልከው ፈጣሪ ስም ማንበጥ ነው፡፡ ድርስ እግዚአብሄር የሾመውን፣ የሁሉ ፈጣሪ የጥበብና የኃይል ባለቤት ካደረገው ከንጉሥ ሰለሞን ዘሩ ለተመዘዘውና ለሥልጣን ከተገባው ዙፋንን ለመቀማት፣ ሥልጣንን ለመንጠቅ፣ በኃይል ለመገዳደር፣ ወዘተ መሞከር መናፍቅነትም ተደርጎ ስለሚፈረጅ ጠያቂ የለም፡፡

በዚህ መልክ እያሉውን ህዝብ ከዙፋን ምኞት ገድቦ በማቆየት በከፍተኛ ሁኔታ ሥጋትን ቀንሶ ንጉሡ የሥልጣን ላይ ቆይታውን ያራዝማል። ከዚህ ባለፈ ደፍሮ የሚመጣውን ለመመከት በዋናነት የወታደር ኃይል በማጠናከር የሚመከቱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዝምድናና በጋብቻ በመያዝ፣ ማባበያዎችን በመስጠትና በመሳሰሉት መንገዶች ንጉሣውያኑ የቆይታ ጊዜያቸውን እያራዘሙ ሲገዙ ኖረዋል።

ንጉሣውያኑ ሃይማኖትን ለማስፈራሪያነት ብቻ ሳይሆን አደጋ በመጣ ወቅትም ድጋፍ ለማግኘትም ይጠቀሙበታል። በ16ኛው ክፍለ-ዘመን አካባቢ ተነስቶ የነበረውና የሁለት ሃይማኖቶች ጦርነት





ተደርጎ እስከመወሰድ የደረሰው የደጋማው ንጉሣዊ ሥርዓትና የቆላማው ንጉሣዊ ሥርዓት ጦርነቶች በተለይም የግራኝ አህመድና የልብነድንግል የማዛት ማስፋፋት ውጊያዎች ሀይማኖትን እንደትልቅ መሳሪያነት ተጠቅሞ የተፈፀመ ስለመሆኑ ታሪክ ይነግረናል። እነዚህ ሁለት ተቀናቃኞች በአገር ውስጥ ያለው ህዝብን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገራትን ከጎናቸው (ፖርቹጋል ከልብነድንግል እና ቱርክ ከግራኝ አህመድ ጎን) እንዲሰለፉ ለማድረግ ሀይማኖትን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ ተጠቅመውበታል። ከዚሁ ጋር በተገናኘም በተለያዩ ዘመናት በግዳጅ የመሪዎችንና የህዝብን ሀይማኖት የማስቀየር ተግባራት በአያሌው መፈፀማቸው ሊጠቀስ ይችላል።

እንደ እኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ የቀደመው ጊዜ ንጉሣዊ ቤተሰቦች ዕድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ ያዋጣናል፣ የሚሉትን ሌሎችም ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ነበር። መርዘኛ ሃሳብ በሥልትና ዘዴ ቀምመው ተንኮልን ወደ ህዝብ መርጨት ከሚጠቀሙት አንዱና ዋነኛው የፖለቲካ መሳሪያ እንደሆነም ይታወቃል። ይህም ህዝቡ እርስ በእርስ እንዲቃቃርና አንድ ጥግ ይዞ እንዲቆም ማድረግ ነው፤ ዓላማው። አንዱን 'ቆንጆ ነህ' ብሎ ሌላኛውን 'ታስጠላለህ'፤ አንዱን አዋቂ ሌላውን ሞኝ፣ አንዱን የቤት ልጅ ሌላውን የእንጀራ ልጅ፣ አንዱን አታቢ ሌላውን ቀራፊ፣ አንዱን አወዳሽ ሌላውን ተወዳሽ፣ አንዱን ምርት ሌላውን ገለባ፣ አንዱን ተሳዳቢ ሌላኛውን ሰዳቢ በሚል ጎራ ለይተው ከፋታቸውን በማናፈስና በማራገብ ከላይ ሆነው የበላይ ጠባቂ የሚመስሉ 'አፈ ቅቤ፣ ልበ ጩቤ' የሆኑ መሪዎች ያሉባት አገር መሆኗን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በዚህም የተነሳ የታሪካችንን አመዛኝ ክፍል ዘር እየተቆጠረ፤ እምነት እየተለየ፣ እርስ በእርሳችን ስንጫረስ መኖራችንን የቃልም ሆነ የፅሁፍ መረጃዎች ያስረዳሉ። ውሀ ቀጠነ ተብሎ ምታ ነጋሪት፣ ክተት ሠራዊት፤ ሲታወጅባት የነበረች አገር መሆኗ ግልጽ ነው። ጅግንነት ይለካ የነበረው በተጣሉ ግዳዮች ቁጥር፣ ሥልጣን ይገኝ የነበረውም በምርጫና በህዝብ ፍላጎት ሳይሆን በመንግሥት ግልበጣ አሊያም በውርስ ስለነበር ህዝብ ከላይ የሚጫንበትን



t.me/OLDBOOKSPDF

ውሳኔ ሳያንገራግር ከመቀበል በቀር ለምን ብሎ የማይጠይቅበት ሀገር ነበረች። በአጠቃላይ ባለሥልጣናቱ ስለ አንተ የማያውቅልህ የምበጅህ እኔ በመሆኔ አንተ ዝም ብለህ የምሰጥህን ተቀበል ይሉ ነበር። ከዚህም ባሻገር የኃይል አጠቃቀማቸውም ጭምር እጅግ ሲበዛ ከሰብዓዊነትና ከፍትሃዊነት የራቀ ነበር። አንዱ የመሣፍንት ዘር ተብሎ ከፍተኛ ቦታ ሲሰጠው አንዱ ደግሞ የተዋረደ በመባል ዝቅ ተደርጎ ይታይ ነበር። ብረት ቢሰራ ቀጥቃጭ፣ ልብስ ቢሰራ ቁጢጥ በጣሽ (ሸማኔ)፣ በባህል መድሀኒት ቢያድን ሥር ማሽ ቅጠል በጣሽ፣ ወርቅ ቢሰራ አንጥረኛ የሚሉ ተቀጥያ ስሞች ይሰጡት ነበር እንጂ በሙያው ክብር አያገኝም።

## 'ጀብዳዊ ጭካኔ' የነገሠበት የኃይልና ሥልጣን ሥርዓት

አንዳንድ ጊዜ ጀብዳዊ ጭካኔንን ወደ ጀብዳዊ ቅንነት ለመለወጥ ጥረት ሲደረግ ይስተዋላል። በዘፈኖችን፣ በሥነ-ፅሁፋችን፣ በታሪክ መፅሀፋችን፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን፣ ሰው በተሰበሰበባቸው ቦታዎች፣ በሀውልቶቻችን... ብዙ ብዙ ነገሮችን ተጠቅመን ጀብዳዊ ጭካኔ እየተወደሰ ይሰበካል።በጥቂት ማር የተለወሰ እሬትን ሙሉ ማር ተደርጎ ትውልድ ይጋታል። ሚዛናዊ ሳይሆን፣ ጭካኔው በቅንነት ተተክቶ ይመሰከራል።ሚዛን ከግራውም ከቀኙም ያለውን ገምግሞ ይዳኛል እንጂ ከመጀመሪያው ለአንዱ ዝቅ ለሌላው ከፍ ያለ ግምት በመስጠት እንደማይዳኝ ይታወቃል። የእኛ ግን በተቃራኒው ሆነ...!

ይህ ጀብዳዊ ጭካኔን ወደ ጀብዳዊ ቅንነት መቀየር ማለት ምን ማለት ነው? ... ይህ ልምድስ ከየት የመጣ ነው? ... የጀመረውስ መቼና እንዴት ነው? ... በማለት እንጠይቅ፤ መልሱንም የጋራ ፍተሻችን ውስጥ እናገኘዋለን። አንድ እውነት ግን መዘንጋት የለብንም፤ በኢትዮጵያ ማህበራዊ፤ ባህላዊና ትውፊታዊ ታሪክ ውስጥ ፖለቲካ ስራ ጥላውን አጥልቶበት እንዳለፈ እንረዳለን።

ከሥር ከምንጩ የደፈረሰ ውኃን ተከትሎ ከወደ አናት የጠራ ውኃ





ማጠጣት አይቻልም። የእኛ መሪዎች እና የፖለቲካ ባህል ግን እንዲያ ሆኖ ነው የተገነባው። ከበቀል ምንጭ የፈለቀ ልንለውም እንችላለን። በሙሉ ዓይን ደፍረው እውነትን ማየት የሚችሉ መሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች ባለቤት ከሆኑ ሀገራት መካከል እኛ የመጨረሻዎቹ መጨረሻ ነን ብንል ያንስ እንደሆነ እንጂ አይበዛብንም። በፖለቲካ ምህዳራችን ገዝፎ ያጠላው ሀቅ፤ የእውነት ሁሉ ምንጭ ራሱ እውነት ሳይሆን ኃይል ነው። ጠቢብነት ብሎም እርቆ አስተዋይነት ከመንበረ ስልጣኑ ተኮራርፏል። በጥላቻ ተጋርዷል። መደማመጥ የድክመት እንጂ የጥንካሬ መገለጫ ተደርጎ አይታወቅም። በሸፍጥ በሰበሰቡት፣ ከደሃ አፍ ነጥቀው ባከማቹት መሳሪያ በለው፤ ንዳው፤ ሂድበት!... እንጂ ይቅርታ አትታወቅም። መጠፋፋት ግን እንደ ክረምት አረም ሠርክ ዙሪያችንን ሸፍኖናል።

በግራኝም ሆነ በልብነ ድንግል ዘመነ-መንግሥት ሂደቱ እንዲያ ነበር። ቴዎድሮስ፣ ዮሃንስ፣ ሣህለ ሥላሴ፣ ሚኒሊክም፣ ተፈሪም፣ መንግሥቱም፣... የጭካኔውን ቀንበር፣ የጥላቻውን ድንበር አግዝፈውና አስፍተው ለቀቁት እንጂ 'ትውልድ ይዳን በኛ ይብቃ!' አላሉትም። የጥላቻው ልክ እስከምን በመሪዎቻችን ደምና አጥንት ውስጥ ዘልቆ እንደገባ ሕያው ምስክር የሚሆነን በመጨረሻውና የማንም መንፈስ በሚታጠፍበት ጊዜ እንኳ የሞት ፅዋው እስከሚሞላበት የመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ከክፋታቸው መንጠል አለመቻላቸው ነው።

ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ለእጄ ኃይለ ሥላሴ በደምም በዘሩንም የቀረቡና የተሳሰሩ የክብር ዘበኛ ጦር አዛዥ የጦር መኮንን ነበሩ። እኚህ ታላቅ ጄኔራል ኋላቀሩ የዘውድ ሥርዓት በህዝቡ ላይ ያደረሰውን መከራና ግፍ በቃ ለማለት ንጉሡ ለጉብኝት ወደ ብራዚል በሄዱበት ወቅት ማለትም ታሕሳስ ወር በ1953 ዓ.ም ከወንድማቸው ከገርማሜ ነዋይ ጋር በመሆን መፈንቅለ መንግሥት አካሄዱ። ዕድልም ከእነሱ ጋር ነበረችና የእዜውን ታላላቅ የጦር ኃላፊዎችና ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን "እቴጌ ታመዋል" ብለው ቤተመንግሥት ጠርተው በቁጥጥር ሥር አዋሉ። በመጨረሻ ግን



t.me/OLDBOOKSPDF

ዕድል ከጄኔራሎቹ ግንባር ፊቷን መለሰች። ይህንንም ጄኔራሉ በሚገባ ተረድተው እንደነበረ የታሪክ ተመራማሪዎች ያመለክታሉ።

በመሆኑም ከዚያ በመለስ ከመፈንቅለ መንግስቱ ጋር ተያይዞ ደም ማፍሰስን የሚጋብዝ ሁኔታ አልነበረም።መፈንቅለ መንግሥት አድራጊዎቹ ግን፣ አቴጌ ታመዋል ብለው የጠሯቸውን የንጉሡ ከፍተኛ ባለሟሎችን በመትረየስ ጥይት አስደበደቧቸው። ኢትዮጵያም ከፍርድ ውጭ ከሚደረግ የጅምላ ግድያ ጋር በአደባባይ ተዋወቀች። ኢትዮጵያውያኑ ዳግም ከፋት ሠሩ፡፡ በአምስት ዓመት የጣሊያን ወረራ ዘመን በጉድባ ሸለቆዋ ቆላ ወርደው ደጋ ወጥተው የታደጓትን የጦር ሰዎቿን አጣች።

ያም ሳያበቃ አፄውም በተራቸው ከብራዚል ተመልሰው ጄኔራል መንግሥቱ ነዋይን ጨምሮ መፈንቅለ ሥመንግስት ሙከራ አድራጊዎቹን በመግደል በርካብና መንበር አገራዊ ታሪካችን በሞት ላይ ሞትን ጨመሩበት።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በሃሳብ የተለዩዋቸውን ወይም የተቃወሙዋቸውን በግፍ ሲገድሉ፣በግፍ ሲያስሩ ወይም ጭካኔያቸውን ሲያሳዩና አገሪቱን የእርቆ እሳቢና ተቆርቋሪ ዜጋ መካን ሲያደርጓት ያ የመጀመሪያቸው አልነበረም። በእድዋ ላይ በተባበረ ክንድ ድል የተመታው ጣሊያን እርባ እመታት ቆጥሮ፣ በመሳሪያ ተደራጅቶ ዳግም ከወረረንና የቅኝ ገዢ ቀንበሩን ማሳረፉን ካረጋገጠበት የማይጨው ውጊያ፣ አፄው ወደ ስደት ሊያመሩ በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ ልጅ ኢያሱ ሠላሌ አካባቢ በግዞት እስር ላይ ነበሩ። እናም አፄ ኃይለ ሥላሴ ልጅ ኢያሱን ከእስር አውጥተው በማስገደል ነበር፣ ወደ ስደት ያመሩት ይባላል። የተቀበሩበትም ቦታ እስከዛሬ ያልተፈታ ሚስጥር ሆኖ ዘልቋል። ለልጅ ኢያሱ የተነፈገ የምህረት ፅዋ ለበላይ ዘለቀ አልተቀዳችም፡፡ ከንጉሡ መቃረኑ በገመድ ስቅላትን አትርፎለታል።

'በ ጊዜ ለኩሉ...' እንዳለ መፅሐፍ፣ አጼ ኃይለ ሥላሲም ከልጅ ኢያሱ





የተሻለ ዕጣ ፈንታ አልነበረም የገጠማቸው። እርሳቸውም በተራቸው በደርግ የጭካኔ መዳፍ በእርጅና ዘመናቸው ሕይወታቸውን ተቀሙ። ይቅርታን በማያውቀው የፖለቲካ ባህላችን እርስ በርስ መጠላለፋችን በከፋ መልኩ ቀጠለ፣ የሚሊዮን ዜጎችን ሕይወት እየቀጠፈ። የቀደሙት ማለትም ባልዘመነው ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው ልማዳውያኑ ንጉሦቻችን ለአፋሽ አጎንባሽ እንጂ የትችት ሀሳብ ለሚሰነዝርባቸው ወገን ቦታ አልነበራቸውም። በሃሳብ የተለያቸውን ያለምህረት ይገድሉ፣ ግዞትም ይልኩ ነበር።

በአደባባይ እየሳቀ በድብቅ የተቃወመን መመረዝ፣ አፍኖ ማጥፋት፣ የሚወጣና የሚያፈራ የተቃውሞ ችግኝን በእንጭጩ መቅጨት፣ የአገርና የሕዝብ ተስፋን ማምከን የሥልጣን ዘመን የሚረዝምበት ዋና መሳሪያ ሆኖ ዘለቀ። በእነርሱ መካነ መቃብር ላይ ዙፋናቸውን የማቆም እድሉ የገጠማቸው የየዘመኑ ገዢዎችም ቢሆኑ በመልክ ካልሆነ በቀር ከግብር አባቶቻቸው አልተለዩም። እንደውም መጠላለፉንና ከመድረክ ጀርባ አደናቅፎ መጣሉን አርቅቀው ቀጠሉበት።

መንግስታዊ የሥልጣን መንበር ላይ የተደላደለው ገዢ ብቻ ሳይሆን ወደዚያ በመንደርደር ላይ ያለውም ዜጋችን ቢሆን የፖለቲካ ባህሉ ከዚያው ከጥንታዊ ጀብዳዊ ጭካኔ የሚቀዳ በመሆኑ ጀብዳዊ ቅንነት የሚያውቅ አልነበረም ቅኝቱ። እናም ኢህአፓ፣ መኢሶን በሚል ጎራ ተከፋፍለው እያሉ የኢትዮጵያ ተስፋዎች የጥይት እራት ሆኑ። በቆራጥና ባንዳ፣ በወዛደርና ላባደር ርዕዮት ተለያይተው የአንድ አገር ልጆች በቀይና ነጭ ሽብር ተላለቁ። ጓድ የጓዱን ሕይወት ለመቅጠፍ አለመመለሱን በኢህአፓ ሀ እና ለ ክፍፍል አንድ ትውልድ የከሸፈ ጥይት ሆኑ። የዚህ ጉዳይ እንቆቅልሽ ይበልጥ የሚጎላው ደግሞ እነዚህ ቡድኖች ዛሬም ድረስ ከመወነጃጀል ተሸግረው የሚስማሙበት ነጥብ አለመኖሩ ነው፡፡ እስከመቃብር የሚወርድ ጥላቻና ፍረጃ!

ወላጆች ጧሪያቸውን ተነጠቁ። አገር ተረካቢ ታዳጊዎች ያለ



t.me/OLDBOOKSPDF

ወንድም፣ ጋሼና እታበባ ከባዱን ሕይወት በራሳቸው መጋፈጥ፣ የእናቶቻቸውና አባቶቻቸውን እንባ እንጂ ሳቅ ሳያዩ ማደግ ዕጣ ፈንታቸው ሆነ። በባህላዊ ንጉሦቻችንና በዘመናዊ አምባገነን መሪዎቻችን መካከል ያለው ልዩነት የዘመን እንጂ የግብር ሊባል እንደማይችል ታሪክ ምስክርነቱን የሰጠውም በዚህ ጊዜ ነበር። ከትላንትናዎቹ ጨካኝ ጀብደኞች ሥልጣን የተረከቡት አዲሶቹም ገዢዎች አባቶቻቸው ባዘገሙበት መንገድ ከማዝገም ውጪ ሌላ ፈለግ መተለም ሳይሆንላቸው ቀረ። ዛሬ ያኗት ዛሬ ከመምሸት ወዲህ የተገኘች ሌላ ቀን ከመሆኗ ባሻገር በሁሉ ነገሯ ቁርጥ ትላንትን መሰለች፣ ትናንትናን ሆነች።

ባህላዊ ንጉሦቻችንም ሆኑ ዘመን አመጣሾቹ ወራሾቻቸው የነገሡበትን ዘመን ብቻ አይደለም ገድለውና ቀብረው ያለፉት። ቀጣይ ዘመንና ትውልድንም እንጂ። ዛሬ እንገታችንን እቅንተን የምንቆምባት አገር ያሳጣን ዕድል ዕጣ ፈንታ ፈቅዳላቸው መንበር ላይ የወጡ ገዥዎቻችን በአደባባይ በረጩት የጥላቻ የታሪክ መርዝ እርማት ተጠምደን እየተጓተትን ለለን። የቅርብም ሆኑ የሩቅ ገዢዎቻችን ከሌላ ጥላኔት እንደመጣ ፍጡር ኢትዮጵያዊነት ላይ የሚዘምቱት፣ አንድነትን የሚታረኑት፣ የዴሞክራሲ ጠላት የሚሆኑት ኢትዮጵያዊነት የፍቅር የብልፅግና እንቅፋት በመሆኑ አይደለም። ይልቁንም ራሱ ፍቅር በመሆኑና የሚዘመትበትም ኃይል እንደሆን ስላመኑ እንጂ። ከነሱ አፈ-ታሪክ በላይ ግርማና ደርዝ ያለው መሆኑም ከነሱ ደጃፍ ውጪ አንድም መጠጊያ ደጅ እንዳይኖር ስለሚሹ ነው።

ግን ደግሞ ተወደደም ተጠላ እያንዳንዱ ሕዝብ እያንዳንዱ ትውልድ ባህሉን፣ ኑሮውን፣ ሕይወቱን... መሠረት አድርጎ ከፍ ያለ ክብርና ሞገሱን የሚቸረው ቅንነት የተላበሰ ጀብዳዊ ጀግንነት ወይም መሸሸጊያ መንፈሳዊ ጥላ ይሻል። ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከባርነት ወደ ነጻነት ለመሻገር፣ መከራና በደሉን ይረሳበት ታዛ ይመኛል።





መሻቱንም ጠቢብ ልጆቹ በአፈ-ታሪክ፣ በዘፈን፣ በግጥም ይገልጹለታል፣ ያስፋፉታል፣ ይሰብኩታል። ትውልድም ከዘመን ዘመን ተቀባብሎ ያሻግረዋል። በዚህ ሁሉ ተፈጥሯዊ ምሽግ በትላንት ሰቀቀን በነገም ተስፋ ባለንበት በዛሬ ከበብ ውስጥም ቢሆን ግን እንደ ጥላሞት ሲላ ሰማያችንን የሚዞር የጀብዳዊ ጭካኔ መንፈስ እንዳጠላብን በቀላሉ መመልከት እንችላለን፤ ግን እንዴት?

### ዳግም 'ጀብዳዊ ጭካኔ' ወዳጠላበት መንበረ ሥልጣን

"እንበሳሣ ምን ይበላል...?"

ጀብዳዊ ጭካኔ በመንበረ ሥልጣኑ፣ በባህላችንም ሆነ በህልውናችን ላይ ያጠላው ጥላ፣ የፈጠረው ችግር ጉልህ አሻራ አትሞብን ያለፈ ነውና ከእንበሣ ተፈጥሮ ጋር እያዋዛን ዳግም ምልከታችንን እንቀጥል። ጀብዳዊ ቅንነትም ሆነ ጀብዳዊ ጭካኔ ምንጩ የአንድ ህዝብ ባህል፣ ለጀግና የሚሰጠው ክብር፣ መገለጫው እንደሆነ ተነግሮ ያለቀ እውነታ ነው። እውቀን ይሁን ወይም ደመነፍስ ተግባቡን ባይታወቅም 'ጀግና እንወዳለን' ሳይሆን 'እናመልካለን' ብንል አይበዛብንም። ዘፈኖችን፣ ሙገሳችን፣ ጌረርሳችን፣ ቀረርቷችን (ሽረ እንደውም አንዳንዴ ማህሌተ ገንቧችን ሳይቀር...) ጉድ ነው። ከጀግናም እንበሣዊ ጀግና። እንከት፣ ሰብር ድቅቅ የሚያደርግ፣ ምህረት የለሽ ጀግንነት። ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ በሁሉም ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ዘንድ አንበሳ ያለው ተምሳሌት ያው ተመሳሳይ ነው፤ ጀግንነት እና ጀግንነት ብቻ። እሮሞው 'ሊንጫ ኪያ' እያለ ጌረርሳውን ቢያወርደው፣ አማራው እንበሳዩን ቢቀባበለው፣ ትግሬው ሁኔታይን ቢሸልለው... የሁሉም የመባያ ጉዳይ አንድ ነው። ከጀግንነትም የሚሻገር ድንቅ ጀግንነት። እርግጥ ጥንካሬን ከአንበሳ ወስዶ ያን መሰል ምሥል መሥራት ፍቁድ መሆኑን ሳንስት ሰፊው እሳቤ ግን ከዚህም የሚሻገር ትርጉምን እንደሚይዝ አንድም እያልን ሌላ እያከልን ጥቂት ነጥቦችን መዳሰስ እንችላለን።



t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም ከሚገባን በላይ ዓይናችንን ከፍተን ራሳችንን ውስጣችንን ማየት የሚገባን ሕዝቦች የሚያደርገንም ሌላ ሳይሆን ጣራ ግድግዳችን፣ አየር አፈራችን አንዱም ሳይቀር ጅማቱን ጨምሮ አንበሣ የሆነበት ሀገር ላይ የምንኖር መሆናችን ለሚቀጥለው ወጋችን መነሻ ተደርጎ ተወስዷል። እውነት እውነት እላችኋለው በዓለም ላይ እንደ ኢትዮጵያውያን አንበሳ አምላኪ ህዝብ አለ ማለት ከባድ ነው። ስሙ ያልታተመበት አንድም የህይወታችን ቅርንጫፍ አናገኝም፡፡ ታዲያ ለተገቢውና ምክንያታዊው የአንበሳ ዉከልና ያለንን ክብር ሳንዘነጋ ማለት ነው፡፡

ከላይ ከንግሥናው መንደር እንነሳ፤ንግሥናው ከአንበሳ ጋር የተያያዘ ነው፤ የንግሥና ስያሜው 'ሞ አንበሳ' የሚል ተቀጥላ ይኖረዋል። የአገራችን ጀግና ስለ ጀግንነቱ ሲናገር ተቀባይነት የሚያገኝ የሚመስለው 'አንበሳ ገዳይ' ሲል ነው። እናም የነፃነት ተዋጊዎቻችን ስያሚያቸው ሌላ ሳይሆን አንበሳ ነው፤ ከአንበሳም ሀበሻ አንበሳ።

'ጥቁር አንበሳ'... 'አንበሳው ክፍለጦር'... በአየርም ሆነ በምድር መጓጓዣችን ስያሜው ላይ አንበሳ አናጣም። የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደ ባንዲራችን ሁሉ ምስላዊ መለያው አንበሳ ነበር፤ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ሎጎ አንበሳ ነበር፡፡ አንበሳ አየር መንገድ፣ አንበሳ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ አንበሳ አውቶቡስ። ይህም አልበቃ ስላለን ዳርማር ጫማ ፋብሪካን ከባለቤቱ ወርሰን አንበሳ ጫማ ፋብሪካ አልነው። ሆቴሊታልና ፋርማሲ. ቢወረድም ፍሰቱ አይለወጥም... 'ጥቁር አንበሳ' ሆስፒታል፣ 'አንበሳ ፋርማሲ'። ይህ አንበሳን የማፍቀር ጽኑ ስሜት በየሁላችንም ውስጥ ሊሰጥ የሚችል እልፍ ፍከራ ሊኖር ቢችልም ፍከራው ከሚነሳበት ሃሳብ ይልቅ የሚደርስበት ጥግ ውሃ የሚያነሳ የመሆኑን እውነት ግን በቀላሉ መረዳት እንችላለን፡፡

ጦርና ተዋጊው ከአንበሳ ጋር፣ በተለያየ ጊዜ የተጠቀምናቸው መገበያያ ገንዘቦቻችን፣ ሳንቲም፣ ብር፣ ባንክና ኢንሹራንስ... በአንበሳ የታጀቡ ናቸው። ለጎብኝ ከፍት የሆነ ያራዊት መኖሪያ በእኛ አገር





'የአራዊት እስር ቤት ወይም ማጎሪያ' አይደለም ስሙ፤ አንበሳ ግቢ እንጂ። ለአንበሳ ካለን ፍቅር የተነሳ ንጉሱን አንቀን ብንገልም ዘሬም ድረስ አንበሳው ከቤተመንግስት፣ ከዩንቨርሲቲ መግቢያ በር ላይ እንደተኮፈሰ ነው፡፡ ከለገሃር ባቡር ጣቢያ በቸርቸር ጎዳና ወጥተን በዶሮ ማነቂያ ወደ ስድስት ኪሎ ዩንቨርሲቲ እናምራ፡፡ ባቡር ጣቢያው ፊት ለፊት ከስደት የተመለሰው አንበሳ በሃውልት ተቀርፆ ቆሟል፡፡ ከፊት ለፊቱ ሶስት መቶ ሜትር ርቀን ሳንጓዝ አንበሳውን የቴሌ ሕንጻ ላይ ተሳፍሮ እናገኘዋለን፡፡

ብዙም ሳንርቅ የወጣበት ገንዘብ አንበሳ ያስመሰለውን የአንበሳ ሐውልት ብሄራዊ ትያትር አጥር ውስጥ ቆሞ ይጠብቀናል፡፡ እግረ መንገዳችንን ወደ ሂልተን ጎራ ካልንም ከበር የሚቀበሉን በቀኝ ባለጎፈር አንበሳ፣ በስተግራ እንስት አንበሳ ከልጆቿ ጋር በሀውልት ተመስላ ነው፡፡... አንበሳ በሌለበት ዘመን እንኳ የተፈጠረው ትውልድ ባደገበት በእሳት ዳር ወግ ሲመገበው ኖሯልና ከሽ ባለ ቁጥር 'አንበሳ ገዳይ' ሲል ይፎክራል። ፉከራውን ተከትሎ ሽለላና ቀረርቶውም አንበሳን እያነሳሳ ይቀጥላል።

**አንበሳው አንበሳው፣**

**አንበሳው ልጅሽ**

**ይኸው መጣልሽ!**

-------

**እናቴም አንበሳ**

**አባቴም አንበሳ**

**ሁላችን አንበሳ...**

በምንም በማንም ሊሻር በማይችል ደረጃ አንበሳ ኃያል ነው፤ የአራዊት ንጉስ። ብዙዎች ስለዚህ አራዊት ገድል በብዙ ዘግበዋል፡፡ የቢቢሲ ዶክመንተሪ ስለዚህ እንስሳ የሚነግረን እውነታዎች አሉ። ከሰው ልጅ አስቀድሞ ድንበር ማስመር፣ ግዛት መከለል የጀመረ



t.me/OLDBOOKSPDF

እራዊት አንበሳ ነው። በሽንቱ ምልክት በማድረግ ግዛቱን ያሳውቃል። ያን ድንበር ጠብ ፍልሚያ የሚሻ ካልሆነ በቀር የማንም እንስሳ እግር ማለፍ አትችልም። ከሚስቱና ለአቅመ - አንበሳነት ካልደረሱ የቤተሰቡ አባላት በቀር። በአንበሶች ምድር ንግሥና በኃይል ነው የሚገኘው። በአንበሳ ምድር መኖር የሚችለው አንድ ንጉሥ ብቻ ነው።

በመሆኑም ከራስ አብራክ የወጡ እና የእኅት የአክስት ልጅ የሆኑ ወንድ አንበሶች ለጉርምስና ሲደርሱ፣ ጎፈሬያቸው ሲበቅል፣ ዝምድና ተሽሮ ይባረራሉ። የሥልጣን ተቀናቃኝ ናቸውና ይሰደዳሉ። አቅም ካላቸው ተፋልመው ለመንበር አለዚያም እግራቸው ወደመራቸውና ከግዛታቸው ውጭ ወደሆነ ቀየ ለስደት ይዳረጋሉ። ተቀናቃኝ ግን ተሸንፎ ቢባረርም ተባሮ አይቀርም። ሲጠነክር ይመጣል። ይፋለማል - ለዙፋኑ። ከቀናው ወንድሙ ወይም የእኅቱ ልጅ የሆነውን ንጉሡን ይገድለዋል። ወይም በስተርጅና እድሜው ለስደት ይልከዋል።

አዲሱ ንጉሥ ድል ባደረገበት ግዛት ኑሮውን የሚጀምረው የቀድሞውን ንጉሥ የሚያስታውሱ ነገሮችን በማጥፋት ነው። ደቦል አንበሳ ከእናቱ ተነጥቆ ይበላል። ቅርጥፍጥፍ ይደረጋል። በእንስሳት ያልተለመደ ለዙፋን የራስን ዝርያ መቅጠፍ ከሰው ቀጥሎ አንበሳ ወይም ከአንበሳ ቀጥሎ የሚታወቀው በሰዎች ዘንድ ነው፤ አይምራቸውም። የራስን ዘር ቅርጥፍጥፍ አድርጎ ሲጨርስ ይቀጥላል፤ ጉዞውን ወደዘር መቀጠያ እንስት አንበሳ በመሄድ በየ5 ደቂቃ ከ32 ጊዜ በላይ ይገናኛታል። አንዱ ቢሰት በሌላው በቀጣይ 31 ሙከራ ዘሩን ለመቀጠሉ እርግጠኛ ለመሆን። ቢቃ ይኸው ነው፤ ሥራው። የአንበሳ ንጉሥ ተግባር።

ዘሮቹን እና ዙፋኑን ከጥቃት መጠበቅ እንጂ ምግብ ማፈላለግም ቢሆን በአመዛኙ የሴቷ አንበሳና የተቀናት ወጣቶች ኃላፊነት ነው። ቢጋራ በሕብረት ብሎ ነገር በአንበሳ አይታወቅም። ዘርሆን ተከተሀ የምታልፈው በጉልበት ብቻ ነው። ያ ያራዊት ንጉሥ ከአፍሪካ ደጅ





ተጠርጎ ወደመጥፋት የተቃረበውና በቅርቡ በኢትዮጵያ መሃል አገር ታየ ተብሎ የተጨፈረለት ያራዊት ንጉሥ እስከ ግብጽ እስክንድርያ ሁሉ ዘልቆ ይርመሰመስ የነበረ እንስሳ ነበር። ገና በደሙ በሥልጣን ለመቆየት በሚፈጽመው ጀብዳዊ ጭካኔ መድከም አይቀርምና የገነባው ግዛትና ዘር ከርሱ ጋር እየተመናመነ እየጠፋ መጥቶ ዛሬ ለሚገኝበት ብርቅዬነት ሊበቃ ችሏል። ሰዋዊው ኑሯችንም ከዚህ ብዙ የተለየ አልሆነም። የሥልጣን ቁንጮ ላይ የተቆናጠጡት ወይም ለመቆናጠጥ ሃሳቡ ያላቸው ሰዎች ባህሪያቸው ከአንበሳ ጋር የተወራረሰ ሆኖ እናገኘዋለን። አንበሳዊ ጀግና አምላኪነታችን ምን ዓይነት መሪ ሸልሞን እንደነበር አፄ ቴዎድሮሥን ማሳያ አድርገን ታሪክን እንፈትሽ።

በዘመነ መሣፍንት ብጥስጥሷ ወጥቶ ዘጎቿም በየጎጡ በሚበቅሉ ሽፍቶችና ነፍጥ አንጋች በነበሩት መኳንንቱና መሣፍንቱ መከራና ፍዳቸውን ያዩ በነበረበት ጊዜ ነበር የቋራው ልጅ ካሳ ብቅ ያሉት። የአንድነት ሥርዓት ለመትከል መጣራቸውን በማየት ከከፍታው ሊሰቅሏቸው የሚሞክሩ አሉ። በዚያው መጠን እድል፣ ዕጣ ፈንታ ንግሥናን እጃቸው ላይ የጣለላቸው እንጂ አንድም የመሪን ብልህነትና አርቆ ማስተዋልን የታደሉ አለመሆናቸውን በመጥቀስ የሚከሷቸውም በርካቶች ናቸው። እንደነዚህ ሰዎች እምነት እኚህ የዘመነ መሣፍንት ንጉሥ በጥንቱ ዘመን መሆኑ በጀ እንጂ ዛሬ ቢሆን ኖሮ እጅና እግር የመቁረጥ ምግባራቸው ከከፋው የአረብ ከሊፋዎች ጋር ሊያስተካክሏቸው ወደኋላ የሚመለሱ አይደሉም።

በርግጥ የዛሬዎቹ ከሊፋዎች እንደሚፈፅሙት ጭካኔ ሁሉ አጼ ቴዎድሮስም ከጠላት ጋር ያበሩ ዜጎች ምርኮኞቹን አርደዋል፣ በቢላ። የሰው ልጅን በመድፍ አፍ ላይ አድርገው ተኩሰዋል። ጆሮ ቆርጠዋል። ምላስ፣ እጅና እግር በተመሳሳይ ቆርጠዋል። ቤት ዘግተው አቃጥለዋል። ገደል ጨምረዋል። ምናልባትም የአፄ ቴዎድሮስን ጭካኔ ከዛሬዎቹ ከሊፋዎች የሚለየውና ከባድም የሚያደርገው አፄ ቴዎድሮስ ሙሉ ቀን ሲገድሉ ውለው ቀኑ ስላልበቃቸው ቆጥረው አሳድረው ቢነጋ ቆጥረው መግደላቸው ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚህ ድሌ ያልዘፈነ ጠላቱ ነው ብለው አዋጅ ለማስነገር እንዳልከበዳቸው ሁሉ ማንም ዘመድ የሞተበት እንዳያለቅስ በአዋጅ አስነግረው ለቅሶ ከልክለው ነበር። ደርግ ልጅህን ገድሎ፣ ሬሳውን መንገድ ጥሎ ወላጅን ማልቀስ አይቻልም፣ ብሎ የከለከለው ከግብር አባቱ አጼ ቴዎድሮስ ትምህርት መውሰዱ ግራሞትን ያጭራል።... 'የሚያስለቅስ በደል ከፈጸመብኝ ባላጋራዬ ይልቅ አታልቅስ ያለኝ ጠላትነቱ ከፋኝ ሲል ትግሬ የተረተው በዚህ የተነሳ ነው። ተፈጥሮን በዕግድ ማስቀረት።

በርግጥ ሥርዓት ሲታወስ፣ ሕይወት ባፍጢሙ ሲደፋ ካልሆነ በቀር ኑሮ የተለያዩ ምዕራፎችን አቅፎ ወይም በምዕራፍ ተከፋፍሎ የሚገኝ ነው። ሳትወለድ አትሞትም። መወለድ፣ ማደግ፣ ወጣት መሆን፣ መጎልመስ፣ ሙሉ ሰው መሆን፣ ማርጀት፣ በመጨረሻም መጃጀት... መሞትና መቀበር። የህይወት ምዕራፍ መደምደሚያው ሞትና ቀብር ነው። በልጅነት፣ በወጣትነት፣ በጉልምስና፣ በስተርጅና በአንዱ ላይ ማንም ቢሆን የሞትን ፅዋ ሊቀምስ ሊጎነጭ ይችላል፡፡ የዚያ ሰው ሕይወት በቋሚዎች ድምዳሜ የሚያገኘው ሲቀበር ነው። በቀሪ ልብ ውስጥ መቁረጫ ምላጩ ቀብር ነው።

ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጎረቤት፣ መንደርተኛ... በቻለው መጠን ሁሉ በቀብር ላይ እንዲገኝ የሚደረገው እንዲቀርጥለት ለማድረግ ነው። ቀብር ኢትዮጵያዊ ባህልም ነው። ደርግ ልጅህን ገድሎ አታልቅስ ብቻ ሳይሆን ሬሳውንም እንዳትቀብር መቁረጫውን ሲከለክልህ ሰብዓዊነትን ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያዊነትም ጋር ነበር ያቆራረጠን።... ደጃች ውቤ የአፄ ቴዎድሮስ አማች ናቸው። የሚስታቸው የጥሩወርቅ አባት። በዚያም ላይ በደግነት የሚታወቁ የዘመኑ መሥፍን ነበሩ። ይህ አምቻነት፣ ጋብቻም ሆነ ደግነት ደጃች ውቤን ከመቅደላ እስር አላዳናቸውም። እዚያው መቅደላ በእስር ላይ እያሉ ነበር፣ ሕይወታቸው ያለፈው። የጳውሎስ ኞኞ የአጼ ቴዎድሮስ ታሪክ እንዲህ በማለት ያን አጋጣሚ ያቀርበዋል።

"ከዚያን አስቀድሞ ማንም ዘመድ የሞተበት እንዳያለቅስ በአዋጅ ተነግሮ ነበር። ደጃች ውቤ ሞተው ልጃቸው ጥሩወርቅ ከተረዱ በኋላ ግን አዋጁ ተነሳ። ለቅሶ ተከልክሎ የነበረው ሕዝብም ለደጃዝማቹ የሚያለቅስ አስመስሎ የተቀበረ የልጁን፣ የባሏን፣ የሚሽቱንና የዘመዱን ሞት ህዘን በማልቀስ ቆረጠበት። ይህን ያስተዋለ ታዛቢም እንዲህ ሲል በመግጠም ታሪክን መዝግቦ አለፈ።

**"የኒታ ደጃዝማች ሁልጊዜ ደግነት**

**ዛሬ እንኳ ለደሃው እንባ አተረፉለት።"**

የሸዋውን አቤቶ ሰይፉን ተዋግተው ድል ባደረጉ ጊዜ የማረኳቸውን ወደ 500 የሚሆኑ የሸዋ ነፍጠኞች አንድ እጅ እና አንድ እግር ቆረጡ። ይህን ጊዜ ባሏ የተቆረጠባት የሸዋ ወይዘሮ፣

"አጼ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ

የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተው ሄዱ" ብላ ገጠመች።

ደጃች ተድላ ጓሉን ለመያዝ በተደረገው ውጊያ የተያዙትን 8 ሺህ ምርኮኛ እንደከብት አሳርደው ገድለዋል። አያረዱ ቢመሽ ቀሪውን ምርኮኛ ቆጥረው አሳደሩ፣ ሲነጋም ቀሪዎቹን ቆጥረው አሳርደው ገድለዋል። ይህን ያስተዋለ ታዛቢም እንዲህ ሲል በመግጠም ታሪክን መዝግቦ አለፈ።

**"እንጥረኛ ብዙ ከንጉሱ ቤት**

**ባላልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት።"**

በወሎው ጦርነት በውጊያ የማረኳቸውን ወለዬዎች እጅ መቆረጥና በገመድ አንገታቸው ላይ እንደከረባት ታስሮ መንጠልጠል ያየ የወሎ ሰው፣

"እራቱንስ ሚሽቱ ታጉርሰው

እረ ቂጡን በምን ያብሰው?" ሲል ገጠመ።

ንጉሱ ጆሮ ቆርጠው ባይበቃቸው ሥቅለዋል። ከዚህም ባስ ሲል ቤት ዘግተው በእሳት ማግደው ሕይወት ቀጥፈዋል። እሱም አልበቃ ቢላቸው ከነህይወት ገፍትረው ገደል ጨምረው ገድለዋል።

አፄ ቴዎድሮስ በጭካኔያቸው እንኳንስ ኢትዮጵያን አንድ ሊያደርጉ ይቅርና በመጨረሻው ሰዓት ያለ እጃቢ ብቻቸውን የተቆጣጠሯትን መቅደላ በአንዲት ጥይት አጥተዋል። አጨራረሳቸው እንደ አጀማመራቸው በድል የታጀበ አልሆነም። የንጉሱ ሃሳብ የአገር አንድነት ነው የሚለውንና ከዚም አልፎ ለቴክኖሎጂ፣ ራሥን ለመቻል ያደረጉትን ጥረት ብንቀበለው እንኳን ማሰብ በሚችል የሰው ልጅ ወላዊ ህልውና ውስጥ የሃሳብ ልዕልና የሚፈተሸው በሃሳቡ ከፍታ ብቻ ሳይሆን ወደ ትግበራ ጫፍ በሚሄድበት መንገድም ጭምር ነው። ይህ ደግሞ የትላንትም፣ የዛሬም ሆነ የነገ ገገር ሀሳብ ይመስለኛል። ከዚህ መነሻ (framework) የሚወጡ ብዙ ቀንበሮች እዚም እዚያም አልፎ ቦታ ቢኖሩም እነርሱ ማለት ከጅብዳዊ ጭካኔ የሚመነጩ እኩይ ተግባራት ናቸው።

"የሸዋውን ንጉስ ሲንቄ ሲንቄ

የትግሬውን ንጉስ ሲንቄ ሲንቄ

የጎጃምንን ንጉስ ሲንቄ ሲንቄ

ወንድ ያለራስዎ ገድለውም አያውቁ!" እንዲል ባለቅኔ የራሳቸውን ሽጉጥ ጠጥተው (የታሪክ ክርክሩ እንዳለ ሆኖ) ሕይወታቸው ሊያልፍ ችሏል።

በርጋታና በጸጥታ ለዘመናት አንቀላፍታ በመፍሰስ ላይ ያለችውን ጥንታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ አገር ድንገት አንቅተው ሥርዓት ልትከል፣ ለውጥ ላምጣ ያሉት ንጉሥ በግራና በቀኝ፣ በደቡብና በሠሜን አንድም ያልዘመቱበት ግዛት፣ አንድም ያልተዋጉት መሳፍንትና መኳንንት አልነበረም። ሸዋ፣ ወሎ፣ ትግሬ፣ ጎጃም፣ አገው ሁሉም የጭካኔ በትራቸውን ቀምሷል። የዘመኑን መንፈስ (sprite of the time) መቃኘት እና በነርሱ ጫማ እግርን አኑሮ





ማሰብ ያስፈልጋል የሚሉ ወገኖች እዚህም እዚያም ያሉ ቢሆንም የተፈጸመውን ያህል ግፍ እና በደል ፈጽሞ ዘመን ላይ ለማላከክ መሞከር ግን ሩቅ የሚያስኬዝ መንገድ አይደለም።

የተደረገውን ላለማድረግ ከዘመንም፣ ከመልከዓ ፖለቲካ ገጽታም፣ ከኢኮኖሚ አቅምም ወዘተ ይልቅ ከጅብዳዊ ቅንነት የሚመነጭ ንጹህ ሰውነት ይበቃል።

በታሪክ ፍርድ እዚህ ምዕራፍ ላይ ግርታ ሊገባን ይችላል። በርካታ አሳማኝ መከራከሪያዎች ሊቀርቡ ይችላሉ። ግራ ቀኙ፣ ፊትና ኋላው በእናብስት የተዋቀረ ሀገር፣ ከታሪክ ጣራ ላይ አንድ ሥበዝ መዞ ስለ አንድነት ቢያወራ፣ ጋፋት ላይ ሰላሰሩት ሴባስቶፖል መድፍ ቢሰብክ ወይም ለመጨከናቸው በሚወዷቸው ባለቤታቸው ሞት ሲያመካኝ ብታገኘው ማዘንም ሆነ መደነቅ አይኖርብህም። ጅግንነት ጅብዳዊ ጭካኔ እንጂ ጅብዳዊ ቅንነት ሆኖ ባያውቅ፣ ባያደና ባይሰማ ነው። በእናብስታዊ የጀግንነት ባህላችን ውስጥ እኔና እኔ ብቻ እንጂ እኛ ወይም አገር የሚለው ትልቁ ስዕል ቦታ የለውም።

አፄ ኃይለስላሴም በዚያው በጥንቱ ባህል ነው የቀጠሉት። በድንቁርና ሊታወረ ሕዝባቸው አይኑን እንዲገልጥ ት/ቤት ከመገንባት ይልቅ በየደብሩ ለክብራቸው መገለጫ ቤተመንግሥት ሲያስገነቡ መኖራቸው ነው የሚነገረው። ኢዮበልዩ ቤተመንግሥት፣ ሆራ ቤተመንግሥት፣ አዳማ ቤተመንግሥት፣ ወንዶገነት ቤተመንግሥት፣ ጅማ ቤተመንግሥት፣ ባህርዳር ቤተመንግሥት፣ ትግራይ ቤተመንግሥት፣ ኤርትራ ቤተመንግሥት፣ ሐረር ቤተመንግሥት፣... አገሪቷን ቤተመንግሥት በ ቤተመንግሥት አደረጓት አፄ ኃይለስላሴም። ሁሉም ቤተመንግሥት የንግሥናቸው መገለጫ ነውና ቢኖሩበትም ባይኖሩበትም የንጉሥ ያህል ይፈራል ይከበራል። ይጸዳል ይነጠፋል። በመንፈስ ብቻ መግዛት አይቻልምና በቤተመንግሥቱ ላይ የጦር ሥርዓት ይተከላል። እርስ በርሱ እንዲጠባበቅም እንዲጠብቅም ሆኖ። ንጉሡን ሳይሆን እርስ በርሱ እንዲበላላ ይደረጋል። አንዱ ሌላኛውን የሚጠብቅ ባለአራት

ደረጃ ደህንነት። ይህ ሁሉ መሆኑ በራሱ ችግር ነው ባይባልም ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ ባለመስጠት የተደረገና የራስን ክብር ብቻ ለማስጠበቅ የተደረገ እንበሳዊ ተግባር መሆኑ ሲታሰብ ልዳማው ብዙ ነው፡፡

ምክንያቱስ? ጅግናህ አንበሳ ነው። አንበሳ ደከም አይገዛም፤ ከደከምክ አትኖርም። ትገደላለህ። በገዛ ወገንህ። ስለዚህ ላንተ አሳሳቢና ዘውትር አስፈላጊው ጉዳይ ኃይልን ማጠናከር ነው። መፈራትን መገንባት ነው። ከነዘርህ… ከነዘርማንዘርህ። እስከብሮ የሚያኖርህ በእንዲህ አይነቱ ምድር ፍቅር አይደለም- ጉልበት እንጂ። ለዚህ ደግሞ እንደ አንበሳ ሁሉ ማስፈራሪያ እንጂ ፍቅር አይሰጠውም… ያን ጉልበት በዲፕሎማሲ አስማምቶ ለመምራት አያውለውም፤ ተቀናቃኙ ያለውን ጀርባ ለማድቀቅ እንጂ።

ልጆቿን መግቦ የማሳደግ ጣጣ ያለባት ሴት አንበሳ ናት። ወንዷማ ጎፈሬውን አቁሞ መተኛት ነው። አድነው ያመጡትን እየቀማ መብላት። ከዚያ ዝንብ እሽሽሽሽ እያሉ በቀን 18 ሠዓት መተኛት። እንዲህም ነግሠው እንዲህም አለፉ አጼ ኃይለሥላሴ። ኮሎኔል መንግሥቱም በንጉሳዊ ካባ ምትክ ወታደራዊ ዩኒፎርም ከመደረባቸው ውጭ በጭካኔያቸው ከአጼዎቹ የተለዩ አልነበሩም። ሠቅለዋል። ገርፈዋል። ረሽነዋል። አቃጥለዋል።

ኮሎኔሉም ጅብዳዊ ጨካኝ ናቸውና ሕዝቡ ይልስ ይቀምሰው አጥቶ ሲረግፍ እሳቸውም እንደ ኃይለሥላሴ ከደሃ ዜጋቸው አፍ ቀምተው ሠራዊታቸውን ቀልበውበታል። የጓሮ አትክልት መኮትኮቻና አፈር መዛቂያ የምታመርትበት የረባ የጎጆ ኢንደስትሪ የሌላትን አገር የታላላቅ ወታደራዊ ኢንዱስትሪ መናኸሪያ ለማድረግ ጋፋት ላይ ጠመንጃ ማምረቻ ፋብሪካ አቋቁመዋል። ሆርማት ላይ ሞርታርና አዳፍኔ ማምረቻ ፋብሪካ ተክለዋል። ዲከ ላይ ፈንጂ ባሩድ ለማውጣት አስቆፍረዋል። በጦር ባይሸነፉ ኖሮ ሕዝቡ በርሃብ እየረገፈ እሳቸው እንደ ዘመናችን ኪም ጆንግኢል ኢትዮጵያን ኒውክሌር ለማስታጠቅ የማይመለሱ ቆፍጣና ወታደር ነበሩ ኮሎኔል





መንግሥቱ ኃ/ማሪያም፡፡

በጣም አስገራሚና አሳዛኝ ቢሆንም ቀለም የቀመሱ ኢትዮጵያውያንም ከዚያው አንበሣዊ የባህል አዙሪት የወጡ ባለመሆናቸው በእሳት ዳር ወግ ሲሰሙ ያደጉትም፣ ሲዘፈን ሲሞገስ የሰሙትም አንበሳና አንበሳ ብቻ ነውና በአንበሳ ምድርም ከአንድ በላይ ንጉሥ አይኖርምና ሶሻሊዝም አይሰራም ተብሎ ተሞክሮ መውደቁ በተረጋገጠበት ዘመን አንድና አንድን ሶሻሊዝምን መረጡ። መቻቻልንም አላወቁምና እርስ በርስ ተላለቁ።

በጣም ከበዛ ጨዋነት ጋር ኃይሌ ፊዳም፣ ዶ/ር ተስፋዬ ደበሳይም፣ ብርሃነመስቀልም ሆነ ሠናይ ልኬ በታሪካቸው መስክረውልን ያለፉት እውነታ የቴዎድሮሥን፣ የኃይለሥላሴና የመንግሥቱ ኃ/ ማሪያምን ግብርን ነበር ብንል አጅግም ስህተት አይሆንም፡፡

ግራና ቀኙ፣ ፊትና ኋላው፣ ደምና ስጋው 'አንበሳና አንበሳ ብቻ' በሚል ግንብ የታጠረ ሕዝብ ከዚህ ውጭ ወይም ከዚህ ማዶ ተሻግሮ ጅብዳዊ ቅንነትን ለማምጣት ይገደዋል። አርሰው፣ ተሸክመው፣ አጓጉዘው፣… የሚበሉት እንስሶች ላይ ስድቡን ሽሙጡን እየሰነዘረ…

"አንበሳው አንበሳው ልጅሽ፤

ይኸው መጣልሽ" ከማለት ውጭ ሌላ ዘፈን አይኖረውም።

በየትኛውም ሰብዓዊ ሚዛን ልጅ ገድሎ ማልቀስ የከለከለ ጨካኝ የሚለው ስም አይበቃውም። የሚያስለቅስ በደል ካደረሰብህ ግፈኛ በላይ ሕመሙ የሚቆረቁርህ ማልቀስ ስትከለከል ነው፤ መቀበርን ስትነፈግ። የህይወት መደምደሚያን፤ የሀዘን መቋረጫን ስትነፈግ። የሆነው ሆነና ለጀግኖቻችን ማሞገሻ ሡብብ ከመኛት መውጣት ይጠይቃል። ጅብዳዊ ጀግንነት ይልቅ ለጅብዳዊ ቅንነት ቦታ የሚሰጥ ሉብ ያሻል።



t.me/OLDBOOKSPDF

የተቢታተኙችውን የአረብ ምድር በአንድ መንግስት፣ በአንድ ከሊፋ ላኖር ነው ብሎ ስለማለና ስለተዝዘተ አይኤስአይኤስን ከሥውነት ተርታ መመድብ እንደማይቻለን ሁሉ፣ ሠውን እንደከቡት ማረዱን፣ በፊንጂ ላይ አስቀምጦ መግደሉን፣ በፍርግርግ የብረት እጥር አስሮ ማቃጠሉን በውነት ስለውነት ይቅር ልንል የምንችልበት ምድራዊ ትህትና ሊኖር አይችልም። እውነት ይኖራል። ሚስታቸው ስለሞቱ፣ ስለከዷቸው ብሎ መከራከሪያ ማንሳት ይቻላል። አይሠራም አያስኬድም። የታላቅነት፣ የእርቅ አስተዋይነትና የመሬ መገለጫው የዓላማ ስኬት ብቻ ሳይሆን ወደስኬትም የተጓዘበት መንገድ ጭምር ነው። ብቻ ደርሰን ብዕር በጃችን ስለጨበጥን የጨካኞችን ስም በወርቅ ብዕር መከተብ፣ ተውኔት መፃፍ፣ ሀውልትና አደባባይ መሰየም ያንኑ ጅብዳዊ ጭካኔ ባህል አድርጎ ከማስቀጠል ባለፈ ወደ እድገት አይመራም። ምክንያቱም እንበሳ ያው እንበሳ ነው። ከነተረቱም፦

"እንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ

ምን ይከፍላል ማን ተናግሮ!"

እንዲል በሁላችን ላይ ፍርደ-ገምድል ዳኝነት ነው የሚነግስብን። ትላንት በተለያየ ዘመን እና ሁኔታ ውስጥ ይህችን ሀገር የመሩ ገዢዎቻችን ምንም እንኳን በጅብዳዊ ጭካኔ ብዙ አሳር ቢጭኑንም ከዚህ ሙተላለፍ በመለስ የሚነሳ ቅን ነገር የላቸውም ማለት ግን እንዳልሆነ ልብ ይሏል፣ በፍጹም። ነገር ግን ለተነሳሁበት ጉዳይ ጠቃሚው ነጥብ ብዙም ደፍረን የማንናገረውን እንዲህ ያለው እውነት በመሆኑ ነው እሱ ላይ ማተኮሬ። ከዚያ በመለስ ምን አለ? እንቀጥል።

## ከጅብዳዊ ጭካኔ መልስ

ከላይ የአገራችን የሥልጣን ሥርዓት ሃይማኖትና ወታደራዊ ኃይል የተጫነው፣ ጅብዳዊ ጭካኔ የሰፈነበት ነው ስንል ግን የቀድሞ መሪዎቻችን ፍጹም ለአገራቸው የማይገዳቸው ነበሩ የሚል





ድምዳሜ ለመስጠት እንዳልሆነ ቀደም ባሉት ክፍሎች በተወሰነ መልኩ ለመጠቃቀስ ሞክሪያለው። ምክንያቱም ለዚህች ሀገር የማማውን ጫፍ ሲመኙና ሲሰሩ የኖሩ መሪዎች የአገራቸውን ከፉ ከማየት የራሳቸውን ሽጉጥ ቢጠጡ መርጠው ለአንዴና ለዘላለም ይቺህን ዓለም ተሰናብተው አልፈዋልና፣ ኢትዮጵያ በባዕድ ልትወረር አይገባም በማለት ጀሮ ዳባ ላለ ህዝብ ከማስረዳት በላይ ወኔያቸውን ታጥቀው ተዋግተውላታልና፣ ስልጣኔን የሰይጣን ስራ በማለት ይኮንን በነበረ ህዝብ መሃል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማምጣታቸው ከሰይጣን ጋር ተዛመዱ ተብለው ታምተውባታልና፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከድንቁርና ሊወጣ ይገባል በማለት አሮጌትና ሽማግሌዎችንም ሳይቀር ሀ ሁ .... እያሉ አስተምረውባታልና፣ እሁንም ድረስ በቅኝ ግዛት ያልተያዙች አገር በማለት በኩራት ታሪካችንን እንድንተርክ አድርገውናልና እንዲሁም ህዝቤ ተራብቧል የማበላው ስጠኝ ብለው በእምነታቸው ለፈጣሪያቸው አልቅሰዋልና መሪዎች ሁሉ ስልጣናቸውን ለእጥፊ ተግባር ብቻ አውለውታል ብለን በጅምላ አንወቅሳቸውም።ሚዛናዊ ትችት እንጂ።

በተቃራኒው አዲስ ዕውቀትን የመቀበል ቀና ሂደትን የመከራ መንገድ ያደረገብን መሆኑንም በማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻል ነው። ምንም እንኳን የኃይል ሚዛን ወታደራዊ አቅሙን አጎልብቶ ግዛቱን መቆጣጠር በቻለው ነጋሽ እጅ መውደቅ ቢችልም፣ ዕምነታዊ ኃይል ላይ በማዘዝ ረገድ በነበረ የሥልጣን ውስንነት ሳቢያ ነገሥታቱ ዘመናዊ ሥልጣኔን የማስፋፋት ጥረታቸው ተወስኖ ለመቅረቱ የቴዎድሮስን እና ከዚያ በፊት የነበሩ ነገሥታትን ተወት አድርገን የአፄ ሚኒልክ እና የአጼ ኃይለ ሥላሴ አርምጃዎችን ከአዋጆቻቸው ተነስተን መመዘን እንችላለን።

ሰራተኛው በሥራው እንዲከበር እንጂ እንዳይሰደብ ከአፄ ምኒልክ የተነገረ አዋጅ።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሞዓ አንበሳ ዘ-እምነገደ ይሁዳ።

ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

ሠራተኛን በሥራው የምትሰድብ ቀወኝ!

አጼ ምኒልክ ይህ አምሮት ቢጋዎች ላይ ይለጠፍ የነበረው ሥም ሠላም ስለነሳቸው እንዲህ በማለት ዳግም በዚህ ሥም እንዳይነቋቸሹ አስጠንቅቀዋል። ለባለሞያዎች የስድብ ሥም እየሰጣችሁ ማፍውንና ጥቋቁን ጠፍ አምሮት እንዶ የሚሉትን አራሽ ገበሬ እያላችሁ፣ የሚነግደውም ወርቁንና ገንዘብን ይዞ በጋባ እንተ ነጋዴ ገባባ እያላችሁ፣ ሰራተኛውን ለተሮሮው ብሎ ጭንበስ ቀና በ.ልላችሁ አጣቢ እያላችሁ በየስራው ሁሉ ትሰድባላችሁ። ቀድሞ ይህ ሁሉ ፍጥረት የተገኘው ከዳምና ከሔዋን ነው እንጂ ሌላ ሁለተኛ ፍጥረት የለም። ይህ ሁሉ ካለመማር የተነሳ የምታደርጉት ነው። ሰራተኛ ካልተበረታታ ሁሉ በዘንተኛ ይሆናል። የመንግሥትም ጠግር ችግር ላይ ይወድቃል፣ አገርም ጠባቂ ታጣለች።

*"በወዲያኛው አገር ግን አዲስ ሥራ አውጥቶ መድፍ፣ ነፍጥ፣ ባቡር እንዲሁም እግዚአብሄር የገለጠለትን ሌላም ሥራ ሁሉ ቢሰራ መሐንዲስ እየተባለ ይመሰገናል እንጂ አይሰደብበትም። ከእንግዲህ ግን እንዲህ ብሎ የተሳደበ እኔን የሰደበ ነው እንጂ ሌላውን መሰደቡ አይደለም። ስለዚህ ሲሳደብ የተገኘ ሰው መቀጫውን አንድ ዓመት ይታሰራል።"*

በማለት ስለ እኩልነት ተናግረዋል።

*ጥር 17 ቀን 1900 ዓ.ም*

እንደ አጼ ምኒልክ ሁሉ አጼ ኃይለሥላሴም ገና አልጋወራሽ ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያን ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማሻገር መድኃኒቱ ትምህርት ብቻ መሆኑን በመረዳት ስላደረጉት ተጋድሎ በገንዘባቸው የበሩትን ተፈሪ መኮንን ተብሎ የተሰየመውን ትምህርት ቤት መርቀው ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ውስጥ እንዲህ በማለት ገልፀዋል።





«... ሰው ስለእገሩ ሲጠየቅ አገሬን እወዳለሁ የማይል የለም። ሆኖም ግን አገሬን እወዳለሁ ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ለምሳሌ አንድ ሰው እወደዋለሁ የሚለውን ወዳጁን በችግሩ ፈጥኖ ካልረዳው በተጨነቀ ጊዜ ደጦ ካልደረሰለት ወዳጅነቱ ፍሬ አይኖረውም። ዛሬ ባለንበት ዘመን አገራችን ኢትዮጵያ ለሥልጣኔ በምታደርገው ጉዞ ትልቅ ችግርና ጭንቅ ገጥሟታል፤ ይኸውም ለሥልጣኔ መሠረት የሆነውን ዘመናዊ ትምህርት ልጆቿን ለማስተማር አቅም ስለአጠራት ነው..."

አዲስ ዕውቀትን የመቀበል ቀና ሂደትን ለመላመድ መረዳት ወደሚለው ቀጠና ያለምንም ክልከላ መዘመት ይኖርብናል። ይህ ቀጠና ከማለስቦች የአተያይ ዝንባሌ የሚወጣና ሰፋ ባለ መልኩ ድርጅታዊ ድንበሮችን የሚያካልል እይታ ነው። በዚህም ምክንያት በተመልካቹና በሚመለከተው ነገር መካከል ግጭት ስለሚፈጠር ተመልካቹ ያለበትን ሥርዓት ጥልቅ ከሆነ የተለየ የዕይታ ማማ ለመመልከት ይገደዳል። የተወሰኑ ቡድኖች በዚህ መልኩ ዕይታን ሲጀምሩ በሥሮቻቸው የሚኖሩ ተከታዮችም ከሥርዓቱ ጋር ያላቸውን ቁርኝትና እንዴት በጋራ እንደሚገለገሉበት ራሳቸውን በማኪተት እንዲመለከቱ ያስችላቸዋል።

በእምነት ፊት አገሪቱ ያላት ጠንካራ መሠረት በእምነታም በአሰታም ሊገለፅ የሚችል ነው። ይህቺ ጥንታዊ አገር ታላላቆቹን ሃይማኖቶች ከሌሎች ሀገራት በተለየ መልኩ ሠላማዊ በሆነ ሂደት ማስተናገድ መቻሏና በህዝቧም ውስጥ መቻቻል የተሞላበት የኑሮ ባህል መፈጠሩ አስደናቂነት ያለው ሲሆን እሁንም ድረስ ኃይልና ሥልጣንን መጋረድ የሚያስችለው ጥንካሬ ያለው ብርቱ ኃይል በመሆኑ እና የቤተ ቋሚ መሠረት ከርሱ የሚቀዳ መሆኑ በቀጣይ ያገሪቱ ዕጣ ፈንታ ላይ የራሱ ተፅእኖ የሚያሳድር ገፅታ ያለው መሆኑን ማገዘቢ ውስጥ ማስገባት ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው።

ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስም ቢሆኑ ወደ አገራቸው ቴክኖሎጂን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለማስገባት ባለቸው መንሳሳት በጋፋት ላይ በባህላዊ መንገድ ብረትን ማቅለጥ የቻሉና "የኢትዮጵያ ህዝብ ደንቆሮ ነው" ብለው የሚያስቡትን አውሮፓዉያን አፍ ለማስያዝ ያደረጉት ጥረት ከልብ ህዝብንና አገርን የሚወዱ ለመሆናቸው አይነተኛ ማሳያ ነው። በሌላው የማንነት ሽራችን ላይ በወርቅ ቀለም የተሳለው ሙሉ መልካችን ደግሞ ከአያቶቻችን የወረስነው የኢብሮነትና የአልሸነፍ ባይነት ሞገሳችን፤ ከጀብዳዊ ጭካኔ ወዲህ ያለው ውብ ገጽታችን ነው፡፡ ስለዚህ ውብ ገጽ ጥቂት እንል ዘንድ ይገባል፡፡

## ጀብዳዊ ቅንነት ጭካኔን ሲሽር

ጀብዳዊ ጥፋትና ጭካኔ ከጀብዳው ቅንነት ጋር የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው። ሳንቲምን ወደ ላይ ወርውረን መሬት ላይ ስንቀበለው የሚያርፍበት ገፅ አንድም ፊት ወይም ጀርባ ከመሆን አይዘልም። በዚህም አግባብ የሀገራችንን ጀብዳዊ ቅንነትን ስንመለከታው ኩራት ነው። የሀገራችን አንድነትን፣ መተሳሳብንና ፍቅርን፣ አብሮ መጠጣትንና መብላትን፣ የሀገር ፍቅርና ወኔን ያንጸባርቃል። በውጭ ጠላት አልንበረከክ ባይነታችንን ምንጩ ሌላ ሳይሆን በቀጥታ ከአያት ቅድም አያቶቻችን የወረስነው ጀብዳዊ ቅንነት መሆኑ አያጠያይቅም። የኢትዮጵያ ህዝብ ስለ አንድ ዓላማ አብሮ መከራና በደልን፣ ሀዘንና ሰቃይን በጋራ ሲካፈል የኖረና ጅረት አቋርጦ፣ ተራራ ወጥቶ ረጅም ርቀት ተጉዞ ይረዳዳ የነበረ ማህበረሰብ ነው።

በምስራቅ አባድርን፣ ከምዕራብ ሼህ ሆጀሌን፣ ከጅማ ተነስተን አባ ጅፋር ቤት ቡና ተጋብዘን፣ በካም ጦና ሀገር ወላይታን አይተን፣ በአባ ታጠቅ ፈረስ ጥምቀትን አክብረን፣ ከበላይ ዘለቀ ሀገር ጣና ላይ ተንሳፈን፣ በሱልጣን አሊ ሚራ፣ በሚኒሊክ በሸዋ አድርገን ወደ መዲናችን አዲስ አበባ ዘልቀን ከገባን በማንነታችን እርስ በእርስ የተሳሰረ የአንድ ሥርወ ዘር ጥንክር ግንድ እንዳለን በሚገባ ሊገለጥልን እንደሚችል ዕሙን ነው። ከዚህ ውጭ ሊሆን የሚችለው አዝማሪዋ ያለችው ነው።





**ከጎንደር ባህር ዳር ስትመላለሽ፤**

**ወረታን አታዉቂ፤ ብሎ ሰው አማሽ።**

ይህ አብሮ የመብላትና የመጠጣት ባህልና ወጋችን፣ አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ የሚለው ሀገራዊ ማንነታችን በተለይም ደግሞ ለሀገር ጉዳይ ከምስራቅ ምዕራብ፤ ከሰሜን ደቡብ ለአንድ ዓላማ መጠራራት መቻላችን የዓድዋ ድል በዓልና የወታደራዊው አምባገነን መንግሥት መንኮታኮት ልዩ የእኛ የኢትዮጵያዊነት መገለጫዎቻችን ናቸው፡፡ ድሉ የጋራ ነው። የድሉ ውጤትም በመላው ኢትዮጲያዊ ደምና አጥንት ከስካሽ የመጣ እንጂ አንድን ወገን ለይቶ የሚቀባበ አይደለም፡፡ በታሪክ የተመዘገበ ማስረጃም ከቶ ሊቀርብ አይችልም።

ቴዎድሮስን ያለ ጎብርዬ፣ ሚኒሊክን ከራስ ጎበና ዳጬ ውጪ፣ ጦናን ያለ ሐሰን እንጃሞ፣ ተሰፋዬ ደበሳይን ከሃይሌ ፊዳ፣... ለይተን ልናስብ፣ ልንወድ ወይም ልንጠላ የምንችልበት ምን ምድራዊ እውነት ይኖራል?። ከቀረበም ግን ታሪኩ አንድም በንጉሣዊ ቤተሰቦች የተገፈ አለበለዚያ ደግሞ ንጉሣዊ ቤተሰቦችን የሚጠላ ወይም ራሱ ንጉሣዊ ቤተሰብ የመሆን ፍላጎት ያለውና በህዝቡ ዘንድ እንዲጠሉ ለማድረግ በፈለገ አካል ብቻ ትርክት ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በእርሱ የሚተሳሰብ አንድ የሆነ ህዝብ ነው። በደሙ ውስጥም ፀረ- ፋሽሽት ጀብዳዊነት ያለው ሲሆን ስለ ሀገሩ ሟች የሆነ ህዝብ መሆኑን በማይጨው፣ በዓድዋ፣ በጎሬ፣ በጅግጅጋ፣ በከሥም፣ በአሳይታ፣... አስመስክሯል። ስለሆነም ኢትዮጵያዊነት በግሉ ርስት ሊያደርጋት የሚችልበት ጀብዳዊ ታሪክ አልነበረም፣ ሊኖርም አይችልም። ኢትዮጵያዊነት ለኦሮሞ ወይም ለአማራ ህዝብ ብቻ ወይም ደግሞ ለትግራይ፣ ለአፋር፣ ለደቡብ፣ ለጉራጌ፣ ለጋምቤላ፣ ለሀረሪ፣ ለቤኒሻንጉል፣... ብቻ ከፍሎና ለይቶ ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦችን ባይተዋር የሚያደርግ ርስት አይደለም። ወደ ዕምነትም ወርዶ ለሙስሊም ወይም ለክርስቲያን ወይም ደግሞ ለባህል አማኞች ብቻ የተከለለ አይደለም። ፈረሱና ሜዳው ብቻ ሳይሆን ጋላቢውም ጭምር አንድ የጋራ ሀብት ነው። ከዚያ ባሻገር ያለውን እውነታና የላምኘህ ተጨፈን ጨዋታ ምንጩ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሊተንተንና ሊንሰላሰል የሚችለው በስነልቦና ሳይንስ ብቻ ነው።

## አዲስ ነገር ያላሳየችን ዓለም እና ጎህ የቀደደባት አገር

ጠቢቡ ሠለሞን ከፀሐይ በታች አንዳችም አዲስ ነገር እንደሌለና ውጤቱም ንፋስን እንደመከተል የከንቱ ከንቱ እንደሆነ በናገርም፣ የአዳም ዘር የትናንት ታሪኩን በመርሳት በፈጠረውም ባልፈጠረውም ደርሶ ጉድ! ሲል መመልከት ሥርከ ዕጣ ፈንታችን ከሆነ ዓመተ ኩነኔ አልፎ ዓመተ-ምህረት መም ላይ ተሰይመን ሌላውም የምህረት ዘመናችን ከፊታችን ተዘርግቷል። በአንድ ወቅት የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ባልቲሞር በሚገኘው የእስላሞች መስጊድ በመገኘት በዚያው በፈረንጆቹ አገርም ሆነ ከዚያም አልፎ በሀበሻ ምድር ወቸ ጉድ! ሲያስብል ማየቱ ይህንኑ ታሪካዊ እውነታ ያስታውሳል።

ጆሮ ያለው ይስማ

'ዋናው ቁምነገር ታሪክ መሥራት እንጂ ታሪክ መፃፍ አይደለም።' ሲል የዛሬዋን ጀርመን አሁን በምናውቃት መልክና ቅርፅ ፈጠራት የሚባለው ጦረኛውና ጨፍጫፊው ኦቶቫን ቢስማርክ ተናግሯል። በዋጋ ደረጃ ሊሆን ይችላል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉት ታሪክን በወጉ ላልፃፉና ላልመዘገቡ ሀገራት ግን ታሪክን ከመስራት ባልተናነሰ መልኩ ታሪክን በተገቢው መልኩ መፃፍ ዋጋ አለው። እስዚያማ በመሪዎች ደረጃ የሃይማኖትን አጥር አልፎ መደጋገፍ፣ መከባበርና መሳተፍ በሀበሻ ምድር እንግዳ ዜና ባልሆነ እንደ ብርቅም ባልተቆጠረ ነበር። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ኖረነው ግን በሰፊው ያልተፃፈው ታሪክ እንኳንስ ለሀገራቱ ዜጋ ኩራቱ ለመላ ጥቁር ሕዝብም ጭምር ይተርፍ ነበር።

መስጊድ ሲሰራ ድንጋይ ያጋዙ ክርስቲያኖች ያሉባት፣ ቤተክርስቲያን ሲታነጽ ለስብከት የድምጽ ማጉያ የገዙ እስላምሞችን ያፈራች፣ የጊዮርጊስ ታቦት በሠላም ተመለሰ አልሀምዱሊላ በሚል ገለታውን





የሚያስገባ እስላምን ያሳየችንን ሀገርና ታሪክ ይዘን በተራ ዜና መደመማችን ታሪካችንን ከመሰነድ ችግራችን ባለፈ ማንነታችንን በጥልቀትና በምጥቀት ከማወቅ ጋር ያለንን ርቀት ጭምር ቁልጭ አድርጎ የሚያሳ ነው።

ሁሉም አይደሉም፣ ግን ብዙዎቹ... ታላላቅና እርቅ አስተዋዮቹ ንጉሶሦቻችን በሃይማኖት መቻቻል ጉዳይ ድንቅ ታሪክ ጥለው አልፈዋል። ከዛሬ ሁለት ምዕተ-ዓመታት በፊት ቀዳሚዎቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች በገዛ አገራቸው፣ በገዛ ወገናቸው በእምነታቸው ሳቢያ ከሚደርስባቸው ግፍና በደል ሸሽተው በተሰደዱ ጊዜ የተጠጉት በኢትዮጵያ ጥላ ሥር ነበር።

ነጃሺ ንጉሣችን የእምነት አጥርን ጥሶ ያደረገው መልካምነት እና ሰብዓዊነት የሞላው ተግባር የዚሁ የመቻቻል መገለጫ የመጀመሪያው ምድራዊ የሰብዓዊነት ተምሳሌት ነው። ዛሬ ላይ በዚህ ሥልጡን ዓለም በጦርነትና መከራ ሳቢያ ከሀገራቸው የተሰደዱ ዜጎችን 'እንቀበል እንቀበል' የሚለው ጉዳይ ታላቅ የፖለቲካ አጀንዳ ሆኖ የአገራት መሪዎች እንደሸማኔ መወርወሪያ ከወዲያ ወዲህ ሲራወጡ ይስተዋላል። ኢትዮጵያውያን ግን ከሃይማኖት፣ ቀለምና ዘር በላይ ለሰብዓዊነት ትልቅ ቦታ ሰጥተው ዛሬ ሳይሆን ትናንት፣ ከብዙ ዘመናት በፊት ስደተኞችን እርሂቡ ብለው ተቀብለዋል።

በታሪክ ወርቅማ ሰነድ የተጻፈው ይህ ድንቅ ተግባር እዚያ የጥንቱ ዘመን ውስጥ ብቻ ታሽጎ የቀረ ጉዳይ አይደለም። ይህን መሰሉ አስተዋይነት አጥርና ድንበር አልፎ ሰውነትን ማከበር ወዲህ በቅርቡ ዘመን ታሪካችንም ውስጥ እናገኘዋለን። ከማን ጋር? ከተባለ.... ከአፄ ሚኒሊክና ከጅማው አባ ጅፋር ዝምድናና ወዳጅነት ውስጥ የሚል ይሆናል ምላሹ። በሚኒሊክ ቤተመንግስት ለአባጅፋር ክብር ሲባል የእስላምና የክርስቲያን ገበታ ጎን ለጎን በግራና በቀኝ ቀርቦ የነበር መሆኑን የምናውቅ ስንቶቻችን እንደሆን አላውቅም።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል ሶስት

መሪ መሆን የሚችሉ ሰዎች ግን የመምራት ሥራቸውን የሚጀምሩት ዛሬውኑ ነው።

የእውነት ለመምራት......

የስኬት ተምሳሌት - እንዲሆን መምራትህ

ውል እንዲይዝ ሥሩ

መምራት እና መግዛት

አይጥፋህ ድንበሩ።

ለምትመራው ጀማ

ራሥህን ካልሰጥህ ስስቱን በመተው

'እኔ' ያለ ቀን ነው፣ መሪ የሚሞተው።

የመምራት ኃይልህን.......

በቅንነት ያዘው በጥበብ አጽድለው

ምክንያቱም.......

ተመሪ ውስጥ ነው

የመሪ ዕድሜ ያለው።



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ አምስት

## ሥልጣንና ኃይልን ለመጠቀም ከልብ መሪ መሆን ያስፈልጋል

በአንድ አገር ላይ የማስተዳደር ኃላፊነትን የተቀበለ መንግሥት "ሶስት ነገሮችን የግሉ ሊያደርግ ይገባዋል" በማለት ምሁራን ይናገራሉ። የመጀመሪያው ነገር ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን ማፍለቅ መቻል ሲሆን ይህም አገርን ባረጀ-ባፈጀ ወይንም ጊዜው ባለፈበት የአመራር ሥርዓት ወደኋላ እንዳያስቀር ያግዘዋል። በየጊዜው ለሚከሰቱ አዳዲስ ችግሮችም መፍትሔን በማፍለቅ የነበረውን መልካም ነገር ማስቀጠል ግድ ይላል።

ሁለተኛው ነገር፣ በሥልጣን አካሄድ ውስጥ አገር ማለት ከተራራና ሸንተረሩ ባለፈ ህብረተሰቡ እንደሆነ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ታዲያ የእነኚህን ዜጎች ፍላጎት ያላሟላ አመራር ለአገር ቆሚል፣ ከማለት ይልቅ አገርን እያጠፋ ነው ማለቱ ሚዛን ይደፋል።

ሶስተኛው ጠቃሚ ነገር 'ውሳኔ ሰጪነት' ነው። አንድ መሪ አገራቱን በሚመለከቱ ማንኛውም ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል። ታዲያ ይህ ውሳኔ የአገርን ሁኔታ የሚወስን በመሆኑ የተጠና ውሳኔ ሰጪነት እጅግ አስፈላጊ ነው።

መሪ በሙሉ ልቡ ሕዝቡን ሊወድና ሊያምነው ይገባል። እራሱን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ሊፈተን ይችላል። ለህዝቡ ራሱን





የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ለመርሆዎቹ የሚገዛ መሆን አለበት። እዚህ ጋ የአንድ ፈላስፋ የተግባር ትምህርትን እናስከትል።

ፈላስፋው በወቅቱ ያስተምር የነበረው ስለ መሪነት ነበር። ታዲያ ድንገት ተማሪዎቹ እንዲከተሉት ይናገርና የኋሊት አህያ መጋለብ ይጀምራል። ተማሪዎቹን ከፊት ለፊቱ እየተመለከተ በአህያይቱ ጀርባ ላይ ተቀምጦ እየጋለበ ሳለ ይህን ሁኔታ ሲከታተሉ የነበሩ አላፊ አግዳሚ መንገደኞች ስለጉዳዩ ይጠይቁታል። ፈላስፋውም አላቸው፤

*"መሪ ህዝብን ሲመራ ወይም አስተማሪ ተማሪዎቹን ሲያስተምር ሁልጊዜም ቢሆን ለሚከተሉት ጀርባውን መስጠት የለበትም፤ ተከታዮቹም ቢሆኑ ከመሪው ጀርባ ያለውን ሁሉ በንቃት መከታተል አለባቸው።"*

አንድ ሰው መሪ መሆን ፍላጎቱ ከሆነ የሚከተሉትን ነጥቦች በልቦናው ሊያኖራቸው ይገባል። በአእምሮው ያመላልሳቸው በምግባሩም ይፈፅማቸው ዘንድ ግድ ነው።

- **ከእለታት አንድ ቀን ከሚል ቅዠት መውጣት!**

መሪ መሆን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው 'ከእለታት በዚህ ቀን መሪ እሆናለው' ከሚል የቅዠት እሥር ቤት መውጣት አለበት። ምክንያቱም ከእለታት አንድ ቀን የሚባል ቀን የለም። በህይወት ውስጥ የተሰጠችን እምር እድሜ ዛሬ ፣ ነገ ወይም ከነገ ወዲያ እንጂ ከእለታት አንድ ቀን አይደለም። በአጭሩ 'ከእለታት አንድ ቀን' በሚል እስር ተተብትቦ ያለተጨባጭ ዕቅድ የሚዳክር ማንም ሰው መሪ መሆን አይችልም። የአንድ ቀን እስረኞች በግምት የሚጓዙ ህልመኞች ናቸው። ንፋሱ የሚፈልጉትን ነገር እያከለፈለፈ እንዲያመጣላቸው ይመኛሉ እንጂ ወገባቸውን ጠበቅ አድርገው መንቀሳቀሳቀስ አይጀምሩም። ምናልባትም ህልማቸውን እውን ሳያደርጉ፣ ከቅዠት ዓለማቸውም ሳይወጡ ህይወታቸው ልታልፍ ትችላለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

መሪ መሆን የሚችሉ ሰዎች ግን የመምራት ሥራቸውን የሚጀምሩት ዛሬውኑ ነው። እነዚህ አካላት አስቀድመው ራሳቸውን መምራት ከመቻላቸውም ባሻገር በአካባቢያቸው ባሉ ሰዎች ላይ በተለያየ ሁኔታ ተፅዕኖ ማሳደር ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች መሪ ለመሆን የግድ ምርጫን አይጠብቁም። አዳዲስ ልምዶችንና ሀሳቦችን በማፍለቅ ሌሎች ሊከተሉት የሚፈልጉት ዓይነት ሰው ሆነው ይገኛሉ። ባሉበት ቦታ ሁሉ ሰዎችን የማነቃቃት ኃይላቸውን ይጠቀሙበታል። ገና መሪ ከመሆናቸው በፊት ራሳቸውን እንደ መሪ ይቆጥራሉ። በመሆኑም የበላዮቻቸውን ሃሳብ ሳይቀር የማስለወጥና ነገሮችን በተለየ አቅጣጫ እንዲሄድ ማድረግ ይችላሉ። በሚያደርጉት ነገሮች በራሳቸው የሚተማመኑና እርግጠኞች ናቸው። ታዲያ ይህ ባህሪያቸው ሌሎችም ጭምር በእነሱ እየተማመኑ እንዲሄዱ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ያበረክትላቸዋል። አለቆቻቸውም ጭምር የሚሰሩትን የሚያውቁ አድርገው ስለሚያስቧቸው በእነዚህ ሰዎች ላይ የሚኖራቸው ቁጥጥር ዝቅተኛ የሚባል ነው።

መሪ መሆን የሚችሉ ሰዎች ራዕይ ያላቸው ሲሆኑ ወደ ራዕያቸው የሚያደርሳቸው ትልቁ መሳሪያ ደግሞ ለራዕያቸው ታማኝ መሆናቸው ነው። ለራዕያቸው እውን መሆን ማድረግ ያለባቸውን ነገሮች በሙሉ ከማድረግ ወደኋላ አይሉም። ስለዚህ መሪ የመሆን ፍላጎት እና የነገ ትልም ያለው ሰው የግሉን ራዕይ በመቅረጽ ከሌሎች ጋር ለሚገጥመው ውድድር ራሱን ዝግጁ ማድረግ ይኖርበታል። ራዕያችን ወደፊት ለምንሆነው ነገር ንድፍ ምስል በመሆኑ ይህንን ንድፍ በውል መንደፍ መቻል ጥሩ መሪ ለመሆን ብዙ ነገር ማለት ነው። ራዕያችን ለነገሮች የምንሰጠውን ዋጋ፣ ልናበረክት የምንችላቸውን ነገሮች እና ህይወትን እንዴት ልንመራት እንደምናስብ የመናገር አቅም አለው። ራዕይ አልባ ከሆንን ግን መሪ ልንሆን ቀርቶ በሌሎች ፍላጎት የምንመራና እንደ ንፋሱ አነፋፈስ ካንዱ ወደ አንዱ የምንንቀዋለል የውሀ ላይ ኩበት መሆናችን እንደማይቀር ልብ ልንል ይገባል።

ይህንንም ዓላማችንን ልናሳካ የምንችልበትን ቦታም መምረጥ እብይ





የመሪነት ቁም ነገር ነው። ከዓላማችን ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ቦታ እየሰራን ከሆነ ሳንንገራገር መውጣትና ፍላጎትን ሊያሳኩ የሚችሉበት ቦታ እና ሀላፊነት ላይ ለመስራት መወሰን ከየትኛውም መሪ መሆን ከሚፈልግ ሰው የሚጠበቅ ድንቅ ውሳኔ ነው። ይህ ካልሆነ ደግሞ የራስን ተቋም በራስ መመሥረትም ሌላው አማራጭ ነው። እምነትን የሚጻረር ሥራ እየሰራን ግን 'መሪ እሆናለው' ብለን የምናስብ ከሆነ ቅቤን በህልሙ ብቻ እንደሚበላ ድሀ ከመቆጠር ውጪ፣ የህልማችንን ደፍ የሚሻገር ራዕይ ለመንደፍ እጅጉን እንቸገራለን።

### ○ ሰዎችን መያዝ

ወደድንም ጠላንም በዚህች ዓለም ላይ ስንኖር ለኛ ስኬትም ሆነ ውድቀት የሰዎች እጅ አለበት። ብዙ ሰዎች ሥራዬን በትክክል እስከሰራሁ ድረስ የምፈልግበት ቦታ እደርሳለሁ፤ ብለው ያምናሉ። እርግጥ ነው፤ ስራን በትክክል መሥራት ዋናው ቁም ነገር ነው። ነገር ግን፣ ሰዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው። ስለዚህ መሪ መሆን የሚፈልግ ኀበዝ ሁሉ እኔ ከማንም ምንም ዓይነት እርዳታ የማልፈልግ ለራሴ የበቃሁ ሰው ነኝ! ብሎ ማሰብ የለበትም፤ በፍጹም። አብሮን የሚሆን፣ ስህተታችንን የሚነግረን፣ አስፈላጊም ሲሆን የሚረዳን ሰው ያስፈልገናል። የሚያማክረን ፕሮፌሽናል የሆነ ሠው ቢኖረን ደግሞ እጅግ መልካም ነው። እነዚህ ከኛ ጋር የሚሆኑ ሰዎች ዓላማችንን ከግብ ለማድረስ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያበረክቱልናል። ነገር ግን፣ ማን በምን ሁኔታ ሊያግዘን እንደሚችል ማወቅ ብልህነት ነው። ምክንያቱም ሰው ለራሱ የሌለውን ሊሰጠን አይችልምና! የኔ ፍላጎት ምንድነው? ታዲያ ይሄንን ነገር ከማን ላገኝ እችላለሁ? ብሎ ራሥን መጠየቅ ከብዙ ድንቅፍቅፍታ ይታደገናል።

### በምናደርጋቸው ነገሮች በሙሉ ወደ በለጠ ብቃት ለመምጣት መጣር

ጥሩ የመፈጸም ደረጃ ላይ መድረስ መሪ ለመሆን በቂ ችሎታ



t.me/OLDBOOKSPDF

ባይሆንም እጅግ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ራሥን ወደ ከፍተኛ የዕውቀትና የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ማድረስ እጅግ ወሳኝ የሆነ የመሪ ክህሎት ነው። ራሥን ለማንኛውም ነገር ብቁ ነኝ! ብሎ ከመኮፈስ ይልቅ ገና ልንለማመዳቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ማሰብ ሩቅ የሚያስጉዝ ሁነኛ መንገድ እንደሆነ ማወቅ ይገባል።

ጎበዝ በመሆንና እጅግ በጣም ጥሩ ሰው በመሆን መካከል ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ መዘንጋት የለብንም። በመሆኑም ምንም እንኳን ህጸጽ አልባ መሆን ባንችልም እጅግ በጣም ጥሩ መሆን ግን አይከብደንም። በተቻለን መጠን ሰዎች በባህሪህም ሆነ በስራ ከፍተኛ ቦታ እንዲሰጡን ማድረግ ተገቢ ተግባር ነው። ይህንን ማድረግ የምንችለው ደግሞ ምን ቦታ ጥሩ እንደሆንንና ምን ቦታ ደግሞ ማሻሻል እንዳለብን ጠንቅቀን በማወቅ እንጂ በሌላ በምንም አይደለም። መሻሻሎችን ለመገምገም የግድ የሌሎችን ምስክርነት ማግኘት አይኖርብንም። የሚሻሻሉ ነገሮችን ዘርዝረን ያሻሻልናቸውንና ገና መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች በአትኩሮት በመመርመር ራሳችንን መመዘን እንችላለን።

## ○ የሹፍርናውን ወንበር ያዝ

መሪ ለመሆን በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ ከሚመች ቦታ ለቆ መውጣትንም ይጠይቃል። አዳዲስ ችሎታን ሊያላብስህ የሚችል የተለጠጠ ዕቅድን አስቀምጥ። በዕቅድህ ላይ አብረው ሊሰሩ የሚችሉ ሰዎችን አሰባስብና አንተ የመሪነቱን ቦታ ያዝ። ይህ የመሪነት አቅምህን ከማሳደጉም ባሻገር የመታየት ዕድልን ይፈጥርልሃል። ብዙ መሪ መሆን የሚፈልጉ ሰዎች የሚሰሩት ትልቁ ስህተት ሌሎች ባወጡላቸው ገደብ ውስጥ ብቻ ሆነው ውጤታማ ለመሆን ማሰባቸው ነው። ምንም እንኳን ጥሩ ችሎታ ቢኖራቸውም በገደብ ውስጥ እስካሉ ድረስ አብረዋቸው ከሚሰሩት በቀር ማንም ሊመለከታቸው አይችልም። አብረውህ ከሚሰሩ ሰዎች ጋር የውሳኔ ሰጪነቱን ስራ ተወጣው። ንግግርህ አሳማኝ፣ ርዕሱን የጠበቀ እንዲሁም ጠንካራ ይሁን። ያልተገባ ነቀፋን ከማስተላለፍ





የተቆጠብክ ሁን። በሌላ አባባል ደግሞ የሌሎችንም ክብር የምትጋፋ ሰው አትሁን።

## ○ ራስህን የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም አስተዋውቅ

አንዳንድ ሰዎች ብዙ መልካም ነገሮችን እያደረጉ ያደረጓቸው መልካም ነገሮች ግን ገሃድ እንዳይወጡ ይፈልጋሉ። ይህ ለመሪዎች የማይሰራ ፍልስፍና ነው። ምክንያቱም ከሠራናቸው ሥራዎች መካከል የሚታወቁት እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው። ያለህን ዕውቀት በገሀድ ሌሎችን ለመርዳት ተጠቀምበት። ለየት ያለ ሃሳብ ሲኖርህ እነዚህን ሃሳቦች ዕውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ ሚዲያዎችን ተጠቀምባቸው። ሥራዎችህ ላይ ያስመዘገብካቸውን ድሎችም ጭምር ሚዲያዎች እንዲያራግቡት አድርግ። ነገር ግን በሥራህ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ሰዎችን በገሃድ ማመስገንህን አትርሳ። ይህ ድርጊትህ በማንኛውም ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ካንተ ጋር እንዲሆኑ ያበረታታቸዋል። ይህ ጉራ ሳይሆን የሥራህና የጥረትህ ውጤት ነው። ይህ ራሥን የማስተዋወቅ ሥራ ሌሎች ባንተ እንዲያምኑ ከማድረጉም በላይ ወደ መሪነት ለምታደርገው ጉዞ ስንቅ ይሆናል።

## ○ ለሌሎች ያለንን የተቆርቋሪነት መንፈስ ማሳየት

መሪ እንድንሆን ከሚያበቁን ነገሮች አንዱ ለሰዎች ያለን የተቆርቋሪነት መንፈስ ነው። ለእነሱ ያለን ሀዘኔታ፣ ፍቅር እንዲሁም መልካም አስተሳሰብ የበለጠ ወደኛ እንዲሳቡ ያደርጋቸዋል። መሪዎች በተቻላቸው መጠን ከሌሎች ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። ፍቅር ነገሮችን በሌሎችም ዓይን እንድንመለከት ይረዳናል። ፍቅር ከሌለን ግን መሪ ብንሆን እንኳን የራስን ጥቅም ከማሳደድ በቀር በህዝቡ ህይወት ላይ ጠብ የሚል ነገርን ልናደርግ አንችልም።

የመሪ ህይወት "እንኳን ወደ ትግሉ መጣህ..." በሚል ተጀምሮ "... ጉዞውን መጨረስ በመቻልህ እድለኛ ነህ" በሚል ማሳረጊያ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚገባደድ ነው። መልካምና አስደሳች ገጠመኞችን የምንጠብቅ ከሆነ ምንጊዜም እንደጠበቅናቸው የምንቀር ይሆናል። ነገር ግን መልካምና ደስታ አሁን ላይ አብረውን እንዳሉ የምናምን ከሆነ ለመቼውም ደስታ የማይለየን እንሆናለን።

እዚህ ላይ አብይ ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ጉዳይ ግብን ከደረሱበትና ድል ካደረጉ በኋላ መቼ ማቆም እንደሚገባ መማር አስፈላጊ መሆኑን ነው። በአብዛኛው ጊዜ የድል ቅፅበት እጅግ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚገባበት ቅፅበት ነው። ድል በሚሟሟቅበት ጊዜ እብሪተኝነትና ከልክ በላይ በራስ መተማመን በግብ ደረጃ ያስቀመጡትን ጥሰው እንዲያልፉ የሚገፋፋ ነው። ከታቀደው በላይ መጓዝ ድል ካደረጓቸው ጠላቶች በላይ ተጨማሪ ጠላቶች እንዲፈጠሩ ያደርጋል። ስኬትን ከፊት ቀድሞ እንዲሄድ ማድረግና በጥንቃቄ ሊታቀድና ሊተነደፈ ዕቅድና ስልት ተለዋጭ ማስቀመጥ አያስፈልግም። ግብን በማስቀመጥ ሲደርሱበት ማቆም ይገባል። ከዚህ በኋላ ለመቀጠል የሚያስችል በጥንቃቄ የተዘጋጀ ዕቅድና ስልት እስከሌለ ድረስ ማቆም ተመራጭ ነው።

መኖሪያ ዓለማችንን በሴት ልጅና በእናት ልንመስላት እንችላለን። በልጅ ዓይን ከእናት የሚገኘው የደስታ መሰረት ጡቷና ከጡቷ የሚፈልቀው ወተት ነው። በዚያው መጠን ይህች እናት ባሏን የምትማርክበትና ደስታ የምትሰጥበት ሚስጢር አላት። ይህም ሆኖ ዕድሜያቸውን ሙሉ የማይበስሉና የደስታ ምንጫቸው ከጡትና ወተት ከፍ የማይል ሞልተዋል። ስለዚህ የዓለምን ምስጢር በጥልቀት መረዳት ይጠበቅብናል።

የመሪነት ሀሁ...

*"ያንተ ድርሻ ፍቅርን መሻት አይደለም። ይልቁንም ፍቅር ወዳንተ እንዳይቀርብ በውስጥህ የገነባሃቸውን ሁሉንም ቅጥሮች እና መሰናክሎች ፈልጎ ማግኘት ሊሆን ይገባል።"*

Mevlana Jalaluddin Rumi
1207-1273 ዓ.ም





ታሪክን በከፋ መልኩ ላለመድገም ወደኋላ ተመልሶ መመርመር በጣም ትልቅ ዋጋ እንዳለው እሙን ነው። ለዚህ ደግሞ እርሳስን መምሰል ያስፈልጋል!

አንድ ትንሽ ልጅ የሴት አያቱ ሲፅፉ እየተመለከተ ነበር። በመሀሉ አቋርጧቸው ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፡፡

"አያቴ! ስለምንድን ነው፣ የምትፅፊው? ...ስለሠራናቸው ነገሮች ነውን? ወይስ የምትፅፊው ሌላ ነገር ነው? ...ፅሁፉ ስለ እኔ ነው፣ የሚያወራው?" በማለት ደጋግሞ ይጠይቃቸዋል።

አያቱም መጻፋቸውን ጋ አደረጉና ለልጅ ልጃቸው፣

"ስማህ!" አሉት፡፡ ቀጠሉና፣

"የምጽፈው በርግጥም ስለ አንተ ነው። ከቃላቱ በበለጠ ግን ጠቃሚ የሆነው ነገር የምጽፍበት 'እርሳስ' ነው። ተስፋ የማደርገውም... አንተ ስታድግ እንደዚህ እርሳስ ትሆናለህ፣ ብዬ ነው።" በማለት መለሱለት።

ግራ የተጋባው ልጅም እርሳሱን አተኩሮ ተመለከተው። ምንም የተለየ ገጽታ አላስተዋለበትም። ሲያድግም እንዴት እንደ እርሳሱ ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ጓጓ፤

"አያቴ! ግን እኮ... ይህ እርሳስ ልክ እንደ ማንኛውም አይነት እርሳስ ነው።" አለ ልጁ።

"እርሱ የሚወሰነው አንተ ነገሮችን ለማየት በምትመርጥበት መንገድ ነው። ማንንም ሠው ከዓለሙ ጋር የተስማሙ ሊያደርጉት የሚችሉ አምስት ድንቅ ባህሪያትን ይዟል።" አያሉ አያቱ ያስረዱት ገቡ።

"የመጀመሪያው ባህርይ... በራስህ ብዙ ትላልቅ ነገሮችን የመፈፀም ብቃት አለህ። ቢሆንም ግን ሁልጊዜም የሚመራህ እጅ እንዳለ



t.me/OLDBOOKSPDF

አትዘንጋ። ያንን እጅም አምላክ እንለዋን። ሁልጊዜም እርሱ በሚመርጥልን መንገድ ይመራናል።

"ሁለተኛው ባህርይ... በምጽፍበት ወቅት አስተውለኸኝ ከሆነ እረፍ እረፍ እያልኩ መቅረጫ እጠቀማለሁ። ያንን ሳደርግ እርሳሱ በመጠኑ መሰቃየቱ ባይቀርም ስጨርስ የበለጠ የተሳለ እና ለስራ ምቹ ይሆናል። አንተም ጥቂት እንግልቶችን እና ሀዘኖችን ማሳለፍ ይኖርብሃል። ያ ግን የተሻልክ ሠው እንድትሆን ያግዝሃል።

"ሦስተኛው ባህርይ... እርሳስ ሁልጊዜም የሰራውን ስህተት በላጲስ ለማጥፋት ዝግጁ ነው። ይህም መልሶ ለማስተካከልም መድፈር መጥፎ ነገር እንዳልሆነ ያሳይሃል።

"አራተኛው ባህርይ... የእርሳስ በጣም ተፈላጊው ክፍል ከውጭ የሚታየው እንጨት አይደለም፤ ከውስጥ ያለው እንጂ። አንተም ትኩረትህን ማሳረፍ ያለብህ የውስጥህ እውነታ ላይ እንጂ የውጭህ ገፅታ ላይ አይደለም።

"የመጨረሻውና አምስተኛው ባህርይ... እርሳስ ሁልጊዜም ምልክት ይተዋል። እሻራውን አኑሮ ያልፋል። በተመሳሳይ መልኩ አንተም የምትሰራው ምንም ነገር ምልክቱን እንደሚተው ልብ በል! ስለዚህም ድርጊትህን ሁሉ በአስተውሎት ለመከወን ሞክር፡፡" በማለት አያት ምክራቸውን ለልጃቸው ሰጥተው አለፉ።

በዚህ ዘመን፤ ግሎባላይዜሽን ከታሪክ የመማሩን ድርሻ ከፍተኛ አድርጎታል። መመልከት ያልቻልነው ትልቁ ጉዳይ የዛሬው ዓለም በራሱ ባለበት ሁኔታ የጥንቱን፤ መካከለኛውን እና መጪውን ጊዜ ልናይበት የሚችል መሆኑ ነው። ወጣቶቻችን ለአገራችን የሶሻሊዝም ርዕዮትን ይመኙ በነበረበት ዘመን ሶሻሊዝም በሩሲያ፣ በቻይና፣ ሶሻሊዝም በኩባ ከንድፈ-ሃሳብ ባሻገር በተግባር ፈጥሮት የነበረው መልክ ምን ዓይነት እንደሆነ፤ እንዴት ተግባራዊ እንደተደረገ፤ ምንስ ፈተናዎች ገጥመውት እንደነበር፤ በጥልቀት ማየትና መመርመር፤





ከአገር ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ጋር ማጣጣምን ይጠይቅ እንደነበር ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ የዚያ ዘመን ታጋይ ምሁሮቻችን ይህን እውነታ ለማየት ሙከራ አላደረጉም። ለእምነት ትልቁ ቦታ በሚሰጥበት አገር፤ እምነት አልባ ርዕዮት በምን መልኩ ወደ ዕድገትና ፍትህ ሊመራ እንደሚችል በምሁራት አልተፈተሸም ወይም አልተተነተነም፡፡ ከአገር ነባራዊ ሁኔታ ጋርም ለማስተሳሰር አልተሞከረም።

ዛሬ ላይም መሠረት አድርገን ለመያዝ የምንመርጠው ርዕዮት በአማላይነቱ ተስበን አማራጭ አድርገን የምንቀበለው ብቻ ሳይሆን በተግባር መሬት ላይ ተፈትሾ፤ 'በምሥራቅና በምዕራብ ምን አስገኘ? ምንስ መሠናክሎች ገጠሙት? መሠናክሎቹን እንዴት አለፋቸው? ' የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳትና በመተንተን መሆን አለበት፡፡ ጠንካራ ጎኑን ለይቶ ማውጣት የሠርክ ጉዳያችን ሊሆን ይገባል። በምሥራቅ ታላላቅ ስራዎች እንዴት ተፈጠሩ? እንዴትስ ፈረሱ? በምዕራብ፤ የገዢ መደብ ጥቅሞች እንዴት ተጠብቀው ቆዩ? በኃይል አሰላለፍ፤ በቃል በሚናገሩትና በተግባር በሚያከናውኑት አካላት መካከል ያለውን ልዩነት ማጤን መልካም ነው።

በጣም ጥንቃቄ ተሰጥቶት መያዝ የሚገባው ጉዳይ አንድ ችግር፤ አንድ መገለጥ፤ አንድ መፍትሔ ያለው አድርጎ የመውሰድ አባዜ ነው። ህይወት ባለብዙ አማራጮች የመሆኗን እውነት በሚገባ አለመረዳትና አንድ በር ከተዘጋ የተዘጋው በር ላይ አፍጥጦ የማለዘን ከፉ አመል ብዙ መስዋዕትነትን ያስከፍላል፡፡ የተስፋ መቁረጥ ዓይነተኛ ዋሻውም ይሄው ነው፡፡ እምነትን መሰረት ያደረገው ርዕዮተ ዓለም በሰፊው ህዝብ ሰርፆ መግባት እንዲችል የርዕዮቱ የሞራል መሠረቶች በተፈጥሯዊ መርህ የተቃኙ መሆን ይገባቸዋል። ይህንን ደግሞና ደጋግሞ በሚዲያ፤ በትምህርት ቤት፤ በቤተ እምነት እና በባህል መገለጫዎች በማስደገፍ የእስተሳሰብ ልዕልናን መፍጠር ይቻላል።ሕዝብን በለበጥ በትር ሳይሆን በልብ እርጩ ማገድ የምንችለው ያኔ ነው። በ1994 ሲሊኮን ቫሊ ሂስቶሪ ማህበር ለስቲቭ ጆብስ ባደረገለት ቃለ መጠይቅ ላይ 'ስቲቭም እንዲህ ሲል



t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር መልስ የሰጠው፡

“እያደግህ ስትመጣ ህይወት ማለት በዚህ ርዕዮተ ዓለም ውስጥ ብቻ መኖር እንደሆነ ይገባሃል፤ ከዚህ ውጭ ግን ግድግዳ መግፋት እንደሆነና ትርፉም ድካምን ብቻ እንደሚወልድ ሲነገር ትሰማለህ።”

ነገር ግን፡ ህይወት በጆብስ ዘንድ ቋሚ ወይም የረጋ ነገር አይደለም፡፡ ሊቀየር እንደሚችል ያምናል።የፋርሱ ሊቅ ጀላሉዲን ሩሚም፡ የኛ ድርሻ ፍቅርን መፈለግ እንዳልሆነ፤ ይልቁንም ፍቅር ወደ እኛ እንዳይቀርብ በውስጣችን የገነባናቸውን ሁሉንም ቅጥሮች እና መሰናክሎች ፈልጎ ማግኘት ሊሆን እንደሚገባ ያሳስበናል፡፡

### ○ ጥሪን ማዳመጥ

የህይወት ግብን ፈልጎ ማግኘት በጥረት የሚመጣ እንጂ እንደመና የሚታደሉት አይደለም፡፡ ይህ ማለት ግን በሰውነታችን ውስጥ ጠቋሚ ኮምፓስ የሌለው፡ በማድረቢያ የሚደረግ የእውር ድንብር ጉዞ ተደርጎ መታሰብ አይኖርበትም፡፡ እናም በርጋታ ማስተዋል፣ የነፍስ ጥሪዎችን በህይወታችን የሚያብብበትን መላ አስቶድግሞ መፈለግና መለየት ያስፈልጋል፡፡ ማንም ስላለው ወይም ደግሞ ዙሪያችን ያለው ቤተሰብና ሕብረተሰብ ትልቅ ቦታ ስለሰጠው ሳይሆን ለራሳችንና ለውስጣችን ከማንም ተፅዕኖ ውጭ የሚሰጠንን የህይወት ማግኔት ፈልገን ማግኘት ይኖርብናል፡፡ ይህ ማግኔት በውጭ ከሚገኙ ኃይል ይልቅ አዕምሮን የምንቀሰቅስበት ጉዳይ በመስጠት፡ በተለያዩ ሀሳቦች መካከል ያለውን ትስስር በመመርመር፤ እውነትን ወደ ተደያ መሰኮች የምትስፋፋበት መንገድ ጠራጊ ይሆናል፡፡ አለምን ስለመቀየር ከማሰብ ይልቅ ራስን ለመቀየር መወሰን ቃላትን እንደሆነ የተናገረውን ሊቅ ድንቅ ሃሳብ እንዳለ መውሰዱ ብልህነት ነው፤ ምክንያቱም ራስን ያላወቀ ማንንም፣ ምንንም ሊያውቅ አይችልም፡፡

የህይወት ግብ ልዩ በሆኑ ሥራዎች ውስጥ በተግባር የሚገለፅ ነው፡፡





እኛ ልናባካው የሚገባ ልዩ እሳት ችሎታ እንዳለ ማወቅ ያስፈልጋል። ይህን ግብ በጥንቃቄ የሚጠብቁት ሲሆን ልክ እንደ ልዩ ኃይል፤ ጥሪ ወይም በውስጡ ግብ ሲሰክበት/የበላይ ሊኮንበት የሚያስችል እድል ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ልዩ ኃይል የሚያዳክመው እንዳይሰማና መኖሩንም እንዲጠራጠሩ የሚያደርግ በሌላ የህይወት ኃይል (ለምሳሌ ማህበራዊ ግፊቶች) ተሸናፊ የመሆን እድል ስለሚያዘነብል ነው፡፡ ወደ ዝንባሌና የህይወት ግብ መጠጋት የሚኖረውን ፋይዳ ካወቁ በኋላ እነርሱን ማግኘት ቀላልና ተፈጥሯዊ ዑደትን የተከተለ ሊመስል ይችላል፡፡ ነገር ግን በመፈለግና በማግኘት ጉዞ ውስጥ ተገቢና ወደ ትክክለኛነት የቀረበ፤ ሊያጋጥሙ የሚችሉ መሰናክሎችን ማለፍ የሚያስችል ዕቅድና ውጥን ሊኖር ይገባል። ይህ ምን ማለት ነው? ቀጥለን እናየዋለን...

### ○ ዝንባሌን የማግኘት መሰረታዊ ዕቅድ

የበላይ ለሚሆኑ ሰዎች፤ ዝንባሌያቸው በአብዛኛው በልጅነት ዘመናቸው ግልጥ ብሎ ሊቀርብላቸውና ሊታያቸው ይችላል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ከእውነተኛ የህይወት ጥሪያችን ተቆራርጠን ልንቀር እንችላለን፤ አንዳንድ ጊዜ ዕለት ከዕለት የምንጠመድባቸው ነገሮች ኖረው፤ ወይም በአንዳንድ ሰዎች ተፅዕኖ ስር ወድቀን፤ በምንሰማውና በምናየው ነገር ተሰበን ወይም ለአንዳንድ ነገሮች በሚኖረን ተጋላጭነት ምክንያት እውነተኛው ዝንባሌያችንን እናጣዋለን፡፡ አንዳንዶች በአጋጣሚ የተገኙበትን ስፍራ ከእውነተኛው ይልቅ የህይወታቸው መዳረሻ እንደሆነ አድርገው ሊወስዱት ይስተዋላል፡፡ ቁምነገሩ ግን የህይወት ጥሪን ፈልጎ ለስኬት መብቃቱ ነው፡፡

የቡድሂዝም እምነት መሥራች እንደሆነ የሚነገርለት ሲድሃርታ ጉተማ የተወለደው ለንግስና ቅርብ ከሆኑ ቤተሰቦች ሲሆን ገና ሳይወለድ በወደፊት ህይወቱ ዙሪያ ሁለት ትንቢቶች እንደተነገሩለት ይገለፃል፡፡ በህልሜ እያየሁ ብላ ስለሚወለደው ህፃን (ሲድሃርታ ጉተማ) ዕጣ ፈንታ አንድ የአካባቢው ሰው አባቱ ዘንድ ቀርቦ

ሲናገር፣ ወደፊት ጉተማ ስመ ገናና እንደሚሆን እና ዘውድ ቢጭን ጀግና መሪ ሊሆን እንደሚችል፣ ወደ መንፈሣዊው ዓለም ቢዘልቅም ተከታዮቹ የበዙለት መሪ እንደሚሆን ገልፆ ነበር፡፡ ቤተሰቦቹ፣ ልጃቸው የትኛውን መንገድ ቢከተልላቸው ደስተኛ እንደሚሆኑ መገመት አያዳግትም፡፡ ታዲያ፣ እንደ ቤተሰቡ ፍላጎትና ጥረት ቢሆን ኖሮ ያ ህፃን ወደ ንግሥናው መንደር አምርቶ ምናልባትም በመቶዎች ዕድሜ ውስጥ የሚረሳ መናኛ ንጉሥ ሆኖ ያልፍ ነበር፡፡ ዳሩ ግን፣ ጉተማ ከመሣፍንቱና ከመኳኳንቱ ጎራ መሰለፉ ደስታን የሚያስገኝለት አልነበረም፤ ስለዚያም የህይወት ጥሪውን አጥብቆ ፈለገ.... ይሄው፣ ቡድሃ (የበራለት/የተገለጠለት) ሆነና በሺዎች የሚቆጠሩ ዘመናት አልፈውም በሚሊዮናት/ቢሊዮናት ከሚቆጠሩ ሰዎች ልብ ውስጥ እንደነገሰ ዘልቋል፡፡

ስለዚህ ዝንባሌን ማግኘት ወይም ወደ ህይወት ጥሪ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ ይህ እንዴት ይሆናል? የሚለው መመለስ የሚጀምረው መሥመራችንን የሳትንበትን አጋጣሚ ወይም ጊዜ መለስ ብሎ ከመገምገም ይሆናል፡፡ ቡድሃም፣ የልጅነት ዕድሜውን ሻሞላ ጨብጦ የጦር ፍልሚያ ሲለማመድ እንዳሳለፈ ይነገራል፡፡ ታዲያ ግን የልጅነት ነፍሱ ይበልጥ የምትሳብበት ሌላ ዓለም ነበራት.. ይኸውም ትኩረቱን ሁሉ በተለየ ቴክኒክና ታክቲክ ድል ስለሚያደርጋቸው ወታደሮች ሳይሆን ስለህይወት ሚስጥር ወደመመርመር እንዲያዘነብል አድርጎታል፡፡ ውትድርናው ግማሽ መንገድ ቢያስጉዘውም ትክክለኛው የህይወት መንገዱ እንዳልሆነ ስለተረዳ የራሱን ቀና መንገድ ለማግኘት ቀላል የማይባሉ ዓመታትን መልሶ መላልሶ እንዲያስብ ተገድዷል፡፡ እናም፣ ወደ ውስጡ መስደዱ እውነተኛው የህይወት ጥሪውን አስገኝቶለታል፡፡

የህይወት ጥሪያችንን እንዲህ እንደ ቡድሃ በራሳችን ጥረት መርምረን ልናገኘው እንችላለን፡፡ አንዳንዴ ግን ጥረታችንን ሊደግፉ የሚችሉ፣ መንገዳችንን የሚጠርጉልንና አይናችንን የሚያበሩልን ጠንካራ እጆች ሊያስፈልጉን ይችላል፡፡ በአብዛኛው ዝንባሌያችን ምን እንደሆነ የሚንፀባረቀው በልጅነት ዕድሜያችን ላይ ነው፤ ስለዚህም





ሊያግዙን የሚችሉ የቅርብ ሰዎች ካሉ ከእነሱ ጋር በመወያየት የቀደመው የህይወት ጥሪያችንን ማግኘት እንችላለን፡፡ በትምህርት ቤት ህይወታችን፣ በቤታችን ውስጥ፣ ከሰፈር ልጆች ጋር ባለን መስተጋብር ወቅት እናንፀባርቃቸው የነበሩ ነገሮች ፍንጭ ይሰጡናል፡፡ አንድ ጊዜ ዝንባሌና ችሎታችንን ከተረዳን በኋላ ወደዚያ ለመመለስ ማመንታት አይኖርብንም፡፡ ምናልባት ሥራ መልቀቅ ወይም መቀየር ላይኖርብንም ይችላል፤ የያዝነውን ሙያ ወይም ሥራ ወደምንፈልገው በማስማማት (ጥቂት ማስተካከያዎችን በማድረግ) ወደ ህይወት ጥሪያችን እንዲያደርሰን ማድረግ እንችላለን፡
፡

የነፍስ ጥሪን ተከትሎ የሚደረግ ጉዞ ሁል ጊዜ ከ'በርታ!' ባይዎች ጋር የሚያገናኝ ጉዞ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ጎዳናውን፣ ምን ነካቶሃል? አብደሃል ወይ?... እያሉ የሚፈታተኑ እንደበቶችንም ጭምር የሚቀላቅልበት አጋጣሚም አለ፡፡ ታዲያ መሰናክሎች ሲበዙ ውድቀት የሚከተለው መንፈሥ ጠንካሮች ሳንሆን ስንቀር እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በርግጥ፣ መሰናክሎች መብዛታቸው የመረጥነው መንገድ የተሳሳተ ስለመሆኑ ጠቋሚም ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም፣ ጫናው ልባችንን ከማሸበር ይልቅ ውስጣችንን ካጀገነው መጠራጠር አይገባንም፡፡

እናም፣ መሪ ትሆን ዘንድ የምትሻ ከሆነ ይሄን እውነት ድጋሚ ላስታውስህ፤

***"የሀይወት ጥሪያቸውን ያልተከተሉ ሰዎች ዘመናቸውን የሚገፉት ተራ በሆነ ሀይወት ውስጥ፣ በዛ ቢባል መካከለኛ ደረጃ ላይ ሆነው እንጂ እንደመሪዎች የማማው ጫፍን ተቆናጥጠው አይደለም፡፡ እንዚህ በሁለቱ ፅንፎች የሚኖሩ ሰዎችን አራርቆ ያስቀመጣቸውም ነገር ሌላ ሳይሆን የሀይወት ጥሪን የመከተልና ያለመከተል ጉዳይ መሆኑን እወቅ!"***



t.me/OLDBOOKSPDF

## ○ ራስህን መግዛት መለማመድ

ወደበላይነት፣ ባለጥልቅ ዕውቀት እና ልዩ ችሎታ ባለቤትነት የምናደርገውን ጉዞ ከዳር ለማድረስ አስፈላጊውን ራስን ሥርዓት ማስያዝ የሚጠይቅ መሆኑ ከምንም በላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። በራስ ልቦና ጥናት ውስጥ ከባህሪ እንግር ተደጋግሞ የሚነገር አንድ ሙከራ አለ። ስምንት ህፃናትን በአንድ ክፍል ውስጥ በማስቀመጥ የሚያስጎመጅ ኬክ ከፊታቸው ተደረገ። አቅራቢው ሰው ሄዶ እስኪመለስ መጠበቅ ከቻሉ ዕጥፍ ተደርጎ እንደሚሰጣቸው ተነገራቸው። አንዳንዶቹ ሲኮንድ መቆየት አልቻሉም። አንዳንዶቹ ደግሞ ለአፍታ ታግሰው እስከ ግማሽ ዘለቁ። እስከ መጨረሻ መቆየት ግን አልቻሉም ነበር። እናም በስተመጨረሻ በሉ። ነገር ግን በጣም ውስን የነበሩት ህጻናት እስከ መጨረሻው መዝለቅ በመቻላቸው ሽልማቱን ማግኘት ቻሉ። እነዚህ በራሳቸው ወቅታዊ ፍላጎት ያልተሸነፉት ህፃናት በህይወታቸውም ዘመን ስኬታማ ሆነው እንደቀጠሉ ጥናቱ ጠቁሟል። በምንኖርበት ዓለም በጣም አጓጓና ጊዜያዊ በሆኑ ጉዳዮች ተሸንፈው ትልቁን ሥዕል ለማግኘት የበቁ ጥቂቶች አይደሉም።

ትልቅ ዋጋ ያለው በውስጣችን ባለ ሥጋዊ ፍላጎት እንጻር ሳይሆን የመጨረሻዋን እርምጃ የመራመድ ድፍረታችን ላይ ነው። በተመሳሳይ በሌላ የሩቅ ምስራቅ አፈ-ታሪክ ውስጥም የመጨረሻዋን እርምጃ ጠብቆ የመራመድ ጥቅም ሲነገር እንሰማለን። ተስፋ-ቢስነት የማያወጣና የሁነፍ ሰው መገለጫ ባህሪ ሊሆን ይችላል። ጠቢብ ሰው ስለ አካባቢው ሁኔታ ቀድሞ መጠየቅና መመርመር እንዲሁም ስለ መጭውም ጊዜ መገመትና መተንበይ ይፈልጋል። በ1990ዎቹ የተጀመረውን የቀላል ሞባይል ቴክኖሎጂ በጥቂት እርቆ አሳቢዎች ያላሰለሰ ጥረትና ትዕግስት በአሁኑ ሰዓት እጅግ ውስብስብና ግራኪ የሚባሉ የሞባይል ቴክኖሎጂዎች ተፈጥረው ወደ ኪሳችን መግባት እንዲችሉ አድርጓል።





አመራርነት በድርጅት ውስጥ በሚገኝ የትኛውም ደረጃ የሚኖርና ሊኖር የሚችል ጉዳይ ነው። ምን ማድረግ እንደሚኖርበትና የጠራ ዕይታ እንዲኖረው፣ ወደፊት ለመሄድ ድፍረት የተላበሰ፣ የመስሪያ ሃብቶችን መሰብሰብ የሚችል፣ በፈጠራዊ ዕሳቤ የተቃኘ፣ እንዲሁም በዋናነት ሌሎችን ለማስተባበርና ለማነቃቃት ጉልህ ድርሻን የሚወስድ ማንኛውም ሰው መሪ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል። በታሪክ ውስጥ ስኬታማ መሪዎች በመባል የሚጠቀሱት ዘላቂና ጠንካራ የሆነ እንዲሁም አዲስ የአመራርነት መንገድ መቀየስና በእሱም ላይ ያለችግር መጓዝ የሚችሉ ናቸው። በይበልጥ እነዚህ መሪዎች በምግባራቸው ቅን መሆናቸውና ሌሎች ዕሴቶችን ጭምር መላበሳቸው እስደማሚ ገፅታን ፈጥሮላቸው ሰዎች በሚያውቁትና ወሰን በሌለው ድንበር ዙሪያ እንዲከተሏቸው የሚያደርግ ዕምነት ማረጋገጥ ችለዋል። ባመኑበት ነገር በፅናት ለመቆም፣ በመከራ ጊዜ ቅንነትንና ዕሴትን እንዳስጠበቁ መቀጠል መቻል ታላቅ ብርታትና የውስጥ ጥንካሬን የሚጠይቅ ነው። አንዳንዶች ራስን የመደገፍ ጥበብን የተማሩ ይሆናሉ። ከአዲሱ የራዕይ መንገድ ጋር የተጣበቁ እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን ሀብቶች የሚለዩና ወደ ተግባር እንዲወርዱ የሚያደርጉ ይሆናሉ።

## ○ መሥመርን መለየት እና እሱንም እስከመጨረሻው አጽንቶ መያዝ

ፍላጎቱ ስላለን ብቻ የአገር መሪ ለመሆን መጣር ትርፉ ድካም ነው። ችሎታም ብቻ ለመሪነት የሚያበቃ ነገር አይደለም። መሪ የምንሆነው የግል ፍላጎቶቻችንን ለማግኘት አይደለም። መሪ ስንሆን ትልቅ ኃላፊነትን እንቀበላለን። ይህም ኃላፊነት አገሪቱ ላይ ስላሉ ህብረተሰቦች፣ ስለአገሪቱ ዳር ድንበር መከበር፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ስለመቅረፍ፣ የአገሪቱን መልካም ሥም ስለመገንባት፣ ለመጪው ትውልድ የሚሆን መልካም ስራን ስለመስራትም ጭምር ነው። ታዲያ እነዚህን ሁሉ ኃላፊነቶች ልንወጣ የምንችለው በመምራት ብቻ መስሎ ከተሰማን በጣም ተሳስተናል። መሪነት ኃላፊነትን ለመቀበል የተዘጋጀ ጽኑ ልብን



t.me/OLDBOOKSPDF

ይጠይቃል። ጽኑ ያልሆነ መሪ ግን ለራሱ ጥቅም ብቻ ከማደሩም ባሻገር ከእርሱ በፊት የተሰሩ ስራዎችንም ጭምር ልክ እንደ እንቧይ ካብ ይንዳቸዋል።

ለቦታው ያልተገቡ መሪዎች ብዙውን ጊዜ ለተለያዩ ነገሮች ዓላማቸውን ሲስቱ መመልከት የተለመደ ተግባር ነው። እነዚህ አሳሳች መንገዶች ከመሪ መሪ የተለያዩ ናቸው። በዓለማችን ላይ በመሪዎች ዘንድ የታዩና ለማመን እንኳን አዳጋች የሆኑ አስገራሚ ክስተቶች አሉ። የእንግሊዙን ልዑል እንደ ምሳሌ ብናነሳ በአንዲት ሴት ፍቅር ከንፍ ብሎ «ዘውዱም ሆነ ስልጣን ጦስ ጥንቡሳሴን ይዞ ገደል ይግባ» እንዳለ በታሪክ ተዘግቦ ይገኛል። በእርግጥ ይህንን ድርጊት ትክክል ነው/አይደለም ለማለት እሱ የቆመበት ቦታ ላይ ሆኖ ማየት ተገቢ ነው። ነገር ግን፣ እንደ አገር ድርጊቱን ስንመዝነው በሴት ልጅ ፍቅር አገርን መተው ትልቅ ክህደት መሆኑን የሚገልጹ ጥቂቶች አይደሉም። ለግል ስሜት ተብሎ አገርን የመምራትን ያህል ታላቅ ተልዕኮ ገሸሽ ማድረግ ከማማው ላይ አውርዶ ትቢያ ውስጥ የሚከት አሳፋሪ ተግባር ነው።

አንዳንድ መሪዎች ደግሞ ለገንዘብ ባላቸው ጥብቅ ፍቅር የተነሳ የአገራቸውን ህልውና ጉዳት ላይ የሚጥል ተግባር ሲከውኑ ይታያሉ። በተለይም የአፍሪካ መሪዎች በውጭ አገራት ባንኮች ውስጥ ያላቸው ገንዘብ አገር ላይ ሊሰራበት ቢችል ትልቅ ተዓምር መፍጠር የሚችል እንደሆነ ጥርጥር የለውም። እንዲከተሉት ከተመረጠ ትክክለኛ ፍኖት በማፈንገጥና ሌላ መንገድ በመከተል ምንም አይነት መልካም ነገር ሊገኝ እንደማይቻል ማወቅ ይገባል። ምክንያቱም በበርካታ የተደበቁ ህመሞችና ስቃዮች ከፉኛ የመጠቃት እድል እንዲያመዝን ያደርጋል። በገንዘብ ተሳስቶ ወይም ቶሎ በመበልፀግ ጉጉት ተገፍቶ ከትክክለኛው መንገድ ለማፈንገጥ ሙከራ ሊደረግ ይችላል። ይህ ጉጉትና ፍላጎት ምንጩ ከቀናኢ ልብ አይደለምና ቀስ በቀስ መጨረሻው በህይወት ውስጥ እርካታ አጥቶ ሁሉንም የህይወት መልክ መስልቶችንና ትርጉም ማጣትን ያከናንባል። ሌላው ቀርቶ ያጋበስነውን ገንዘብ በውል ሳንጠቀመው





እንዲሁ ባከኖ እኛንም አባክኖን ይቀራል። ልቅ የሆነ የገንዘብ ፍላጎታችን እንደልከፍት እየባሰ ከቀደመው ጊዜ እጅግ ባጠረ መንገድ ገንዘብ የሚያስገኙ ሌሎች አማራጮችን እንድናገኝ ያቅበዘብዘናል። የኋላ ኋላ የሚፈጠረው የባዶነት ስሜት ከእቅም በላይ ስለሚሆን እርሱን ለመሙላት የትኛውም ዓይነት የእምነት ሥርዓት፣ አደንዛዥ ዕፆች ወይም ሌላ ማንኛውም ማዘውተሪያ ሥፍራ የማይመከቱት ድብታ ውስጥ መውደቃችን እርግጥ ይሆናል። በእንዲህ መልኩ ነገር ካከተመ በኋላ ወደ ትክክለኛው መንገድ የመመለሱ ሂደት ፈታኝና መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ይሆናል።

## ○ ኔትዎርክ መዘርጋት (የግንኙነት መስመር- ድር ማበጀት)

ከቀደሙት የላቀውን ከፍታ ለማየት በቀደሙት ታላላቆች ትከሻ ላይ መሳፈር ግድ እንደሚል የሂሳቡ ሊቅ ሰር አይዛክ ኒውተን አበክሮ ይገልፃል። የበላይነት አለመወሰን፣ በአካልና በህይወት ማዘዝ፣ መረጃን እና ፍጥነትን የሚፈልግ ታላቅ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ መሪነት በሰብዓዊና ቁሳዊ ሃብት ላይ መወሰንንና ማስተባበርን የሚጠይቅ ስለመሆኑ ብዙዎች ይጠቅሳሉ። እነዚህ ወደ ላቀው ከፍታ ለመውጣት የተደላደሉ መንሸዎቻችን እንጂ በራሳቸው ግቦች አይደሉም።

ህይወት አጭር ጊዜ ያላት መሆኗ ለመማርና ለመፍጠር የሚኖረው ጊዜ የተገደበ እንዲሆን ያደርገዋል። ምንም ዓይነት መቅናት ሳይኖር እውቀትና የተግባር ልምድን ከተለያዩ ምንጮች ለማግኘት ዓመታትን ሊያባክኑ ይችላሉ። በዚህ ፈንታ በባለ ጥልቅ ዕውቀት ባለቤቶች የተጠቀሙትን ምሳሌዎች መከተልና ተገቢውን መካሪና ተቆጪ ማግኘት ግድ ይላል።

ትክክለኛ የሆነ መካሪ የሚባለው ፍላጎት ወዴት ማተኮር እንዳለበትና ምን ዓይነት ተግዳሮት ሊደጋጥሙ እንደሚችሉ የሚረዳ ነው። ዕውቀትና ልምዳቸው ከጊዜ በኋላ የራስ ይሆናል። እውነታን



t.me/OLDBOOKSPDF

ያገናዘበ ምክረ-ሀሳብ የሚሰጡ በመሆናቸው በፍጥነት እንዲሻሻል ያደርጋሉ። ፍላጎቶችን በትክክል የሚሞላና ከህይወት ግብ ጋር የሚያገናኝ መካሪን ከመረጡና ዕውቀቱንና ልምዱን ወደ ውስጥ ካዋሀዱ በኋላ በጥላቸው ሥር መቆየትን በመሸሽ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ዓላማ ሊሆን የሚገባው ከመካሪዎች ጥልቅ ዕውቀትና ብልሀት በላይ የላቀ ሆኖ መገኘት ነው።

መካሪ የሚፈልጉበት ምክንያት ቀላል ነው። ህይወት አጭር ቆይታ ያላት በመሆኗ እጅግ በርካታ የሚገለገሉበት ጊዜና ጉልበት ስለማይኖር ነው። የሚፈልጉትን ነገር ከመዕህፍት፣ ከራስ ተሞክሮት እና ከሌሎች በሚገኝ ተሞክሯዊ ምክር ትምህርት ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ግን ሂደቱ ማግኘትና ማጣት የሚፈራረቅበት ይሆናል።

መካሪዎች አቋራጭን ሳይሆን ሂደት የሚፈስበትን መስመር የሚያመላክቱ ናቸው። ሁልጊዜ ጥልቅና ፍሬያማ የሆነ ዕውቀት ይሰጧቸው የነበሩ የራሳቸው መካሪዎች ያሏቸው ሰዎች ናቸው። ተከታታይ የሆኑት የልምድ ጊዜያት ዋጋው የማይተመን ትምህርትና ስልቶች እንዲቀስሙ አስተምረዋቸዋል። ይህ ዕውቀትና ልምዳቸው የራስ የሚሆንበትን አጋጣሚ መጠቀም ያስፈልጋል። ስራን ተመልከተው ትርጉም ያለው ግብረ መልስ በመስጠት ልምምዱ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን እገዛ ያደርጋሉ። በራሥ እርምጃ አስር ዓመታት የሚወስደው ምናልባት ቀድመው ከተጓዙበት ምክር ማግኘት ከግማሽ ባነሰ ጊዜ ሊጠናቀቅ ይችላል። በዚህም ነገሮችን የመማር ሂደት ውስጥ ጊዜን ብቻ ሳይሆን ከመባከን የሚታደጉትን ትኩረት በመስጠት የሚማሯቸውን ነገሮች ወደ ውስጥ የተዋሀዱ እንዲሆኑ ያደርጋሉ። በዚህ ውስን ጊዜ፣ ዕድገትና ምጥቀት ተፈጥሯዊ መልኩን ባልቀየረ ሁኔታ እንዲያብብ ይሆናል።

ይልቁንም፣ በማኪያቬሊ የኃይል መወጣጫና ሥልጣን ማስጠበቂያ ፍልስፍና የተጋረደውን እጥፉ አካሄድ ከውስጣችን አስወግደን ለአንድ ዘመንና ወቅት ከሚያገለግል አሠራር ወጥተን ዘመናትን በተደላደለ መሠረት ላይ ለማቆም የነፍስ ዕውቀት መሠረት





ያደረገውን ምስራቃዊ ፍልስፍና ሣይንሳዊ አቅጣጫን ከተከተለው የምዕራብ ፍልስፍና ጋር በማስተሳሰር ኃይልና ሥልጣን በፅኑ መሠረት ላይ እንዲቆም መትጋት ይኖርብናል።

## የተሳካላቸው መሪዎች መገለጫ ባህሪያት

መሪዎች ሁሉ የተሳካላቸው ናቸው ማለት አይቻልም። የነገሮች ስኬትም ሆነ ውድቀት በመሪዎች ባህሪ ብቻ ይወሰናል ማለትም ምኝነት ነው። ምክንያቱም ሌሎች ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችም ጭምር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እንዲህ በቀላሉ የሚታይ ስላይደለ ነው። ይሁንና አብዛኛዎቹ ውጤታማ መሪዎች የሚጋሯቸው ባህሪያት አሏቸው። እስኪ እነዚህን ባህሪያት አንድ በአንድ እንመልከታቸው።

### ○ በራስ መተማመን

ውጤታማ መሪዎች በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸው። የተሳካለት መሪ ለመሆን የመጀመሪያው ነገር በራስ መተማመኑን መገንባት ሲሆን ይህ ሲባል ግን ራስን ጥሩ ሰው አድርጎ ከመውሰድ በላይ በመሪነት አቅሙ የሚተማመን፣ መሰናክሎችን በጥበብ የሚጋፈጥ፣ በምንም አጋጣሚ አጣብቂኝ ውስጥ ቢገባ ያለውን አቅም አሟጦ መውጫ ቀዳዳ እንደማያጣ ፅኑ እምነት ያለው ነው። በአጭሩ የተሳካላቸው መሪዎች በራስ መተማመናቸው የሚመነጨው ማድረግ ያለባቸውንና ማድረግ የሌለባቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ከመሆናቸው ላይ ነው። ስለዚህም በእነሱ ሥራ ተሞጋሽም ሆነ ተወቃሽ ራሳቸው ሊሆኑ እንደሚገባ ያስባሉ እንጂ ኃላፊነትን ከላያቸው ገሸሽ ሲያደርጉ አይታዩም። ለራሳቸው ታላቅ ግምትን በመስጠታቸው ምክንያት እገራቸው በእነሱ ምክንያት ወደ ታላቅነት እንደምትታመራም ጭምር ይተማመናሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF

### ○ የውሳኔ ሰጪነት ችሎታ

መሪዎች በሚያጋጥሟቸው ክስተቶች ውስጥ የውሳኔ ሰዎች ናቸው። ይህ የውሳኔ ሰጪነት ባህሪያቸው በጊዜ ውስጥ ያዳበሩት ነው። ምንም እንኳ በአወዛጋቢ ሁኔታዎች ውስጥ ቢኖሩም መጨረሻ ላይ ግን የሚሰጡት የተጠና ውሳኔ በአገራቸው ላይ ተፅዕኖን ለመፍጠር ያስችላቸዋል። ያላቸው የእርና የሥራ ላይ ልምድ የነገሮችን መንስኤና ውጤት፣ በነገሮች መካከል ያለውን ዝምድና ቀድመው እንዲረዱ ያግዛቸዋል። ታዲያ ውሳኔያቸውን ዝም ብለው ሌሎች ላይ የሚያራግፉ ሳይሆን ሌሎችም ሀሳባቸውን እንዲረዱ ያደርጋሉ።

### ○ ጥሩ ተግባቦት

ስኬታማ መሪዎች የመግባባት ችሎታቸው ከፍተኛ ነው። ይህ የመግባባት ችሎታ በሌሎች ላይ ተፅዕኖ እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል። አብረዋቸው የሚሰሩትን ተጠቅመው ዓላማቸውን በትክክል ለማሳካት ይረዳቸው ዘንድ ይህ የመግባባት ችሎታቸውን እንደ ቁልፍ መሳሪያ ይጠቀሙበታል። እነዚህ እሳቤዎችን እንዲሮጡላቸው በሚፈልጉት የመሮጫ መም (መስመር) ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩላቸው ማድረግ ይችላሉ። ከሌሎች አገራት መሪዎችም ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ይህንን ችሎታቸውን ተጠቅመው ለወከሉት አገር ትርፍን ያስገኛሉ።

### ○ የማሳመን ችሎታ

እነዚህ መሪዎች ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት ንግግር አሳማኝ ነገሮችን ይናገራሉ። ንግግራቸው ትክክለኛውን መረጃ በቅቡልነት ጊዜ በማቅረብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ተቀባይነት የማግኘት ዝንባሌያቸው ከፍተኛ ነው። የሚያስተላልፉት መልዕክትም ሌሎችን የሚያነቃቃ፣ ዓላማውን ከግብ የሚያደርስ፣ አቅጣጫ የሚሰጥ ነው። ከንግግራቸውም ባሻገር ድርጊታቸውም አሳማኝ ነው። ይህ የማሳመን ችሎታቸው ተቃዋሚዎቻቸውንም ጭምር





ከጎናቸው ለማሰለፍ ይረዳቸዋል። እነዚህ መሪዎች ተወዳጅነትን ያተረፉና መቼም ቢሆን በስራቸው ሥራዎች የሚታወሱ ናቸው።

### ○ የነገሮችን አካሄድ ቀድሞ የመገመት ችሎታ

በመሪነት ቦታ ላይ ማንኛውም ሰው ቢቀመጥ ሊቸገር ከሚችልባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ወደፊት ሊመጣ የሚችለውን ገምቶ አቅዶ መንቀሳቀስ አለመቻል ሲሆን ጥሩ መሪዎች ግን የነገሮችን አካሄድ የሚያጠኑ ናቸው። እነዚህ መሪዎች ስራቸውን የሚጀምሩት ቁጭ ብለው ምን አይነት ውጤት እንደሚገኝ እናያለን በሚል የቸልተኝነት ስሜት ሳይሆን ውጤቱን አስቀድሞ በማየት ነው። በዚህም ምክንያት መፍትሔ አፍላቂዎች ናቸው ያሰኙላቸዋል፡፡ ይህ ችሎታቸው አለፍ ሲልም 'ባለ ራዕይ መሪ' የሚል ተቀፅላ ያሰጣቸዋል።

### ○ የተለያዩ ሰዎችን ምልከታ ከግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ ልብ

እነዚህ ሰዎች የማድመጥ ችሎታን የታደሉ በመሆናቸው ሰዎች የሚያቀርቡትን ሃሳብ በመቀበል አንድን ነገር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመመልከት ይጥራሉ። አድሎ ሳያደርጉ ማዛን የሚደፋውን ሃሳብ ብቻ ይቀበላሉ። ውጤታማ ያልሆኑ መሪዎች ከሌሎች ሃሳብን መቀበልሽንፈት መስሎ ሲታያቸው እነዚህኞቹ መሪዎች ግን ጉድለታቸውን ለመሙላት ይጠቀሙበታል።

### ○ አሳታፊነት

ብልህ መሪዎች "ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒት" የሚለውን አባባል ትክክለኛነት ይገነዘባሉ። በመሆኑም ሌሎችን ቀሳታፊ በማድረግ ሥራዎች በጥራትና በተሻለ ፍጥነት እንዲከናወኑ ያደርጋሉ። ነገር ግን፣ የሚያሳትፏቸው ሰዎች እየሰሩት ያለው ነገር ምን አይነት ውጤት እያስገኘ እንደሆነ በንቃት ይከታተላሉ። ይህ የአሳታፊነት ባህሪያቸው ሥራዎችን በቅልጥፍና እንዲሰሩ ከማስቻሉም ባሻገር

ከተለያዩ አካላት የተለያዩ አይነት የችግር አፈታት ዘዴዎችን እንዲቀስሙ ያደርጋቸዋል። ሆኖም ግን፣ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ሲኖሩና አፋጣኝ እርምጃ ሊወስድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን ውሳኔ ይሰጡበታል። ስለዚህ በአንድ አይነት የአመራር ስልት ላይ ሙጭጭ ከማለት ይልቅ እንደ ሁኔታዎች ራሳቸውን ማስተካከልም ይችላሉ።

### ለሌሎች ጥቅም የሚሰጥ አመራር መዘርጋት

ብዙ መሪዎች ለራሳቸው ፍላጎት ቅድሚያ ይሰጣሉ። በቤተ መንግስታቸው ውስጥ ቁጭ ብለው ጮማውን እየቆረጡ፣ ውስኪውን እየጠጡ ከመኖር በቀር ለምስኪኑ ህዝብ የሚራራ ልብ የላቸውም። አገር በረሃብ እየታመሰች፣ በበጀት ዕጦት ስራዎች በጅምር እንዲቀሩ እየተደረገ እነሱ ግን ለግል ፍጆታቸው ረብጣ ገንዘብ ይሸሽጋሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት አካሄድ አንድ መሪ ሊኖረው ከሚገባ የማይጠበቅ ወራዳ ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም የሚያደርጉት ነገር ከቆሙለት ዓላማ ጋር እጅጉን የተራራቀ ነውና። የራሳቸውን ፍላጎት እንኳ መስመር ማስያዝ አልቻሉምና አገርን የመምራት አቅሙ ያንሳቸዋል። ሃሳባቸውም የራሳቸው የኑሮ ሁኔታ ላይ ብቻ መሠረት ያደረገ ስለሆነ የህዝብ ኑሮ ተመልካች የሌለው ይሆናል። የተሳካላቸው መሪዎች ግን ለህዝባቸው ብለው መከራን መቀበል ቢኖርባቸው እንኳ አያንገራግሩም፤ ልክ እንደ ኔልሰን ማንዴላ። እነዚህ መሪዎች ትክክለኛ የሆነውን ነገር ከማድረጋቸውም ባሻገር ቀድሞ ትክክል ያልነበሩ ነገሮችንም ጭምር ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዙ ያደርጋሉ። ምንም እንኳን ይህ ተግባር አንዳንድ ጥቅማቸው የሚነካባቸው ወገኖችን እንደሚያስከርፍ ቢረዱም የሚመርጡት ሚዛን ወደሚደፋው ነው።

**አታምልከው ፈርተህ፣ አታቀርቅርለት፣**

**አታጎንብስ ከቶ፤**

**ብረት ነው ጠመንጃ፣ የማይገል ራሱን፣**

**ተመሮ ተከፍቶ።**





የሀገራችንን አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር እናስታውስ፣ 'እሳት በሌለበት ጢስ አይኖርም'። በርግጥም በእሳትና በጭስ መካከል ተፈጥራዊ ግንኙነት ይኖራል፡፡ ግን ደግሞ የጢስ ምንጩ እሳቱ ሳይሆን የእንጨቱ እርጥበት መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እንደምሳሌ ለማገዶ የምንጠቀምበት እንጨት ደረቅ ከሆነ ወይም የእሳት ምንጫችንን ወደቡታ ጋዝ ብንቀይረው እሳት ቢኖርም ጢስ የመኖሩ ነገር አጠራጣሪ ነው። በአመዛኙ ፍርዳችን ወደተሳሳተ አቅጣጫ እንዲያዘነብል የሚያደርገው እንዲህ ዓይነቱ በምክንያትና ውጤት መካከል ያለውን ትሥሥር ወይም የችግሩን ሥረ-መሠረት ካለመረዳት እንደሆነ ልብ ማለት ይኖርብናል፡፡

### ውሳኔን ከፍረጃ የፀዳ ማድረግ

ከዳር እስከዳር በሁሉም ሥርዓቶችና መዋቅሮች በመሠረታዊነት ተመሳሳይ ችግሮች የሚያጋጥማቸው ይሆናሉ። እነዚህ የሚያጋጥሙ እክሎች ንቃትን በመላበስ ከዋኜዎች የሚነሱበትን ውስጣዊ ሥፍራ መለወጥን የሚፈልጉ ናቸው። ይህም እንዲሆን ሁለት ሥፍረቶችን (Dimensions) በአንድ ጊዜ መማርና መረዳት ያስፈልጋል። እነዚህም ስፍረቶች የሚነገረው፣ የሚደረገው እና የሚታየው (ለእይታ ገሀድ የሆነው ግዛት) እንዲሁም ከዋኜዎች የሚነሱበት ውስጣዊ ስፍራ (እሳቤና ድርጊት የሚመነጭበት ለእይታ የተሰወረው ግዛት) ናቸው።

የሰው ልጆች ኑሮ በሁለት ዓለም ውስጥ ነው። የመጀመሪያው ሁሉም አይነት አካላት ለእይታ ምርኮኛ የሆኑበት ውጫዊው ገፅታ ብቻ የሚታይበት ዓለም ነው። ነገር ግን ከዚህ እይታ ጀርባ የተደበቀ፣ እነዚህ አካላት በእርግጥ እንዴት እንደሚከወኑ፤ ሥሪታቸውን፣ ክፍሎቻቸውን እና ጠቅለል ያለ ውህደታቸውን የያዘ ሌላ ሁለተኛ ክፍል አለ። ይህ የዓለም ዓይነት በቶሎ ምርኮኛ የማይሆኑለት፣ ለመረዳት ከባድ የሆነ፣ እውነታን ለማየት የሚጥር አዕምሮ ብቻ እንጂ በዓይን ሊታይ የማይችል ነው። በሳል መሆን ጥልቅ የሆኑና ደርዝ ያላቸውን ነገሮች ማውራት ብቻ ሳይሆን



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቃቅን የሚባሉ ጉዳዮችን ጭምር መረዳት ሲጀመር ነው።

ይህ 'እንዴት' የሚለው ክፍል ነገሮች እንዴት እንደሚንቀሳቀሱና እንደሚለወጡ የሚያሳይ የህይወትን ምስጢር የያዘ ነው። 'እንዴት' እና 'ምን' የሚለው ክፍል በዙሪያ ባሉ ነገሮች ላይ ሲተገበር የሚስተዋል ነው። የተፈበረኩ ማሽኖችን እንጂ እንዴት እንደሚሰሩ አያውቁም፤ የተወሰኑ ሰዎች የሆነን ነገር ሲያመርቱና ለገበያ ሲያከፋፍሉ እንጂ እንዴት ቡድን እንደተዋቀረ የሚያውቁ አይሆኑም። በተመሳሳይ ሁኔታ በሰዎች ገፅታና አቋም መማረክና መመሰጥ እንጂ ከጀርባ ያለውን የሥነ-አዕምሮ ጨዋታና ምን እያደረጉ ወይም እየተናገሩ እንደሆነ የሚያውቁ አይሆንም።

ራስን በተቻለ መጠን የምንጠቀምበትን ቴክኖሎጂ፣ የምንሰራበትን ቡድን መዋቅራዊ አሰራር፣ የሙያን ምጣኔ ሃብት፣ አጠቃላይ የሥርዓቶችን ልብ ምት በጥልቀት የምናገኝበትን አጋጣሚ መፍጠር ያስፈልጋል። ምንጊዜም ነገሮች እንዴት ይሰራሉ? ውሳኔዎች እንዴት ይሰጣሉ? ቡድኖች እንዴት መሥተጋብር ይኖራቸዋል? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳትና ምላሻቸውን ለማግኘት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ዕውቀትን በእነዚህ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ዙሪያ እንዲሽከረከር በማድረግ እውነታን በተመለከተ ጥልቅ የሆነ አረዳድና እርሱንም ለመለወጥ የተራዘመ ኃይል እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል።

ለበሽታችን ፍቱን መፍትሄ ከመስጠት የሚያግደንም፣ ሁሌም በታማሚነት እንድንዘልቅ የሚያደርገንም ይኸው ሥረ-መሠረትን አጥርቶ ለመረዳት ያለን ውስንነት መሆኑን ከሚቀጥለው ተረታዊ ምሳሌ መረዳት እንችላለን።

ሰውየው ወዳጁን፣ "ስለምን ሚስትህን ገደልከ?" ብሎ ይጠይቀዋል።

ወዳጁም "ከሌላ ወንድ ጋር ስትተኛ አገኘኋት" ሲል ይመልሳል።





"ታዲያ ሰውየውን መግደል አይሻልም ኖሯል...?" ሲል ጠያቂው አስተያየት አዘል ጥያቄውን ያስከትላል።

"እንዲያማ ካደረኩ የኔ ሥራ በየጊዜው የእርሷን ውሽሞች ሲገድሉ መኖር ሆኖ ቀረ ማለት ነው!" በማለት ይመልሳል።

ይህ ሰው በሚስቱ ላይ ያደረገው ነገር ትክክል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከመወሠናችን በፊት ሌላ ገጠመኝ እናስከትልና በአንድ ሚዛን ለማነፃፀር እንሞክር፡፡

አንድ ጥበበኛ ወጣት እጅግ በሚያምርና ዕይታን በሚስብ ወንዝ ዳርቻ ተቀምጦ ሳለ በንፋስ ተገፍቶ ወደ ውኃው የወደቀ እጅግ በጣም አስፈሪ ጊንጥ ይመለከታል። የጊንጡ ህይወት እንዳያልፍ ብሎ በማሠብም ይታደገው ዘንድ ወስኖ ሊያወጣው እጁን ወደ ወንዙ ሰደደ። ጊንጡ ግን ህይወቱን ሊታደግ ለሚጥረው ሰው ምላሹ መናደፍ ሆነ፡፡ በጊንጡ አፀፋ የተደናገጠው ወጣት በቅፅበት የሚንዘረው እጁን አነሳ፡፡

ነገር ግን፣ አንዲትም ደቂቃ ሳይዘገይ ስቃዩን እንደተሸከመ ለሁለተኛ ጊዜ የዚያን የጊንጥ ህይወት ለማዳን እጁን ዳግም ሰደደ። አጅሬ ጊንጥም ለሁለተኛ ጊዜ ተናደፈ። ወጣቱ በሲቃ ውስጥ ሆኖ እየተዝለፈለፈ የተነደፈ ጣቱን በጨርቅ ጠቅልሎ ለሶስተኛ ጊዜ እጁን ወደ ጊንጡ ከመሠንዘር አልቦዘነም፡፡ ይሄን ጊዜ፣ ድራማዊ የሚመስለውን ትዕይንት በቅርብ ርቀት ሆኖ ሲከታተል የነበረ አንድ ሰው በመገረም እንዲህ ሲል ጮኸ፤

"አንተ ሰው! ምን እስኪያደርግህ ነው የምትጠብቀው? እየነደፈህ ለምን ልታድነው ትጥራለህ? ለምን አትገድለውም?" ይለዋል፤

ወጣቱ ግን፣ ለዚያ ግለሰብ የሚሆን ጆሮ ያለው አይመስልም፡፡ ላመል እንኳ አንገቱን ወደ ሰውዬው ሳይመልስ ጊንጡን ለማዳን ጥረቱን ቀጠለ። በመጨረሻም ተሳክቶለት ጊንጡን ከሞት ታደገው።

ከዚያም፣ ቀድሞ ጊንጡን ስለመግደል ምክር ለግሶት ወደነበረው ግለሰብ እያማተረ እንዲህ ሲል በጩኸት ተናገረ፤

"ስማኝ ወዳጄ... መናደፍ የጊንጡ ባህሪ ነው፤ የኔ ባህሪ ደግሞ ማዘንና ማሠብ ሆነ። ታዲያ ስለምንድን ነው የኔ ባህሪ ከርሱ ባህሪ የከፋ እንዲሆን የምትመክረኝ?" አለው።

ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ እንዲህ እንደ ጊንጡ በመናደፍ እያቆሰሉህና እያደሙህ፤ እየዝዘዙህና እየሸረከቱህ የሚመሳሰሉ ሰዎች ቢኖሩም ዕምነትህ ባንናፀፊህ መልካም ሥነምግባር ልትገራቸውና ሊታቀርባቸው ግድ ይልሃል። በዙሪያህ ያሉ አካላት ወደ እልህና አላስፈላጊ ስሜት ውስጥ እንድትገባ ቢያደርጉህና ያልሆነ ሥነምግባር ውስጥ እንድትዘፈቅ ቢወተውቱህም ጆሮ ልትቸራቸው አይገባም።

ጨለማ በራሱ ከብርሃን በተቃራኒ የቆመ ነገር ሳይሆን የብርሃን አለመኖር የወለደው ነገር እንደሆነ ሁሉ፣ ችግርም በሃሳብ እጦት የሚፈጠር መሆኑን ዕወቅ። በሚደርስብህ መከራና ችግር ሁሉ እስቀድመህ ወደሌሎች ጣትህን ከመቀሠርህ በፊት በቅድሚያ ወደ ራሥህ መመልከት ይኖርብሃል። ሌሎችን ከማረም በፊት ራሥህን ለማረም ወኔ ይኑርህ። እንዲያ ባደረግከም ጊዜ ከሌሎች ጋር በየዕለቱ የምትፋጅበት አጋጣሚ ይቀንሳል። በዚህም ነገሮችን እንደወረዱ የማስተናገድ ልማድህ ተቀይሮ ነገሮችን ወደ መመልከት/ማስተዋል ደረጃ መሸጋገር ትጀምራለህ። ይህ የለውጥ ሂደት ቀላል፣ ነገር ግን ዋጋ ሊያስከፍል የሚችል ታላቅ ጉዳይ ነው። በትክክል ነገሮችን ለመመልከት ጥያቄዎችንና ፍላጎቶችን ግልፅ ማድረግ፣ ትኩረት ወደ ሚደረግበት ዓውድ ማዘንበል፣ እንዲሁም ከመፈረጅ ስሜት ነፃ መሆን ያስፈልጋል። 'የመፈረጅ ስሜትን መተው' ማለት ያለፉ ንድፎችንና ልማዶችን መሠረት አድርጎ መመልከትን በመተው አዲስ የሆነ፣ መገረምና ጥያቄ ማንሳት የሚያስችል ቦታ መፍጠር ነው።





## በውሣኔ ወቅት የሠከነ ልብን መረዳት

ለውጥን ለማምጣት የሚደረጉት አብዛኛዎቹ ጥረቶች እንዳይሰምሩ የሚያደርጋቸው ምክንያት ጥሩ የሆነ ዕሳቤ ወይም ከፍተኛ ምኞትና መነቃቃት ያለው መሪ በመጥፋቱ ሳይሆን ተከታዮቻቸው መሪዎቻቸው ከፊት ለፊት የሚታያቸውን የለውጥ ምዕራፍ ለመመልከት አለመቻላቸውና ይህንንም መነሻ አድርጎ ለመሥራት አለመሞከር ነው። ሰዎች ለውጥን የሚቃወሙበት ብቸኛ ምክንያት አስቸጋሪ ለውጦችን እንዲያመጡ ሲጠየቁና በተጨማሪ የለውጡን አስፈላጊነት ለመረዳት የሚያስችል የተመቻቸ ዓውድ ሲነፈጉና እንዲሁም ምናባዊ እይታ ሳይኖራቸው ሲቀር ነው። በዚህም ምክንያት የአመራርነት መሠረታዊ ሥራ ሰዎች የመመልከት ዓቅማቸውን በአንድ ላይ ፈልገው እንዲደርሱበት ማስቻል ይሆናል። እዚህ ላይ አንድ ታሪክ ለአብነት ማንሳት ይቻላል።

አባት የሚጠባ ልጁን እንዲጠብቅለት ከውሻው ጋር ቤት ውስጥ ትቶት ወደ አደን ይሄዳል። ከአደን ሲመለስ ውሻውን በደም ተጨማልቆ በሩ ላይ አገኘው። ታዲያ ሰውዬው አፉ በደም የተጨማለቀውን ውሻ ተመልክቶ የልጁን መበላት ቅንጣት ታክል ባለመጠራጠሩ በንዴት ከአደን የተረፈውን ጥይት ውሻው ላይ አርከፈከፈበት። ከዚያም የተበላ የልጁን ቁርጥራጭ ሰውነት ሊመለከት ጠብመንጃውን የሞተ ውሻው ላይ ወርውሮ ወደ ቤት ውስጥ ሮጦ ገባ። ግን የገጠመው ነገር ካሰበው በተቃራኒው ሆነ። ልጁ ላይ አንዳችም መጥፎ ነገር አልደረሰም ነበር፤ ይልቁንስ ከፊት ለፊት በደም የተጨማለቀ ተኩላ ሞቶ ተመለከተ። ለካ ውሻው እንዲያ በደም የተጨማለቀው ያንን ምስኪን ህፃን ከተኩላ አፍ ተሩልሞ ሲያስጥል ነው። አባትም ስሜቱ አሸንፎት የዕድሜ ልክ ፀፀት የሆነበትን ስራ ፈፀመ።

ታሪኩ እንደሚያስረዳው፣ ላይ ላዩን በሚያይ ዓይንህ ብቻ ተመልከተህ ፈጥነህ መፍረድ እንደሌለብህ ነው፤ የሰከነ ልብህን ለፍርዱ ሹመት ስጠው፤ በችኩላ ሥህተት ሠርተህ ህይወትህን



t.me/OLDBOOKSPDF

በሙሉ የሚፀፀትህ ነገር ውስጥ እንዳትገባ ይታደግሃል። ለውሳኔ አትቸኩል! 'አንድ ሰው በእርግጥ አንድ ዓይኑ ጠፍቶ ቢመጣ ዓይኑን ያጠፋው ሰው እስኪመጣ ድረስ አትፍረድለት። ምክንያቱም ዓይን አጠፋ የተባለው ሰው ሁለቱም ዓይኑ ጠፍቶበት ይሆናልና!' ይህ ጥበባዊ የዳኝነትና ውሳኔ ሰጪነት ምክር ከልቦናህ አይጥፋ። የአንጎል ውሳኔ ዝብርቅርቅና ወቅታዊ እንደሆነ ልታውቅ ይገባል።

አንዲት እናት በታክሲ ሹፌር ስለተደፈረች ልጅ በዜና ብትሰማ ልጇቿን በታክሲ ወደ ትምህርት ቤት ላለመላክ ልትወስን ትችላለች። ሆኖም ግን ከሳምንት በኋላ በሌላ ዜና ይህቸው እናት ህፃናት በመንገድ ላይ አደጋ እየደረሰባቸው መሆኑን ስትሰማ ደግሞ ልጇቿን በታክሲ ለመላክ ትገደድ ይሆናል። ከዚህ ሌላም ነገር ቢፈጠር ሌላ ዓይነት ውሳኔ ልትወስን እንደምትችል እርግጥ ነው። በመሆኑም የአዕምሮ ውሳኔ በጊዜና ምክንያት የሚቀያየር እንጂ ወጥ የሆነ የማይቀያየር ነው፣ ብሎ መናገር ያዳግታል።

ውሣኔ ሰጭነትና ዳኝነት በጥበብ ካልተያዙ የሚያስከፍሉን ዋጋ ከምንችለው ዓቅም በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይም የኃይልና የሥልጣን ባለቤት ስንሆን ዋጋ እስከፋይነቱ ከዚህም ይልቃል። በሥልጣን ላይ የሚወሠኑ ውሣኔዎችም ሆኑ ተግባራዊ የሚሆኑ ድርጊቶች የሚፈጥሩት በጎም ሆነ መጥፎ አስተዋጽኦ በአገር ደረጃ የገዘፈ ነው። ያልተጤኑና ቀድመን መጨረሻቸውን ያላየናቸው ተግባራት ወዳልታሰበ አቅጣጫ ሊያመሩ ይችላሉ።

የጀርመኑ ሂትለር ያደረጋቸው ነገሮች ዛሬም ድረስ ጀርመናዊያን የሚያፍሩበትና ጥቁር ጠባሳውን ጥሎ ያለፈ ከስተት መሆኑ ይታወቃል። ጎረቤታችን ደቡብ ሱዳን ነጻነቷን ባገኘች ማግስት ወደ ብጥብጥ ማምራቷና ይህንን ችግር ከስሩ ለመንቀል የተዘጋጀ ባለሥልጣን አለመኖሩ እንዲሁ የመሪዎች አርቆ ያለማየት በሽታ ነው።





## አዲስ አቅጣጫ

የመጨረሻውን እርምጃ አሳምሮ በድፍረትና በዕውቀት መራመድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በዘመናችን ውጤትን ሳይሆን ለውጤት የሚደረገው ዙሪያ ጥምጥም ጉዞ በራሱ ጉዞ ተደርጎ የሚታይበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። ብዙ ጊዜ ከሥራና ውጤት ይልቅ አንድ ጥራዝ ሪፖርት ስለጉዞ ሲቀርብ ይስተዋላል። ይህም ሁሉንም ነገር እስከ መጨረሻው ማቀድ አለመቻል የሚፈጥረው ሳንካ ነው። ለዕድልና አጋጣሚ የሚተው ምንም አይነት ነገር ሊኖር አይገባም። በተግባራ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ አጋጣሚዎችን፣ ማነቆዎችን፤ ልፋትን ዋጋ ሊያሳጡና ላያሳጡ የሚችሉ ዕድልና ዕጣዎችን በመለየት ከወዲሁ በዕቅድ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል። አስቀድሞ የመጨረሻውንና እርሱን ተከትሎ የሚመጣውን ደረጃ በማቀድ በመካከል በሚኖሩ ገጠመኞች መዳከም እንዳይኖር እንዲሁም የትና መቼ እንቅስቃሴን መግታትና ማስቀጠል እንደሚገባ ለማወቅ ያስችላል።

ብዙዎች የእንቅስቃሴያቸውና የድካማቸውን ፍሬ ሳያጣጥሙ መሀል ላይ የቀሩት አሁን ላይ ሆነው መጨረሻቸውን ማቀድ ስላልቻሉ ነው። ይህን ዕቅድ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ አማራጮችንና ወቅታዊ ሁኔታዎችን ተከትሎ የሚመጡ ለውጦችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል። ምሉዕነት የሚጎድለው ዕቅድ የመጨረሻ ሪፖርቱ ውጤት አልባና በጉዞ የተሞላ ብቻ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ምሉዕ የሆነ ዕቅድና በውጤት የታጀበ ሪፖርት ጠንካራና ደካሞች የሚለዩበት አንዱ መስፈሪያና ሁነኛ ሚዛን ስለመሆኑ የምታስረዳ አንዲት የምስራቅ ዓለም ወግ እንመልከት።

በጣም የተለየ ችሎታ ያለው አንድ አንበሣ በአገር በምድሩ ዝናው መናኘት ይጀምራል። ይህ አንበሣ እጅግ ብልህ ከመሆኑ የተነሳ፣ ማንንም በልቡ መጠራጠር ሳያሳድር ከቀረበው፣ አንዳችም ጉዳት ሳያደርስ እንደታማኝ ውሻ እጅን እስከመላስ ይደርሳል። ይሁንና



t.me/OLDBOOKSPDF

በልባቸው ሥጋትና ፍርሃት አሳድረው በመጠራጠር የቀረቡት እንደሆነ ግን ይቆጣል፤ አልፎ አልፎም መቆጣት ብቻ ሳይሆን፡ እንዲህ ያለ መጥፎ ሃሳብ ስለኔ እንዴት ሊኖርህ ቻለ? በሚል ስሜት ጉዳት እስከማድረስ ይጓዛል፡፡

ይህንን የአንበሣውን ዝና የሰማ አንድ የሩቅ አገር ሰው ይህን ተዓምር በዓይኔ ማየት አለብኝ በማለት ከአንድ ዓመት በላይ በጉዞው ያጋጠመውን መከራና ችግር ተቋቁሞ አንበሣው ወዳለበት አካባቢ ይደርሳል። ወደ አንበሣው መግቢያ ትኬት የሚቆረጥበት ሥፍራ ደርሶም አንበሣውን በርቀት እየተመለከተ ከቆመበት መንቀሳቀስ አልሆንልህ ይለዋል። በዙሪያው የነበሩ ሰዎችም ይህን የሩቅ አገር ተጓዥ እንዲህ በማለት ያደፋፍሩታል፤

"ሊዚህ አንበሣ በነበረህ ፍቅር የተነሳ ቤት ንብረትህን ትተህ ለአንድ ዓመት ተጉዘህ እዚህ ደርሰሃል። እንግዲያው አሁን ምን ያስቆምሃል?! አንድ እርምጃ ጠጋ በል እንጂ..." እያሉ ያደፋፍሩት ነበር፡፡ ነገር ግን የሩቅ አገር ተጓዡ ሰውም ሆነ በዙሪያው ያሉ ማናቸውም ቢሆኑ ያቺን የመጨረሻ እርምጃ ሊራመዱ አልደፈሩም። ሁሉም፤ 'የእስከዛሬው ሁሉ ቀላል ነበር፤ ይህቺ የመጨረሻ እርምጃ ግን ሲበዛ ከበደችን!' በማለት ተደምመው በሃሳብ እንደተዋጡ ቀሩ።

በታሪክ ፊት ደማቅ አሻራ አትመው ያለፉ ታላላቅ የፖለቲካም ሆኑ የንግድ መሪዎች እዚህም እዚያም ሞልተዋል፡፡ ታዲያ ለዚህ ለገናና ስማቸው መሠረት የሆነውን ሁነኛ ከንውን ብንፈትሽ በመስካቸው የመጨረሻዋንና ከባዷን እርምጃ በመራመዳቸው እንደሆነ እንረዳለን፡፡ የአሳት እራት ሆኖ ተፈጥሮ ወደሚፋጅ ነበልባል አልቀርብም ማለት የማይቻል ነገር ነው፤ ቢያንስ ቢያንስ ከሁለት አንዱን ተፈጥሯዊ ህግ ማጉደል ይሆናል። እሳቱ ወይ እሳት አይደለም፤ አለበለዚያም እሳቱን ሸሽቶ የቀረው እውነትም እሳት እራት አይደለም።

በርግጥ በወንዝ ላይ እንደተጣለ ገቡቱ ከሆንን ውሳኔያችን ላይ





አጠራጣሪ ነገሮች መከሰታቸው አይቀርም። የጉዟችን አቅጣጫ የሚወሰነው በእኛ ሳይሆን በወንዙ ነው፤ ብለው የሚሟገቱ ይኖራሉ። በተቃራኒው ሰው መሆን በዕጣ ፈንታችን ላይ የመወሰን ሙሉ ኃይልና ሥልጣን ያላብሰናል፤ ብለው የሚከራከሩም አይጠፉም።

በሌላ በኩል፣ ነገ የዛሬ ውሳኔያቸው ውጤት እንደሆነ እምነው ነገአቸውን ለማሳመር ደፋ ቀና የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች የነገው ስኬት በዛሬ ውጣ ውረድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን የሚያምኑ ናቸው፡፡ ጉዞው ረጅምና አሰልቺ ነው፤ ፈተና የበዛበትና ትዕግስትን የሚፈታተን ነው። ቶማስ ኤዲሰን አምፖል ለመስራት ሺህ ጊዜ በሕይወት መስመር ወድቆ ተነስቷል፤ ሺህ ጊዜ ተፈትኗል። ነገር ግን የመጨረሻውና ወሳኙ አንድ እርምጃው ከተሳሳተባቸው 999 ርምጃዎች የተሻለና ድንቅ ነበር።

ከፊት ለፊት ተዘርግቶ በሚታየው መንገድ ላይ ራስን ከማስጓዝ ይልቅ መንገዱ ራሱ ጉዟችንን እንዲወስን፣ እግራችንን ይዞ እንዲመራና እንዲወስደን መጠበቅ ሞኝነት መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። በተቃራኒው ካሥብን ግን አንዲት እርምጃ እንኳን ሳንጓዝ ስለመንገዱ ወጣገባነት ስናላዝን መኖራችን ግድ ይሆናል፡፡

**ምን ነካው መንገዱ?**

**....እንዲ ስሙኝማ**

**መንገዱ ምን ነካው? እኔን የጠመደ፤**

**ርቁ እንዳልጓዝ እግሬን የጠመደ፤**

**ጥርጊያ ነው መንገዱ ምቹ እየተባለ፤**

**እኔ ስሄድበት እሾህ አበቀለ፤**

**ቁልቁል ነው አይደክምም ሲባልለት ከርሞ፤**

**እኔ መድረሴን ሲያውቅ ዳገት ሆነ ደግሞ።**

ጻዓም ቅኝ ግዛት፥ ሙያና አብነታዊ ተምሣሌት

በአገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ቁም ነገርን በቀልድ እያዋዙ በቅኔ መሰል ያቀርቡ እንደነበሩት አለቃ ገብረሃና ሁሉ፤ በዓረቡ ዓለም ከሚነገሩ ታሪኮች፥ ቀረቶች፥ ምክሮች እና ቀልዶች ውስጥ ስሙ ከማይጠፋውና እጅግ ተወዳጅ የሆነው ሰው ከተናገረው ቀልድ ውስጥ አንዱን እንንሳ፡፡ ሰውዬው የቱርኩ ሙላ ናስሩዲን ነው፡፡ ጥበበኞቹ ሱፊዎች ጥበባዊ ምክሮቻቸውንና ዕውቀቶቻቸውን ለማስተላለፍ ቀዳሚ ምርጫቸው ያደርጉታል፡፡ ቁምነገር ከማያጣው ታሪኮቹ መካከል አንዱቷን እዚህች ጋ አምጥተን እንመልከታት፡፡

በጥበቃ ላይ ተሰማርቶ የነበረ አንድ ፖሊስ በዋናው መንገድ ላይ በማለፍ ላይ ሳለ ከመንገድ መብራቱ ሥር ናስሩዲን አንንብሶ የሆነ ነገር በመፈለግ ላይ መሆኑን ያስተውላል። ጥቢቃው ቀልጠፍ ብሎ፤

"ናስሩዲን ምን እየፈለክ ነው?" ሲል ይጠይቀዋል።

ናስሩዲንም፤ "የቤቴ መግቢያ በር ቁልፍ ወድቆብኝ ነው" ሲል ይመልሳል።

በጥበቃ ላይ ተሰማርቶ የነበረው ፖሊስ መጠራጠሩን ትቶ ከናስሩዲን ጋር በጋራ ቁልፉን መፈለግ ይጀምራል። በታው ቁልፍ ሳይሆን የወደቀ ጠፍን ማስለቀም የሚያስችል ይ!... ያለ የመንገድ ዳር መብራት የተለኮሰበት ሆኖ ሳለ የቁልፉ አለመገኘት ግርታ ውስጥ የከተተው ጠባቂ ካንነበበት ቀና ብሎ...

"ናስሩዲን ቁልፍህን እዚህ ቦታ ስለመጣልህ እርግጠኛ ነህን?" በማለት ጥያቄ ያቀርብለታል።

ናስሩዲን ሲመልስ፤ "ለነገሩ እንኳን ቁልፉ የወደቀብኝ እዚህ ሳይሆን ቤቴ መግቢያ ጨለማ ውስጥ ነው። ለፍለጋው ግን ጨለማው ውስጥ ከመድናበር እዚህ ብርሃኑ ላይ ይሻላል ብዬ ነው" ሲል ተናገረ።





ወደ ሰድገት የሚያሻግረንን ድልድይ ሰይተን እውቀን ሙሉ አትኩሮታችንንና ስሜታችንን ወደርሱ አለመመለሳችን ወደባሰ አዘቅት ውስጥ እንደከተተን የሚያስረዱ በርካታ ማሣያዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡... ትናንት በሌሎች የተሜኑብን የኢኮኖሚና ፖለቲካ ሥርዓቶች ብቻ ሳይሆኑ፤ እኛን የማይመስለው የሚዲያ ፖሊስና ስትራቴጂዎችን ዓይነተኛ ማስረጃና ሸጋ መማሪያዎች ናቸው።

ዓለማችን ድንበር ተሻጋሪ የሆነ ፍላጎትንና ዕሳቤን ማራመድ በሚፈልጉ ኃይሎች በምዕራብም ሆነ በምሥራቅ እየተናጠች ትገኛለች። ምዕራብ መራሽ የሆኑ ግዙፍ ኩባንያዎች ከዲፕሎማሲያዊና ፋይናንሳዊ ጉዳይ ጀምሮ እስከ ወታደራዊ ግንኙነትን በመመሥረት የተፈጠሩበትን መኖሪያ በመልቀቅ ፀሐናቸውን በመላው ዓለም እያስፋፉ ይገኛሉ። ዓለምን ወደ አንድ ለማምጣትም ከፍተኛ የሆነ ሚስጥራዊ ሥራ በመስራት ላይ እንደሚገኙና ውሳቸው ያልተጨበጠ መረጃዎች በየጊዜው በሚዲያ ላይ ይለቀቃሉ። የሊበራል ሚድያ ኢንዱስትሪም ራሱን ከእነዚህ ዓለም አቀፍ ፍላጎቶች መካከል በማድረግ የሉአላዊነት የመገናኛ ብዙሀን መገለጫ የሊበራል ጆርናሊዝም እንዲሆን እያደረገው ይገኛል።

ታሪክ በግልፅ እንደሚያስቀምጠው የምዕራባውያኑ የመንግስትና የግል መገናኛ ብዙሀን አሠራርና አካሄድ በራሳቸው መንገድ የተቃኙ ነው። ሁሉንተናዊ ልዕልናቸውን በእያንዳንዷ እንቅስቃሴ ለማስረፅና ለማሳካትም ከመዋዕለ-ህጻናት ጀምሮ የተማረው ትውልዳቸው ላይ በረጅም ጊዜ ይሰራሉ፤ በኋላም የርዕዮተ-ዓለሙ አቀንቃኝና ጠበቃ ሆነው ይቀጥላሉ። ይህን እውነታ ጀርመናውያኑ የፍልስፍና ሊቆች ቴኦዶር አዶርኖ እና ማክስ ሆሚየር "Dialectic of Enlightenment" በሚል ርዕስ በፃፉት ፍልስፍናዊ ትንታኔ፤ የባህል ኢንዱስትሪው ህብረተሰቡን በዕውነትና ምትሃት መካከል ያለው ልዩነት እስኪጠፋው ድረስ እደንዘዙታል። በመሆኑም የመጪው ዘመን ሥርዓታዊ ለውጥ የሚታሰብ ባይሆንም ተስፋ እለ ከተባለም

ብቸኛው ተስፋ እዚህ ጥምቀት ውስጥ ያልተነከሩ ብቻ ብፁአን ናቸው፣ ይላሉ። በመፅሀ

ሃፋቸውም የባህል አብዮት ከሆሊውድ ፊልሞችና ሙዚቃዎች ጀምሮ ሁሉንም ዓይነት የመዝናኛ ውጤቶች የሚያካልል የሆነ የመጨረሻው ዘመን የነፃ ገበያ ዋነኛ ክስተት ነው። የእነዚህ ዕውቅና ያገኙ ባህሎች ፈጠራና ንድፍ ዕሳቤ ደግሞ እያደገ የመጣውን የብዙሀን ካፒታሊስት የመዝናኛ ፍላጎት ከዳር ለማድረስ ይሆናል፣ ብለው ያስቀምጣሉ።

አዶርናና 'የባህል አብዮት' ለሚለው ቃል የተለየ ትኩረት በመስጠት 'የብዙኀን ባህል' ከሚለው ቃል በላቀ የተመረጠው የባህል አብዮት የሚለው ቃል ከብዙኀን የመነጨ እንደሆነ ላለማሳየት ነው፣ በማለት ያስቀምጣል። ሁሉም የባህል አብዮት ውጤቶች ማለት በሚያስችል ሁኔታ ፈጠራና ንድፋቸው መሠረቱን ያደረገው ትርፍን መሰብሰብ ላይ ነው። በዚህ አግባብ ጥበብ ራሱን ችሎ የሚገኝ ሳይሆን በምርት ኢኮኖሚያዊ ዝምድና ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ምርት ነው። ለዚህም በዋናነት መከራከሪያ ሀሳብ አድርገው የሚያቀርቡት ባህልን የገቢ ማስገኛ ማድረግ የአዕምሮ ውጤት የሆነው ሃሳብ ገቢ እንዲያስገኝ ማድረግ ነው፣ ሲሉ ይገልፃሉ።

በዚህ አረዳድ የባህል ኢንዱስትሪው ውጤት የሆኑት የሚድያ አማራጮች ለህዝቡ ተደራሽ የሚያደርጉት አገልግሎት ዋነኛ ትኩረት ትርፍን ማሰባሰብ እንጂ ብዙኑ ህዝብ ከሚቀርቡት አገልግሎቶች ትናንትን አውቆና መሠረት አድርጎ ዛሬ ላይ በመሆን ነገን የተሻለ ለማድረግና ለመተግበር የሚያስችለውን፣ ከተለያዩ ብሽርታዎችና ያልጠሩ ዕሳቤዎች ነፃ የሆነን ዕይታ ማቅረብ ላይ እምብዛም ትኩረት የሚያደርጉ አይሆኑም። ይህንንም አስመልክቶ የባህል አብዮት የሚያንናፅፈው ብቸኛ ነገት በጥልቀትና በአንክሮ ማሠብና ማስተንተን እለመቻልን ነው፣ ብለው ያስቀምጣሉ።

ፀሀፊዎቹ ዳሰሳቸውን በመቀጠል 'የባህል አብዮት' ነፃ (ራስ ገዝ)





አስተሣሠብንና ትችት ማቅረብን በማስወገድ ገገር የሆነውን መደብ ብቻ በጭፍን እንዲያገለግሉ እንደሚያደርግ ገልፀዋል:: ገገርው መደብ ላይ የሚስተዋሉ ጉድፎችንና አንከናችን በቀላሉ በብዙሀን ትኩረት ውስጥ እንዳይወድቁ ቀላል የሆነ የሚዝናኑበት ነገር (ከእውነት የራቀ እምነት) ለህዝቡ ማቅረብ ላይ ደፋ ቀና ሲያበዙ ይስተዋላል።

ኢትዮጵያ ምዕራባውያን አገራት ከሚከተሉት የዕድገት ትርጓሜ ይልቅ የራሷ የሆነ ዕይታ ያላት አገር ናት። በመሆኑም ፋት የሆነና ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ ከማገናዘብ የራቀው የሊበራል ጆርናሊዝምን ብቸኛ አማራጭ አድርጎ ለመቀበል ማለም ብቻ በቂ አይሆንም። ውድድር የሰፈነበት የነፃ ገበያ መፍጠር የሚያስችሉ ዘመናዊና ሊበራል የሆኑ ጋዜጠኞች መካከለኛ የኑሮ ደረጃ እርከን ውስጥ ከሚገኙት ህዝቦች መካከል አሉን ወይ? የሚለው ተገቢ ጥያቄ ይሆናል። መልሱም በጭራሽ የሌሉንና ወደፊትም እነዚህን መሰል ጋዜጠኞች ማፍራትና ማጎልበት እንደሚኖርብን የሚጠቁም ይሆናል።

በሙያዊ አገላለፅ በሠሜኑ ንፍቀ ክበብ የሚገኙት ያደጉ አገራት 'ዕድገት' የሚለውን ሃሳብ፣ በነፃ ገበያ ውስጥ ማን አገኘ? ማንስ አጣ? የሚለውን ከግምት ውስጥ ያላስገባ አዲስ የተፈጠረ ሃብት እንደሆነ ነው የሚለኩትና የሚረዱት። ማግኘትና ማጣት ሰዋዊ ባልሆነው ነፃ ገበያ ውስጥ ሽልማትና ቅጣት ናቸው። ይህን መሠሉ የዕድገት ጽንሰ ሀሳብ ትርጓሜ በውስጡ ያካተተ አቅጣጫ በአንፃሩ ለኢትዮጵያ የሚሰራ ነው ብሎ መቀበል ያስቸግራል።ስፊ ወሰን ያለው የግል ዘርፍና ሲቪል ማህበራት እንደልብ ባልተስፋፉበት ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ ቁጥር ያለውን የብዙሀን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል መንገድ መቀየስ ያስፈልጋታል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ዕድገትን ከልማት ጋር አጣምራ ማስኬድ ሲጠበቅባት ከዕድገቷ ጋር ያልተመጣጠነ የፖሊቲካል ኢኮኖሚ ፍልስፍና መከተሏ ኪሳራን ይዞባት መምጣቱ አይቀሬ ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

የሊበራል ጋዜጠኝነት ማህበራዊ መሠረት የሆነው በበቂ ሁኔታ የተማረ፣ መረጃ ያለው፣ ከተሜና ኢንዱስትሪያዊ፣ ግለኝነት የሚስተዋልበት እና በሣይንስ የተቃኘ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ እምብዛም መሰረት ያለው አይደለም። ሊበራል ጆርናሊዝም ባደጉት አገራት ብቻውን ተነጥሎ ዘርፉን ለማሳደግና ለማዳበር ግብና ተልዕኮ ተቀርፆለት የሚሰራበት ሳይሆን ከመሠረቶቹ ጋር ጎን ለጎን የሚያድግ አንድ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው። በልማት ጋዜጠኝነት ዘውግ ግን ይህ የማህበረሰብ ማህደር ከሊበራል ጆርናሊዝም እንዣር ባነሰ ጊዜ እንዲዳብር፣ እንዲስፋፋ እና እንዲያድግ የሚፈለግ አንድ ፕሮጀክት ይሆናል።

ኢትዮጵያ ዘመናዊ ጋዜጠኝነትን በስራ ላይ ለማዋል አመቺ ማህበራዊና የባህል መሠረቶች በተጨባጭ የማይገኙባት አገር ናት። ጥንታዊ ባህል የነገሰባት፣ ከፍተኛ ቁጥር ባለው አርሶ አደርና አርብቶ አደር የተሞላች፣ እንዲሁም ኢንዱስትሪና ሙያ ወለድ በሆኑ ግብሮች ላይ የተሰማሩ ዜጎች እምብዛም የማይገኙባት መሆኗ ነው። ዘመናዊ ጋዜጠኝነት ግላዊነትንና ትርፋማ አካሄድን ተቀዳሚ ምርጫው ሲያደርግ ኢትዮጵያውያን ግን በወል የመኖርና የቡድን መብትን ለማረጋገጥ የሚጥሩ ማህበረሰቦች ናቸው። ኢትዮጵያ ብዙ ያልተማሩ ዜጎች የሚገኙባት ሀገር ስትሆን፣ ዘመናዊ ጋዜጠኝነት ግን በአብዛኛው የተማሩት ላይ መሠረቶቹን የሚያደርግ ይሆናል። ዘመናዊ ጋዜጠኝነት ድንበር አልባና ተራማጅ የሆነ፣ ኢንዱስትሪያዊ ንድፍን የተከተለ፣ የቋንቋና ብሔር ተዋፅኦን በጥቂቱም ቢሆን የማያረጋግጥ ነው። ኢትዮጵያ ህብረ ብሔራዊ በሆኑ የጎሳና ቋንቋ ወሰኖች የተቀየጠች ምድር ናት። በተጨማሪም የመረጃው ተደራሽነትና የአጠቃቃም አግባብነት የብዙሀኑን የአገሪቱን ገጠራማ ክፍል ያገናዘበ ነው ብሎ መውሰድ ያዳግታል። በዚህም አግባብ የአገሪቱን የጋዜጠኝነት ነፃ ፍላጎት ማራመድ ስንመለከት 'የመታውን ይምታ፣ ያወደመውን ያውድም' ዓይነት አካሔድ እንዳለው መረዳት ይቻላል።

ይህም ማለት ኢትዮጵያ ከነአካቴው ዘመናዊ የጋዜጠኝነት ዘዬን





መተግበር አይኖርባትም! ማለት ሳይሆን ተጨባጭ ሁኔታዋን ያገናዘበና እርሷን የሚመስል የጋዜጠኝነትና ሚድያ ንድፍ ያስፈልጋታል ለማለት ነው። ኢትዮጵያ እራሷን የሚመስል ሶሺዮ ባህላዊ እና ዲሞግራፊያዊ ምሥልና ፍኖት የተላበሰ ሚድያና ጋዜጠኝነት ያስፈልጋታል።

ውስን ሀብታችን ውራጅ እና ራሳቸው ባለቤቶቹ ለጣሉት ዕሴት ሳይሆን ለላቀው ከፍታ መነሳሳት መዋል ይኖርበታል። በሙዚቃ ስም የቁሳቁስ ጩኸት፣ በስፖርት ስም እርግጫ፣ በማነቃቃት ሥም ድባቴ ውስጥ የሚያስገቡን፣ እራሳችንን እንድናውቅ ሳይሆን እንድንረሳ... የሚያደርጉን ከመሆን ይልቅ፣ የጋራ ዕሴቶቻችንን እንድናጎለብት የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል።

ዘርፉ በእድሜው ለጋነትና በትምህርትም ያልተደገፈ ከመሆኑ ባሻገር በአመዛኙ ከመሪዎች ጋር ተቀጥላ ሚና ሲጫወት በመኖሩ ዘለቄታ የሌለው፣ ነባሩን አዲስ ባለተራ የሚተካው እንጂ የሚማርበት ባለመሆኑ፣ በኅብረተሰቡ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በጋዜጠኞቹም ጭምር ሙያው በክብር የሚታይ ሳይሆን የቸገረው ጊዜ የሚገፋበት ተደርጎ ይቆጠራል። ይህ ብሩህ አዕምሮ ያላቸው ወጣቶች እንዳይቀላቀሉት ጋሬጣ ፈጥሮ የቆየ ሲሆን ተአማኒነት የሌለው፣ ህዝብን የማያንቀሳቅስ፣ ወደ ተሻለ ምዕራፍ መሻገር የማይችል ሽባ አድርጎት ቆይቷል። ይህን ገፅታ በመለወጥ አብረዎችን ለማሳየት ሙያው እንደ ሕዝባዊ አገልግሎት ተይዞ በአገራዊ ልማት ተጋድሎ ላይ ገድል መፈፀም የሚያስችል የተከበረ የሙያ ዘርፍ ተደርጎም ሊቆጠር ይችላል። በጋዜጠኝነት ሙያ ዘርፍ ተሰማርተው መልካም ስማቸውን በደማቅ የታሪክ ቀለም ጽፈው ያለፉ ተምሳሌቶቻችን ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ይሆናሉ።

ለአፍሪካ ሕብረትና እድገት ተጠቃሽ ሚና ከተጫወቱ አፍሪካውያን መካከል የቀድሞው የጋና ፕሬዝዳንት የነበሩት ኩዋሜ ንክሩማ ይጠቀሳሉ። ንክሩማ፣ የ'Accra Evening News' መስራችና አሳታሚ ነበሩ። ጋዜጣውንም የልማት ጋዜጠኝነት ተልዕኮን



t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲወጣ መሪ ሚና በመጫወት ቀዳሚ አድርገውታል። በተመሳሳይ ዶ/ር ናንዲ አዚኪዌ (1904-1996) የመጀመሪያው የናይጀሪያ አፍሪካዊ ፕሬዝዳንት ሲሆኑ 'African Morning Post' ጋዜጣ መስራችና አዘጋጅም በመሆን አገልግለዋል።

ጆሞ ኬንያታ (1894-1978) በመራር ትግል ኬንያን ከእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ ቀንበር ያላቀቁ ታላቅ አፍሪካዊ አርበኛ ናቸው። የመጀመሪያው የነፃይቱ ኬንያ ፕሬዝዳንት ከመሆናቸው በተጨማሪ የ'He Who Brings Together' ጋዜጣ መስራችና አሳታሚ ነበሩ። በእርግጥ የፖለቲካ አመራርና የጋዜጠኛነት ሙያ እንዳች ቁርኝት ያላቸው ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ የሚያደርገን ሌላም አውነታና ሕያው ተምሳሌት አለ።

ጁሊየስ ኔሬሬ (1922-1999) የአፍሪካ ሶሻሊዝም ፅንሰ-ሃሳብ አፍላቂና አቀንቃኝ የነበሩ ታላቅ መሪ ናቸው። እኚህ ስመጥር የአፍሪካ ሰው የታንዛኒያ ፕሬዝዳንት የነበሩ ሲሆን ለአፍሪካ ህብረት መቋቋም ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ከዚህ በተጨማሪም 'Uhuru' የተሰኘው የፓርቲያቸው ጋዜጣ መስራችና አሳታሚ ነበሩ።

አፍሪካን ተሻግረን ተመሳሳይ ተምሳሌት ማግኘትም ከባድ አይደለም። ቤንጃሚን ሃሪሰን (1833 –1901) 23ኛው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩ ሲሆን በስልጣን ዘመናቸው ለአፍሪካ አሜሪካዉያን ዜጎች የመምረጥ መብትን ከማጎናፀፋቸው በላይ በጋዜጠኝነት ሙያቸውም ስለነፃነት አቀንቅነዋል። ዱዋት አይዘንሀወር (1890–1969) በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ላይ የተሳተፉና የህብረቱ ጦር ጠቅላይ አዛዥ በመሆን ያገለገሉ ታላቅ የጦር ሰው የነበሩ ከመሆናቸው በተጨማሪ ከ1953-1961 በነበሩት ጊዜያት 34ኛው የአሜሪካን ፕሬዝዳንት በመሆን ያገለገሉና ጋዜጠኛም በመሆን የሰሩ ታላቅ መሪ ናቸው። ቤኒቶ ሞሶሎኒ (1883 –1945) ጋዜጠኛ እና የጣሊያን የብሄራዊ ፋሲስት ፓርቲ መሪ ነበሩ። ከ1922 እስከ 1943 ድረስም የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስቴር በመሆን





አገልግለዋል።

ኒኮሎ ማኪያቬሊ (1469-1527) ጣሊያናዊ ዜግነት ያለው የፖለቲካ ፈላስፋ፣ ገጣሚና ሙዚቀኛ ነው። 'The Prince' በተሰኘ መፅሃፉ ላይ ባሰፈራቸው የፖለቲካ ንድፈ ሀሳቦች በዓለማችን ከፍተኛ ተፅእኖ ካሳረፉ ሥራዎች መካከል አንዱ ነው።

ካርል ማርክስ (1818-1883) The Communist Manifesto and Das Kapital፡ በተሰኙ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ንድፈ ሀሳብን የያዙ ሥራዎቹ ዓለምን ከአዲስ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቅኝት ጋር ያስተዋወቀ ፈላስፋ፣ የኢኮኖሚ ሊቅ፣ የታሪክ ምሁርና ሶስዮሎጂስት ሲሆን የጉልምስና እድሜውን በአመዛኙ በጋዜጠኝነት ያሳለፈ፤ 'New York Tribune'ን ጨምሮ በአውሮፓና አሜሪካ ተነባቢ ለነበሩ ክስድስት ላላነሱ ታዋቂ ጋዜጦችም ቋሚ አምደኛ ነበር።

ወደ ብርሃን ለመሸጋገር የምናደርገው ጉዞ የሌሎችን ዱካና ፈለግ በመከተል የሚገኝ አይደለም። ራሳችን ጨለማ ውስጥ የጣልነውን መጣቢያ ቁልፍ እዚያው ጨለማ ውስጥ በመሆን ለመፈመድ የሚያግዙንንና ቅሬጥሮ ያደለችንን ብርቅ የሆኑ ፀጋዎች ፈልገን በማግኘት ወደ ሁለንተናዊ እድገትና ልማት በሚያሸጋግር ሂደት እንዲታጀቡ ማድረግ ይኖርብናል።

ምስጋናው ግሸን ጎኛ ቫማዎች ነን በሚል ወደ አማርኛ የመለሰውን ስውፍ በማጠናከሪያነት ለመጥቀስ እንሞክራለን። ባንድ ምሽት ሰውየው በባሕር ዳርቻ ባለው የወደብ ከፍታ ቦታ ትንሽ ሻማ ይዞ መሀኑነት ይጀምራል። በዚህ ጊዜ 'ወዴት ነው እየሄድን ያለነው?' ሲል ሻማው ጥያቄ አቀረበለት።

"እየሄድን ያለነው ከቤቱ ባሻገር ከፍ ብሎ ወደሚታየው ቦታ ነው። በዚህም ለመርከቡ የወደቡን አቅጣጫ ማሳየት እንችላለን" አለው።

"እንደምታየው የእኔ ብርሃን በጣም ውስን ናት። እንዴትስ ከርቀት


t.me/OLDBOOKSPDF

ያለ መርከብ በእኔ ብርሃን ተመርቶ ወደቡ ጋር መድረስ ይችላል?" አለ ሻማው።

"ምንም እንኳ ያንተ ብርሃን ትንሽ ብትሆንም የምትችለውን ያህል ማብራትን አታቋርጥም። የቀረውን ነገር ለእኔ ተወው" አለው ሰውየው። በዚህ ንግግራቸው መሀል እያሉ ከከፍታ ቦታው ደረሱና ሰውየው ትልቁን የፋኖስ ብርጭቆ እያሳየው ሻማውን በማስጠጋት ፋኖሱን ለኮሰው። ወዲያውኑም የተለኮሰው ፋኖስ የባሕሩን አካባቢ በብርሃን ጸዳል ሞላው።

እኛ ሻማዎች ነን። ከእኛ የሚጠበቀውም የሻማነታችንን ያክል ማብራት ነው። ቀሪው የሥራችን ስኬት ላይ ፈጣሪ ይታከልበታል። የአንዲት ትንሽ ሻማ መብራት ወይም የክብሪት እሳት ጫካ ሙሉ እሳት እንደምትፈጥር ሁሉ በእያንዳንዳችን ያለች የብርሃን ምሳሌ ስናውቅም ሳናውቅም ለሌሎች ሕይወት መለወጥ ምክንያት ትሆናለችና ብርሃናችንን ሳናሳንሳት እንድትበራ እድል እንስጣት።

ዕድገትም ቅብብሎሽ ነው። እኛ ማድረግ የምንችለውን ሰርተን ለተገቢውና ለሚጠበቅብን ስናስረክበው እሱም በፈንታው ዳር ያደርሰዋል። ሻማዋ ለፋኖሱ እንዳቀበለችው ማለት ነው። ይህ ነው፣ ለዕድገት የድርሻን መወጣት ማለት፤ ሻማነታችንን ማበርከት፤ የሚጠበቅብንን መወጣት።

ሌላ ማሳያ ታሪክ ላክል፤... አንድ አዳኝ ገበሬ ስለ ውሻው ጉብዝና እንዲያደንቅለት የቅርብ ጓደኛውን ይዞት አካባቢያቸው ወደሚገኝ አንድ ባህር ይዞት ሄዶ ነበር፣ አሉ። ገበሬውም ውሻውን ባሰለጠነው መሰረት ዳክዬዎችን እንዲይዝ ያደርገውና ከጓደኛው ጋር ይመለከታሉ። በመጨረሻም ገበሬው ውሻው ያደናቸውን ዳክዬዎች ከውሃው ውስጥ ወደ ዳር ሲያወጣ፣ "አየህ!... የኔ ውሻ ምን ያህል ጎበዝ እንደሆነ?" በማለት እየተኩራራ መናገር ይጀምራል፡፡ ጓደኛው ግን ሲመለከት የነበረው ውሻው እንዴት ያለ ጥበብ ይጠቀም እንደነበረ ሳይሆን እንዴት ይሳሳት እንደነበረ ስለሆነ 'እንደዚህ





አድርጎ መያዝ ሲችል አንድ ዳክዬ አምልጣዋለች፤ እንደዚህም ማድረግ አልነበረበትም...' እያለ የውሻውን ትንሽ ስህተት እጉልቶ ደግሞ ደጋግሞ በመናገር የውሻውን ጉብዝና ገደል ይከተዋል፡፡... ልክ ወገቡ ድረስ ውሃ እንደተሞላው ብርጭቆ... በውሃ ስለተሞላው የብርጭቆው ክፍል ሳይሆን ስለጎደለው የብርጭቆው ግማሽ አብዝቶ ይናገራል፡፡ የዘመናዊ ጋዜጠኝነትም ልክ እንደውሻው ጥቂት ስህተት አጉልቶ እንደሚያወራው ሰው ወይም የተሞላው የብርጭቆውን ክፍል ከመናገር ይልቅ ስለጎደለው አብዝቶ እንደሚያወራው ሰው ነው፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ምዕራፍ ስድስት

## ነብይ በሀገሩ አይከበርም፤ ታላቅ መሪም ሁልጊዜ በህዝቡ አይወደድም፣

*በትረ-ሙሴና ጄነራል ፓርክ፡*

መግቢያና መውጫው፣ መዋያና ማደሪያው የጨነቃት አንዲት ወፍ ከሰው እንደበት ተውሳ እንዲህ ተናገረች አሉ፤

**እትዬ የት ልደር፣**

**እካብ ላይ ብሰራ እባቡ መከራ፣**

**እዛፍ ላይ ብሰራ አሞራው መከራ፣**

**ምድር ላይ ብሰራ እረኛው መከራ፣**

በኃይማኖታዊም ሆነ በማህበራዊ ሣይንስ አስተምህሮት፣ የሰው ልጆች ሁሉ ቅዱስ ተፈጥሮና ነፍሳዊ ፍላጎት ነጻነት እንጂ ባርነት አለመሆኑ ተቀባይነት ያለው እሳቤ ነው። ይህም ፈጣሪ የሰው ልጆችን ከባዶነት ወደ ምሉዕነት፤ ከሟችነት ወደ ህያውነት ማራኪ ቅርፅን በማላበስ ከአካባቢው ጋር እንዲገናኙ የሚያደርጋቸውን የስሜት ህዋሳት እንዲሁም ይህን ግንኙነት በምክንያታዊነት ትርጉም መስጠት የሚያስችላቸው አዕምሮ ባለቤት አድርጎ ፈጥሯቸዋል። የፍጡሮች ሁሉ ባለቤት የሆነው ፈጣሪ የፈጠራቸውን ፍጥረታት ለፈጠራቸው ዓላማ የሚያድሩ እንዲሆኑ ለማድረግ እሳቤውንና



t.me/OLDBOOKSPDF

መሻቱን በውስጣቸው ከማኖር ይልቅ ጥሩውን ከመጥፎ፤ ጠቃሚውን ከጎጂ፤ እውነቱን ከሀሰት፤ ብርሃኑን ከጨለማ ይለዩበትና ይመርጡበት ዘንድ ነፃ የሆነ ፈቃድንና ምርጫን ማጎናፀፍ መርጧል።

ይህ የራስ ፍላጎትና ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነገሮችን የማግኘት ነፃነት የሰው ልጅ የህይወቱ እስኳል፣ የመኖሩ ምስጢር እንዲሁም መሠረታዊ የፍጥረቱ ክፍል ነውና የሚፈለገውን ነገር ለማግኘት የሌሎችን ይሁንታ የሚናፍቅ ጠባቂ ሳይሆን ተፈጥሮ ያበረከተችለትን የነፃነት እክሊል በራሱ እንዲሁም በጭቁኖች ላይ ለመድፋት ክቡር የሆነውን ህይወቱን ለመሰዋዕትነት እስከማቅረብ የደረሰና የሚደርስ ሆኖ እናገኘዋለን።

ከዚህ የእውነታ መሠረት በመነሳት ሰብዓዊነትን ወደ ትክክለኛ መሠረቱ ለመመለስ የምናደርገው ትግል በጭቆና ሥር ያሉ ሕዝቦች እስካሉ ድረስ ትክክለኛ ጊዜው ዛሬ ነገ ሲባል የማይችል፣ ተከታይና ዲጋፊ ደቀ-መዛሙርር የማያጣ መሆኑ ይታሰባል፡፡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ሕይወታችን ውስጥ የጋራ ተጠቃሚነታችንን የሚያረጋግጡ እርምጃዎቻችን ሰፊ ተቀባይነትን የሚያተርፉ ቅዱስ ተግባራት በመሆናቸው በዙሪያችን የሚኮለኮለው ጋሻ ጃግሬ እልፊ አእላፍ ሠራዊት እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

ብዙዎች በዚህ እምነት ተጉዘው ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በታላቅ ተስፋ መቁረጥ ቅስማቸው ተሰብሮ ፊታቸውን አዙረዋል፡፡ በርግጥም ነጻነትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ትግል በመንዳደር ደረጃ ፈተና ውስጥ የሚከቱት አካላት ኃይል አሳዳሪዎቹና ገዢዎቹ ብቻ ሳይሆኑ፣ የነፃነት አርበኛ የሆኑት ነፃ አውጪዎች እና ነፃ የሚወጡትም ብዙሀን ጭምር መሆናቸውን ታሪክ ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡ ጉዞውም ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነና ልክ እንደ ወፈቱ ዙሪያ ገባው በፈተናና አጣብቂኝ ስለመከበቡ በአንድ የሩቅ መለኮታዊ እና የቅርብ ጊዜ ተምሳሌቶች ማሳያ አድርገን





እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል።

በክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች ቅዱሳን መፅሃፍት ላይ ጥንቁቅና ተማሪ ለሚሆኑ ተፈላጊውን ትምህርት ለመስጠት ታስቦ የህይወት ታሪኩ የተወሳለትን፣ ፈጣሪ ልዩ መልእክተኛና ነብይ አድርጎ የያዕቁብ ልጆች ወደ ሆኑት ወደ እስራኤላውያን የላከውን፣ የሙሴን ታሪክ ለተነሳንለት ሀሳብ ተምሳሌት አድርገን መመልከት እንችላለን። የሙሴ የመሪነት ታሪክ ውስጥ ጥልቅና ሰፊ የእርነት ትግል፣ ጥበብ የተሞላበት ጉዞ፣ ያለ በቂ ዝግጅትና እሳቤ ለነፃ አውጪነት መሪ ሆኖ መመረጥ የሚፈጥረውን መደናበር… ወዘተ ተንፀባርቀውበት እናገኛለን፡፡ ነፃ ወጪው አካል ስለነፃነት ያለው እንጭጭ የሆነና ያልበሰለ ዕውቀት ትዕግስት ከማስጨረስ አልፎ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ፣ ከሥልጣን ተገዳዳሪዎቹ የሚሰነዘሩ ፈተናዎችና ነፃነትን ለመቀዳጀት በሚደረገው ትግል ላይ የሚፈጥረው ውክቢያና አከል፣ እንዲሁም ለተግዳሮቶቹ መፍትሄ ለመስጠት የትግል ስልቶችና አቅጣጫዎችን መቀያየር ከብዙ በጥቂቱ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በጊዜው እሥራኤላውያን በግብፅ ምድር ረዘም ላለ ጊዜ የአገሪቱ የስልጣን እንደራሴዎች በሆኑት ፈርኦኖች የግፍ አገዛዝ ሥር ነበሩ። እሥራኤላውያኑ በፈርኦኖቹ የሚደርስባቸው ገደብ አልባ የሆነውን ግፍ፣ መከራ እና እንግልት የህይወታቸው ክፋይ የሆነ ዕጣ ፋንታቸው እስኪመስል ድረስ በፀጋ ተቀብለውት ይኖሩ ነበር። ቅጥ ያጣ የባርነት ሥርዓት ውስጥ በመሆን ይደርስባቸው የነበረው መራር እንግልትና መገፋት፣ መዋረድና ዝቅ መደረግ፣ ስቃይና ሰቆቃ፣ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍጥረት ክፋይ የሆነውን በራስ ፈቃድና ነፃነት ያሻውን የማግኘትና የመሆን ፍላጎት እንዲዘነጉትና ራሳቸውን ለመበደልና ለሌሎች መገልገያ የተፈጠሩ እቃዎ ቢስ እንደሆኑ እንዲያስቡ ጫና ፈጥሮባቸዋል።

በአትሮኖሱ ላይ የተዘረጋው የህይወት መፅሀፍ እንደሚገልፀው ህይወት ምንጊዜም ተቃራኒ በሆኑ የስሜት ፅንፎች ምህዋር ላይ ሽክርክሪቷን የገነባች መሆኗን ነው። ደስታን ከሀዘን፣ ማግኘትን



t.me/OLDBOOKSPDF

ከማጣት፣ ሠላምን ከአመፅ፣ ብልህነትን ከሞኝነት፣ አማኝነትን ከተጠራጣሪነት፣ ወዳጅነትን ከጠላትነት፣ ነፃነትን ከባርነትና አላዋቂነትን ከአዋቂነት ጋር ጣምራ በማድረግ አንዱ ሌላውን... ሌላው ደግሞ ይኸኛውን በውድም ሆነ በግድ አንድም ወደ ላይ ወደ ምጥቀት ወይም ደግሞ ወደ ጥልቁ ውርደት ይዞት የሚነጉድና የሚጋልብ መሆኑ ነው። በመገፋት ጠፍር ተተብትበው፣ በባርነት ቀንበር ታስረው፣ ህይወት ማለት ማጣት እንጂ ማግኘት፣ ማጎብደድ እንጂ ቀና ማለት፣ ማገልገል እንጂ መገልገል፣ ማዳረስ እንጂ መድረስ መሆኑ ትርጉሙ ተዛብቶባቸው ሲኖሩ ህይወት አንዱን መልኳን ብቻ እያሳየች በአኩይ አለንጋዋ ስትገርፋቸው የምትኖር ይመስላል። ታዲያ ይህን ጊዜ በእንግልት ብዛት የደከሙ ገላዎች፣ በመዋረድና በመናቅ የተጎዱ ሥነ-ልቦናዎች፣ በጥላቻና በጭካኔ ግፍ የተፈፀመባቸው፣ ሰብዓዊነቶች ማረፊያ ይሆናቸው ምቹ ምኩራብ፣ ማገገሚያ ይሆናቸው ዘንድ እውን የሚሆን ተስፋ እንዲሁም መከሻ እንዲሆናቸው ዋጋው ከፍ ያለ ክብር ማግኘት የሚያስችል ነፃነትን ማለምና ተስፋ ማድረግ ይጀምራሉ።

እሥራኤላውያኑ ይኖሩበት ከነበረው የባርነት ቀጠና ፈጣሪ ወደ ነፃነት ግዛት እንዲያሻግራቸው ግፈኞች በሆኑት ፈርኦኖች እንክብካቤ ያደገውን ሙሴ ከመካከላቸው መርጦ ነፃ አውጪና መሪ አድርጎ አስነሳላቸው። ሙሴም ከፈጣሪው ዘንድ እሥራኤላውያኑ እየደረሰባቸው ካለው ግፍና ጭቆና ነፃ በማውጣት ሕዝቡንም ይዞ ወተትና ማር ወደ ሚፈልቅባት የራሳቸው ወደ ሆነችው የተስፋይቱ ምድር እንዲያመራ ትዕዛዝን ተቀበለ። ለዚህ ታላቅ ገድል እጩ የሆነው ሙሴ ተጨቋኝ ለሆኑት እስራኤላውያን ባዳ ያልሆን የአብራካቸው ክፋይ የሆነ መልዕክተኛ ነበር። በተመሳሳይ ግፈኞች ለነበሩት ፈርኦኖች ሙሴ ማለት የእነርሱ ካልሆነ ግዛት ወይም በጭቆናቸው ሥር ካሉት እሥራኤላውያን ያደገ ሳይሆን ከእንቀልባ ጀምሮ በእነርሱ እንክብካቤና ልዩ ፍቅር ያደገ፣ የአይናቸው ማረፊያ፣ የመኳንንታቸው ልዩ ብሥራት ተደርጎ የሚቆጠር ነበር።

ልክ የሌለው መገፋትና መበደል ተደጋጋሚ ዕጣችን ሆኖ ሳለ





በመገፋት ላይ እምቢ ባይ ዘማች አብዮተኛ ውጪ ካለ ባዕድ ሳይሆን ውስጣችን ከሆነ እርበኛ ማግኘት እንዳንዴ በቅርብ የማናስተውለው ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ በግፍ የያዝናቸውና ጭቆናችንን በቃ ብለው የምንፈራውን የነፃነት ጥያቄ እንዲነሳና እድማሱን እንዲያሰፋ የሚያስችሉ የለውጥ አራማጆች እምብዛም ትኩረት ከነሳነው ጉያችን የሚወጡና ውስጠ ጓዳችንን በሠላሙ ጊዜ ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው።

ለዘመናት በባርነት ቀንበርና በሙብት እፊና ተረግጠው ለቆዩት እሥራኤላውያን መድህን ተደርጎ በፈጣሪ የተመረጠውና የተላከው ሙሴ ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት መታጨቱን በይሁንታ ለመቀበል በከፍተኛ የስሜት መናወጥ ውስጥ ማለፍ ግድ ሆኖበት ነበር። በሰዎች ስብሰብ ዙሪያ ሃሳቡን በሚገባ ለማስተላለፍ አይናፋርና ኮልታፋ የሆነን ግለሰብ ታላቅ ባለግርማና ተፈሪ ወደሆነ የብዙኃን ንጉሥ ማሸጋገር ከባድ ይመስላል፤ "ሕዝብን ከፍጡር ባርነት ወደ ፈጣሪ ባርነት እንዳሻግርና ወደ ተስፋይቱ ምድር እንድመራቸው ፈጣሪ ልኮኛልና ልቀቅ፤ ፈጣሪህ እኔንም አንተንም ያስገኘ ህያው የዓለማት ጌታ መሆኑን አበስርሀለሁ!" ብሎ የአምላኩን ጥሪ እንዲያስተጋባ ትዕዛዝ መቀበልም እጅግ ፈታኝ ነበር። ይህም ሊታሰብ የማይችል መደናገጥን፣ ፍርሃትን፣ በራስ ያለመተማመን ስሜትን በውስጡ የፈጠረ ሲሆን 'እኔ ማን ስለሆንኩ ነው ለዚህ ታላቅ ተልዕኮ ዕጩ የምሆነው' የሚል ጥያቄን እንዲያነሳ አድርጎታል።

ለዚህ ታላቅ ገድል መታጨቱን ከፈጣሪው በቀረቡ ልዩ ልዩ ተአምራት እንዲያረጋግጥ እና በውስጡም ምንም ዓይነት ፍርሃት ሊሰማው እንደማይገባ ከተደረገ በኋላ ግን ዕቅድና ትልሙን ያጋራውና ይቀበለው ዘንድ ወንድሙ አሮን አጋሩ እንዲሆን ተደረገለት። ይህም ከፊቱ ለሚጠብቀው ብርቱ ትግል ከፍተኛ ብርታትና የራስ መተማመን አስገኝቶለታል።

እፊናና ግፍን ከነአካቴው ድባቅ በመምታት የሚፈለግ ድልና ነፃነትን



t.me/OLDBOOKSPDF

ለመቀዳጀት ወደሚያነሳሳ ትግል ለመግባት ጊዜው በውል የሚታወቅ አለመሆኑን ልብ ይሏል። ብሶትና ምሬት እርግዝናቸውን ጨርሰው ነፃነትን ለመውለድ የተወሰነ የጊዜ ገደብ፣ የተመረጠና ብቁ ሆኖ የሚጠባበቅ አዋላጅን አናገኝም። ማን የገፈት ቀማሽ፣ ማን ደግሞ ነፃ አውጪ እንደሆነ የሚያሳየን ክፍፍል የለም። በባርነት ሥር ካሉት መካከል ዘመኑን በሙሉ ለነፃ አውጪነት ዝግጁ መሆኑን ያልተረዳ፣ ትግሉን ወደ ስኬት ለማድረስ በቂ ችሎታና ክህሎት እንዳለው የማይታሰብ ምስኪን የኋላ ኋላ የነፃነትን ችቦ ለኳሽ፣ የድሉን ጮራ ፈንጣቂ፣ የተድላና ምቾት አብሳሪ ሆኖ እናገኘዋለን። ባለፉት የአገራችን ታሪኮች ብሶት የወለደውን ነፃነት ፊታውራሪ በመሆን ያስገኙትን በምን አይነት የህይወት እርከን እንዳለፉ ማስታወስ ብቻ በቂ ነው። በዚህ ጊዜም ብቁ አለመሆንን በመረዳት የሚፈጠር ውስጣዊ የስሜት መረበሽ ተፈጥሯዊ መሆኑንና ነገር ግን ይህን ስሜት በመቆጣጠር የተሰጠ ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ራሥን ማብቃት እንዲሁም በትግል ጉዞ ምርኩዝ የሚሆን አጋርን ከጎን ማሰለፍ አዋጭ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል።

ሙሴና አጋር ተደርጎ የተላከለት ወንድሙ አሮን ያነገቡትን ታላቅ የትግል ጥያቄ ወደ ፈርኦኑ ይዘው ሲቀርቡ ለጥያቄያቸው የተሰጣቸው ምላሽ አዎንታዊ አልነበረም። ፈርኦኑም ሙሴን በእንክብካቤውና በጥበቃው ስር ሆኖ በምቾት እንዲያድግ እንዳደረገው፣ ይቅር የማይባሉና የማይታለፉ ግድፈቶቹን በይቅርታ እንዲታለፍ ማድረጉን ለእነዚህና መሰል ውለታዎች አመስጋኝና ተገዢ እንጂ ተገዳዳሪ መሆን እንደማይገባው ከንቱ ውትወታና ስላቅ ያቀርብ ጀመር። በተቃራኒው በሙሴ በኩል ያለውን የማይዛነፍ የነፃነት ጥያቄ አቋምንና ይህን ጥያቄውን ዳር ለማድረስ ያለውን ቁራጥነት ፈርኦን በተመለከተ ጊዜ ቀጣይ እርምጃው ምን ሊሆን እንደሚችል ማስጠንቀቅ ጀመረ። ይህም የለውጥን ሀሳብ ይዘው በተነሱት ላይ ብርቱ የሆነ የቅጣት በትሩን ሊያሳርፍ እንደሚችል ዛቻና ማስፈራሪያ በመስጠት እንዲሁም ማዋከብን በመምረጥ ለበደት እስኪዳረጉ ድረስ የተለያዩ ስልቶችን ይተገብር ጀመር።





ግፈኞችና ጨቋኞች ከእኩይ እሳቢዎቻቸውና ድርጊቶቻቸው ይቆጠቡና በተቃራኒው የሚፈለግን ለውጥ ያስገኙ ዘንድ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ተቀዳሚ ምላሻቸው ከይሁንታ ይልቅ እምቢታ፣ ከመረዳት ይልቅ ድንፋታ መሆኑ እርግጥ ነው። ለእምቢታቸውም ማጠናከሪያ የለውጥ አቀንቃኞቹን በስላቅ፣ በፌዝ እና በተለያዩ ውለታዎች በመሸበብ እድር ባይ እንዲሆኑ ከማድረግ ጀምሮ በዚህ የማይመለሱ ከሆነ ግን ወዳልተፈለገ እርምጃና ቅጣት እንዲያመሩ እንደሚገፋፏቸው ማስፈራራትን ምርጫቸው ያደርጋሉ። ነገር ግን ለዚህ ሁሉ ማዋከብና ከያዙት የትግል ዓላማ እንዲሸሹ ለሚያደርሱት ውርጅብኞች የአላማ ፅናትን፣ የጠነከረ የእምነት ቋጠሮን በልቡና ማሳደር ይገባል።

ሙሴ በፈርኦን ላይ ይዞት ለተነሳውን የነፃነት ጥያቄና የትግል አቅጣጫ አሉታዊ ምላሽ የሰጠው ፈርኦን ብቻ አልነበረም። ከባርነት ቀንበር የማላቀቅ አጀንዳ ያነሳላቸው ሕዝቦች ቁጥምር ተስፋ አስቆራጭ የሆነ ፊት አሳይተውታል፤ ጥርጣሬና እድር ባይነት ከገዛ ወገኑ ተቀብሏል፤ የኔ የሚላቸው እሥራኤላውያን በፍራቻ የተሸበቡ ሆነው ለትግሉ ሙሉ ይሁንታቸውን ነፍገውታል። እስራኤላውያኑ ሙሴ ለቆመለት ዓላማ ጀርባቸውን እንዲሰጡ፣ ፈርኦን ጌታቸው እንደሆነና ማንኛውንም ዓይነት ፍላጎታቸውን ሊያሟላ የሚችል መሆኑን፣ በተቃራኒው ሙሴ አጃቢ ደንገጡሮችም ሆኑ የወርቅ ክታብ የሌለው ተራ ደሀ እንደሆነ በአሳሳች ፕሮፓጋንዳ ያጠምቃቸው ነበር። እሥራኤላውያኑም ለረዥም ዘመናት የተጨቆኑ ሕዝቦች መሆናቸው፣ ራዕይና ተስፋ የሚሉት ቃሎች ከቃል የዘለለ ትርጉም ለነርሱ አለማያዛቸው፣ በገሀዱ ዓለም ብኽርታ ለመታወር ፍርዳቸው የላላ መሆኑ፣ ከብርና ዝና፣ ሀብትና ምቾት መገለጫው የሆነ እንዲገዛቸው በመሻት ለሙሴ ጥሪ ጆሮ ሳይሰጡ ለፈርኦን ያደሩ ሆኑ።

ተፈጥሯዊ ክፍል የሆነውን የሚፈለግን ነገር በራስ ፈቃድና ነፃነት የማግኘትና የመጠቀም ፍላጎትን ዕውን ለማድረግ በኩታቶችና ድሪቶዎች የተጀበነን ነፃነት ፈልቅቆ ለማውጣት የሚገጥሙ



t.me/OLDBOOKSPDF

መሰናከሎችን መረዳት ግድ ይላል። ይህ መሰናከል ደግሞ ድሪቶውና ኮተቱ አፍኖ በያዛቸው ሕዝቦች ዘንድ የሚፈጠር ሲሆን የያዙትን ጥያቄ እንዲመረምሩና 'ለማን ብዬ ነው?' በሚል ስሜት ወደ ኋላ እንዲያፈገፍጉ የሚያደርግ ነው። ንቃትም ብቃትም የሌለውን ሕዝብ ይዞ ወደ ተስፋ ማሻገር የሚፈልገውን ታላቅ የሥጉ-ልቡና ዝግጅት ቀድሞ በማጠናቀቅ ከጭቁኖች የሚገጥም ተቃርኖ ልብን ሰፋ አድርጎ መቀበል ያሻል።

ሙሴ ለፈርኦን ያቀረበውን የነፃነት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማሳመኛ የሚሆኑ የተለያዩ ተዓምራትን በጌታው ፈቃድ ለማቅረብ ተገዶ ነበር። ተዓምር መፍጠሪያ በትሩ በግብጽ ምድር እንቁ የተባሉ ደጋሚዎችን ድግምት መና ማድረጓ፣ ታላቅ ረሀብን ወደ ምድረ ግብፅ መጥራቷ፣ ምርትን የሚያወድም የአንበጣ መንጋ ማዝነብ መቻሏ፣ በሽታን በአገሬው ሰው ላይ አብዝታለች። መኖሪያ መንደራቸው በእንቁራሪቶች ተወርሯል፣ የናይል ወንዝም ሊጠጡት ሲቀርቡ ወደ ደምነት ተቀይሯል... በዚያው በሙሴ በትር አማካኝነት። ፈርኦኑና ጭፍሮቹም በእነዚህ ሁሉ ተዓምራት በመደናገጥና መፍትሄን ማስገኘት የማይችሉ አቅመ ቢስ መሆናቸውን በመረዳት በተደጋጋሚ ሙሴን ለፈጣሪው ምልጃ በመላክ ከደረሰባቸው መቅሰፍት ቢዛ እንዲሆናቸው ተማፅኖን ሲያቀርቡ ተስተውለዋል። ከመቅሰፍቶቹም በዳኑ ቅፅበት ዳግም ወደ ነበሩበት የትዕቢትና ኩራት ስሜት በመመለስ የሚሰሩትን ግፍና በደል እንዲገፉበት ሆኗል። በመጨረሻም ሙሴ ሕዝቦቹን በመያዝ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማሻገር ከፈጣሪው በተቀበለው ትዕዛዝ መሰረት ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ጀመረ። ይህን ያወቀው ፈርኦንም በከፍተኛ የእብሪትና ንዴት ስሜት ውስጥ በመሆን ጭፍሮቹን ይዞ ይከተላቸው ጀመር።

ከእሥራኤላውያኑ መካከል ከኋላቸው ፈርኦኑና ጭፍሮቹ ጥቃት ሊያደርሱባቸው እየተከተሏቸው መሆኑን፣ ከፊታቸው ደግሞ የሚያጋጥማቸውን ጋሬጣ (የቀይ ባህር) በተረዱ ጊዜ ሞት አይቀሬ ዕጣቸው እንደሆነ በመለፈፍ የሽብርና ሥጋት ዲስኩራቸውን





መንዛት ጀመሩ። ሙሴም የሕዝቦቹን ጭንቀትና ፍርሃት በመረዳት ፈጣሪያቸው መፍትሄ እንደሚያስገኝና ሽብርና ሥጋት ሊያድርባቸው እንደማይገባ ሊያፅናናቸው ቢሞክርም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ የገቡት ሕዝቦቹ ወደ ኋላ ወደ ግብፅ ምድር ተመልሰው ዳግም በባርነት መኖርን እንደሚመርጡ ይናገሩ ጀመር። በመጨረሻም ሙሴ ከፈጣሪው በተቀበለው ትዕዛዝ መሠረት ባህሩን በበትሩ ከፍሎ ሕዝቦቹን ሲያሻግር በተቃራኒው ሊያጠፋቸውና የቅጣት ኃይሉን ሊያሳርፍባቸው ከኋላ ይከተላቸው የነበረው ፈርኦን ከመላ ጭፍሮቹ ጋር በተከፈለው ባህር ውስጥ ሰጥሞ ቀርቷል፤ የእጉል ኩራትና ትዕቢት ውጤት ምን እንደሆነ ከፈርኦን መማር ይቻላል።

ወደ ድል በር ለመግባት በሚደረገው የዋዜማ ትግል በታጋዮች ላይ የሚስተዋል ራሥን መስዋዕት የማድረግ ፍርሀት፣ የማፈግፈግ ስሜት፣ የተቃራኒ ኃይል ግዝፈት የሚፈጥረው ሽብርና ድንጋጤ የማይታለፍ የቀን ጨለማ እንደሆነ መታሰብ አይኖርበትም። በእንፃሩ ባልጠበቅነው ጫፍ የድል ችቦ እንደሚለኮስና ከእነዚህ ጨለማ ከሚመስሉና በትግል ላይ ቀዝቃዛ ስሜት ከሚፈጥሩ አጋጣሚዎች ጀርባ ፍንጣቂ ብርሀንና እሸናፊ ወደ መሆን እልፍኝ የሚወስዱ የድል ፋናዎች መኖራቸውን መረዳት ያሻል። የትግሉ መሪና አቀጣጣይ በመሆንም ጊዜ በተከታዮች ላይ የሚስተዋሉ መሰል ስሜቶችን ጠንቅቀው የሚረዱና የተፈጠረባቸውን የስሜት መበረዝ በማረጋጋትና በማቀዝቀዝ ዳግም ወደ ትግሉ እንቅስቃሴ ትኩረት እንዲያደርጉ ማድረግ ያሻል።

ሙሴ እሥራኤላውያንን በፈጣሪው እርዳታ የቀይ ባህርን በሠላም ማሻገር ከቻለ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚያደርገው ጉዞ በከባድ ፈተና የታጀበ ነበር። ከእሥራኤላውያኑ የሚሰነዘሩ ጥያቄዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዙ እንጂ እየቀነሱለት አልመጡም። ከምግብና መጠለያ ጥያቄ ባሻገር፣ ሙሴ እሱን መርጦ ከሾመው አምላክ በሚያደርር እኳኋን እሥራኤላውያኑ ጣዖታትን የማምለክ ፍላጎታቸውን እንዲያሟላላቸው መጠየቅ ጀመሩ። ሙሴም



t.me/OLDBOOKSPDF

የሕዝቦቹን ገራገርና ቀኘኝነት በመረዳት በጉዞ ወቅት የትግል መሪ መሆኑን የሚያስመሰክሩ ታላላቅ ተዓምራትን በፈጣሪው እርዳታ ማድረግ ችሏል። አዳዲስ አደረጃጀትና ሥርዓት አስተዋውቋል፤ ተዓምራትን ማድረጉም ቀጥሏል።

"ልጆቻችንንም ሆነ ከብቶቻችንን ስለምን በምድረ በዳ ላይ እንዲያልቁ ታደርጋለህ?" በማለት ዳግም ትተውት የመጡት ሽንኩርት፣ ባቄላ እና ምስር ለምግብነት ይቀርብላቸው ዘንድ ከመጠየቅ አልተመለሱም። ታዲያ የሙሴ ጥንካሬ የተረጋገጠው በእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎችና ውትወታዎች ሳይሸበር የተሰጠውን ተልዕኮ ከዳር አድርሷል። ምንም እንኳን እሱ የተስፋይቱን ምድር በእግሩ መርገጥ ባይችልም ከፍተኛ ትግል በማካሄድ ሕዝቡን ከባርነት ወደ ነፃነት ለማሸጋገር ችሏል።

ጭቁናች በጨቋኞቻቸው ነፃነትን በተመለከተ የሚሰጣቸውና እንዲያውቁት የሚደረገው የተዛባ እሳቤ በቀላሉ ከውስጥ ተፍቆ የሚወጣ አይደለም። ይህም በፍርሃት የተከበቡ እንዲሆኑ በማድረግ ተስፋንና ነፃነትን ያለምንም ክፍያ ለማግኘት የሚራወጡ እንዲሆኑ ያደርጋል። ድልን የሚናፍቅና ስለ ስኬት የሚከፈለውን መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ የሚሆነው ትውልድ በውስጡ ሽንፈት የሚቆጨው፣ መታገልና ማሸነፍ ምኞቱ የሚሆን ነው። የትግል መሪ መሆንም ይህን መረዳትና ተከታዮችን አስተባብሮ የሚናፈቅ ድልን ለማስገኘት የአመራር ስልቶችን መጠቀም የሚፈልግ ይሆናል።

ወደ ነፃነት፣ ወደ ልማት የሚደረግ ጉዞና መድረኩ ሁሌም በእነዚህ የሁለት ፅንፍ ፈተናዎች የታጀበ ነው። ይህም ሆኖ ግን መሪነት ትልቅ ኃላፊነት ነውና እንቅፋቱን በፅናት መሻገር ያስፈልጋል። መርቶ የማያውቅ መምራትን የሚቀበልበት፣ ንግግር አለማወቅና መከላከፍ ሠበብ የማይሆንበት ይልቁንም አማራጮችን ሁሉ ተጠቅሞ የተሻለውን ነገ የማረጋገጥ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያሻል።





ደቡብ ኮርያ ከ1960 ዎቹ በፊት እረፍት በሌለው የጦርነት ቀጠና ስትታመስ እንደነበረ የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ነገር ግን ኮሪያ በአሁኑ ጊዜ ፈጣን የሆነ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ከጃፓን፣ ቻይና፣ አሜሪካ እና ከመሳሰሉት የዓለም ምርጥ አስር አገራት ጋር የምትሰለፍ እንደሆነች ይነገርላታል። የዛሬይቱ ኮርያ ለመላው ታዳጊ ሀገራት በተለይም ደግሞ በዕድገት ጎዳና ወጣ - ገባ ለሚሉ ሀገራት ሞዴል ልትሆን እንደምትችልና ታዳጊ ሀገራትም ኮርያ የረገጠችውን ድንጋይ ረግጠው ማለፍ እንዳለባቸው የአሜሪካው ፕሬዘዳንት የሆኑት ባራክ ሁሴን ኦባማ በኬንያ በ2009 በነበራቸው ድህነትን የማስቆም ስትራቴጂ መድረክ ላይ ሲናገሩ ተደምጠዋል።

የኮርያ ሕዝብ ከሳር የተሰራ ጫማ ከመጫማት እስከ የዕለት ጉርሱን እስከ ማጣት ድረስ ለበርካታ ዓመታት ሲሰቃይ የኖረ ሕዝብ ነበር። ያ ሕዝብ ከተጫነው ድህነት የተነሳ የራስ ፀጉሩን እስከ መሸጥ ደርሶ እንደነበርም ታሪክ ያስረዳል። በመላው እስያ መሠረታዊ የሆነውን ሩዝ ለዜጎቿ በበቂ ሁኔታ መመገብ የተሳናትም ሀገር ነበረች። … በግማሽ ምዕተ-ዓመት ዕድሜ ውስጥ ግን ያን የድህነት ነቀርሳ ከኮሪያ ከስሩ ነቅሎ በመጣል ለኮሪያ ስኬት መሠረቱን የጣሉት፣ ከስኬቱ ጀርባ የነበሩት ቁልፍ ሰው ማን ነበሩ? ብለን የጠየቅን እንደሆን በዴሞክራሲያዊ መሪነታቸው ብዙም የማይወደሱት ፕሬዘዳንት ፓርክ ቹንግ ሂ ጎልተው ብቅ ይላሉ።

ሜጀር ጄነራል ፓርክ ከውትድርና ወደ ፕሬዝዳንትነት የመጡት በከፋ ጭቆናውና በሙስና የተዘፈቀውን የራሂ መንግሥት በመፈንቅለ መንግሥት በማስወገድ ነበር። ጄነራሉ በአገራቸው መረጋጋትን ለማስፈን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ኃይላትን ጠቅልለው በሥራቸው ከማድረጋቸውም በላይ፣ እንደአርሳቸው መረዳት ከሆነ፣ 'ስኬታማ የሚባለው የዲሞክራሲ ፍኖት የነፃነት ትግሎችን፣ የመናገርና የፕሬስ ነፃነትን የሚገድብ፣ የራሱ ወሰን ያለው ዲሞክራሲ ነው፣ ብለው የሚያምኑ የጦር ሰውም ነበሩ። እናም ከእርሳቸው በፊት በሩቅ ምስራቅ ታሪክ በጃፓን ከተደረገው የዕድገት አማራጭ ውጭ ተሞክሮ የሌለውን የኢኮኖሚ



t.me/OLDBOOKSPDF

ሥርዓትና የዕድገት መንገድ በመቀየስ የኮሪያን ህዳሴ ማብሰር ችለዋል።

ፕሬዝዳንቱ የኮንፊሺየስ እምነት ተከታይ የሆነው ሕዝባቸው የዕድገት ዕሳቤ ላይ ተፅእኖ ማሳደሩን ሲረዱ ወደ አዲስ አቅጣጫ የሚያስኬድ የሥልጣኔ አቅጣጫ በመከተል እንቀሳቅሰዋል። ጀነራሉ በህይወት ዘመናቸው ከ30 በላይ በሆኑ መስኮች ላይ ማለትም በግብርናና ደን ልማት፣ በኢኮኖሚና እንዱስትሪ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በትምህርትና ጤና፣ በህብረት ሥራ ዘመቻ እና በሌሎችም ላይ በርካታ ስኬቶችን አስመዝግበዋል። ከእነዚህ ስኬቶች መካከል የፕሬዘዳንቱን ትኩረት በይበልጥ ገዝቶ የነበረው የሕብረት ሥራ ዘመቻ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ።

በ1970 በፕሬዝዳንት ፓርክ የተጀመረው የሕብረት ሥራ ዘመቻ ወይም የቀጠና እንቅስቃሴ ለዓመታት ዘልቆ በገጠርና በከተማ ሲደረግ ኖሯል። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የአገር ፍቅር፣ የህብረት ወይም አብሮነት ወኔ፣ ጠንካራ የሆነ የሥራ ሥነ ምግባር፣ እችላለሁ! የሚል መንፈስ ብቻ ሲሆን፣ ማንኛውም ግለሰብ ዘር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋና ብሔር ሳይለይ ለአንድ ዓላማ፣ ለአንድ አገር በመስራት አገራዊ ፍቅሩን መግለፅ የሚችልበት መንገድ ነው። በሣይንስና ቴክኖሎጂ መስከ እንዲሁም በትምህርት ፖሊሲ ረገድ ከዚያ በፊት የነበረውን ዕሳቤና የምዕራባውያን ፖሊሲን ወደ ጎን በመተው ጀነራሉ ምንም እንኳን እንደ ሙሴ ሁሉ የዛሬዋን ኮሪያ ለማየት ባይታደሉም፣ ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ድህነትና ኋላ ቀርነት ከፈጠሩት ባርነት እንደ ገና ዳቦ ከላይም ከታችም እሳት እየነደደባቸው ታግለው ለልማትና ነፃነት አብቅተውታል።

በጀኔራል ፓርክ መሪነት የኮሪያ የትናንት ታሪክ በዛሬ ተለውጦ በአሁኑ ጊዜ የአንድ ኮርያዊ ግለሰብ ዓመታዊ ገቢ ከ25,000 የአሜሪካን ዶላር በላይ ሲሆን፣ የአገሪቱ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ወደ 1.151 ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንደሚገመት መረጃዎች ያመለክታሉ። ከሁሉ በፊት ፓርክ ከሌሎች አገራት





መንግስታት ለየት የሚያደርጋቸው በሣይንስና ቴክኖሎጂ ላይ ያላቸውን ከፍተኛ የሆነ ፍቅር ከዳር ለማድረስ የተጠቀሙት ጥበባዊ አካሄድ ነበር። ይኸውም ጀነራል ፓርክ ፖለቲካ እንደ ማንኛውም አገር ለኮሪያም ኢኮኖሚያዊ ግንባታ እንደሚያስፈልጋቸው በሚገባ የሚያቁ ናቸው። ነገር ግን ምን ዓይነት ፖለቲካ መከተል እንዳለባቸው የወሰኑት ፍፁም ቅንነት በተሞላበት መንገድ ነበር።

ፓርክ ይከተሉት የነበረው ፖለቲካዊ ሥርዓት ምሁራዊ ቢሮክራሲ ሲሆን አመራርነትን ከብቃት ጋር በማስተሳሰር፣ ከሙተዛዘልና የመሃይም ሹመት ርዕዮተ ዓለም የወጡ ምሁራዊ መንግሥት ማስፈን የሚፈልጉ መሪ ነበሩ።

ይህን መሰሉን ምሁራዊ መንግሥትና ሹመት በአብዛኞዎቹ የአፍሪካ መንግሥታት ዘንድ ለማስፈን ማሰቡ ብዙም የማይዋጥ ሀቅ ነው፡፡ የአፍሪካ አገራት መሪዎች፣ ያልተማረ ማህበረሰብ ገዥና አስተዳዳሪ እንዲሆን የመፈለጋቸው እውነት ጥያቄ የማያስነሳ ሀቅ ነው፡፡ የዚህ ምክንያቱ እንደየሰው አመለካከት ልዩነት ያለው ቢሆንም፣ እንደ ብዙሃኑ ዕሳቤ፣ መሪዎቹ ያልተማረው ሁሉን አሜን ብሎ ይቀበላል ብለው ከማሰባቸው የመነጨ ነው፡፡ በአፍሪካ፣ በመሪነት ቦታ ላይ የሚገኙት ሰዎች የትምህርት ደረጃቸው እጅግ ዝቅ ያለ መሆኑና በተቃራኒው ሥርዓቱ ገፍቷቸው ከአገር ውጭ የሚኖሩ ዜጎችና በየማረሚያ ቤቱ ዘብጥያ ወርደው የሚገኙ ምሁራን ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ ማሳያ መሆን ይችላሉ። በዚሁ መነፅር የያኔዋን ደቡብ ኮሪያ ስንመለከት በወቅቱ አገሪቱን ሲመራ የነበረው ጀነራል ፓርክ ያደረገው ጥረት ቢኖር፣ ትውልደ ኮሪያዊ ምሁራንን ከያሉበት በመሰብሰብ ለፖለቲካው ታማኝ የሆኑ ሹመኞች ማድረግ ነበር።

እዚህ ጋር ቆም ብለን ማሰብ ያለብን ጉዳይ ሁሉም ህዝብ ለአገሩ በቅንነት የመስራት ፍላጎት እንዳለው ነው። መንግሥትና ህዝብ ደግሞ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖር ቤተሰብ ነው። ነገር ግን፣ የሚረዳውን በማይረዳው አመለካከት ሥር ለመጣል የሚደረገው እንቅስቃሴ ምሁራንን የሚያስከፋና የሚያስኮርፍ ከመሆኑ ባሻገር



t.me/OLDBOOKSPDF

የማያስብ አገር እንዲፈጠር፣ ድህነትና ብጥብጥ ነግሶ እንዲወጣ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ነው።

ፓርክ ተሳክቶላቸው ብዙ ታላላቅ ነገሮቻቸው ኀልተው የሚታዩላቸው መሪ ሆኑ እንጂ፣ ከፍተኛ እንግልት ደርሶባቸዋል። ጄኔራሉ 7 የግድያ ሙከራ ተካሂዶባቸው ከሞት ተርፈዋል። በጠላት ጥቃት ሚስታቸውን አጥተዋል። በኋላም በቅርብ ሰዎቻቸው፣ ማለትም በደህንነት ሚኒስትሩ ለስብሰባ ተጠርተው ነው በዚያው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ውስጥ በጥይት ተደብድበው የተገደሉት።

አብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ ድህነት፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ የዕውቀት ችግር፣ ኋላቀር ባህላዊ ተፅዕኖና የሠላም ማጣት ተደማምረው የሕዝቦች ሁለንተናዊ ዕድገትን ፈተና ውስጥ ጥለውታል። ከዚህ ፈተና ለመውጣት የሚያስችል መሠረት የሌላቸው መሆኑ ደግሞ ችግሮቻቸውን ከባድና ውስብስብ፣ ተስፋቸውንም የጨለመ አድርጎባቸዋል። አዳጊ አገሮች በብዙ ነገሮች የሚመሳሰሉ ሲሆን በድህነት ውስጥ መገኘታቸው፣ ህዝቦቻቸውም የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች በተሟላ መልኩ ተጠቃሚ መሆን አለመቻላቸው በዋናነት ይጠቀሳሉ። ኢኮኖሚያቸውን የመሰረቱት በግብርና ላይ መሆኑና ዕድገቱም ኋላቀር በመሆኑ ራሳቸውን እንኳን ለመመገብ አልበቃቸውም፤ በርካታ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራቸውም አልምተው ለመጠቀም የኢኮኖሚና የዕውቀት አቅማቸው ውስንነት አልፈቀደላቸውም። በዚህ የዕልመት ጥላ ውስጥም ለዘመናት ኖረዋል።

በመሆኑም ከዚህ አዙሪት ፈጥነውና ጠንክረው መውጣት ካልቻሉ የነገው ዕጣ ፈንታቸው የባሰ ድህነት ብቻ ሳይሆን እንደ ማህበረሰብ መጥፋትም ሊሆን እንደሚችል መረዳት ግድ ነው። በተለመደው 'ከሆነ ይሆናል፣ ካልሆነም ይቀራል' ከሚል የዕድገት እርምጃና አማራጭ በተቃራኒ ልማትን ማረጋገጥ የህልውና ጉዳይ መሆኑን በቃልም በተግባርም የሚታይበት አዲስ ሥር ነቀል የለውጥ





አስተሳሰብ በመፍጠር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህም ደግሞ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ተግባራዊነትን ጨምሮ ሁሉንም አቅም መጠቀም ፍልሚያው በሚካሄድበት ዓውደ ውጊያ ማስማራት ይጠይቃል። ለራሥና ቤተሰብ ብቻ እያሰቡ፣ አገርና ህዝብን ለተደላደለ ኢኮኖሚ ማብቃት አይቻልም።

በግራና በቀኝ፣ በታችና በላይ ጉዟችንን የሚፈትን እውነታ መኖሩ በተረጋገጠበት ሂደት ውስጥ ከተጫነን የሥጋና መንፈስ ባርነት ተላቀን ድህነትን ታሪክ የማድረግ ጉዟችንን ለማሳካት በስሜትና በደመነፍስ ሳይሆን በርጋታ፣ ስረ ነገርና ስረ መሰረትን ጨብጠን ህግን ለዓላማ ሰብሮ፣ሃሜትን በሚያስቀር ግልፅነት ተግባብቶ እንደሎጥ ሚስት በእንቅልፍ ልቦና ወደዚያ ተመልከተን ወደኋላ መመለስ ዕጣ ፈንታ፣ ዕድል ተርታ እንዳይነጥቀን እንደታማኙ እንስሳ ወደትፋታችን ላለመመለስ በመልካም አራሚ መሪዎች ሰብሰብ ይህቺን ጥቁር ባሕር አቋርጠን የምታጓጓ ጥቁር ምድር ለመፍጠር ከላይ እስከታች እጅ ለእጅ ተያይዘን ዕድገታችን ሰውነታችንን መሠረት አድርጎ እንዲመጣ፣ የብዙዎችንን ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጥ ሆኖ መቃኘት ያለበት ብቻ ሳይሆን እንደመንግሥት ሁሉ ምሁራንም በታላቅ ሆደ ሠፊነት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል አራት

*‹‹ወዴት እንደምትጓዝ የማታውቅ ከሆነ ማንኛውም መንገድ ወደ ግብህ ይመራሃል፡፡››*

ጆርጅ ሃሪሰ

ልጓዝ ስትል እኮ......

መድረሻውን መትለም

ያ’ሳቢ ጸጋ ነው፣

ከደመ ነፍሳውያን እንለይበት ዘንድ

ተፈጥሮ ያለበሰን

ከላይ የተቸርነው፡፡

ከመጓዝህ በፊት

ግብህን ማስመርያ

ነፍስ ተሰ’ቶሀል፣

ምክንያቱም...............



t.me/OLDBOOKSPDF

ውዴ አንተን ጎርፍ ያይደል

ሰው አ'ርጎ ፈጥሮሃል፡፡

ይሄ ካልሆነ ግን......

መድረሻውን ማያውቅ

ህልሙን ያልማተረ ተጓዥ እንደ ልቡ

የደረሰበት ነው የመድረሻ ግቡ፡፡





# ምዕራፍ ሰባት

## የኑሯችን ጀልባ የሚገፋበት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ርዕዮትና አጠራጣሪው መዳረሻ

በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ እንደ ሀገርና ህዝብ የተሳፈርንበትን ጀልባ መዳረሻ በመወሰን ረገድ ጀልባውን የሚገፋው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ርዕዮተ-ዓለማዊ ንፋስ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በጉዟችን መጨረሻ የትኛው ወደብ እንደምንደርስ በእርግጠኝነት ማወቅ ባንችልም እንኳ እርሱን መሠረትና መነሻ አድርገን መገመት ብልህነት የተሞላው አካሄድ ነው፡፡ ከአመራር ጥበብና ስብዕና ባሻገር፣ የእርካብና መንበርም ዕጣ ፈንታ የሚወሰንበት ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ፣ የትኛው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ርዕዮት ከምን ነባራዊ ሁኔታ ምን ውጤትን ለማስገኘት ተፈጠረ? በተግባር ጉዞው ምን መልካምና አስከፊ ፈተና ገጠመው? በተጨባጭ ምን ውጤት አስመዘገበ? ብሎ መጠየቅና መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

የፖለቲካ ርእዮተ ዓለም፣ አገር ለመምራትና ለሀገሪቷ ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት የምንከተለው ሣይንሳዊ የፖለቲካ አመራር ንድፈ ሀሳብና ተግባር ጥምረት ነው፡፡ ይህ ሣይንሳዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ በአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ለማስመዝገብም ይሁን በዓለም ላይ ታላላቅ ዕድገቶች እንዲመዘገቡ ለማድረግ ዋናው አንቀሳቃሽ ሞተር ሆኖ ያገለግላል፡፡ በየትኛውም የዓለማችን ክፍሎች የመጡ ዕድገቶች መርህ እነሱን የሚመራው ርዮተ-ዓለም ነፀብራቆች ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡ ባለንበት ዘመን በዓለማችን አራት ዋና ዋና



t.me/OLDBOOKSPDF

የርዮተ ዓለም አስተሳሰቦች ያሉ ሲሆን እነሱም፡- ሶሻሊዝም፣ሶሻል ዲሞክራሲ፣ኒዮ ሊበራሊዝምና አብዮታዊ ዲሞክራሲ ናቸው፡፡

ሶሻሊዝም፣ እንደአማራጭ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ርዕዮት የቀዝቃዛው ጦርነትን ማብቃት ተከትሎ ከተጨባጭ የሕዝብ አስተዳደር ወደ መፅሃፋዊ ፍልስፍና ቢሸጋገርም፣ ዛሬምድረስ በቻይና፣ ኩባና ሰሜን ኮሪያን በመሳሰሉት ሀገራት ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን ዋነኛ ማጠንጠኛውም ህዝባዊነት ነው፡፡ የሶሻሊዝም ህዝባዊ መሠረቶች ጭቁን ላባደርና አርሶ አደሩ ሲሆኑ ኢኮኖሚው ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የዋለ ነው፡፡

የሶሻል ዲሞክራሲ አራማጆች ደግሞ በዋናነት የስካንዲኔቪያ ሀገራት ሲሆኑ፣ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ፍትሀዊነትን የማያረጋግጥ በመሆኑ፣ መንግስት ከሚሰበስበው ግብር ደሀውን የሚረዱ የተለያዩ ሥርዓትን ቀርጾ ተግባራዊ ማድረግ ስላለበት፣ የመንግሥት በኢኮኖሚው ጣልቃ ገብነት ከፍ ማለት አለበት የሚል አስተሳሰብ ነው፡፡

ሊበራሊዝም በአሜሪካ እና በምዕራባውያን በሰፊው የሚተገበር ሆኖ፣ ዋና ማጠንጠኛውም ግለሰባዊነት ነው፡፡ አራተኛው ርዕዮተ ዓለም አብዮታዊ ዲሞክራሲ ወይም የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ ሲሆን በአንዳንድ የደቡብ አሜሪካ፣ በሩቅ ምሥራቅ እና አፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ እየተተገበረ ያለ ርዕዮት ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ እንደ ሀገርና ህዝብ ልንሳፈርበት የሚገባውን የፖለቲካና ኢኮኖሚ ርዕዮት በጠራ ዕውቀት መወሰን እንድንችል በምርጫ ገበታችን ብፌ ላይ ተዘርግተው የምናገኛቸውን በካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ ርዕዮት ማዕቀፍ ውስጥ የኒዮ ሊበራሊዝም እና ልማታዊ መንግሥትን እንፈትሻለን፡፡

ከዓለም አገራት የታሪክ ድርሳን ላይ በትክክል መረዳት እንደሚቻለው ዛሬ ዋነኛና የብዙዎቹ አገራት ተመራጭ የኢኮኖሚ





ሥርዓት ተደርጎ የሚወሰደው ካፒታሊዝም በሊበራሊዝም ፖለቲካዊ ፍልስፍና እየተመራ፣ አገራትን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪያዊ ልማት መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያደርጉ በመደገፍ የኢኮኖሚ ዕድገትና የብልፅግና መሠረት ሊሆን ችሏል፡፡

በዚያው መጠን ካፒታሊስታዊው የኢኮኖሚ ሥርዓት በረቀቀ ሥልትና በተደራጀ አካሄድ የብዝኀኑን ጉልበትና ሃብት በዝብዞ ለጥቂት ዕድለኛ ባለሃብቶች በረከት ሆኗል የሚል ክስ ይቀርብበታል፡ ፡ በዚህም ምክንያት ሚሊዮኖችንም ወደድህነት አረንቋ በመግፋት በፈጠራቸው ቀውሶችና ምስቅልቅሎች ሳቢያ የአንደኛውና የሁለተኛውን የዓለም ጦርነቶች መቀስቀስ ዋነኛ ምክንያት በመሆን ለዓለማችን ሚሊዮን ዜጎች ሕልፈትና ከፍተኛ ሃብት ውድመት ምክንያት መሆኑን የሚያትቱ ምሁራን በርካቶች ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ይህ ሥርዓት በውስጡ ያሉትን ቅራኔዎች በሰላማዊ መንገድ በማስማማት ዓለምንና ሕዝቦቿን ወደተሻለ ሕይወት ይመራቸዋል ወይስ ወደሌላ ተመሳሳይና የከፋ ቀውስ ያደርስ ይሆን? የሚለው ወደፊት የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚያ በመለስ ግን የወቅቱ ብቸኛ አማራጭና ተመራጭ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ እኛ እንደተመራማሪ ደግሞ የተባለውን ከመቀበል ባሻገር ያስኬዳል ወይ? የሚለውን ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ያዋጣናልስ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡

### የኒዮ ሊበራሊዝም ጽንሠ-ሀሳብና ውጤቶቹ

በካፒታሊስቱ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የገበያ ውድድርና የሰዎች ግንኙነት የሚገለፅበት መሠረታዊ ፍልስፍና የሚመነጨው 'ሰዎች ራስ ወዳድ ናቸው፤ እያንዳንዱ ሠው ከራሱ በላይ ለማንም አብልጦ አያስብም' ከሚል ዕሳቤ ሲሆን ዜጎችን እንደ ደንበኛ በመቁጠር፥ 'ዲሞክራሲያዊ ፍላጎታቸውን የሚያራምዱት በመግዛትና በመሸጥ፤ ሂደቱም በራሱ የሚሸልምና የሚቀጣ ነው' ብሎ ያምናል፡፡ ስለሆነም በኒዮሊብራሊዝ ዕሳቤ መሠረት፣ ገበያ በተፈጥሮ በማቀድ በፍፁም ሊገኙ የማይችሉ ጥቅሞችን በማስገኘት በኩል ወደር የማይገኝለት መሆኑን የርዕዮቱ አራማጆቹ ያስረዳሉ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

በእኩልነትና በነፃ ውድድር የገበያ ሥርዓት ውስጥ 'ገበያው በራሱ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚገባውን ማግኘቱን ያረጋግጣል። ጠንክረው በመስራት 'ጠቃሚ ነገርን የሚያስተዋውቁ ሁሉ የገበያ ሽልማትና ተጨማሪ ሃብትን ለማግኘት ሲችሉ ደካሞች ደግሞ በገበያ ቅጣት ከስረው ይወጣሉ። በዚህ ሂደት በማህበረሰብ መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶችን የዕድገት መሠረት በመሆናቸው መታየት ያለባቸው በበጎ መልኩ ነው። ይህም በረጅም ጊዜ እያንዳንዱ ግለሰብ እንዲበለፅግ ማድረጉን በማብራራት በተቃራኒው ፣ በማህበረሰብ መካከል ዕኩልነት እንዲኖር ማድረግ ወይም ልዩነቶችን ለማጥበብ የሚደረግ ጥረት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝንና በሞራል ደረጃም ተቀባይነት የሌለው እንደሆነ የሚሞግቱ አካላትም አሉ። ከዚህም ሌላ የግል ሀብትና የሀብት/ንብረት ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ያልተንዛዛ መንግስታዊ አስተዳደርም የዕድገት መሠረት መሆኑን ኒዮሊበራሊስቶች ያስረዳሉ።

'ነጻ ገበያን መሰረት ያደረገ የንግድ ውድድር ሊገደብ እንደማይገባው' አበክረው የሚከራከሩት የኒዮሊብራሊዝም አስተሳሰብ አራማጆች፣ ነፃ የገበያ ውድድርን ለማግታት መሞከር ነፃነትን የሚጋፋ ጭቆና አድርገው ይቆጥሩታል። ግብር እና ቁጥጥር በተቻለ መጠን መቀነስ ይኖርባቸዋል። ለዚህም፣ በመንግስት የሚሰጡ አገልግሎች መቀነስ የግድ ሲሆን ሊኖሩ የሚገባቸው አገልግሎቶችም ከሆኑ ወደ ግል ባለቤትነት መዛር ይኖርባቸዋል ሲሉ ይሞግታሉ። የላባደሮች (የሰራተኛ ማህበራት)፣ ድርጅቶችንና የማህበራቱ የመደራጀት አቅም የገበያ መዛባት የሚያመጡና በሂደቱ የሚፈጠሩ ተሸናፊዎችንና አሸናፊዎችን የሚያስተጓጉሉ እንደሆኑ ኒዮሊበራሊስቶች ያስረዳሉ።

በካፒታሊስቱ የኢኮኖሚ ሥርዓት ከግብርና ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ሽግግር ባደረጉ፣ ገበያው በተደላደለበትና መንግስታዊው ቢሮክራሲ በተጠናከረባቸው አገራት በርግጥ መንግሥት በልማት ሥራ ራሱን ከመጥመድ ይልቅ በፖሊሲና ሕግ ማስፈፀም ላይ ትኩረቱን ቢያደርግ የውጤታማነት ደረጃው ከፍተኛ





ሊሆን መቻሉ አያጠያይቅም። የካፒታል፣ የመሠረተ-መዋቅርና የሰለጠነ የሰው ሃብት ውስንነት ችግር ባለመኖሩ፣ ዜጎች የመግዛት አቅሙ እስካላቸው ድረስ የተሻሻለ ምርትና አገልግሎት የማግኘት ችግሩ እንደሌለባቸው ጥራትና ቅልጣፌም የገበያው መገለጫ መሆኑ አያጠያይቅም። በዕድገት ያልገፉ ሀገራትና ገበያን ያልመሰረቱ ኢኮኖሚዎች እንዴት ወደ ዕድገት ሊያመሩና የመዋቅር ሽግግር ሊያመጡ እንደሚችሉ የኒዮሊብራሊዝም ርዕዮተ ዓለም ብዙ የሚለው ነገር የለም ሲሉ የሚተቹ ምሁራን ጥቂት አይደሉም።

መንግስት የገበያ ጉድለት ምንጭ እንጂ መፍትሄ ስላልሆነ፣ ከገበያ እጁን ማራቅ እንዳለበት የሚያስረዱት የኒዮ ሊብራብራሊዝም አቀንቃኞች፣ አንዳንድ ጊዜ የሚተገብሯቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከቃልና ተግባራቸው ጋር ተጣጥመው ሲዘልቁ አይታዩም። እንደማሳያም፡-

በአሜሪካና በምዕራብ አውሮፓ አገራት ገበሬዎቻቸው ከገበያ እንዳይወጡ ድጎማ ሲያደርጉ ይታያሉ። መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ቀጥተኛ እጁን አስገብቶ ገበያን ለማረጋጋት ወደ ኋላ የሚል እንዳልሆነ ሌላው ቢቀር እ.አ.አ በ2007/2008 የፋይናንስ ተቋማትን ቀውስ ተከትሎ ባንኮቹን ለመታደግ ከካዝናው አውጥቶ የሸለማቸው ጥሬት ማስረጃ ይሆናል። በተመሳሳይ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በነበረው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሳቢያ በመላው ዓለም የተንሰራፋውን አስከፊ ሁኔታ ለመቋቋም የጆን ሜይናርድ ኬንስ የማንሰራሪያ ፍልስፍናዎች፣ ማለትም ሙሉ በሙሉ የሰው ኃይል ቅጥር (full employment) እንዲኖር ማስቻልና ከድህነት ነፃ መውጣት የሚሉት ድጋፎች በአሜሪካና በአብዛኞዎቹ የአውሮፓ አገራት በሰፊው ተግባራዊ ተደርገዋል። በባለሃብቶች ላይ ከፍተኛ የግብር መጠን በመጣል አዳዲስ የህዝብ አገልግሎቶችና ደህንነትን ለማጠናከር የሚያስችሉ ማህበራዊ ግቦችን ለማሳካት ከየትኛውም አካል የሚሰነዘር ነቀፌታን ባለመፍራት መንግሥት በሰፊው እንቅስቃሴ ያደርግ እንደነበር ታሪክ ማስረጃ ይሆናል።



t.me/OLDBOOKSPDF

በ1970ዎቹ አትላንቲክን በሚያካልሉ በሁለቱም ግዛቶች በከፍተኛ ደረጃ የመንግሥት ጣልቃ ገብነትን የሚያበረታታው የኬኔዥያን ፍልስፍና ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎች መፈረካከስ ሲጀምሩ የኒዮሊብራሊዝም ፍልስፍናዎች ቀዳሚውን ቦታ ይዘው ብቅ አሉ:: "ለለውጥ ጊዜው ሲመጣ በቀላሉ መተካት የሚችል አማራጭ ተቀምጧል" ሲል ሚልተን ፍሪድማን እንደተናገረው መሆን የጀመረው ከዚያ ወዲህ ነው:: ፍልስፍናውን በሚደግፉ ጋዜጠኞችና በፖለቲካ አማካሪዎች በመታገዝ የኒዮሊብራሊዝም ፅንሰ ሃሳቦች በተለይም 'የገንዘብ ፖሊሲን እንዲያንሰራራ ያግዛሉ' ተብለው የተቀመጡ ነጥቦች በጂሚ ካርተር አገዛዝ ሥር ትገኝ በነበረችው አሜሪካ እና በጃም ካላሀን አገር እንግሊዝ ተግባራዊ ተደርገዋል::

በእንግሊዝ ማርጋሬት ታቸር፣ በአሜሪካ ደግሞ ሮናልድ ሬገን ወደ ሥልጣን መምጣትን ተከትሎ የፍልስፍናው ፅንሰ-ሃሳቦች በግልጽ በየአደባባዩ በስፋት ተግባራዊ የሚሆኑበት አጋጣሚ ተፈጠረ:: ለሀብታሞች በከፍተኛ ደረጃ የግብር ቅነሳ፣ የሰራተኛ ማህበራት መፍረስ ወይም በከፍተኛ ደረጃ መዳከም፣ የመንግሥት ጣልቃ ገብነትን ማስወገድ፣ በመንግስት ይዞታ ስር ሆነው የሚሰጡ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ መዘዋወር በዚህ ወቅት የታዩና የርዕዮተ-ዓለሙ መገለጫዎች የነበሩ እሴረጅ ናቸው:: በአብዛኛው የዓለም ክፍል ዲሞክራሲያዊ ስምምነት ሳይደረግ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅትን(IMF)፣ የዓለም ባንክን፣ እና መሠል ስምምነቶችን እና የዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅትን በመጠቀም የኒዮሊብራሊዝም ፖሊሲዎች በየአገራቱ እንዲስፋፉና እንዲሜኑ ተደርጓል::

እያሉ የአፍሪካ አገራት፣ እንዲሁም ከሶሻሊዝም ሥርዓት ወደዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በመውተርተር ላይ የነበሩ የምስራቅ አውሮፓና የእሲያ አገራት በኃይል በተጫኑባቸው የመዋቅር ማሻሻያ ሥርዓት ሳቢያ ለኢኮኖሚ ውድቀትና ለሕዝባዊ ዓመፅ መፈጠርና ድቀት የተዳረጉት በዚሁ ነባራዊ ሁኔታቸውን ባላገናዘበ የኢኮኖሚ ርዕዮት በመመራት እንደነበር የቅርብ ጊዜ





ትውስታ ነው:: በርግጥ፣ ይህ ርዕዮት ዛሬ አብቅቶለታል... እንኳንና በሌሎች አገራት በመነጨበትም ምድር ተግባራዊ ሊሆን ያልቻለ አሥተምህሮት ነው፣ ብለው የሚሞግቱ ወገኖች ባይጠፉም:: በተግባር ርዕዮቱ የከሸፈ አስተምህሮት ቢሆንም ግን ታዲ ዛሬም በጠንካራ መሠረት የተገነባ መዋቅር ስለለው እናቱን እንደተቀጠቀጠ እባብ አፈር ልሶ እየተነሳ ሕይወት በመዝራት የዓለምን የጉዞ አቅጣጫ ሲወስን፣ ጦርነቶችን ሲለኩስና ሲያጠፉ መታዘብ ብዙም እንግዳ ያልሆነ ክስተት ነው::

ከኒዮሊበራሊዝም ርዕዮት አራማጆች ጋር በተያያዘ በተሳሳተ የትርጓሜ ዓውድ ሲሽከረከር የምናገኘው ተጨማሪ የአስተሳሰብ ወለምታና ሌላ ገፅታ ሃብት ነው:: በብዙ ሰዎች ዕሳቤ ሀብት የልፋትና ድካም ውጤት፣ የልዩ ችሎታ ችሮታ ተደርጎ ይወሰዳል:: በርግጠኝነት በልፋትና ድካም ጠንክሮ በመስራት የሃብት ባለቤት መሆን የቻሉ የሉም ማለት አይቻልም:: በስንፍናቸው ሳቢያ ለድህነት የተዳረጉ መኖራቸውም እውነት ነው:: በዋናነት የሃብትና ድህነት መሰረቱ ግን ስንፍናና ጠንክሮ መስራት ከመሆኑ በላይ የመልካምና መጥፎ አጋጣሚዎች ድምር ውጤት ነው፣ ማለትም እንችላለን::

የተሻለ ትምህርት፣ የተሻለ ጤና፣ የተሻለ አማራጭ... በውጤቱም የሀብታም ልጅ ሀብታም፣ የደሀ ልጅ ደሀ እይነት እውነታን መፍጠሩን የማይካድ ሀቅ ነው:: ካፒታል በ21ኛው ክፍለ-ዘመን በሚል ርዕስ ዳጎስ ያለ የጥናት መጽሐፉን ለንባብ ያበቃው ቶማስ ፒኬት ለኢንቨስትመንት የሚመደብ ከፍተኛ ካፒታል ከሚያስገኘው የትርፍ ደረጃ ጋር ቀጥተኛ ትስስር እንዳለው የሚገልፅልን በአሜሪካ የሚገኙና 850 አካባቢ የሚጠጉ የግልና የሕዝብ ዩንቨርሲቲዎች ላይ ለሁለት አስርት ዓመታት የተሰበሰበ መረጃን በማቅረብ ነው::

ለኢንቨስትመንት ከፍተኛ በጀት ከሚመድቡት የመጀመሪያዎቹ ዩንቨርሲቲዎች መካከል ሃርቫርድ፣ ዬል ፣ፕሪስተን 10 ቢሊዮን ሲሆን፣ MIT 15 ቢሊዮን በመመደብ ይታወቃሉ:: በዚሁ ቅደም

ተከተል 60 የሚሆኑ ዩንቨርሲቲዎች አንድ ቢሊዮን ገደማ፣ 66 የሚሆኑ ዩንቨርሲቲዎች ከ100 ሚሊዮን እስከ አንድ ቢሊዮን፣ 186 ዩንቨርስቲዎች ከ100 ሚሊዮን እስከ 500 ሚሊዮን፣ 498 የሚሆኑ ዩንቨርሲቲዎች ደግሞ ከ100 ሚሊዮን በታች የሚመድቡ ናቸው። በዚሁ የኢንቨስትመንት ካፒታል መሠረት ከፍተኛ መዳቢዎቹ እስከ 10.2 የሚደርስ አማካኝ ትርፍ በመቶኛ ሲያገኙ ዝቅተኞቹ ደግሞ 6.2 በመቶ አማካኝ ትርፍ ያስገኛሉ። በመሆኑም የላቀው ሃብታችን የተገነባው ለሌሎች መልካም አጋጣሚ በመንፈግ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ የጋራ ተጠቃሚነትን የማስፋት እርምጃ ተጠናክሮ ሊታይ ይገባ የነበር ቢሆንም በተግባር የሚስተዋለው እውነታ ግን የተገላቢጦሹን ከስተት ክስተት የሚያረጋግጥ ሆኖ ይስተዋላል።

በጣም አስከፊውና አሳሳቢው ክስተት ኒዮሊበራሊዝም እንደ ርዕዮት ዛሬም የጠንካራ ኃይል ባለቤት መሆኑ ነው። የወደደውን ይደግፋል፣ የጠላውን ይገፋል። በማን ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ... በነማንስ ላይ ወረራ መካሄድ እንዳለበት በግልፅ እንዳንዴም ከመጋረጃ ጀርባ የሚወስን የቱ ቴክኖሎጂ በየትኞቹ ሀገራት እጅ መግባትና አለመግባት እንዳለበት አቅጣጫ የሚያስቀምጥ በዚያውም መሠረት እንዲፈፀም ወሰኖ የሚንቀሳቀስ ድንበር ተሻጋሪ ባለረጅም እጅ ነው። የቆመላቸውን ባለሃብቶች እስከጠቀመ ድረስ የኒዮ ሊብራሊዝም ፍልስፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚ እንዲሆን እጅ መጠምዘዝ የሚያስችል ታላቅ ኃይል በዙሪያው ያከማቸ ስብስብ ነው።የአንድ ሀገር መንግሥት የሚተዳደሩበት ሕዝቦች ቢፈቅዱም ባይፈቅዱም የመሪዎችን እጅ ጠምዝዞ ውሳኔ ያስቀይራል። ፓርላማዎች የሚያስተላልፉትን ውሳኔ ውድቅ ያደርጋል።ዓለማችን ላይ ቢጋራና ሁለንተናዊ ጥረት በቀላሉ ሊወገዱ የሚችሉ ችግሮች ችላ ተብለው ስር እንዲሰዱ ፤ የአየር ንብረት ለውጥ ችላ መባሉን ፤የሲጋራ ሽያጭን ለማስቆም፣ ወንዞችን እና የውሃ ምንጮችን ከብክለት ለመታገድ፣ ኩባንያዎች ከማዕድን ቁፋሮ የሚያወጡዋቸውን በካዮች እንዳፈቅዳቸው እንዳይለቁ ለመከልከል፣ የኢነርጂ ከፍያዎችን ለመቀነስ፣ ወይም በፋርማሲ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ከህዝብ እንዳይመዘብሩ ለማድረግ የተላለፉ በርካታ





ውሳኔዎችን ውጤት አልባ እንዲሆኑ በማድረግ ኒዮ ሊበራሊዝም አሉታዊ ሚና የተጫወተ ሲሆን ጥቅማቸውን የሚያስከብርላቸው ባለብዙ ሚሊዮን ኮርፖሬቶችን ከጀርባው አሰልፏል።

እኒህ ከርዕዮቱ ጀርባ ያሉ ባለ ሥውር እጆች በእነርሱ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዓለም አቀፍ ተቋማትን በመጠቀም የተዛረጋቸውን ወገኖች ከሰው የሚረቱባቸው መሳሪያዎች ከመሆናቸው በተጨማሪ አመዛኞቹም 'በባለሀብቶችና በመንግሥት መካከል ያሉ አለመሰማማቶችን መቅረፍ' በሚል የተዘጋጁ የንግድ ስምምነቶች ናቸው። እናም እንደቀን ፀሐይ የጠራውን ዕውነታ ወይም ተጨፈኑና እናሞኛችሁ፣ በማለት በሬን ካራጁ... አጥፊን ከጠፊው... ማገር በተለወሰ መርዝ አስማምተው ለማኖር ፡ሠፊው ህዝብ ከአባብ እንቁላል እርግብ እንዲጠብቅ ሁሉንም አቅም በመጠቀም በስብከታቸው ገፍተውበታል።ይህም ከዚህ በታች የሰፈረውን ተረት ለማስታወስ ምክንያት ይሆናል።

አህያና ጅብ በአንድ ዘመን፣ በከፋት ላይፈላለጉ ተከባብረው ሲኖሩ ተማምለው ነበር፣ ይባላል። እንደ ቃላቸው ተስማምተው ሲኖሩ እያ ጅቦ የበኩር ልጁ ሞተበት። ይህ አጋጣሚ ለጅቡ ሀዘንን፣ ለአህዮች ደግሞ ጭንቅን ወለደ። አህዮች ሊያስተዛዝኑ እያ ጅቦ ዘንድ ለመሄድ አሰበው 'ይተናኮለን ይሆን! ' የሚል ሥጋት ወደኋላ ጎተታቸው። እንዳይቀሩም 'ምን ተብሎ ይቀራል!'፤ ደግሞ 'መልካም ጉርብትናን አፍርሳችኋል' ቢል ማን ከልካይ አለበት። የውስጥ ሙግታቸው ለመሄድ በመወሰን ተደመደመ።

"እያ ጅቦ... ምንም ቢያነክሱ፣ ግርማ አለው ድምፅዎ፣

ምንም ጥንብ ቢበሉ፣ ነጭ ነው ኩስዎ።" ብለው ይገባሉ፣ ወደ ለቅሶው ስፍራ።

ጥቂት አረፍ እንዳሉ፣ እያ ጅቦ ወደ አጠገባቸው መጥቶ ያመሰግናቸዋል። በሃዘን መስበሩን ያጫውታቸዋል። በጨዋታው



t.me/OLDBOOKSPDF

መሃልም፣ "ወዳጆቼ በእኔ የደረሰ በእናንተ አይድረስ! ከከፉ ይሰውራችሁ!! በድንገት የበኩር ልጄን በሞት ተነጠቅሁ። ሳላስብ... ሳልዘጋጅ... የእኔ ነገር እንዲህ ሆነ... በዚህ ቢቃህ ባለኝ... ይኸው በቤቴ የሚላስ የሚቀመስ አጣሁና ለለቀስተኞቼ የማቀርበው አጣሁ" ይሉቸዋል።

"ታዲያ ምን ተሻለ?" በሀዘኔታ አህዮች ይጠይቃሉ።

"መቼስ ከናንተ በላይ ወዳጅ የሆነ ገበና ከታች የለኝም። እንዲያው ለዛሬ... (አያ ጅቦ እንደ ማመንታት እየቃጣው) እንዲያው ለዛሬ እንግዳ መሸኛ እንዲሆነኝ፣ ከሀፍረትም እንድወጣ የታችኛው ከንፈራችሁን ብትሰጡኝ?"

አህዮቹ ጨነቃቸው። እምቢ ቢሉት ደጁ መጥተዋል። ሊዘነጣጥላቸው ይችላል።

ይሁን፣ ብለው ሙሉ በሙሉ ከመበላት በከንፈር መገላገል በስንት ታዕሙ... ሆሆይ!! "አያ ጅቦ ከሚያፍሩ እኛ ከንፈር እንጣ" ብለው ከንፈራቸውን አስረከቡ።

አያ ጅቦ ከለቀስተኞቹ ጋር ሆኖ ለዕዝን የቀረበለትን ከንፈር አጣጥሞ በላ፣ በለቀስተኛ ደንብ በተሰየመለት ቦታ እንደተቀመጠ።

አህዮቹ፣ እግዜር ያጥናህ! ብለው ወደ ቤታቸው መሄጃ ጊዜቸው ደረሠ።ለመሄድ ከመነሳታቸው አፍታ ቀደም ብሎ አያ ጅቦ ቁጣ ቁጣ ይለው ጀመር። "እኮ እንዴት... እንዴ...ት!!" አያ ጅቦ እንባረቀ።

"ምን ሆነ...? ምን ሆነ?" አህዮች ተደናግጠው ተጠያየቁ።

"እኮ እንዴት... የበኩር ልጄን በሞት ተነጥቄ በባዶ ቤት ባዘን መቀመጤ ሳይበቃ በልጄ ሞት ትገለፍጣላችሁ... እንዴት ተደርጎ!!!"

አህዮች ድንጋጤያቸውን መቆጣጠር እንደተሳናቸው በያሉበት





ሲርበተበቱ አያ ጅቦ ተነስቶ እያንዳንዳቸውን ዘነጣጥሎ ጨረሳቸው።

በከፋ ድህነት ውስጥ እና በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ለሚገኙት የዓለማችን ሀገሮች የኒዮሊበራሊስቶች ውልና ስምምነት ሀገራቱን ወደ ባሰ ውድቀትና ጥፋት ከማሸጋገር በዘለለ የሚጨበጥ ተስፋ ያስገኝላቸዋል ተብሎ የማይጠበቀውም በዚህ የተነሳና ያላቻ ጋብቻ ሂደቱ ነው።

**የልማታዊ መንግሥት ጽንሠ-ኃሳብና ውጤቶች**

በኒዮ ሊበራሊዝም ርዕዮተ-ዓለማዊ ቅኝት የካፒታሊስቱን የኢኮኖሚ ሥርዓት ወገባችንን አጥብቀን እንድንያያዘው የሚሞግቱን የመኖራቸውን ያህል፣ የለም! እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በድህነት ለተተበተቡ ሀገራት የካፒታሊስት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በልማታዊ መንግሥት* ርዕዮት አስደግፎ ማስኬዝ ነው - መፍትሄው፣ የሚሉ ወገኖችም ጥቂቶች አይደሉም።

ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ የሚያስደምም የኢኮኖሚና ማህበራዊ የመዋቅር ለውጥ በማምጣት ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ሥርዓትን መገንባት ከቻሉት የምሥራቅ እስያ አገራት እነ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን፣ ሲንጋፖርና መሰል አገራት የዕድገት ጉዞ ተሞክሮ በመነሳት በልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ላይ ብዙ ተጽፏል። እነዚህ አገራት በተጓዘበት መንገድ ያሉ ውጣ ውረዶች፣ ያስመዘገቡት ዕድገትና ውድቀት፣ እንዲሁም አሁን ያሉበት ደረጃ ሠፊ ትንታኔ ተሰጥቶበታል። እነዚሀ አገራት በመሰወን ረገድ ያላቸው ጥንካሬ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የባህል እና መሠል መሥተጋብሯዊ ልዩነቶች የሚፈጥሩት ተፅዕኖ እንደተጠበቀ ሆኖ ልማታዊ መንግሥት ያስገኘላቸው ጥቅምና ያስከተለባቸው ተፅዕኖ ዛሬም ሌሎች ሀገራት በዝርዝር ሊያጠኑት የሚገባ እያጠኑትም ያለ ጉዳይ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF

የተለያዩ ጸሀፍያን ለልማታዊ መንግሥት የተለያየ ትርጉም ስለሚሰጡት ሁሉን የሚያስማማ ወጥ ትርጉም ማግኘት ከባድ ነው። የልማታዊ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ትርጉም በግርድፉ ልማትን ዕውን ማድረግን ዋነኛው ግቡ በማድረግ ልማትን የሚያፋጥኑ ፖሊሲዎችንና ህጎችን በማውጣትና የሚፈጸሙበትን ሥርዓትም በመዘርጋት መንግሥት የልማቱ ግንባር ቀደም ዋነኛ ተዋናይ የሆነበት ስሥርዓት ነው ማለት ይቻላል። እንደ ካስቴልስ (Castells) ፍቺ አንድ መንግሥት ልማታዊ ነው፣ ሊባል የሚችለው ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት የማስመዝገብ አቅም በመገንባት ይህንኑ ቅቡልነት መሠረት በማድረግ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ባለው ኢኮኖሚያዊ መሥተጋብር ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብና መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ዕድገቱን ማስቀጠል በመቻሉ ላይ የተመሠረተ ነው። ቻልምረስ ጆንሰን (Chalmers Johnson) በበኩሉ የልማታዊ መንግሥትን ምንነት ሲያብራራ የምጣኔ ሀብት ከፍፍልና ሥርጭት የሚወስንበት፣ ቅንጅታዊ መሥተጋብር በሌላቸው የገበያ ኃይላት ላይ በጥገኝነት የተወሰነ እንዳይሆን ለማድረግ በሁለንተናዊ የዕድገት ሂደቱ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን ፍጥነትም ሆነ አቅጣጫን የሚወስን መንግሥት 'ልማታዊ መንግሥት' ሊባል እንደሚችል ይገልፃል።

በደምሳሳው ግን የልማታዊ መንግሥት ንድፈ ሃሳብ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከማህበራዊ እድገት ጋር በማጣመር አገራዊ ሀብትን በመንግሥት ቀጥተኛ አቀናጅነትና ፈጻሚነት ድህነትን በመቀነስ መዋቅራዊ የማህበረሰብ ለውጥን ለማምጣት የሚተጉ አገራትንና መንግሥታትን የሚገልጽ ነው፣ ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

ብዙ የዓለም አገራት እነዚህን የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጦችን ተከትለው የኢኮኖሚ ዕድገት ፖሊሲዎቻቸውን እንደጊዜው ሁኔታ ቀይረዋል። ነገር ግን ከ1950 እና 1960ዎቹ ጀምሮ ያለማቋረጥ በኢኮኖሚ ዕድገት እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ የመንግሥታትን ሚና ያለማቋረጥ አስቀጥለው የነበሩ አገራት ፖሊሲዎቻቸውን





ቀያይረው ከነበሩት የበለጠ ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግበዋል። ለዚህም እንደምሳሌ የሚጠቀሱት "የእስያ ነብሮች" ተብለው የሚጠሩት አገራት እነ ሆንግ ኮንግ፣ ሲንጋፖር፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን ናቸው። እነዚህ አገራት በ1960 ዎቹ ከነበሩበት ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የግብርና ኢኮኖሚ በ1990 ዎቹ በቴክኖሎጂ እና በዕውቀት ወደሚመራ የከፍተኛ ገቢ ባለቤት ወደሆነ ኢኮኖሚ ተሸጋግረዋል።

የእነዚህ አገራት ተአምራዊ ዕድገት በዓለም አቀፍ ደረጃ መንግሥታት በኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ሊኖራቸው ስለሚገባ ሚና አዲስ ምዕራፍን የከፈተ ከመሆኑም በላይ በነጻ ገበያ አራማጅ የኒዮሊበራል አገራት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ሳይቀር መንግሥታት በኢኮኖሚ ሥርዓት ወስጥ ሰፋ ያለ ሚና መጫወት እንዳለባቸው እየታመነበት መጥቷል። በውጤቱም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የድህነት ቅነሳ ፖሊሲዎች ለመንግሥታት ሚና ዕውቅናን እንዲሰጥ አስገድዶት አልፏል። ለምሳሌ፦ በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነድ (PRSPs) እና የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ (MDGs) መንግሥታት የሚያወጡትና የሚተገብሩት ሰፋ ያለ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ተቀባይነትን ሊያገኝ ችሏል።

በተያያዘም የእነዚህ አገራት ፈጣን ዕድገት በልማት ውስጥ የተቋማት ሚና ቀድሞ ይሰጠው ከነበረው ዝቅተኛ ቦታ የተለየና የተሻለ ቦታ እንዲሰጠው እድል ፈጥሯል። በመሆኑም ከተፈጥሮ ሃብትና የንግድ ሁኔታ በላይ የመንግሥታት ተቋማዊ አቅም ለአገራት የዕድገት ደረጃ መለያየት እንደ ዋና ምክንያት ተቀባይነትን እንዲያገኝ አድርጎታል።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ አሰርት-ዓመታት አካባቢ የምሥራቅ እስያ አገራት ተዓምራዊ ዕድገትን ያጠኑ የዓለም አቀፍ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ምሁራን ልማታዊ መንግሥትን የሚገልጹት መንግሥት በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ላይ የበላይነት ያለው፣ መንግሥት መር የማክሮ ኢኮኖሚ ፕላኒንግ ወይም መንግሥት-መር ካፒታሊዝም በማለት ነው። ከዚህ እንጻር ጠንካራ የመንግሥት



t.me/OLDBOOKSPDF

ጣልቃ ገብነት ሳፈ ቁጥጥር፣ የተለጠጠ ዕቅድ መኖር ዋነኛ የልማታዊ መንግሥት መገለጫዎች ናቸው ተብለው ይጠቀሳሉ፡፡

መዘንጋት የሌለበት አንድ ተጨማሪ እውነታ አለ፡፡ በተትረፈረፈ ተሞክሮ ውስጥ እንዲቱን ነጠላ ሰበዝ መዝዞ ማጠቃለያ መስጠት ይቻላል፡፡ውጤቱ ግን አደገኛ ነው፡፡ በ1960ዎቹ መጨረሻ የአገራችን ምሁራን ለአገራችን ቀጣይ ዕጣ ፈንታ የቀናው መንገድ የቱ ነው? ብለው ጠይቀው የተሻለውን ለመምረጥ መጣራቸው የሚያስመሰግን ሆኖ ሳለ፣ ምኞታቸውን ዳር ሊያደርሱ ያስችለናል ያሉትን የማርክሲዝም ርዕዮት ቀድመው በጥልቀት ባለመፈተሻቸው አገራችን ለ17 ዓመታት በጨለማ ውስጥ እንድትደናከር ምክንያት በመሆን የማይረሳ ጠባሳውን አትሞ አልፏል፡፡ ዛሬም ቢሆን የፅንሰ ሃሳቡን መልካም ገፅታ ብቻ ሳይሆን ውድቀቶቹንም አብጠርጥሮ ማየት፣ ከዚያም ጋር እያይዞ እኛ ምን ደረጃ ላይ ነው፣ ያለነው? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡ በቅድሚያ 'ያሻናል ወይ...?! ከዚያም አዋጭነቱስ?!' ብሎ መጠየቅ ግድ ይላል፡፡ "ሞኝ ከራሱ ስህተት ብልሆች ግን በሌሎች ስህተት ይማራሉ" እንዲል የሀገራችን ሠው... አካሄዳችን በብስለት መመራት አለበት፡፡ እንደተሳካላቸው ልማታዊ መንግሡታት ያልተሳካላቸውንም መንግሥታት መኖራቸውን በማሰብ ለምን እንዳልተሳካላቸው መፈተሽ የተሻለ ተጠቃሚ ያደርገናል፤ እነርሱ ከፈፀሟቸው ስህተቶችም ይታደገናል፡፡

### የልማታዊ መንግሥት ስኬት በምስራቅ እስያ

ኋላቀር ከሆነውና በእርሻ ላይ ከተመሰረተው የግብርና የኢኮኖሚ በመውጣት በ1960 እና 80 ዎቹ አካባቢ በ30 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ቴክኖሎጂና ዕሴት የጨመሩ ምርቶችን በማምረት ተዓምራዊ የሆነ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መዋቅራዊ ለውጥ ያመጡት የምሥራቅ እስያ አገራት የሆኑት ሲንጋፖር፣ ደቡብ ኮሪያና ታይዋን ብዙውን ጊዜ የልማታዊ መንግሥት ስርዓት ውጤታማ ተሞክሮዎች ተብለው ይጠቀሳሉ፡፡





ከሌሎች የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብን ካራመዱ እና ከሚያራምዱ አገራት አንጻር ለምሥራቅ እስያ አገራት የልማታዊ መንግሥት ስኬት መሠረቶች የሆኑት ጠንካራ የሥራ ባህል ያለው ማህበረሰብ መኖር እና ለልማታዊ መንግሥት ተግዳሮቶች ናቸው የሚባሉት ደግሞ 'ሰፊ የሆነ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህልና የመሳሰሉት ልዩነቶች በህዝቡ ውስጥ እምብዛም ያለመኖሩ እንደሆነ ይገለፃል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ጋኒ (Ghani) ገለጻ የእነዚህ አገራት ስኬት በሁለት መሠረተዊ ነገሮች ማለትም የሥልጣን መሠረተ-አወታሮች (infrastructural powers) እና ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት (political commitment) ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡ እንደ ጋኒ ዕሳቤ የልማታዊ መንግሥት ፕሮጀክት ዕውን ይሆን ዘንድ ሥርዓቱ አብዛኛውን የግዛቱን ክፍል በእጁ አድርጎ መልክ ያለው ዕዝ የሚተዘረጋበትና ፖሊሲ ቀረፃ ተግባራዊ በማድረግ ከፖሊሲው ተግባራዊነት ጋር ተጨባጭ ውጤት የሚያስመዘግብበት ስቅምንም አጣምሮ የያዘ መሆን ይገባዋል፡፡ እንዲሁም የልማታዊ መንግሥት ፖሊሲ በረጅም ጊዜ ግብ ላይ ያተኮራል፡፡ሩቅ ተመልካች ነው፣ ሁሉን አሳትፎ ዘለቄታዊ ጥቅም የሚያስገኝ፣ በግለሰቦች ወይም በጥቂት መሪዎች ምክንያት ህልውናው አደጋ ላይ የማይወድቅ መሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም ልማታዊ መንግሥት የግል ዘርፉን የሚያንቃቃ፣ የሚመራና የሚቀርፅ፣ እንዲሁም ከግሉ ዘርፍም ሆነ ከውጭ የሚመጡ የጥቅም ጉዳዮችን የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ አስፈላጊውን መደላድል በመፍጠር የተሻለ ጥቅም ለማግኘት ደፋ ቀና የሚል ነው፡፡

የሥልጣን መሠረተ አውታሮችን በእጁ አድርጎ ዝም አይልም፤ በሚገባ ይጠቀምባቸዋል፤ እንደ ልማት መሳሪያም ይገለገልባቸዋል፡፡ የአጭር ጊዜ ጥቅም የሚያስገኝ የኪራይ ሠብሣቢነት አመለካከትን የማይቀበል ብቃት ባለው የሰው ኃይል የሚገነባ ሲሆን የግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲዳብር በቅርበት የሚከታተልና ሁለንተናዊ ድጋፍና እገዛም የሚያደረግ ነው፡፡ እኚህ ከምሥራቅ እስያ አገራት ስኬታማ ልማታዊ መንግሥት በስተጀርባ የሚጠቀሱ የስኬት መንገዶች ናቸው፡፡ ስለሆነም በመካከላቸው ያለው የጉዞ ሂደት



t.me/OLDBOOKSPDF

ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህ አገራት የየአገራቸውን ትክክለኛ የልማት አቅጣጫ ተልመው በቁርጠኛና ታታሪ አመራሮቻቸው ተግባራዊ ሲያደርጉ የኢኮኖሚ ዕድገትን ከማህበራዊ ዕድገት ጋር መሳ ለመሳ ማሳካት ችለዋል፡፡ አገራዊ ሀብትን በመንግስት ቀጥተኛ አቀናጅነትና ፈጻሚነት ለድህነት ቅነሳ አውለዋል፤ መዋቅራዊ ለውጥም አስገኝቶላቸዋል፤ ይህ ስለተቻላቸውም የልማታዊ መንግሥት ምርጥ ተሞክሮ ሲነሳ የእነዚህ አገራት ሥም አብሮ ተደጋግሞ ይጠቀሳል፡፡

በኮሪያም ሆነ በታይዋን እንዲሁም በሲንጋፖር የተተገበሩት የልማታዊ መንግሥት ሥርዓቶች በጠንካራና ከተፅእኖ በፀዳ ሩቅ ዓላሚ አመራሮች እንዲሁም ህቀኛና ለልማት ጥሩ መሳሪያ የሚሆን ጠንካራ ሲቪል ሰርቪስ መገንባታቸው በመልካም ተሞክሮነት ሊወሰድ የሚገባው ነው፡፡ በጨቋኝ መንግሥታዊ አስተዳደር ውስጥ ተግባራዊ የተደረገው የኮሪያና ሌሎች የእስያ አገራት ልማታዊ መንግሥት ውሎ አድሮ ራሱን ወደ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መመለስ ቢችልም ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሏል፡፡ ኮሪያ ለተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥት፣ ሲንጋፖር ለህዝብ ከፍፍል ተዳርገው ጉዳትን ማስተናገዳቸው እንደምሳሌ ይጠቀሳሉ፡፡

ከዚህም መማር የሚቻለው ልማታዊ መንግሥትን ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ዴሞክራሲያዊም ሆነ ጨቋኝ ሲሆን መቻሉን፤ ይሁን እንጂ የልማታዊ መንግሥት መሠረት በዴሞክራሲያዊ መሠረት ላይ መታነፅ ግን መንግስትን ለላቀ ጠንካራ አቅምና ከድንገተኛ የከፍፍል አደጋ ሊታደገው መቻሉን ነው፡፡

### የልማታዊ መንግሥታት ውድቀት በላቲን አሜሪካ እና አፍሪካ[3]

የልማታዊ መንግሥታት በእስያ በተለይም በሲንጋፖር፣ ታይዋን፣

3 V. Fritz and A. Rocha Menocal. (2006) (Re)building Developmental States: From Theory to Practice.





እና ደቡብ ኮሪያ ያስገኘውን ስኬት በላቲን አሜሪካ እና አፍሪካ አገራት ሊደግመው ያልቻለበትን ምስጢር በተመለከተ ብዙ ጥናቶች ብዙ ብለዋል፡፡ የመንግሥት መር ልማታዊ ስትራቴጂዎች በሁለቱም አህጉራት በ1950 ዎቹ በስፋት የታመነባቸው እና የተተገበሩ ሲሆን በተወሰነ መልኩ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተስፋፍተው ዕድገት መመዝገባቸው ባይቀርም በ1980ዎቹ እና በ1990ዎቹ በተከሰተው ዓለማቀፋዊ የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀውስ ምክንያት የተጀመሩ የለውጥ እንቅስቃሴዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መቀልበሳቸውን ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በተነጻጻሪ ሲታይ የአፍሪካ ቀዳሚ ልማታዊ መንግሥት ተሞክሮዎች፣ በሙሉ በተለይም በገጠማቸው ከልክ ያለፈ የብድር ጫና ምክንያት በውድቀት የተደመደሙ ሲሆን የላቲን አሜሪካ ልማታዊ መንግሥታት ግን ከእስያ ልማታዊ መንግሥታት አንጻር ወደኋላ የመቅረት እንጂ ሙሉ በሙሉ ውድቀት ውስጥ የገቡ አልነበሩም፡፡

በአብዛኛው ሲታይ በ1960ዎቹ የአፍሪካ አገራት ገና ከቅኝ ግዛት ነጻ እየወጡ የነበረበት ወቅት ስለሆነ የልማታዊ መንግሥት ወይም የመንግሥት መር ልማት አቅጣጫ ያለ እንቅፋት ተቀባይነት ያገኘበት ወቅት በመሆኑ በበርካታ አገራት መሰረታዊ ዕድገቶችን (ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ) ማስመዝገብ ችሎ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ የጋናና የኬንያ ፈጣን የዕድገት ጉዞዎች በተለይም በትምህርትና ጤና መስኮች የተመዘገቡ ፈጣን ለውጦች በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ በላቲን አሜሪካም፣ አርጀንቲና፣ ብራዚል እና ሜክሲኮ በኃይል ዘርፍ እና በአውቶሞቢል ኢንዱስትሪው ያስመዘገቡትም ዕድገት ይጠቀሳል፡፡

ምንም እንኳን በአፍሪካም ሆነ ላቲን አሜሪካ 1970ዎቹ አካባቢ የተስተዋለው ውድቀት እንደየ አገራቱ ነባራዊ ሁኔታ ሊለያይ ቢችልም የሚመሳሰሉባቸው ምክንያቶች ያይላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በአፍሪካ የጀማሪ ልማታዊ መንግሥታት ውድቀት ምክንያት ተደርጎ

4 hana, Congo, Mauritius, Botswana, Tanzania, Côte d'Ivoire. Botswana and Mauritius are widely regarded as relatively successful developmental states in Africa.


t.me/OLDBOOKSPDF

በአብዛኛው የሚወሰደው የፖለቲካ ስርአቱ በጠንካራ መሰረት ላይ ያልነበረ መሆኑ እና በጥቅም በተሳሰሩ የፖለቲካ ልሂቃን የበላይነት /Neo patrimonialism, clientelism, patronage, prebendalismየተያያዘ መሆኑ ነው። በተቃራኒው የላቲን አሜሪካ ልማታዊ መንግሥታት ውድቀት ምክንያት ደግሞ የመንግሥትን ዓቅምና ሥልጣን ባዳከሙ የፖለቲከኞችና የቢዝነስ ተቋማት ህገወጥ የጥቅም ትስስር /corporativism/የህዝብን ፍላጎቶች እናሟላለን ብለው በቆሙ ነገር ግን በተሳናቸው መንግስታት /Populism/ ምክንያት የተነሱ የፖለቲካ ቀውሶች ናቸው። በዚህ ረገድ ለአፍሪካም ሆነ ለላቲን አሜሪካ ልማታዊ መንግሥታት ወድቀት የጋራ ምክንያት ተደርገው የሚወሰዱት ውጤታማ ያልሆኑ ኢንቨስትመንቶች፣ የነዳጅ ዋጋ ንረት፣ በቀዝቃዛው ጦርነት ምክንያት የሀያላን አገራት ጣልቃ ገብነት ነበሩ። በውጤቱም የመንግሥት መር ልማት በሁለቱም አህጉራት ተንገራግጮ ቆሞ ያለፈበት ከ1980-1990 ያለው ጊዜ የባከነው አስር አመት /lost decade/ በመባል ይታወቃል።

በሌላ በኩል ለአፍሪካም ሆነ ላቲን አሜሪካ ልማታዊ መንግሥታት ውድቀት ከእስያ አንጻር ሲታይ እንደ ዋና ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው በታሪክ ሂደት አገራቱ አልፈውበት የነበረው የቅኝ ግዛት ታሪክ ያስከተለው ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ውጤትም የተለያየ መሆኑ ነው። ሰስቱም አህጉራት ከቅኝ ግዛት ነጻ የወጡባቸው ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች ለተለያዩ ዕድሎችና ተግዳሮቶች የዳረጓቸው በመሆኑ የልማታዊ መንግሥት ትግበራ ሂደት ውጤትንም በዚህ መልኩ በአሉታዊና አዎንታዊ መንገድ ለያይቶታል።

የአፍሪካና ላቲን አሜሪካ የቀዳሚ ልማታዊ መንግሥታት ውድቀት መገለጫ ተደርገው ከሚጠቀሱ ምክንያቶች በዋናነት የሚቀመጠው ከፖለቲካው ይልቅ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቱ ሲሆን በመንግሥት የተያዙ ከፍተኛ የልማት ድርጅቶች ውጤታማ ያለመሆን እና አክሳሪ እየሆኑ መምጣት፣ በጣም ሰፊ ወጪ የሚያስወጣ ነገር ግን





ውጤታማ ያልሆነ ቢሮክራሲ መፈጠሩ፣ ከአቅም በላይ የሆነና ኢኮኖሚው ሊሸከመው የማይችል የውጪ ብድር መጠራቀም፣ የወጣበትን ያህል ማገልገል ያልቻለ ደካማ የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ከአገር ውስጥ ገቢ የማመንጨት አቅም ውሱንነት በተጨማሪ የመንግሥት ገቢ በአብዛኛው እስተማማኝ ካልሆነ የውጭ ንግድ ላይ የተመሠረተ መሆኑ፣ የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ባልተጠናከሩበት ሁኔታ የውጭ ምርትን በአገር ውስጥ የመተካት ስትራቴጂን /import substitutiton industrialization-ISI/ ተግባራዊ ለማድረግ ትግል ውስጥ መግባቱ[5] ዋጋ እንዳስከፈለ ነው ተንታኞች የሚገልፁት።

በሌላ በኩል ከፖለቲካል ኢኮኖሚ ሥርዓት አተገባበር አንጻር በልማት የተገኘውን ሃብት ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ለማህበረሰቡ ማከፋፈል መቻል ወይም አለመቻል በልማታዊ መንግሥታት ቀጣይነት እና ውድቀት ላይ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ ጥናቶች አረጋግጠዋል። በመሆኑም በእስያ ስኬታማ የሆኑ ልማታዊ መንግሥታት ሃብትን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ በማከፋፈል ማህበረሰቡ በልማት መስመሩ ላይ እምነት እንዲኖረውና መጠነ ሰፊ ድጋፍ እንዲሰጥ ያደረጉ ሲሆን በተመሳሳይ ወቅት መጥተው የነበሩ በአፍሪካ እና በላቲን አሜሪካ የታዩ ልማታዊ መንግሥታት ግን በልማት እንቅስቃሴው የተገኘ ሃብትን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ማከፋፈል ካለመቻላቸውም በላይ ሃብቱን ለፖለቲካ ስርዓቱ ማስቀጠያ መሳሪያ በማድረግ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ስር እንዲሰድድ ዕድል ፈጥረዋል። በውጤቱም የአገር መዋዕለ ንዋይ በግለሰቦች የሚዘረፍበት ሥርዓት፣ ውጤታማ ያልሆነ የጥቅመኛና ሙሰኛ የፖለቲካ ልሂቃንና ተከታዮቻቸው ባለሥልጣናት እና ባለሀብቶች ጥምረት እና ሴራ የተተበተበ የመንግሥት ሥርዓት /state capture/ እንዲገነባ እድል ፈጥሯል።

---

5 በልማታዊ መንግስት ያደጉ የኤሽያ ሀገራት ተሞክሮ በአብዛኛው ISI የተከተሉት ለአጭር ጊዜ ሲሆን በፍጥነት ወደ የውጭ ንግድ መር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደተሸጋገሩ ያሳያል። በተጨማሪም መንግስታት የልማት መዋዕለ ንዋይን የማሰባሰብና ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም መቻላቸው ለውጤታማነታቸው አስተዋጽኦ አድርጓል።



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ የሙስና መኖር በእስያም ሆነ በአፍሪካ እንዲሁም ላቲን አሜሪካን ጨምሮ የልማታዊ መንግሥታት የጋራ መገለጫ ሲሆን በሌላ በኩል ደረጃው ከፍ ብሎ በ'state capture' ፖለቲካል ኢኮኖሚ ውስጥ መግባት እና አለመግባት ለየአገራቱ ያስገኘው ውጤት የተለያየ ነው። ይኸውም ለአፍሪካ እና ላቲን አሜሪካ ልማታዊ መንግሥታት ውድቀትን ሲያስከትል ለእስያ ልማታዊ መንግሥታት ግን የስኬት በር ከፍቷል። በመሆኑም በአፍሪካ እና ላቲን አሜሪካ ለውድቀት በተዳረጉ ልማታዊ መንግሥታት ውስጥ የሚወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች አጠቃላይ አገራዊ ዕድገትን ከማስገኘት ይልቅ በጥቅም በተሳሰሩ ቡድኖች ተጽዕኖ ስር የወደቁ ሆነዋል። በውጤቱም የሲቪል ሰርቪስ ሰርአቱ ይጄነው የሚባል ውጤት ያላስገኘ በተቃራኒው ደግሞ የሙስና ሰለባ የሆነና የግል ጥቅማቸውን በሚያሳድዱ ግለሰቦች መረብ ውስጥ ተተብትቦ መውጣት የተሳነው ደካማ ሆኗል።

በሌላ በኩል የፖለቲካ አመራር ብቃት ጉድለት ለልማታዊ መንግሥታት ውድቀት ሌላው ምክንያት ነው። በአፍሪካ እና ላቲን አሜሪካም የሆነው ከዚህ የተለየ አይደለም። በእነዚህ አገራት የነበሩት መንግሥታት ጠንካራና ሩቅ ተመልካች የሆነ ተከታይ መሪ ማፍራት አልቻሉም። ይኸም ለውድቀታቸው እንደ ምክንያት ተቀምጧል። የመንግሥት ሥርዓትና መሪው ጠንካራ ያለመሆኑ ለልማታዊ መንግሥት ወሳኝ የሆነውን የመንግሥት ሥር መሰደድ እና ነጻ መሆን ጥምረትን /embedded autonomy/ ማሳካት እንዳይችሉ አድርጓል።

ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ በብዙ የአፍሪካ እና ላቲን አሜሪካ አገራት ለመገንባት የተሞከረው የሊብራል ዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በአብዛኛው ያልተሳካ በመሆኑ መንግሥታቱ ቅይጥ ባህሪ ወዳላቸው እምባገነንና ከፊል ዲሞክራሲያዊ መንግሥትነት እንዲቀየሩ እድል ፈጥሯል። በመሆኑም በልማታዊ መንግሥታት እንደ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ የሚወሰደው የተማከለና ጠንካራ የውሳኔ አሰጣጥ (concentration of decision





making power) ሥርዓት ሳያሰፍን ግልጽ የሆነ የሥልጣን ተዋረዱን የጠበቀ መዋቅር (clear hierarchical structure) ሳይዘረጋ እና በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ በዕኩልና በተመጣጣኝ የሚመራ ሳይሆን ወይም በምትኩ ሳያስቀምጥ እንዲሁ መሃል ሰፋሪ ሆኖ ቀርቷል። በውጤቱም የልማታዊ መንግሥት የሚፈልገው ጠንካራ የመንግሥት ሥርዓት በአብዛኛው ወደ ደካማ ቅይጥ ሥርዓት ተለውጧል።

በግራም ሆነ በቀኝ ዛሬ ላይ ሆነን ኒዮሊበራሊዝም ካጠላበት የካፒታሊስት ሥርዓት ይልቅ ካፒታሊስታዊ ሥርዓትን በልማታዊ መንግሥት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዞ በማስደገፍ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማረጋገጥ ጠንክሮ ከመስራት ውጭ በዕድገት ወደ ኋላ ለቀሩ አገራት የምርጫ ሳይሆን የሕልውናም መሠረት መሆኑ አያጠያይቅም። አጠያያቂው ጉዳይ በአፍሪካ ያለው የፖለቲካ ባሕል ኋላቀር መሆን፣ ከአገር ይልቅ የዘርና ጎሳ ስሜት መግነን በተነፃፃሪ ምሁራዊ ደረጃን ተላብሰዋል የሚባሉ የልማት ሠራዊቶች በግል ጥቅም የተሸበበበት እውነታ መኖሩ ነው። ይህም ቢሆን አማራጩ እሱና እሱ ብቻ በመሆኑ ከራስ ሁኔታ ጋር አዛምዶና አጣጥሞ እንዲሁም ከስህተት በመማር ወደላቀ ከፍታ ማቅናት ያስፈልጋል። 'ልማታዊ መንግሥትን ከዲሞክራሲ ጋር አጣጥመን መተግበር ግዴታ ነው። ልማት በዲሞክራሲም ሆነ በጨቋኝ መንግሥታት ጥላ ስር መምጣት መቻሉን ታሪክ አሳይቶናል።ይሁን እንጂ ልማት ከዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጋር ተጣምሮ ሊተገበር የሚገባው ከምንም ነገር በላይ ያለንበት ድህነትና ኋላ ቀርነት በምንም ጉዳይ ቢሆን የሚባክን ኃይል ሊኖረን የማይገባ በመሆኑ ነው።ዲሞክራሲ ደግሞ ሁሉንም ሕዝባዊ ኃይል ወደ አንድ ማዕከላዊ ነጥብ በማምጣት ተጠቃሚነትን ያጠናክራል።ሕዝባዊ ኃይል ስንል የግራ የቀኙ የሀብታም የድሃው፣ የከተማ የገጠሩ፣ የደጋፊ ተቃዋሚው... የሁሉንም ኃይል ማለታችን ነው፣ የብዙሃንና አንፃራዊ የጥቂቶች ቁጥር ያላቸውን የእናሶችን ኃይል ባካተተ መልኩ ማለታችን ነው፡



t.me/OLDBOOKSPDF

'ትንሽ ነው፤ አይረባም!!' የሚባል አንድም የህብረተሰብ ክፍል የለም፡፡ ቁንጫ ትንሽ ብቻ ሳትሆን በቀላሉ እይታ ውስጥ የማትገባ ደቂቅ ፍጡር ናት... ግና እሷም ብትሆን በጦር ሜዳ ውሎ ግንባሩን ያላጠፈውን ጀግና ዝናሩን ታስፈታዋለች፤ ቀበቶው ታስወልቀዋለች፡፡ ልማትም በዲሞክራሲ ሥርዓት ሲደገፍ አገር ይቀናል፤ የሁለንተናዊ ኃይል ባለቤት ያደርጋል፡፡ ማንንም ሳይንቁ ሁሉንም አስተባብረው ከሰሩ በህብረተሰብ መካከል መራራቅን ሊፈጥር፣ ሊከፋፍለን የሚነሳው ኃይል ከንቱ ይመታል፡፡ በኮሪያ የገጠመውን አይነት መራራቅን እና ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥት ማስቀረት የምንችለውም በዚህ ብቻ ነው፡፡

በመጨረሻውና በመደምደሚያው ምዕራፍ ሊጨበጥ የሚገባው ቁምነገር ቢኖር፣ የትኛውም ርዕዮትና ፅንሰ ሃሳብን በትክክል በመረዳትና ተገቢውን ፍቱሻ አድርጎ ተግባር ላይ በማዋል እንጂ እንደ ሃይማኖት ስላመኑበት ብቻ ወደታለመው ግብ እንደማያደርስ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የተደጋገመ እንጉርጉሮ ወይም አንድ አይነት ዜማ የተንም ያህል ቢጥም መሰልቸቱ አይቀሬ ነው፡፡ ዓመት አልፎ ሌላ ዓመት ሲተካ፣ ጊዜ ሲቀያየር ቆም ብሎ ማሰብና የወቅቱን ጥሩ ዜማ ከነበረበት ላይ የራስን ለዛ አክሎ የበለጠ አጣፍጦ መጫወት ሲገባ ያንኑ ደግሞ ደጋግሞ ማላዘን አይበጅም፡፡

የምንኖርባት አለም ውጫዊ ተፅዕኖን ጨርሶ የማያስወግዱባትናትና ውሊታን መፈፀም፤በአንድ ገበታ ተቀምጦ መደማመጥን የሚያስችለው መልካም ፈቃድ ብቻ ሳይሆን በተዋዋይ ወገኖች መካከል ያለ ተመጣጣኝ ጥቅም መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ አለበለዚያ የጀፌ አሞራውና የአንበሳው የውሊታ ታሪክ ዞሮ እኛ ላይ ከመድረስ የሚያግደው ነገር አይኖርም፡፡

እንዲህ ነበር የሆነው፤እያ አንበሣ በዋርካው ሥር የጣለውን ፍሪዳ አንድ ጉንጭ እንኳ ጎርሶ ሳያጣጥም በስጋ ውስጥ የተቀበረች የአጥንት ስንጥር ጉሮሮው ውስጥ ትሰነቀራለች፡፡ ውጪ ነፍሲ.. ግቢ ነፍሲ.. ትግል ውስጥ ይገባል፣ አንበሣ፡፡ ታዲያ! በጣር ላይ እያለ ቀና





ሲል ፍሪዳ ከጣለበት ወርካ ቅርንጫፍ ላይ ጀፌ አሞራ ተቀምጦ ያያል፡፡

"ጀፌ አሞራ ስለነብስ አድነኝ...?" ይላል፣ በተማፅኖ፡፡

"ምን ሆኑ ጌታ አንበሶ...?"

"የአጥንት ስንጥር ጉሮሮዬ ላይ ተሰካ... እባክህ አውጣልኝ!"

"ካወጣሁልዎት እያ አንበሶ... ምን ይሸልሙኛል?" ይላል፣ ጀፌ አሞራ በተጣለው ፍሪዳ ላይ አይኑን እያንከራተተ፡፡

"ከዚህ ጭንቅ ብቻ አውጣኝ እንጂ ማንንም ያልሸለምኩትን ሽልማት እሰጥሃለሁ..."

ጀፌ አሞራ ቁልቁል ተንደረደረ... በተከፈተው የአንበሣ አፍ ውስጥ መንቁሩን እስከ አንገቱ ድረስ አስገብቶ ስንጥሯን ከአንበሣ ጉሮሮ ላይ በመንቀል አጥንቷን ወደ ራሱ ጉሮሮ እያንቀረቀበ ተመልሶ ወርካው ላይ ያርፋል፡፡ እያ አንበሶ ለማንም ያልሸለሙትን ሽልማት ለመቀበል ቋምጧል፡፡

"ይበሉማ! ጌታ አንበሶ... ሽልማቴን ያቀብሉኝ?"

አንበሣ የስንቱን ወገብ በሰባበረው ክርኑ ጉሮሮውን እያሻሸ ያልተጠበቀ መልስ ሰጠ፤ "አይ ጀፌ አሞራ... አየር ላይ ሰፍፍ ብለህ ስትበር ብልህ... ብልህ ትመስለኝ ነበር"

"ብልህ ማለት...!?" አሞራው ደነገጠ፡፡

"'ከአንበሳ መንጋጋ ማን ያወጣል ስጋ!' የሚባለውን ተረት አታውቀውም መሰለኝ...

"[illegible]ረ አውቃለሁ..."

"ታዲያ፣ ከአንበሳ አፍ ውስጥ ገብቶ ሳይበሉ ከመውጣት በላይ ምን ሽልማት አማረህ!!" በማለት ያሾፍበታል።

ከዚህ ተረት ጋር በተመሳሳይ፣ ኢትዮጵያም እንደአገር አንድ ወቅት ላይ በአፄ ዮሀንስ አራተኛ ዘመን ከደርቡሽ ጋር ጦርነት ውስጥ እስከመግባት ያደረሰው አጋጣሚ መዘዙ የተጠነሰሰው ሱዳን ምድር ላይ ተከብበው የነበሩትን የእንግሊዝ ወታደሮችን ለማስጣል አገሪቱ በገባችው ብልጠት የጎደለው ውለታ እንደነበረ ያስታውሷል።

## ስንብት

ህይወት እና ሞት ወደን የማንጠራቸው ገፍተንም የማናስቀራቸው የተፈጥሮ መልኮቻችን ቢሆኑም የሰው ሰዋዊ ተልእኮ ግን የሚለካው ሞቱም ህያው ከመሆን ቁልፍ ተግባር አንጻር ነው፡፡

**የታሪክህ ድርሳን ተገልጦ ሲነበብ፤**

**አልፈህም የማያልፍ**

**ልብ ላይ ያተምከው ከታጣበት ቀለም፣**

**'ኖርኩኝ' ብትል እንኳን**

**'አዎ ኖሯል' የሚል አንድም ፍጡር የለም፡፡**

**ደግሞ በዝያኛው ገጽ፣**

**'እሱ ማነው?' ሲባል.... 'እሱ እኮ...' ተብሎ ...**

**በበጎ 'ሚነሳ ...... በኩራት 'ሚወሳ**

**ካለህ ቅዱስ ተግባር ለሌላው 'ሚጠቅም**

**ሞት ስጋህን እንጂ......**

**ያንተን ህያውነት በፍጹም አይነጥቅም፡፡**

በሞት ምን የሚታጣ ነገር አለ?

"ከትልቅ ወይም ከትንሽ ቢሆን መወለድ ሞያ አይደለም፡፡ ራስን ለታላቅ ታሪክ መውለድ ግን ሞያ ነው፡፡





(ከአጼ ምኒልክ ህውልት ግርጌ ስር ተጽፎ የሚነበብ)

ሞት ለሟች ዕረፍት ነው። ሆኖም ግን ለቋሚ አንድም ግልግል ሲሆን አንድም ኑዳማ ነው። ሰው ሁሌ እንዳማረበት ቢኖር፣ ፈገግታው ባይደበዝዝ፣ ውበቱ ቢዘልቅ፣ ባይረግፍ፣ ጣዕረ ሞቱ ባይኖር፣ ከቀብር መቀስቀስ ቢቀር፣ ነገሮች እንዴት መልካም በሆኑ ነበር። ግና ሞት ይሙት ብለን ብንረግመው እንኳን አይቀርም። አምርሮ የመጣ ጊዜ ትንሽ አቆየኝና መልካም ላድርግ አይሰራም። የተሰጠህ ሠዓት አልቋልና የባከነ ደቂቃ ሲኮንድ አለህ ሞክር! እንባልም። "Re admission" ለሞት አይፈቀድም፤ በምንኖርበት ዓለም (ምድር) ላይ ኮርስ ያልቃል፣ በመጨረሻው ዓለም ውጤት ይሰጣል። ያወቀ ተጠነቀቀ፣ ለመጨረሻው ጥሩ ሰነቀ፤ በዚያን ቀን መልካሙ የገጠመው ደስ ይበለው፡፡ ያጣ ግን ራሱን እንጂ ሌላ አይውቀስ። ሰው ማመኑ አይጎዳውም፤ አምላኩን ቢታዘዝ ለራሱ ነው፡፡ ምንጊዜም ፀሎትና ዝማሬው አቤቱ! መንገድህን አመላክተን! ዕውቀትን ስጠን! ዕውቀታችንን በትክክለኛው መንገድ እንጠቀም ዘንድ የሚያስችለንን ጥበብም ለግሰን! ማለቱ ይሻለዋል። የጣፈጠንን ህይወት መራራ የሚያደርገውን ሞት ዘውትር ማስታወስ ይገባን ዘንድ ስለ ሞት ከተገለጹት ማስታወሻዎች የሚከተለውን እንመልከት።

ሞት የሰው ልጆች ሁሉ የሚቀምሱት በጣም ለብዙዎቹ መራራ ለጥቂቶቹ ደግሞ አሳማሚ ግን ጣፋጭ የሆነ ነገር ነው። ሁሉም ሰው ይሞታል። በታሪክ ውስጥ ከአካላዊ ሞት ስለመትረፉ የተነገረለት አንድም ሰው አይገኝም። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም የሰው ልጆች ይስማማሉ። ሞት አንድ ቢሆንም የሁሉ ሰው ሞት ግን እኩልና አንድ አይደለም። በሞቱ ዓለምን የሚጎዳና ብዙ ነገር የሚቀንስ ሰው እንዳለ ሁሉ በሞቱ ዓለምን አንዳች ነገር የማይጎዳና ምንም ነገር የማይቀንስ ሰው አለ። ከመቃብር ሥር ሆነው በመልካም ሥራቸውና ባበረከቱት በጎ አስተዋጽኦ ታሪክ ከመቃብር በላይ የሚያስታውሳቸው ህያው የሆኑ ሰዎች አሉ። ከዚህ በተቃራኒ ከመቃብር በላይ ሆነው የሚፈጽሙት መልካም ሥራ፣



t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያበረክቱት በጎ አስተዋጽኦ ባለመኖሩና በሚሰሩት ሙት ሥራ ሰው ከመቃብር ሥር እንዳሉ የሚያስባቸው ሰዎችም አሉ።

አንድ ሰው በህይወት መኖሩ ለራሱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለማህበረሰቡ በጣም ብዙ የሆነን ነገር እንደሚፈጥር ሁሉ፤ በህይወት መኖሩ ለራሱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለማህበረሰቡ ምንም አይነት ጥቅም የሌለው፣ ህያውነቱ ከሞቱ እኩል የሚሆንበትና የሚያመዝንበት ሰውም አለ።

ፈጣሪ በወሰነው የህይወት ክልል ውስጥ እየኖረ፣ ቀናውን መንገድ እየተከተለ፣ ትክክለኛውን የአምልኮት ተግባር እየተገበረ፣ የህይማኖቱን መርህ ይዞ ጠቃሚ ነገር ለራሱ፣ ለቤተሰቡና፣ ለማህበረሰቡ የሚያበረክት ሰው በሞቱ አንድም እንኳን ፊቅ የሚል ነገር አይኖርም። እርሱ በመሞቱ የሚመገበው አንድ ገበታ ላይ የሚወጣ ወጪ ሊቀንስ ይችላል። በሞቱ ምክንያት ግን ሰፊ የዕውቀትን ሃብት አይቀንስም። እርሱ በመሞቱ ሰዎች ሊታብሩት የሚያቋርጡት ስራ ይኖራል እንጂ የሚያቋርጥባቸው መልካም ነገሮች ግን አይኖሩም። በመጥፎ ሰው ሞት በጣም ብዙ መጥፎ ነገሮች አብረው ይሞታሉ። በአባብ ሞት መርዙ እንደሚቀበረው ሁሉ መሬት እረፍት ታገኛለች፡፡ በመልካም ሰው ሞት ብዙ መልካም ነገሮች ይሞታሉ፤ በንብ ሞት ማር እንደሚጠፋው ሁሉ መሬት ታለቅሳለች፤ በአዋቂዎች ሞት ጥበብ በጎዳና ትጮሀለች።

አንተ ከየትኛው ወገን ነህ? ከመጨረሻው ወይንስ ከመጀመሪያው? ሞትህ ሰዎችን ይጎዳል ወይንስ አንተን ብቻ ይጎዳል? ሞትህ ብዙ ነገሮችን ያሳጣል ወይንስ አንተን ብቻ ያሳጣል? በመልካምነትህ፤ በበጎ አስተዋጽኦ አበርካችነትህ ታሪክ ያስታውስሃል ወይንስ በከንቱነትህ፤ ጥቅም የማትሰጥ በመሆንህና ያበረከትከው መልካም ነገር ስለሌለ ታሪክ ይረሳሃል?

ምንጊዜም ተቀባይና ወሳጅ ከመሆን በፊት ሰጪና አድራሽ መሆንን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ዓለም ላይ አንድ ጭማሪ ነገር ማድረግን እንጂ አንድ ጭማሪ ነገር መሆንን መጠንቀቅ ይገባል። የላይኛው





እጅ ከታችኛው ይሻላል። ሰጪ መሆን ተቀባይ ከመሆን ይሻላል። አመንጪ መሆን የመነጨውን ከመጠጣት ይበልጣል። የሰንፍና እቅፍ ውስጥ ከመሸሸግ የትጋት ጥላ ስር ማዘውተር ይሻላል። ታሪክ አንባቢ ብቻ ከመሆን ታሪክ መስራት የበለጠ ያኮራል። ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት የሰሯቸው መልካም ስራዎችና ያበረከቷቸው በጎ አስተዋጽኦዎችን ማድነቅ ጥሩ ነው።

ተጠቃሚ እንጂ ጠቃሚ አለመሆናችን፣ ሸክም እንጂ ተሸካሚ አለመሆናችን፣ ችግር እንጂ መፍትሄ አለመሆናችን፣ ተመጋቢ እንጂ መጋቢ አለመሆናችን ሊሻር የማይችል እውነት እየሆነ የመጣ ይመስላል። ሌሎች ሰዎች ባበረከቱት መልካም ነገር መጠቀም እንችላለን። እኛ ግን ለሌሎች ሰዎች መልካም ነገር ማበርከት ያቃተን ይመስላል። አንዳንዶቻችን ጥቂት ጊዜ ፈረስ እንሆናለን፤ ብዙ ጊዜ ግን ብዙዎቻችን ፈረሱን የሚጎትተውን ጋሪ ነን።

እርግጥ ነው፣ ሞት ህይወትን ይተካል፤ ልዩነቱ በመተካካቱ አንዳንዱ ማትረፍ ሲቻል ብዙ ጊዜ ግን በባዶ መሸኘቱ ላይ ነው፡፡ በሞታቸው ማትረፍ የሚችሉ አሉ፤ ሞታቸው ለሌላ ህይወትን የሚሰጥ፤ ሞታቸው ለሌላው ውልደት የሚሆን ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህኞቹ ኖረው ከሚያተርፉት ይልቅ ሞታቸው የሚያስገኘው ጥቅም ይበልጣል፡፡ ልክ እንደ ሸረሪቱ...

ይህ ሸረሪት በህይወት ዘመኑ ፆታዊ ግንኙነት የሚያደርገው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ሸረሪቱ ፆታዊ ግንኙነት በሚያደርግበት ወቅት ሴቷ ሸረሪት ጅራቱን ይዛ መብላት ትጀምራለች። ወንዱ ሸረሪትም ስሜት ውስጥ ስለሚሆን ሴቷ እንደምትበላው አይገባውም። በመጨረሻም ወንዱ ሲረካ እርሷም በልታ ትጨርሰዋለች። ከዚያም ወንዱ ሸረሪት ይሞታል፤ ሴቷ ግን ትፀንሳለች፤ ትወልዳለችም። ታሪኩ ከሞት በስተጀርባ ስላለው ህይወት፤ ካረጀው ታሪክ ስለሚወለደው አዲስ ታሪክ በሚገባ የሚያስተምር እንደሆነ እስባለሁ።

አንተ በመሞትህ ምን የሚታጣ ነገር አለ? እምነትህ ምን ነገር



t.me/OLDBOOKSPDF

ያጣል? እውቀት ምን ነገር ይጎልበታል? መልካም ስራ የትኛው ወዳጁን ያጣል? በጎነት የቱ ወንድሙ ይሰወርበታል? ይህንን ደጋግመህ ጠይቅ።

በአንተ ሞት ምን ይታጣል? ምን ይሰበራል? ምን ይቀነሳል? አዋቂ ሆነህ በዕውቀትህ ሰዎችን ጠቅመሃል? ምሁር ሆነህ ማህበረሰብህን አገልግለሃል? ዶክተር ሆነህ በሽተኞችን ፈውሰሃል? መሐንዲስ ሆነህ ሰዎች የሚጓዙበትን መንገድ ቀይሰሃል? ሐብትህን አውጥተህ የተራበን አብልተሃል? የታረዘን አልብሰሃል? ሆስፒታል ገንብተሃል? ውሃ አፍልቀሃል? ቤተአምልኮት አንፀሃል? በጭንቀት የተወጠረን ሰው ረድተሃል? ልጆችህን በእምነት ጎዳና አንፀህ በእውቀት አሳድገሃል? ወይስ በተቃራኒው?

ትናንቱን የማያውቅ ትውልድ ዛሬን መኖርና ነገን መገንባት አይችልም። ያለፈው የአገራችን ታሪክ አኩሪና አንገትን ቀና የሚያደርግ ስለሆነ በርሱ እርካታ ይሰማናል። ነገር ግን ያን ታሪክ የሚመስል ሌላ ደማቅ ታሪክ ካልፈፀምን የዚያ አኩሪ ታሪክ ተሸካሚዎች እንጂ ባለቤቶች ልንሆን አንችልም። በመንገድ ዳር ላይ ውሻ የሚልሰው አጥንት በአንድ ወቅት የስጋ ዘር መሆኑና ከስጋ ጋር የሚያዛምደው ታሪክ ስለነበረው ውሻ የሚልሰው አጥንት ከመሆን የሚመልሰው፣ ዝቅና ከፍ የሚያደርግለት አንዳች ነገር የለም። ሆኖ መገኘት ከሁሉ በላይ ተመራጭና ጠቃሚው ነገር ነው። ሰው እስከሆንን ድረስ ስንሞት እንቀበራለን፤ ስንቀበር ግን ከቀብር በላይ ስማችንን የሚያስታውሰን አንድ መልካም ነገር ለእምነታችን፣ ለማህበረሰባችን እና ለሰው ልጆች በአጠቃላይ እናበርከት። ታሪክ የሚወቅሰን ሳይሆን ታሪክ የሚያወድሰን ሰዎች መሆን አለብን። በሞታችን እኛ ብቻ ሳንሆን ከእኛ ጋር በጣም ብዙ ነገሮች እንደሚታጡ ግንዛቤ መወሰድ አለበት።





## መንገድና ድልድይ

በእንግሊዛዊው የታሪክ ተመራማሪ አርኖልድ ቶቢ አረዳድ በቀላልና ግልፅ አማርኛ ሁሉም ታሪክ የፈተናና ምላሹ ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በአካባቢችን ፈተና ይደቀንብናል፡፡ ግለሰቦች፣ ተቋማት ወይም ኅብረተሰብ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ በዚሁም መሠረት አካባቢያቸው ለደቀነባቸው ፈተናና ተግዳሮት ውጤታማ መልስ መስጠት የቻሉ ግለሰቦች፣ተቋማት ወይም ኅብረተሰብ ታሪክ ሠሪ ሲሆኑ ዘመናቸው ለደቀነባቸው ፈተና ተገቢ ምላሽ መስጠት የተሳናቸው ደግሞ ታሪክ ሆነው ያልፋሉ፡፡

ወደድንም ጠላንም የነገይቱ ኢትዮጵያ ሕልውና የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ለተደቀኑብን ፈተናዎች በምንሰጠው ምላሽ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በርግጥም ምላሽ የዕውቀት ውጤት ዕውቀት ደግሞ የመመላለሻ መንገድና ድልድያችን ነጸብራቅ ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ለአልፍ ዓመታት የተመላለስንበት የዘመን መንገድ ከዕውቀት ይልቅ ለሀይል ጉብጅልና ከጦረኛነት ጋር ብርቱ ቁርኝት ያለው ደመ-ነፍሳችን ተጨባጭ መረጃን በመተንተን፣ በማሰላሰል ወደ ድምዳሜ ከመድረስ ይልቅ ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊትን የምላሽ አማራጮቻችን ሁሉ መፍለቂያ ምንጭ አድርጎብን ቆይቷል፡፡ ያን መሠሉ መንገድና ድልድይ ዛሬ ርቆ የሚያስጉዝ አይደለም፡፡ የድንጋይ ዘመን ተሸሮ በብረት ዘመን የተተካው ድንጋይ ከምድር በመጥፋቱ አልነበረም፡፡ ለውጥና መሻሻል ተፈጥሯዊ ሂደት በመሆኑ እንጂ፡፡ በሌላም በኩል ሥር የሰደደ ብልሹ ሥርዓትን መገዳደር የለውጥ መጀመሪያ መሆኑም መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም፣ ዛሬን እያለ ለሚኖረው ህዝባችን ስለቀጣይ የህይወቱ ዕጣ ፈንታ፣ ስላልፈለገ ሳይሆን ከተስቦልና ድካም ብዛት ማሰቢያ ጊዜ አጥሮት ላንቀላፋው ምስኪን ዜጋችን ልሂቃን ፣ የምር ልንጨነቅለትና ልንጠበብለት ይገባል።

በጥሬ ትርጓሜው ሳይንስ ተጨባጭ መረጃን መሰረት በማድረግ



t.me/OLDBOOKSPDF

የዕውቀት ማግኛ መንገድ ነው። ዳግም እንዳለመታደል ሆኖ ማህበረሰባችን በተጨባጭ መረጃ ላይ ተድገፎ ውሳኔ መስጠትና ዕለት በዕለት ሣይንስን የሕይወት ምርኩዝ በማድረግ ረገድ የሠፊ ክፍተት ባለቤት ነው። ደመ-ነፍሱ ታይላለች። በመረጃና ትንታኔ ሳይሆን በስሜት መንገድ ደምቆ ይታያል። ዝበያ በሌለበት ነፃ ዝበያ የእማራጮች ሁሉ እማራጭ ነው ሲባል – ጠያቂ የለም። ግን መታወቅ ያለበት ልማት የብርሃን እንጂ የጨለማ ውጤት አይደለም። መልካም አስተዳደርን ከብርሃን ውጪ ጨለማ ውስጥ ልናገኘው አይቻለንም። ብርሃን ያለንፃነት አይኖርም። በእጅራጭ የመከበር፣ የሥልጣን መንበር ላይ የመፈናጠጥ አባዜ ነው የጨለማ ውጤት፣ ራሱንም አገርንም ወደ ጨለማ የሚመራ።

አውሮፓ በህዳሴ ዘመኗ ወደፊት መራመድ ከመጀመሯ በፊት አንድም ፈጠራ ብልጭ ለማለት ያልቻለው ሰብዓዊነት በራቀው የጭቆና አዝዝና ዕምነት ሰፍኖ ስለነበር ነው። ስር የሰደደ ቆሻሻ ስርዓትን መጎዳደር የለውጥ መጀመሪያ ነው።

የዓለማችን የሥልጣኔ ማማ ከተቆቀረባቸው እምዶች መካከል - ኢንደስትሪ ቢባል ማብርና የሃይል ምንጭ ብንል ጤና ፣ ትምህርት ብንል መገናኛ ሌላው ቀርቶ መዝናኛችን እንኳ ሳይቀር - አመዛኙና ዋናው ክፍል ምንጩ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ነው። በዚህ መጠን ሳይንስ ዓለማችን ላይ ጉልህና ደማቅ አሻራውን ማተም ያስቻለው ዕውቀታዊ ግኝቶቹ ቴክኖሎጂያዊ የመፍትሄ አማራጮች መገኛ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሳይንስ እንደ አንድ የአስተሳሰብ መንገድ ጥያቄን ፣ግልፅነትን ፣ ክርክርን የሚያበረታታ፣ ተጨባጭ መረጃን ፣ መሻሻልና የአዳዲስ አማራጮች መፈጠርን የሚያጠናክር ባሕል በውስጡ ስላካተተ ጭምር መሆኑ ይታወቃል። በሳይንስ ባህል ውስጥ የኔ መንገድ አለበዚያ ወዲያ ሂድ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። ሳይንስ ሁሌም ለአዳዲስ ሃሳቦች እና ለሁሉም ዓይነት ጥያቄዎች በሩን ከፍት አድርጎ የሚጠብቅ ለአተያይ ልዩነትና ክርክር ታላቅ ዋጋ የሚሰጥ አዳዲስ ግኝቶችና ድምዳሜ የተደረሰባቸው መላምቶች የሚቀረፁት ቀጣይ መሻሻልና እድገትን በር እንዲከፍቱ





እንጂ ቀጣይ ጉዞን እንዲያደናቅፉ የሚከለክሉ የብረት አጥር ሆነው አይደለም። በመሆኑም የሳይንስ ግኝቶችና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንደ ማስተማርና እንደማስተዋወቅ ሁሉ ማህበረሰባዊ የሳይንስ ባህልን ማጎልበት ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

በሀገር ደረጃ የሳይንስ ባህል እንዲጎለብት፣ ዜጎች በሳይንሳዊ አመለካከት የታነፀ የጋራ መርህና ዕሴትን በመጋራት፣ የግልጽነት፣ የመቻቻልና የአሳታፊነት ባህልን ማዳበር እንዲችሉ መንገዱን መጥረግ ቀዳሚ ጉዳይ ነው። ማንኛውም ፖለቲካዊ ውሳኔዎቻችን ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት አድርገው መቀረፃቸውን መፈተሽ ያስፈልጋል። የኢንዱስትሪ አብዮትን ያረጋገጠው የእንግሊዝ ፖለቲካዊ ጉዞ ቁልፍ መገለጫ በወቅቱ ይወጡ የነበሩ ፖሊሲዎችና ይሰጡ የነበሩ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ሳይንሳዊ መንገድን የተከተሉ መሆናቸው ላይ ፍተሻ ይካሄድ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል።

እውቀት መንገዱ አንድና አንድ ብቻ አይደለም። ከባሕልም ከእምነትም ከመኖርም ይመጣል። እምነታዊ ትስስር ፋይዳ ቢስ አድርገህም አትየው። በራሱ መንገድ ፋቅ ግብ አለው። ለማህበረሰብ መንፈሳዊ ሽፋን መጠለያ ይሰጣል። ችግሩ የሚመጣው የፖለቲካ ሥርዓታችን ምንጭ እናድርገው ስንል ነው። እኛና እነሱ በሚል ቀኖና ይከፋፍላል። መድሃኒትነቱን ለቆ አደጋ ይደቅናል።

ፖለቲካዊ ትስስር፣ ርዕዮት፣ ልዕልና፣ አሰራር፣ አደረጃጀት… የጎሳና የዘር መሠረትን ሲቆራኝ ዘርና ደምን ቆጥሮ ሲመጣም ከዕምነት ያልተለየ የከፋ ከባድ አደጋ ነው። በስብእዊነት ደረጃው ተፈጥሯዊ ቢሆንም መሰረቱ ማካተትን ይገድባል። ከህይማኖትም ይጠባል። ምንም እንኳ ወደመንበር መወጣጫ የሀይል መሠረት ምቹ እርካብ ቢሆንም መንበሩ ግን ልል መሆኑም በዚህ የተነሳ ነው።

በሥንጥር ላይም ቢሆን በፅኑ መሰረት ላይ መቆም ይኖርብናል። ወደ አገር ግንባታ በማስመሪያ እየተለካ አይዘለቅም።መንገዶችን አሳታፊ፣ ውይይትን የሚጋብዝ ሆኖ መብቀል ይኖርበታል።አገር፣

ብሄርና ሀይማኖት የዕስት ማዕዘን ጫፎች ናቸው። መደላድላቸው ሲጣመር እንጂ ሲመች መዘን የምንጫወትባቸው የዕጣ ካርታዎች አይደሉም።ልጓም ሆነው የሚያገለግሉንም ባንድነት አጣምረን ስንይዛቸው እንጂ ወደ አንዱ ማጥበቅ ብዙ ምዕራፍ አያስጉዝም ፡እቅጣጫ ያስታል።

በሌላ መልኩ ተፈጥሯዊው እውነታ ደግሞ ሰውነትም ሆነ አንጎል እንዳችም ዓላማ እንዳችም ትርጉም እንዲኖራቸው ተደርገው መበጀታቸውን ሹክ ሊለን ይችላል፡፡ ስለዚህ አንተ ማለት የምርጫህ ውጤት ነህ የሚሉ ኤክሲስቴንሺያሎችም ተበራክተው ይገኛሉ። ከዚያ በተቃራኒው፡ ለዚህች ዓለም ትልቁ ዓላማና ሥራ ሰው እንደሆነ በመግለጽ ትልቁን ጥበባዊ ጉዞ እንዲከተል የሚያሳስቡ ድልድዩና መንገዶችም በቁጥር ቢያንሱም በዚህች ዓለም መመላለሳቸውን እናውቃለን፤ ሰምተንም እናምናለን።

እዚህ ላይ ትኩረት ልትሰጠው የሚገባው ጉዳይ የሥልጣን ምኑም ነገር ዘላለማዊ አለመሆኑን ነው፡፡ አባብ በህይወት እያለ ጉንዳንን ይበላል፤ አባብ ሲሞት ጉንዳኖች ይበሉታል። ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ይለወጣል። በህይወትህ የማንንም ዋጋ አታሳንስ! ምናልባት ኃይለኛ ትሆን ይሆናል፤ ነገር ግን ጊዜ ካንተ የበለጠ ኃያል ነው። አንድ ዛፍ መቶ ሺህ ክብሪቶችን ሲሰራ አንድ ክብሪት ግን መቶ ሺህ ዛፎችን ታቃጥላለች። አንድ መጥፎ ስራ ጥሩ ድርጊቶችን ታጠፋለች። ዋናው ነገር ሰዎችን የምታከብር፤ በአስተሳሰብ ዘመናዊ፡ ሁልጊዜ ጥሩ አመለካከት ያለህ እና መቼም ታማኝ የሆንክ መሆን ይኖርበሀል።

ጥንታዊ ሮማውያን ዓለምን እንዳይረሱ፡ የመጡበትን እንዳይዘነጉ ጭምር በድል ደስታ ላይ ሆነው፣ ሁላችንም ሟቾች ነን! ይሉ ነበር፡፡ ማንነት አሻራ ነው፣ መረሳት የሌለበት፤ በድልም ሆነ በሽንፈት ጊዜ። ተከታዮችን ማፍራት መቻል ከአመራር ፅንሰ ሀሳቦች ውስጥ አንዱ ነው። በሰዎች ልብ ውስጥ ራዕይህን መትከልና ለራዕዩ መሳካት ሰዎች ነቅተው እንዲሰሩ ማስቻል ደግሞ የመሪዎች ሚና ነው።





ይህን ለማድረግ በሰዎች ዘንድ የጠበቀ ታማኝነት ሊኖርህ ይገባል። በስራ ቦታ፣ በቤተሰብ፤ በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች እና በሌሎች ዘርፎች በሰዎች ዘንድ ታማኝነትን ማግኘት ከባዱ ስራ ነው። ለዓላማችን ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ለማፍራት በቅድሚያ ራሳችን ታማኝ ሆነን መገኘት ይኖርብናል። ለሰዎች ታማኝ ስንሆን ሰዎች ለኛ ታማኝ ይሆኑልናል። ራሳችን ታማኝ ባልሆንበት ሁኔታ ከሰዎች ታማኝነትን መጠበቅ ደግሞ የማሞ ቂሎ የበኩር ልጅ ያደርጋል። ለትዳር አጋሮቻችን፤ ለጓደኞቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን፡ ለአለቆቻችን ታማኝ ስንሆን ነው - ከሰው ታማኝነትን ማግኘት የምንችለው። ከዚህ ውጭ ለቀጣዩ ብሩህ ዘመን መንገድና ድልድይ መሆን የማይታሰብ ነው።

መንበር ታማኝነት በተግባር የሚገለፅበት እሴት ነው። እያንዳንዳችን ምን ያህል ለራሳችን ታማኝ ነን? ምን ያህልስ የምንሰራለትን አላማ ለማሳካት የተቻለንን ሁሉ እንጥራለን? ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው ምላሽ የመንበር ታማኝነትንም ሆነ የተስተካከለ ቤተሰብ ለመመስረት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ትርጉምና መልክ ያለው ስራ ሰርቶ ለማለፍ ከምንም በላይ ሊያዝ የሚገባው ነገር እንደሆነ በመውሰድ አንተም ጠጠርህን ጥለህ ማለፍ ይጠበቅብሃል!!!





t.me/OLDBOOKSPDF

መንበር ከጠመንጃ አፈሙዝና አፈሙዝ ብቻ በሚፈልቅበት ሀገራችን አመራር ጥበብ አመራር እውቀት ተደርጎ አይታሰብም፡፡ደራሲ ዲረዓዝ ይህን ዘመን ያስቆጠረ ዕሳቤ በመለወጥ አመራር ሳይንስ ፣መሪነት ጥበብ እንደሆነ በግል፣በቡድን፣ በማህበረሰብ ከዚያም ከፍ ብሎ እንደሃገር ራሳችንን ልናስተዳድርበት ስለሚገባው ጉዳይ ጠጣሩን የንድፈ-ሃሳብ ቋጥኝ አላልተው መሬት በማስነካት የመሪነትን ሚስጥር እንካችሁ ይሉናል፡፡

ዶ/ር ምህረት ደበበ

የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵን ወደ ስልጣኔና ዕድገት ለማሸጋገር ምሁራኖቿ ጃፓንን እንደምን ሠለጠነች፣ መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር ምንገጽታ ይኑረው በማለት ዳር ዳሩን ይሽከረከሩበት የነበረውን ቁልፍ ጉዳይ ከሸፈነው አይናፋርነት በማላቀቅ እርካብና መንበር በሚል ርዕስ የዘመናችንን የስጋት ምንጭ ብቻ ሳይሆን መፍትሄያዊ አማራጩንም በመዘርዘር ለዛ ባለው ቋንቋ ለአንባቢ በማቅረብ ደራሲ ዲራዓዝ የመጀመሪያው ኢትዮጵዊ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ዶ/ር አብዱልረዛቅ ሙህዩዲን

Printed by Central Printing Press
Tel. +251-11-466 5781/82

t.me/OLDBOOKSPDF